# "የደነበረው በቅሎ"

## የአስተምህሮ "ልጓም" ይሻል

2ኛ ዕትም



ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን

"የላይኛው ሳይነግረን ፈረደብን እንዳይባል ... በቋንቋችን የተነገረ እነሆ አንድ ጩኸት! ቤተ ክርስቲያን ትሰማው ይኾን?"

ሰሎሞን ጥላሁን (ፊደንቶ ዩኒቨርሲቲ፣ ሀገረ አሜሪካ)

# "የደነበረው በቅሎ"

## የአስተምህሮ "ልጓም" ይሻል

ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን

ጥር ፳፻፯ የምሕረት ዓመት

ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

***የደነበረው በቅሎ***


በሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን © ፳፻፮ ዓ.ም.



ዐታሚ፦ ርኆቦት አታሚዎች
ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

በድጋሚ በጥር ፳፻፮ ዓ.ም. ታተመ



© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

*ያለ ደራሲው ፈቃድ ይህንን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ለማባዛት፣ ለመገልበጥ፣ ለመቅረጽ ወይም በማንኛውም ሌላ ዘዴ በስፋት ለመጥቀስ አይቻልም። ነገር ግን፣ ሐሳቡ ለጥናት፣ ለማስተማሪያነትና ለመሳሰሉት ዐላማዎች በተወሰደ ጊዜ ሁሉ ተገቢ ሥነ ጽሑፋዊ የምንጭ አጠቃቀስ ሥርዐትን በተከተለ መንገድ፣ የመጽሐፉ ርእስ፣ የደራሲው ስም፣ የታተመበት ዘመን ተገልጦ ሊጠቀስ ይገባል።*

ልዩ መግለጫ ካልተሰጠ በስተቀር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ ከአሳታሚው በተሰጠ ፈቃድ የተወሰዱት የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1954 ዓ.ም. (© መብቱ በሕግ የተጠበቀ) ካሳተመው *ጎ.ሰ.ት* (በተለምዶ *ነባሩ* ከሚባለው) ቅጂ ነው። ነገር ግን አጽንዖት ለመስጠትና ከዚህ መጽሐፍ ጽሑፍ ለየት ብሎ ለአንባቢ እንዲታይ ታሳቢ በማድረግ ጥቅሶቹን *ዘንበል ባለ* (Italic) የሆህያት አጣጣል ወይም ቅርጽ የለወጥኋቸው እኔ ነኝ።

ዐልፎ፣ ዐልፎ ከ*ዐመት* መጥቀሴ ስላልቀረ፣ ይኸንኑ በቦታው አመልክቻለሁ። *ዐመት* ቢብሊካ ኢትዮጵያ በ1993 ዓ.ም. ያሳተመው *ዐዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም* (© መብቱ በሕግ የተጠበቀ) ነው።


***Yedeneberew Bekilo***


By Solomon Abebe Gebremedhin © 2014
All Rights Reserved. This book contains materials protected under International and Federal Copy Right Laws and Treaties. Any unauthorized reprint or use of this material is prohibited. No part of this book may be reproduced or transmitted in any form or by any means, electronic or mechanical, including photocopying, recording or by any information storage and retrieval system without express written permission from the author/publisher.



ISBN: 978-99944-970-0-3



ጥያቄ፣ አስተያየትም ኾነ ጊስ ካለዎ፣ ለጸሐፊው በሚከተለው አድራሻ ሊጽፉ ይችላሉ፤
ለሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 27912 ኮድ 1000
ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።
E-Mail: soloabebe@gmail.com
ስልክ: 0913074448



የሽፋን ንድፍ፦ ወንድም በረከት ታደሰ


# አበርክቶት

ይህ መጽሐፍ ለውድ አባቴ

ለአቶ አበበ ገብረ መድኅን

እና

ከመምህሮቼ አንዱ ለነበሩት

ለመጋቤ ሐዲስ ዶ/ር ክሪስቶፈር አለን ቤታም

በፍቅርና በአክብሮት ተበርክቷል።

# DEDICATION

This book has been dedicated to:

my father,

Ato Abebe Gebremedhin

and,

one of my professors,

Dr. Christopher Alan Beetham,

with love and respect.

## መታሰቢያነቱ

ለእውነት ሟቾች ሁሉ

# አስተያየቶች

በርግጥም በቅሎዋ፣ እንደ ልማዷ፣ ደንብራለች። በተቀመጡባት፣ በራሷ፣ በቅርቧ ባሉት እና በንብረት ላይ አደጋ እያደረሰች ነው። ጌታዋም፣ እርሱም ደግሞ እንደ ልማዱ፣ የሚገሯትን ሰዎች (እንደነ ሰሎሞን እና እንደነ ማነው ስሙ? ያሉትን)፣ የተለያዩ የበቅሎ መግሪያ መሣሪያዎቹን በማስያዝ ከየአቅጣጫው እያስነሣላት ነው።

እናንተዬ! እኔስ በእግሯ ስከላ፣ በአፏ ዛብ፣ የሚኾንበትን ቀን ናፈቅሁትም፣ ፈራሁትም። መናፈቄ እርሷም፣ እንደ ልማዷ፣ እንደገና ወደ መንገዱ ተመልሳ፣ እንደገናም በወግ ዕቃዎቿ ሁሉ አጊጣ፣ የምትሰግርበት ቀን (የተሐድሶ ቀን) ስለሚኾን ነው። መፍራቴ ግን "የልጆቿን ምክር አልሰማ ብላ መከራ ሊመክራት ይሆን?" ብዬ ነው።

በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)
*ቀበና ሁለት ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን*

## እነሆ አንድ ጩኸት!

*መጽሐፋ ባነሣው ርእሰ ነገር የተነሡ ጥያቄዎች በሚገባ ተመልሰዋል፤ የሥልታዊ ነገረ መለኮት ገጽታ አለውና በየሥፍራው ተመሳሳይ ታሪካዊ እውነቶችን ዋቢ እያደረገ ዳግም እንዲደመጡ በማስተጋባት፣ "ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፣ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት"* (ዕብ. 2፥3) *የሚል መንፈስ የሚታይበት ሰጹብ የዕቅበተ እምነት ሥራ ነው! በሥነ ጽሑፍ ደረጃው የልቀት መሥመርን ያሠመረ ከመኾኑም ባሻገር ምሁራዊ ቃናው ተጨማሪ ተአማኒነት ሰጥቶታል፤ ለዚህ ነው ይህንን መጽሐፍ ነጋሪ ብቻ ሳይኾን አስተማሪ ኾኖ ያገኘሁት። መማር አልጨረስሁም ለሚሉ ሁሉ፣ ትምህርት ቤት ሳይሄዱ፣ በርእሰ ጉዳዩ ሊማሩበት ይችላሉ። ይህ መጽሐፍ የዘመን ጩኸቶችንና ያልተሰሙ ድምፆችን ያሰባሰበና ከዱር ጉዞ መላሽ ነው፤ የላይኛው ሳይነግረን ፈረደብን እንዳይባል በሰው በኩል ለሰው በልካችንና በቋንቋችን የተነገረ እነሆ አንድ ጩኸት! ቤተ ክርስቲያን ትሰማው ይኾን?*

ሰሎሞን ጥላሁን
*ሬጀንት ዩኒቨርሲቲ፣ ሀገረ አሜሪካ*

## "ተሳስቼ ነበር"

በቅርቡ ባላሳትመውም፣ ውሎ አድሮ ለንባብ የማበቃው፣ መጽሐፍ አለኝ። መጠሪያው *ተሳስቼ ነበር* የሚል ነው። የዚህን ዝግጅት አንዳ መልእክት ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት በ*ማቴቴስ* መጽሔት ላይ ቤተ ክርስቲያንን መትከል ወይስ መከፋት በሚል ርእስ ነገር ላይ "ተሳስቼ ነበር" ብዬ መጻፌን አልዘነጋውም። ይህንንም ያደረግሁት በአደባባይ ለተገለጠ ስሕተት የአደባባይ ምልሽ በመስጠት ማረም ግድ መኾኑን በማመን ነበር።

ዘንድሮ ደግሞ ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን *የደነበረው በቅሉ* በሚል [ርእስ] የአስተምህሮ ልጓም አስፈላጊ መኾኑን ሊያሳውቀን ተነሥቷል። መጽሐፉ ምጥን ገጾች ያሉት ቢኾንም፣ የእርጋታ ንባብን ይሻል። ግራ ቀኙን በማጤን፣ ለካስ እንደ ቤርያ ሰዎች ካልኾንን፣ ወየውልን ያሰኛል። መጽሐፉ ራሳችንን አካትተን ሁሉን እንድንፈትሽ ግድ ይለናል። ፍተሻው ተሳስቻለሁ፣ ተሳስተናል ወይም አስተውናል በማስኘት ከነነቱ ሩጫችን ይገታናል።

በርግጠኛነት ዛሬ ብዙ ምእመን፣ ብዙ ሰባኪ፣ ብዙ መጋቢ፣ ብዙ ዘማሪ በሀገሪቱ እየተርመሰመሰ ነው። አብዛኛው በዕለታዊ ኑሮ "ጠበል ፈለቀ" በተባለበት ስፍራ ፈጥኖ በመድረስ ያገኘውን እየሸመተ ነው። ይሕ ዐይነት ሸመታ ደግሞ ጉዳትን ያስከትላል። *የደነበረው በቅሉ* ይህን ሊያሳየን ተጻፈ። እንኪያስ የክርስቶስ ነኝ ያለ ሁሉ ዘመኑ ሳያልፍ ከወዲሁ እንዲጠነቀቅ ጥሪ ቀርቦለታል።

ሰሎሞን፣ በመጋቢነት ጸጋውና ጥሪው በ *የትሩፋን ናፍቆት* መጽሐፉ የመከረንን ምክር አሳድጎ፣ ዛሬም ሁሉን በመመርመር ፍሬያማ ኑሮን በቃሉ መሠረት እንመዝንም እንኖርበትም ዘንድ ሁላችንን ይጋብዛል።

ስሜ ታደሰ (መጋቢ)
*የኢትዮጵያ ባፀብል ባፕቲስት ቸርች ፌሎሺፕ ፕሬዚዳንት*

ሰማዩን ጥቋቊር ደመናዎች እንዣበዉበታል። ደመና ገፋፊ ብሩህ ጸሐይ የቃሉ ወገግታ ነው፤ ደመና በታኝ ብርቱ ነፋስ ቅዱስ መንፈስ ነው። ወንድማችን ሰሎሞን ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለችበትን እውነታ፣ በብልኃተኛ ጥጥ ፈልቃቂ አያያዝ እየጐለጐለ አውጥቶ፣ አሳየን፤ እልባሌውን ከኹነኛው እንድንለይ አነቃን። ታዲያ እኛ ምን እናድርግ? ጕልጕሉን ጥጥ እያባዘትን፣ እየነደፍን እያደራን ጥሩ ሸማ እንሥራ፤ ሙሽራይቱንም እናልብሳት።

ንጉሤ ቡልቻ
*ኮምፓስ-ኢትዮጵያ፣*
"ቃሉ ያበራል" ፕሮጀክት

አሁን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትና በክርስቲያንነት በምንታወቅ ቍጥራችን ጥቂት ባልኾንን ሰዎች ዘንድ የሚታየውን ሕይወት ሳስብ፣ *"እኔ ነውሬን ወዴት ልሸከም?"* (2ሳሙ. 13፥13) የሚለው የትዕማር ጥያቄ ወደ አዕምሮዬ ይመጣል።

በዕድሜ ታናሽ፣ በአዕምሮ ብስለትና በአመለካከት ግን ትልቅና ገና ብዙ ሊያደርግ የሚችለው ወንድማችን ሰሎሞን አበበ በዛጋጀው *"የደነበረው በቅሉ"* በሚለው መጽሐፍ አማካይነት በቤተክርስቲያንና በክርስቲያኖች መካከል የሚታዩትን፣ ሊወገዱ የሚገባቸውንና "የጨውነትና ብርሃንነት" አገልግሎት እንዳንሰጥ ወደ ኋላ የሚጎትቱንን ነገሮች በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ ምን ርምጃዎችን ብንወሰድና ምን ውሳኔዎች ብናደርግ ነውራችን ተወግዶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋትና ለምድራችን በረከት ለመኾን እንደምንችል በጥሩ ኹኔታ አቅርቦልናል።

ይህንን በፍሬ ነገርና በሥነ መለኮታዊ ሚዛናዊነት ግልጽ በኾነ መንገድ የተዘጋጀ መጽሐፍ አንብቤ ተባርኬአለሁ፤ ማድረግ ያለብኝንም ተረድቼአለሁ። ከዚህም የተነሣ እያንዳንዱ ክርስቲያን፣ ቤተሰብ፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና የቤተ ክርስቲያን አጋዥ የኾኑ ድርጅቶች መጽሐፉን እንዲጠቀሙበት እመክራለሁ፤ አበረታታለሁም።

ሺፈራው ወልደ ሚካኤል
*ከልጆች ዕድገት ሥልጠናና ምርምር ማእከል (CDTRC)*

*"እነሆ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው እናገባለን፣ ሥጋቸውንም እንመራለን"* (ያዕ. 2፥3)። ሐዋርያው ይህን ያለው በአስተማሪነት ዐውድ ውስጥ መኾኑን ልብ ይሏል (ቍ. 1-2)። የአፍ ንግግራችን፣ አስተምህሯችንና ጠባያችን በርግጥ "ልጓም"— የቅዱስ ቃሉና የመንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር — ያሻዋል። ቍጥጥርን ግን ማን ይወዳል? *"የጌታ መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ"* በማለትና ቃሉን ያለ መንገዱ በመውሰድ ያለ ቍጥጥር መለቀቅን የምንመርጥ የለንም? *መንፈሱ ራስን የመግዛት ቢኾንም* (2 ጢሞ. 1፥7)።

በአሽከርካሪው ቸልታም ኾነ በሌላ ምክንያት፣ ከቍጥጥር ውጭ የኾነ ተሽከርካሪ የሚያደርሰውን የንብረትና አሠቃቂ የሕይወት ጥፋት ሁላችንም እናውቀዋለን። ለራሱ የደኅንነት ቀበቶ ያሠረ "ሾፌር" ግን በአመዛኙ ከሚደርስበት የአደጋው ጉዳት ሊያመልጥ ወይም ጉዳቱን ሊቀንስ እንደሚችልም ይነገራል። አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳያደርግና "ሳይታሠር" የሚያሽከረክር ሾፌር ግን ከተያዘ ሊቀጣ ይችላል። አልያም ምክርና ማስጠንቀቂያ መቀበሉ አይቀርም ብለን እናስባለን። ዓላማው ጉዳትን በመከላከል የተሳፋሪዎችን ደኅንነት መጠበቅ ነው።

ወንድማችን ሰሎሞን፣ በዚህ መጽሐፉ፣ ለራሳችንና ለምናገለግለው ሕዝብ ደኅንነት ሲንል ለመቈጣጠሪያው መንፈሳዊ "ልጓም" ሕይወታችንን እንድንሰጥና ይህንንም ሳናደርግ ቀርተን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳት አድርሰን እንዳንገኝ በወንድማዊ ፍቅር ይመክረናል፤ ያስጠነቅቀናል፤ በ"ነቢያዊ" ጩኸቱም ያነቃናል (የምንነቃ ካለን)። በእውነት ላይ ቆሞ ማስጠንቀቂያ መስጠትም የእውነተኛ ነቢይ ሚና ነው። የማስጠንቀቅም ዓላማው የሚመለከታቸውን ሁሉ ከአደጋ ማትረፍ ነውና፣ ይህን አዎንታዊ ውጤት እንጠብቃለን።

እንግዲህ፣ መንፈሳዊ መሪዎችና የቃሉ አገልጋዮች እንደ ኾንን የምናስብ ሁላችን፣ ለራሳችን ስተን ብዙዎችን ከማሳት እንድንተርፍ፣ ከጥፋትም እንድንጠበቅ፣ በሰከነ ልብ ይህን መጽሐፍ እናንብብና እንመከር። "ከባሰውም ፍርድ" እንድንድንና *"መልካም፣ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ..."* ለመባል፣ በሞቱ የዋጀንና ለአገልግሎቱ የጠራን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋው ይርዳን (ያዕ. 2፥1። ማቴ 25፥21)።

ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)<br>
ከሐዋሣ ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

❧✻☙

*"የደነበረው በቅሎ"፦ የአስተምህሮ "ልጓም" ይሻል፡-* የተሰኘውን [መጽሐፍ ረቂቅ] አንብቤ ስጨርስ የተሰማኝ ስሜት ደስታና ሥጋት የተቀላቀለበት ነበር። ደስ ያለኝ እጅግ የተዋጣለትና የጊዜው መጽሐፍ ሊታተም መዘጋጀቱን ዐስቤ ሲኾን፣ ሥጋቴ ደግሞ፣ ከሀገራችን የማንበብ ባህል አንጻር፣ በስንቱ ሰው እጅ ገብቶ ይነበብ ይኾን? ከሚል የመጣ ነበር። ስለኾነም ሥጋቴ ተወግዶ ደስታዬ ፍጹም እንዲኾን፣ ይህን ጠቃሚ መጽሐፍ አማኞች ሁሉ አንብበው ራሳቸውንና ቤተክርስቲያንን ከዘመኑ የትምህርት ነፋስ እንዲጠብቁ እመክራለሁ።

ጌታሁን ታደሰ (መጋቢ)<br>
የኢትዮጵያ አማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት

❧✻☙

መስቀል አልባ ክርስትና፣ ክርስቶስን ጥግ ላይ ያቆመች ቤተክርስቲያን፣ ሰው ሰው ብቻ የሚሸትት አስተምህሮ የነገሠበት ዘመን እኛ እንደምንኖርበት እንደዚህ ያለ ጊዜ ያለ አይመስለኝም።

እኛም ጥቍሩን ጥቍር፣ ነጩንም ነጭ ማለት አቅቶን በምንንገላታበት በዚህ ወሳኝ ወቅት፣ ይህች መጽሐፍ፣ የክርስትና እምነት በሕይወት መኖሩም ኾነ የዕድሜ ቍጥሩ የሚለካው በአስተምህሮው ንጽሕናና በመጽሐፍ ቅዱሳዊነቱ ነው ስትል ትሞግተናለች። ለወጣቱ ትውልድ፣ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀሙ ከባድ ቢኾንም እንኳ፣ ላለንበት ዘመን ወሳኝ መልእክት ይዛለችና፣ ከማንበብ ውጭ ሌላ ምርጫ የለንም። በተለይም፣ የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ተማሪዎች እንዲሁም ምሩቃን እንዲያነብቧት አበረታታለሁ።

ዘላለም አበበ<br>
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያን ተማሪዎች ኅብረት<br>
(EvaSUE) ፕሬዚዳንት

3.4 “የወጣት አልወጣት” ውጥረት ....................................144
3.5 ቅርስና ውርስ አልባ እምነት ....................................146
3.6 ለጥቃት የመጋለጥ ስንጥቃት ....................................150
3.7 የደቀ መዝሙርነት መዳከምና የምግባር ብልሽት....................151
3.8 የስሙና ትምህርቱ መነቀፍ ....................................153
4. የህመሙ ፍኖት፦ ምን እናድርግ? ....................................157
4.1 ለቅዱሱ መንፈስና መጽሐፍ ሥልጣን መገዛት....................158
4.2 “መንፈስን አታጥፉ” ....................................164
4.3 ትኩረት ለስብከተ ወንጌልና ደቀ መዝሙርነት....................168
4.4 ትኩረት ለቃለ እግዚአብሔር ጥናት ....................................170
4.5 ትኩረት ለነገረ መለኮት ትምህርት ....................................172
4.6 ትኩረት ለዕቅበተ እምነት ....................................173
4.7 ጉባኤያትና ፋይዳዎቻቸው ላይ ከለሳ ማድረግ ....................176
4.8 ኅብረቱ ቢያብር ያዋጣ ይኾን?....................................179
5. ማጠቃለያ፣ ቍጭትና ተስፋ....................................185
5.1 ማጠቃለያ....................................185
5.2 ያመለጡ ዕድሎች?....................................189
5.3 ዳግትና ተስፋ....................................194
5.4 ያላረመሙ ዝይዎችን ፍለጋ....................................207
5.5 ማሳረጊያ....................................210
ዋቢ መጻሕፍት ....................................217
መፍትሔ ቃላት....................................227

# ምስጋና

እነሆ፣ ይህም ሥራ መጽሐፍ ኾኖ ይወጣ ዘንድ የመለኮት ረድኤት ዐገዘኝ። እንግዲያስ፣ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው ማለት ሲያንሰኝ። አዎ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የኾነው አምላክ እግዚአብሔር ይክበር፤ ይመስገን።

የውዷ ባለቤቴ ዓሌክስ (ዓለም ንጋቱ) እና የልጄ ላላ (ላኤል ሰሎሞን) ድጋፍ፣ ጸሎትና ማበረታታት ባይታከልበት ኖሮ ይህ ሥራ በዚህ መልክ አይጠናቀቅም ነበር፤ ቀድሞውንስ ይጀመር ነበርን? አይመስለኝም። እናም፣ “ቡሩክ ኹኑ” ብላችሁስ። ይህ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላና ወደ ማተሚያ ቤት በተላከበት ዋዜማ እግዚአብሔር ቤታችንን በተጨማሪ የሐሤት ምንጭ ይባርከው ዘንድ በጐበኘበት ምሕረት የተሰጠችን ዐዲሷ ልጃችን ሕፃን ዮሐና ሰሎሞንም ቡራኬው አይቀርባትም።

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት መነሻ የኾኑኝ አጋጣሚዎች አሉ። ለዐምስት ጊዜያት በዐምስት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ለተሰባሰቡ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዳቀርብ በተጋበዝሁ ጊዜ ያዘጋጀኋቸው የሴሚናር ጽሑፎች ነበሩ። እነዚህን ጽሑፎች የተመለከቱ አንዳንድ ወገኖች ጽሑፎቹ በርከት ላሉ ተደራሲያን ቢቀርቡ ፋይዳቸው ከፍ ሊል እንደሚችል ይነግሩኝ ነበር። እኔም ሐሳቡን በመቀበል በሥራው ስለ ገፋሁበት ይህ መጽሐፍ ተገኘ፤ ስለዚህ እነዚህን ወገኖች ማመስገን ይገባኛል።

በተጨማሪ፣ ጥናታዊ ጽሑፎቹን እንዳዘጋጅና ለተለያዩ መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምእመናን እንዳቀርብ ዕድሉን ለሰጣችሁኝ ተቋማት ምስጋና አቀርባለሁ። ስማቸውን ለመጥቀስም፣ የቤተር ላይፍ አገልግሎት[1]፣ ለኢትዮጵያ መጽሐፍ

---

[1] *ቤተር ላይፍ አገልግሎት* ባዘጋጀውና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተጓዳኝ ማኅበራት ወኪሎች በተገኙበት ከመጋቢት 20-22 ቀን 2004 ዓ.ም. በዐዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች በተካሄደው ዐውደ ጥናት ላይ *የእስተምህሮ ችግሮች በድኅረ “ነጻነት”* በሚል ርእስ ያቀረብሁት ጽሑፍ ነው።

ቅዱስ ማኅበር[2]፣ ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን ነገረ መለኮት ትምህርት ተቋማት ኅብረት (AETIE)[3] እና ለኢትዮጵያ *ሚሌኒየም* 2000 *ፕሬየር ቼይን*[4] ነው፤ "እግዚአብሔር ያከብርልኝ" ብያለሁ።

መቅድሙን የጻፈልኝን ወንድሜን መጋቢ ዮሐንስ ሞሐመድን አመሰግናለሁ። የመጽሐፉን ሽፋን ንድፍ የሠራው ወንድሜ በረከት ታደሰ ነው፤ በዐጭር ጊዜ ትውውቃችን ላሳየኸኝ ወንድማዊ ፍቅርና ትሕትናህ፣ *ቤኪ*፣ አመሰግናለሁ፤ ጣቶችህንም ጌታ እግዚአብሔር ይባርክልህ ብያለሁ።

የኅትመት ወጪውን ከፊል ክፍያ ለማስያዝ እንድችል ላገዙኝ ለመጋቢ ሚካኤል አክብሮቴን አገልጻለሁ። በተለይም፣ እንደሁልጊዜው፣ መጽሐፉን በመጠነኛ ቅድመ ክፍያ ብቻ (በዱቤ) ለማሳተም በጎ ፈቃዳቸውን ለሰጡኝ፣ ትሕትና በተሞላው መስተንግዶና በሥራቸው ጥራት ለሚያገለግሉኝ የርኆቦት ማተሚያ ቤት ባለቤቶችና ሠራተኞች ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ረቂቁን አንብበው እጅግ ጠቃሚ አስተያየቶቻቸውን የሰጡኝ ወገኖቼ ብዙ ናቸው። አቶ ሺፈራው ወልደ ሚካኤል፣ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ፣ መጋቢ ጌታሁን ታደሰ፣ መጋቢ ስሜ ታደሰ፣ መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻ፣ አቶ ሰሎሞን ጥላሁን፣ አቶ ዘላለም አበበና ዶ/ር ንጉሤ ተፈራን ከልቤና በእውነት አመሰግናቸዋለሁ፤ ቡሩካን ኹኑ፤ ለበጎ ነገር ሁሉ ብዙ።

[2] የክርስትና ዐደራን ጠብቆ ለመጪው ትውልድ በማስተላለፍ ላይ ባተኰረውና በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከሐምሌ 18-19 ቀን 2005 ዓ.ም. በዐዲስ አበባ ሐርመኒ ሆቴል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ *የእምነት ውርርስ እንዳያነክስ፦ ክርስትናና ተረካቢው ትውልድ* በሚል ርእስ ያቀረብሁት ጽሑፍ ነው።
[3] የወንጌላውያን የነገረ መለኮት ተቋማት ኅብረቱ (AETIE) የነገረ መለኮት መምህራንና ተማሪዎች በተገኙበት በ2005 ዓ.ም. ባዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ *የክርስቲያን አስተምህሮ አስፈላጊነት ከ"እምነት እንቅስቃሴ" አንጻር* በሚል ርእስ በጸሐፊው የቀረበ ጽሑፍ።
[4] የጸሎት ሰንሰለት አገልግሎቱ ከ50 የኢትዮጵያ ከተሞች ተውጣጥተው ለ21 ቀናት የጾምና ጸሎት ጉባኤ በዐዲስ አበባ ከተማ ለተሰበሰቡ አገልጋዮች መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም. *ክርስቲያናዊ አስተምህሮና ደቀ መዝሙርነት* በሚል ርእስ ያቀረብሁት ጽሑፍ ነው።



# ቀዳሚ ቃል

በኢትዮጵያ ያለች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከምንጊዜውም በበለጠ አስቸጋሪ ወቅት ላይ ትገኛለች። ቀድም ባለው ጊዜ ስሕተት ሲባሉ የነበሩ ትምህርቶች ዛሬ በየአትሮኖሱ ላይ፣ በታላቅ ድፍረት፣ "ዐዲስ መገለጥ" ተብለው ይለፈፋሉ። ይህ ሳያንስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸው ልምምዶች አብያተ ክርስቲያናትን መሙላታቸው ፀሐይ የሞቀው ጒዳይ ነው። በተጨማሪም፣ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መዛነፍ የብዙ አማኞችን ሥነ ምግባራዊ ዐቋም ፈትኗል፤ ብዙዎችንም በማዛል ከሩጫው ሜዳ አስወጥቷል። ስሎሞንም፣ በሰላ ብዕሩ፣ ይህንን ክርስትና መሳይ ነገር፣ እንደ ይሁዳ፣ *"ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት"* (ይሁዳ 1፥3 *ዐመት*) ስንል "እንድንጋደለው" ይሞግተናል፤ ይሸነቁጠናል።

*የደነበረው በቅሎ* ከፋ ዜና ለፋፊ ጽሑፍ አይደለም። ይልቁንም ለዚህ "ድንበራ" የመንስኢ ምክንያቶችን በመግለጽ በዚሁ ከተቀጠለ ቤተ ክርስቲያን እያጋጠማት ያለውን አደጋ የሚያትት ቢኾንም፣ ገና ተስፋ እንዳለ በማብሠርም ከቈዘምንበት እንድንነሣ የሚያበረታታ ነው እንጂ።

ድግግሞሹ ከመብዛቱ የተነሣ ሐሰትን ከእውነት ለመለየት ጆሮዎቻችን በደነዘዙበት በዚህ ዘመን ይህ መጽሐፍ ትንቢታዊ በኾነ መልኩ ከዕንቅልፋችን የሚያነቃ ደወል ይመስላል። አማኞች የዚህን መጽሐፍ ጥሪ ሰምተው ወደ መጽሐፉ ከተመለሱ፥ በኢትዮጵያ ያለች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ይበልጡኑ ታብባለች፤ እግዚአብሔርም በምድራችን ላይ ይከብራል።

ስለዚህ ሰሎሞንንና እርሱን የሚመሳሰሉ ለቤተ ክርስቲያን መታደስ የሚተጉና በጤናማ ነገረ መለኮታዊ አስተሳሰብ የዳበሩ አገልጋዮችን እግዚአብሔር እንዲያበዛልን እየለመንን ይህን መጽሐፍ በጥሞና በማንበብ ተግባራዊ ምላሽን እንስጥ። ሰሎሞን የሩጫው አካል የኾኑችንውን ይህችን መጽሐፍ እንካችሁ ብሎናል፤ እኛም ሰሚ ጆሮዎቻችንን እንንፈገው።

ዮሐንስ ሞሐመድ (መጋቢ)
*ከሂዩስተን፣ ሀገረ አሜሪካ*

# የምን "በቅሎ"?

እውነት የምን በቅሎ? ለዚህ መጽሐፍ መጠሪያ ይኾን ዘንድ ካልጠፋ ርእስ ይህን መሳይ "ያልተለመደ" ነገር መጠቀም ለምን አስፈለገ? መደንበርንስ እዚህ ምን አመጣው? ብዙ ጥያቄዎች ሊነሡ እንደሚችሉ እገምታለሁ። መጠየቁም አግባብ ነው። ለማንኛውም ስለ ጉዳዩ ጥቂት ነገር መናገሩ ይበጃል።

"በቅሎ እንስሳ ነው" በማለት ልጀምር? በልጓም ካልገሩት እንጣጥ ባይ ዘላይና አገርጋሪ ፍጥረት በመኾኑ ይታወቃል። በደንባራነቱ እየወገሸ (እየደነገጠ) አግድም ሲያስመሱም ሳለ የኮሽታ ድምፅ ቢሰማ የባሰ ያስበረግገዋልና ነው "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" መባሉ። ለማንኛውም በቅሎ ከለማዳ እንስሳት አንዱ ነው። ጥሩ ባለሞያ ሊገራው ከቻለ ልጓም ይገባለትና መፋነኑና ድንበራው ይገታለታል። እኔ ግን ይህን መጽሐፍ የጻፍኩት ስለ እንስሳው ገድዶኝ አይደለም (1ቆሮ. 9፥9-10)። ስለ ሰው እንጂ፤ ከሰውም ደግሞ "በውስጥ" ስላለነው "የቤት ልጆች" ስለ እኛው ነው (1ቆሮ. 5፥12)።

የርእሱን ፋይዳ የምናገኘው ዘይቤ ጠቀስ ምጸታዊ ንግግር ተጭኖት መቅረቡን ከግምት አስገብተን ያየነው እንደ ኾነ ነው። ከሥነ ቃል ሀብቶች መካከል የሚመደቡ ፈሊጣዊ አባባሎች፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮችና ምሳሌያዊ ትእምርቶች "ከኅብረተ ሰብ ኑሮ ጋር በእጅጉ የተሳሰሩና ... ማኅበራዊ ቅርስ"[5] እንደ መኾናቸው፣ ቋንቋዊ ተግባቦትን በደንብ ያበለጽጋሉ። ምስል ከሣቾች ኾነው የሚገኙበት ጊዜም ብዙ ነው። ሰፊ ትንታኔ የሚፈልገውን ነገር ሰብሰብ አድርገን

[5] እማዋይሽ መለሰ፣ ሰሎሞን ወልዱና መስፍን መሰለ (አዘጋጆች)፣ *የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች* (ዐዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ፣ 1982 ዓ.ም.) 10።





እንድናቀርብ ይረዱናል። በተጨማሪም አይረሴነታቸው መዘንጋት የለበትም፤ ስሜትን ጨምድደው ስለሚይዙና በአዕምሯችን ታትመው ስለሚቀሩ በቀላሉ እናስታውሳቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ፣ በተመሳሳይ ኹኔታ፣ በዘመኑ የነበሩ ዐውደ-ገብ (*context oriented*) ዘይቤያዊ አነጋገሮችንና ምሳሌያዊ ትእምርቶችን በመጠቀም የእስራኤልን ሕዝብ ሕይወትና ተመክሮ የገለጠበት አግባብ በርካታ ነው።

ለምሳሌ እንዲኾነን የተወሰኑትን እንመልከት። በትንቢተ ሆሴዕ መጽሐፍ ላይ *"ኤፍሬም እንዳልተገላበጠ ቂጣ ነው"* (ሆሴ. 7፥8) መባሉን ዐስቡ። ዘለፋ ይመስላል፤ ግን አይደለም። ያለብዙ ዝብዝብ ሊተላለፍ የተፈለገው ሐሳብ በቀላሉ ይገባናል። የሰሜኑ እስራኤል መንግሥት ሕዝብ በዙሪያቸው ከነበሩ አምልኮ ባዕድ ተከታይ አረማውያን ጋር በመቀላቀላቸው ምክንያት መንፈሳዊ ሕይወታቸው ምን ያህል እንደ ተበላሸ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር በኩል ቊልጭ ብሎ ይታየናል። እስራኤል ያህዌን ትቶ ርዳታ ፍለጋ ወደ ግብፅና አሦር ዐይኑን ማቅናቱን ለመንቀፍ ደግሞ፣ *"ኤፍሬምም አዕምሮ እንደሌላት እንደ ሰነፍ ርግብ ነው"* (ሆሴ. 7፥11) የሚል ሌላ ተነጻጻሪ ዘይቤ በመጠቀም እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲወቅሰው እናገኛለን።

መዝሙረኛው በበኩሉ ከማስተዋል መንገድ የተሳሳቱትንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የተሳናቸውን ቸልተኛ ሰዎች በሚወቅሥበት ሌላ ሥዕላዊ ምሳሌ አማካይነት ሲገሥጽ፣ *"በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጕሙአቸው፥ ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትኹኑ"* (መዝ. 32፥9) በሚል ኀይለ ቃል ተጠቅሞ እናገኘዋለን። እንግዲህ እነዚህን የሚመስሉ አገላለጾች በመጽሐፍ ቅዱስ ጭምር የተለመዱ ናቸው ማለት ነው። "የደነበረው በቅሎ" ፈሊጣዊ አባባልም የተቀዳው ይህን ከመሰለ የአነጋገር ዘይቤ መንጭቶ መኾኑ ነው። ስለዚህ ነው ይህ መልከአ-እንስሳዊ ፈሊጣዊ አነጋገር (*ዞምርፊዝም*) ጥቅም ላይ የዋለው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ “ድንበራውስ ምንድነው?” የሚል ሳይኾን አይቀርም። “መደንበር” በቁሙ “ፍርሀት፣ ሽሽት፣ ዝላይ” ማለት ነው። ለተነሣንበት ሐሳብ ይበልጥ የሚቀርበውን ትርጓሜ ስንመለከት ግን፣ “መሳሳት፣ መጨናበር፣ መወናበድ፣ በትክክል ማየትና ማድረግ አለመቻል”[6] ማለት ሲኾን፣ በአጠቃላይ “መደናበር”/“ድንበራ” ተብሎ ይገለጻል። በደንብ ያልተገራ በቅሎ መደንበሩ/መደናገሩ አይቀርም። በመለኮታዊ ትምህርትና ጸጋ ያልተገራ ሰው ሕይወትና ልምምድም ከስሕተት ሊርቅ አይቻለውም። ስለዚህ አስቀድሞ በጥንቃቄ ከስሕተት በመጠበቅ መገራት፣ ተሳስቶ ሲገኙም ታርሞ መመለስ አማራጭ የለውም ማለት ነው።

ትምህርትና ልምምዳችን ይቅርና የአንድ ሰው አንደበት እንኳ እንደ ቋያ እሳት የፍጥረትን ሩጫ ሊያጋይ ስለሚቻለው፣ እርሱን መቈጣጠር ታላቅ የቤት ሥራችን መኾኑ ተነግሯል። ቍጥጥሩ ደግሞ የተገለጠበት ተምሳሌታዊ ማሳያ አራዊትና አዕዋፍትን ከመግራት ጋር የተያያዘ ነው (ያዕ. 3፥5-8)።

ለማንኛውም “የደነበረው በቅሎ”ን ምጸታዊ አገላለጽ በቀጥታ የተዋስሁት ከወዳጄ ወንጌላዊ ደሉ አስተያየት ነው። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ድምፅ የኾነው *ብርሃን* መጽሔት፣ በሚያዚያ 2006 ዓ.ም. ላይ ለንባብ ሲበቃ፣ ካተኰረባቸው ነገሮች አንዱ “የቡሽሪ ነውጥና ግርግር” ጕዳይ ነበር። ይህን አስመልክቶ በተነሡ ሐሳቦች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ከተጋበዙ ወገኖች መካከል አንዱ ወንድሜ ደሉ ጸጋዬ ነበር። እሱም ታዲያ በወቅቱ ስለ ተፈጠረው ግርግር አስተያየቱን ሲሰነዝር፣ ሐሳቡን የጀመረው “በቅሎው እኮ ከደነበረ ቈይቷል!” በማለት ነበረ። “የደነበረው በቅሎ” መጽሐፍ ርእስ ከዚያ አስተያየት ውስጥ ተቀድቶ ጀመረ።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የዘመናችን ግርግር የተገለጸበትን ይህን አስተያየት መለስ ብሎ ለማስላሰል ሞክሯል። “በቅሎውን ያስደነበሩት” በርካታ ነገሮች እንደ

---

[6] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፤ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት* (ዐዲስ አበባ፡- ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም) 468።





መኾናቸው፣ ሐሳቡ ለመጽሐፉ ርእስነት እንደሚስማማ ዐሰበ። ከድንበራው መግፍኤዎች አንዱ የአስተምህሮ መሳከር ሲኾን፣ መፍትሔውም የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ልጓም ነውና፣ የሐሳቡን አግባብነት በመጋራት ለመጽሐፉ ርእስነት ቢውል መልካም መስሎ ታይቶታል።

ይህን መሳይ አገላለጽ የእስራኤል ነቢያት መጠቀማቸውን ለማሳየት ሁለት ተጨማሪ ምንባባት እንመልከት። እግዚአብሔርን በመተው የአረማውያንን አማልክት ስትከተል የነበረችው እስራኤል “የምትፋንን ግመል መስለሻል” ተብላለች። *“በቈላ ያለውን መንገድሽን ተመልከቺ፥ ያደረግሽውንም ዕወቂ በመንገድም ላይ እንደ ተለቀቀች እንደ ፈጣን ግመል ኾነሻል”* (ኤር. 2፥23)።

ወደ ኋላው እያፈገፈገ ወደ ቃል ኪዳኑ ለመመለስ አሻፈረኝ ያለውን ሕዝቡን እግዚአብሔር በገሠጸበት የኤርሚያስ መጽሐፍ ውስጥ ሌላ ኀይለ ቃል አለ። እንዲህ ይላል፤ *“አደመጥሁ ሰማሁም፤ ቅንን ነገር አልተናገሩም፤ ማናቸውም፦ ምን አድርጌአለሁ? ብሎ ከክፋቱ ንስሐ የገባ የለም። ወደ ሰልፍም እንደሚሮጥ ፈረስ እያንዳንዱ በየመንገዱ ይሄዳል”* (ኤር. 8፥6)።

እንግዲህ፣ ባለፉት ኹለት ዐሠርት ዓመታት፣ በምድራችን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በአስተምህሮና ተያያዥ ጕዳዮች አኳያ እየታየ ያለውን ኹኔታ ለማንጸር ይህን ከላይ የተጠቀሰና “የደነበረው በቅሎ” የተሰኘ ምጸታዊ አባባል ለዚህ መጽሐፍ በርእስነት ተጠቅሜበታለሁ። ይህንንም ለማብራራት የሞከርኩበትን ኹኔታ አንባቢዎች ይገነዘቡልኛል የሚል እምነትና ተስፋ አለኝ።

በተጨማሪ፣ በቅሎ በደነበረ ጊዜ ማለዘቢያ መፍትሔው ልጓም እንጂ ቃጭል አይደለምና፣ በእኛም መካከል ለታየና ለሚታየው ግርግር መድኀኒቱ “ልጓም” ዝግጁ ኾኖ ይጠብቀናል፤ “ልጓሙ” የሚገኘውም በጊዜና በሥፍራ ርቆ አይደለም። ይኸው፤

*ሰምተን እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ወደ ሰማይ ወጥቶ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል በሰማይ አይደለችም። ሰምተን*

> *እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ባሕሩን ተሻግሮ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል ከባሕሩ ማዶ አይደለችም። ነገር ግን ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው* (ዘዳ. 30፥12-14)።

ይህ ጸሑፍም ዋነኛውን መፍትሔ ለማሳየት የሞከረው በዚሁ አግባብ ከመኾኑ የተነሣ፣ በንዑስ ርእስነት የቀረበው ሐሳብ የሚያጠነጥነው በ“ልጓም” ተመስሎ በቀረበው ክርስቲያናዊ ዛቢያ ላይ ነው፤ *አስተምህሮ* በምንለው!

ወንጌላዊ እንዳለ ገብረ መስቀል ከሰባት ዓመታት በፊት ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ባቀረቡት አንድ ያልታተመ ጽሑፋቸው ውስጥ ያስቀመጡትን እዚህ መጥቀሱ ሐሳባችንን ይበልጥ ያዳብርልናልና እንጥቀሰው፤

> አስተምህሮ በፈረስ ቢመሰል የቀሩት አገልግሎቶች ደግሞ በጋሪ ይመስላሉ። ልጓሙ እስትንፋሰ መለኮት ያለበት ቃለ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ የግል ሕይወታችንና አምልኳችን፣ የኅብረት አምልኮ እና አገልግሎታችን፣ አስተዳደርና አመራራችን፣ ሥርዐቶቻችንና ወጎቻችን በቃሉ ልጓምና በአስተምህሮ ፈረስ እየተመሩ ነው? ወይስ የሚመሩን ሌሎች ሰብአዊና መንፈሳዊ ኀይሎች ናቸው?[7]

ጥያቄው ሞጋች መኾኑ ግልጽ ነው። ይህን ጥያቄ መመለሱ ግን የሁላችንም ኀላፊነት ነውና ወደ ጠርዝ ልንገፋው የሚቻለን አይመስለኝም፤ አዎ፣ “የደነበረው በቅሎ የአስተምህሮ ልጓም ይሻል”።

[7] እንዳለ ገብረ መስቀል፣ *የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙበት ወቅታዊ ኹኔታ፦ መንፈሳዊ ችግሮች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖዎችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች* (ዐዲስ አበባ፦ ያልታተመ ጽሑፍ፣ 1999 ዓ.ም.) 2።



# መንደርደሪያ

ክርስትና የመድኅኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ (ቲቶ 3፥4) የተገኘ እውነት ነው። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ላይ የተመሠረተው ተስፋ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ ትሥጉት (*ሥጋ መልበስ፣ ሰው መኾን*)፣ በሞቱና በትንሣኤው ብርሃን ተጨባጭ ኾነ። እነሆም፣ የጌታ ኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርትና *ሥራው* ምስክር ከኾኑት ቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ላለፉት 2000 ዓመታት ቅዱሱ የእግዚአብሔር ወንጌል እየተሰበከ ኖሯል (ማር. 16፥8፤ ሉቃ. 24፥47)። ኢትዮጵያ ሀገራችንም የዚህ ታላቅ በረከትና ጕብኝት ስለ ደረሳት፣ የምሥራቹን ቃል የተቀበሉቱ ወገኖች፣ በክርስቶስ ክርስቲያን በወንጌልም አማኞች ሊኾኑ በቅተዋል።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ክርስትናን በቀዳሚነት ከተቀበሉ ጥቂት ሀገሮች ተርታ የምትሰለፍ ሀገር ናት። የራሱ ጕድለቶች ቢኖሩትም፣ ነባሩ የክርስትና እምነት፣ በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ታሪኩ፣ ከ1600 ዓመታት በላይ አስቈጥሯል። በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ) አማካይነት በ4ኛው ምእት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ የተሰበከው ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን ይፋዊ ምሥረታ በምክንያትነት እንዳገለገለ ጠንካራና ታማኝ ታሪካዊ ማስረጃዎች ይጠቀሱለታል።[8]

[8] ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳቤዎስ ጀምሮ ይህን ታሪክ መዝግበው ያቈዩ ሰነዶች ይህንኑ እንደሚመሰክሩ የታወቀ ነው። ይህኛው ታሪካዊ ሐቲት የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባትን አስመልክቶ ደምበኛው ዘገባ (*Standard Version*) ሊባል የሚችልና እስከ ዛሬም ድረስ ማንም በማስረጃ ሊያስተባብለው ያልሞከረው ነቢብ ነው። John Foster, *Church History: The First Advance* (London: SPCK, 1991) 110-11.

አንዳንድ ትውፊታዊና አፈ ታሪካዊ ምንጮችን መነሻ የሚያደርጉ ጽሑፎች እንደሚዘግቡት ከኾነ ደግሞ፣ የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከዚያም ይቀድማል። በዐዲስ ኪዳን ውስጥ በምናገኘው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ውስጥ እንደ ተጠቀሰው፣ ፊሊጶስ በጋዛ መንገድ አግኝቶ ክርስቶስን የሰበከለትና ያጠመቀው ጃንደረባ *“ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ የንግሥት አዛዥ”* (ሐዋ. 8፥27) እንደ መኾኑ፣ የክርስትናን እምነት በ34 ዓ.ም. ገደማ ወደ ሀገራችን ይዞ የገባው ቀዳሚ ሰው መኾኑንና ወንጌልንም በመስበክ ቤተ ክርስቲያን መትከሉን የሚናገሩ ወገኖች አሉ።[9]

ሌሎች ወገኖች በበኩላቸው፣ በጃንደረባው “ኢትዮጵያዊ” መኾን ላይ ጥያቄ ባይኖራቸውም፣ በጥንቱ ዓለም በዚህ ስም የሚጠራው መልክአ ምድራዊና ሀገረ መንግሥታዊ ብያኔ አኳያ በሚያጠነጥኑ ሙግቶች ላይ በመመርኰዝ፣ ክርስትና ወደ እኛዋ ኢትዮጵያ በዚያን ወቅት ገብቷል መባሉ ላይ ጥያቄ ያነሣሉ።[10] ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌልን ለኢትዮጵያውያን ሲሰብክ በሰማዕትነት ማለፉን ይናገራል። ኾኖም የኢትዮጵያዊው *ስንክሳር* ኢትዮጵያ የአንድም ሐዋርያ ደም በግፍ ሳይፈስባት ክርስትና የገባባት ምድር እንደ ኾነች በመናገር ያስተባብላል።[11]

እንግዲህ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ዐበይት ታሪካዊ ኹነቶች መካከል በቀዳሚነት የተከናወነው የትኛውም ቢኾን እንኳ፣ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ከክርስትና እምነት ተነጥላ ለመታየት የማትቻል ሀገር ኾናለች። ስለዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

[9] *መሠረት ስብሐት ለአብ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋጽኦ* (ያልታተመ) 9።
[10] የእነዚህ ወገኖች መከራከሪያ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከጥንቷ ኢትዮጵያ ጋር አንድ አይደለችም ከሚል ሐሳብ የሚመነጭ መኾኑ ነው።
[11] Sergew Hable Selassie, “The Establishnment of the Ethiopian Church,” in *The Church of Ethiopia: A Panoroma of Histoy and Spritual Life,* 2nd Print (Addis Ababa: EOTC, 1997) 3.





ከዚህ ጋር መታየት ያለበት ደግሞ፣ የዓለምአቀፉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አካል እንደ መኾኑ፣ ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥም የራሱን ውጣ ውረዶች ዐልፏል። ያተረፈውን ያህል ያከሰረውም አይጠፋም፤ ያበጀው መኖሩ እውነት ቢኾንም ያልተሳካለትም ቀላል አይመስለኝም። ኾኖም ግን እዚህ ለመጥቀስ የተሞከረው የክርስትና ታሪካችንን ጥንታዊነት፣ የእምነታችን አሻራና ውርስ ረጅምነት ማውሳት ብቻ ነው። ክርስትናችን የረጅም ዘመን ታሪክና የደለበ ውርስ ባለቤት መኾኑ የሚያከራክር አይመስለኝም።

ወንጌላዊው[12] ክርስትና በበኩሉ፣ በኢትዮጵያ ምድር በወጉ እግሩን ካስገባ፣ ገና ከአንድ ምእት ዓመት በላይ አልዘለለም። ዘመኑ ቢያንስም *ታዲያ አሰሚታው*[13] (በጎ ተጽእኖው) ቀላል እንዳልነበር ይነገራል። በስመ ክርስትና የሚኖሩትን በወንጌል ትምህርት ከማደስ በተጨማሪ ወንጌል ባልደረሰበት የሀገሪቱ ክፍል ክርስቶስን አስተዋውቋል፤ አብያተ ክርስቲያናትን ተክሏል። በእግዚአብሔር ጸጋ የተሠራው ብዙ ነበርና፣ ወንጌላውያኑ ያበረከቱት አስተዋጽዖ ላይ ጭፍን ጥርጣሬ ማሳደር አይቻልም። ጥረታቸው ከስብከተ ወንጌል አገልግሎት ጐን ለጐን በተካሄዱ ማኅበረ ሰብ ዐቀፍ ልማቶች ላይ ያተኰሩ ሁለንተናዊ አገልግሎቶችና አበርክቶዎች የተቃኙ እንደ ነበሩ ታሪካቸው ይመሠክራል። ይህን ማተት የተነሣንበት ሐሳብ ባለመኾኑ ባንገባበትም እንኳ የእግዚአብሔር ረድኤት ምልክት ኾኖ ማገልገሉን መጥቀስ ግን ተገቢ ይመስለኛል።

ወንጌላዊውን የክርስትና እምነት የተለየ ካደረጉት ነገሮች መካከል እንደኛው እታመንበታለሁ የሚላቸው መሠረታዊ አስተምህሮዎቹ የቆሙባቸው አዕማድ

[12] ወንጌላዊውን ክርስትና ለብቻው ነጥሎ ማየት ያስፈለገበት ምክንያት፣ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት በቀጥታ በወንጌላዊው የክርስትና ክፍል ላይ ብቻ የሚያጠነጥን በመኾኑ ነው። ስለዚህ በጽሑፉ ውስጥ “የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን” የሚል ሐረግ እንኳ ጥቅም ላይ ውሎ ቢገኝ፣ በአመዛኙ ወንጌላውያኑን አብያተ ክርስቲያናት ብቻ የሚመለከት ይኾናል ማለት ነው።
[13] በባዕዱ ቋንቋ “*Impact*” የተሰኘውን ቃል ለመተካት መነሻው “አሰማ” (“ሰ” አይጠብቅም) የኾነውን “አሰሚታ” የሚል ቃል ተጠቅሜአለሁ። በዚህ መልኩ የቃሉን ርባታዊ አወቃቀርም ኾነ ትርጒማዊ ፋይዳ የተዋስኩት ከጋሽ ንጉሤ ቡልቻ ነው።

(ምሰሶዎች) ከበካይ የትውፊት[14] እድፍ የጸዱና የተጠበቁ፣ እንዲሁም ለመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የሚገዙ ናቸው ብሎ ማመኑ ነው። ይህም ሲባል ወንጌላዊው ክርስትና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎቹ ርቱዕነት (የቀና፣ የተስተካከለ፣ ቀጥ ያለ መኾን) ጥንቃቄ ያደርጋል። ለእነዚሁ ትምህርቶቹ ጸንቶ መኖርም ተገቢውን ዋጋ በአስፈላጊው ጊዜ ለመክፈል አያመነታም።

ስለ ኾነም፣ ክርስትና እኒህ ዐበይት አዕማዶቹ ከተጓደሉ፣ ከተዛነፉ፣ ወይም በልዩ ልዩ መንገድ ተከርክመው ይዘታቸው ላይ ለውጥ ከተካሄደባቸው እምነቱ ድውይ (የታመመ፣ የተቀጨ) ይኾናል። በሌላ አባባል፣ ትምህርቱ በእንግዳ ትምህርት ከተበከለ፣ ከተበረዘና ከተከለሰ የክርስትና አስተምህሮ ተፋልሷል እንላለን። በተጨማሪ፣ ጤናማው የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ በተቃናና በተደራጀ መልክ የማይሰጥና የማይተላለፍ ከኾነ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ተግባሯና መለኮታዊ ዐደራዋ እንደ ተዘነጋ ይቈጠራል።

ስለዚህ፣ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አስተምህሯዊ ተፋልሶ በዘመናችን ተከሥቶ እንደ ኾነ ማሠሥና አግባብ ያለው ክርስቲያናዊ ትምህርት ትኵረት ሳይነፈገው በመስ ጠት ላይ መገኘት አለመገኘቱን "በወፍ በረር" መቃኘት ይኾናል። በዚህ ላይ ተመሥርቶም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን (ብሎም ሌሎች አገልጋዮችን) እና ምእመናንን ስለ ጉዳዩ ማሳወቅና መጐትጐት የጽሑፉ ዐቢይ ዓላማ ነው።

[14] ይህ ቃል ማለትም *ትውፊት* እንደ አገባቡ አዎንታዊም አሉታዊም ትርጓሜ ሊይዝ ይችላል። *ትውፊት* በግዕዝ ቃልነቱ "ስጦታ፣ ልማድ፣ ትምህርት፣ ወግ፣ ታሪክ ሃይማኖት፣ ሥርዐት፣ ከጥንት ከአበው ሲወርድ ቃል በቃል ሲነገር የመጣ" የሚል ፍች እንዳለው ሊቁ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይናገራሉ (*መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* [ዐዲስ አበባ:- ደስታ ተክለ ወልድ በአርትስቲክ ማተሚያ ቤት እንዳሳተሙት፣ 1948] 397)። በተጨማሪ የአለቃ መሠረትን ትርጓሜ ማየትም ይቻላል፤ "‹ትውፊት› ማለት ቅብብል ወይም ርክክብ ማለት ነው። ይኸውም አንዱ ከሌላ የተቀበለውን ወይም የተረከበውን እንዲሁ ለሌላ አሳልፎ ይሰጠዋል፤ ወይም ይተውለታል፣ ማለት አስረክቦት ይለቃል። ተከታዩም እንደዚሁ ያደርጋል። እንግዲህ በዚህ ዐይነት ቅብብሉ ወይም ርክክቡ፣ ከትውልድ ወደ ተከታዩ ትውልድ እየተላለፈ የሚቀጥል ጊዜና ታሪክ ሁሉ ‹ትውፊት› ይባላል" (*ሰጽንዖት* የእኔ)። መሠረት ስብሐት ለአብ፣ *ትውፊታዊ ኅሳበ ዘመንና ታሪኩ፡ በኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን አቋም* (ዐዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም) 1።





ከዚሁ ጐን ለጐን አንድ ቍልፍ ነገርም ዐብሮ መታየት አለበት። የክርስትና ሕይወት ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ የተሰጠ የደቀ መዝሙርነት ሕይወትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኑሮ ጠባይ እንደ መኾኑ፣ የክርስትና አስተምህሮ መፋለስ ከገጠመው የምግባር መበላሸት ተከትሎት መከሠቱ አይቀሬ ይኾናል። በዚህ ረገድ የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ከገጠሟት ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች መካከል የምግባር ብልሽትን የወለደ የአስተምህሮ ትርምስ በዋነኛነት ከሚጠቀሱት መካከል መኾኑንም እንመለከታለን።

በመኾኑም በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ በዐምስት ዐበይት ክፍሎች በተዋቀሩ ሦስት ተያያዥ ሐሳቦች ላይ በማነጣጠር ዋነኛውን ርእሰ ጉዳይ ለማቅረብ ተሞክሯል። በመጀመሪያው ክፍል የእምነት ዐደራን የመጠበቅና የማስተላለፍ ኀላፊነት ከክርስትና ትምህርት ጋር የተቈራኘበትን አግባብ ያስቃኛል። በክፍል ሁለት ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድኅረ "ነጻነት"[15] ያጋጠሟትንና ከአስተምህሮ ጋር የተያያዙ ችግሮችን፣ ለማሳያ ያህል፣ በመጠኑ ይዳስሳል። ቀጥለን ደግሞ እነዚህ ችግሮች በአግባቡ ምላሽና ማስተካከያ ካልተሰጣቸው ሊያስከትሉ የሚችሉትን ድርስና ተያያዥ መዘዞች በሦስተኛው ክፍል ውስጥ በመጠኑ እናያለን። ቀጥሎም፣ በግልም ይሁን በጋራ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ርምጃዎች ወይም መፍትሔዎች ለማመልከት ያስችለን ዘንድ፣ የተወሰኑ ምክረ ሐሳቦችን በጥቅምታ መልክ በክፍል አራት ውስጥ ለማንሣት እንሞክራለን። የጽሑፉ ዋና ሐሳብ የሚገባደደውም እዚያ ላይ ይኾናል ማለት ነው።

[15] በውይይታችን የጋራ መግባባት እንዲኖረን፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ድኅረ ነጻነት" የምለውን ጊዜ ምንነት ማመልከት ይገባኛል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ነጻነት" የሚለው ሐሳብ፣ በዘመን ድልድል አኳያ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች (በአንጻራዊነትም ቢኾን) ሕጋዊ ከለላ የተሰጠው "የአምልኮ ነጻነት" የተቀዳጁበትን ድኅረ 1983 ዓ.ም.ን ለማመልከት ታስቦ ነው። በርግጥም፣ የመንግሥት ለውጡን ተከትሎ በኅዳር 1987 ዓ.ም በጸደቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት የእምነትና የሃይማኖት ነጻነት (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 11፣ 27 እና 29 ይመ.) የማይገሠሡ ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ኾነው ከመደንገጋቸው በተጨማሪ፣ ቀደም ብለው ይታዩ የነበሩ ጉድለቶች ላይ አስተዳደራዊ የማስተካከያ ርምጃዎች ሲደረግ መቈየቱ ይታወቃል።

ዐምስተኛው ክፍል እንደ ዕዝል/ዐባሪ የሚታይ ሲኾን፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከምናየው ዝብርቅርቅ በላይ አሻግረን ማየት እንደሚኖርብን ለማበረታታት የቀረበ ሐሳብ ነው። ያሳለፍናቸውን ዕድሎችና ያልሠራናቸውን ተግባሮቻችንን ዞር ብለን እንድንመለከት በማሳሰብ “ቅዱስ” ቍጭትን ያጭራል። ካለንበት ኹኔታ ውስጥ እንዳንወጣ አስቸጋሪ ዳገት መስሎ ከፊታችን የተገተረ ነገር ቢኖርም እንኳ፣ ከአምላካችን ጸጋና ረድኤትን ተቀብለን እንደምናልፈው ያበሥራል፤ ያበረታታል። “ዳገቱ” ቢኖርም እንኳ ተስፋ አለንና ነው ይህ ክፍል ያስፈለገው። እርሱንም ታዲያ ስንደርስበት እናገኘዋለን።

ወደ ንባቡ ከመግባታችን አስቀድሞ ግን አንድ ማስገንዘቢያ ብጤ መጠቈም እወዳለሁ። ይኸውም፣ ይህ ጽሑፍ ርእሰ ጒዳዩን አስመልክቶ የተሰናዳ ዳጐስ ያለ ጥናታዊ ዘገባ ተደርጎ መወሰድ እንደማይኖርበት ማሳሰብ ነው። ይህ ሲባል ግን፣ ጽሑፉ በዘፈቀደ የተጠናቀረና “ጆሮ ጠገብ” እንቶ ፈንቶ የታጨቀበት ዶሴ ነው ማለት አይደለም። በተከታዮቹ ጥቂት ገጾች የቀረበው ይህ ሰነድ በስሚ ስሚና በአሉባልታ ላይ ተመሥርቶ በቢሮ ጠረጴዛ ላይ “የተወጠወጠ” ግምታዊ ዘገባ አለመኾኑን መግለጽ ተገቢ ይመስለኛል።

ይልቅስ፣ መሠረታዊ ማጠንጠኛውን ሳይለቅ ወጋዊ (*Formal*) እና ኢወጋዊ (*Informal*) በኾነ መልኩ በጽሑፉ አቅራቢ የተደረጉ ጥናቶችን በመንተራስ፣ መጠይቆችን በመበተንና ሐሳቦችን በማሰባሰብ፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱና ድጋፍ ሰጪ ተጓዳኝ ድርጅቶች ውስጥ የሚያገለግሉ “ለመሬት የከበዱ” ወገኖችን ቃለ ምልልስ[16] በመቀበል፣ እንዲሁም እንደ አንድ ክርስቲያንና አገልጋይ ጸሐፊው በራሱ የታዘባቸውንና ያስተዋላቸውን ጒዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በተጨማሪም፣ ተዛማጅ በኾኑ ሐሳቦች ላይ ያነበባቸውን ቁም ነገሮችና የመረመራቸውን ቀዳሚ የጥናት ሰነዶችና ያልተሰሙ ድምፆችን

[16] ይህን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ፣ በተለያዩ የወንጌላውያን ክርስትና ቤተ እምነቶች የሚያገለግሉ መጋቢዎችን፣ ዋና ጸሐፊዎችን፣ መምህራንና ወንጌላውያንንና ምእመናንን አነጋግሬአለሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የሚያገለግሉ የነገረ መለኮት መምህራንን እና የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችንም አካትቼአለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፣ በኢወጋዊ ውይይቴ ወቅት ተጓዳኝ ክርስቲያናዊ ድርጅቶችን የሚያስተባብሩ ወገኖችን ስፍራ ለመስጠት ሞክሬአለሁና በርእሰ ጒዳዩ ላይ ያላቸውን ምልከታ አጋርተውኛል።





በማገናዘብ የደረሰባቸውን ግኝቶችና ድምዳሜዎች በጥንቃቄ (ዐልፎ ተርፎም በፍርሀት) የሚያቀርብበት ነው። በሌላ በኩል ጥሪም ነው፤ ኾኖም ዐዲስ ጥሪ አይደለም፤ ሰሚ ያላገኙ ተመሳሳይ ጥሪዎችን ደጋሚ እንጂ።

ስለኾነም፣ ይህ ጽሑፍ በርእሰ ጒዳዩ አንጻር ያለንበትን ኹኔታ በማሳየት የሚያነቁ፣ ቀደም ብለን ለነቃንም ተጨማሪ ጒትጐታን በማቅረብ የሚሞግቱ ሐሳቦችን በመወርወር ለውይይት፣ ለጸሎትና የማስተካከያ ርምጃ ለመውሰድ አንዳች እገዛ ካበረከተ፣ ዓላማውን ተወጥቷል ብዬ እገምታለሁ።

በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ ማንንም ሰው ለማስከፋት ታቅዶ የተጻፈ ነገር የለም። በተለየ መንገድ ማንንም ለማስደሰትም አይቋምጥም። አስፈላጊ በኾነበት ቦታ የአንዳንድ ሰዎች ስም ተጠቅሶ ቢገኝ እንኳ፣ ለማስረጃነት የቀረበ ከመኾን አይዘልልም። የምንገዛለት እውነት እስካለ ድረስ ለማረምና ለመታረም መዘጋጀት ይኖርብናል። ምክንያቱም፣ *“ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልምና”* (2ቆሮ. 13፥8)።

ዐልፎ ዐልፎ ጠንከር ያለ ድምፀት ያላቸው ገጾች ይኖራሉ። አስፈላጊ ይመስሉኛል። አሁን ካለንበት አርምሞ (ዝምታ) አንጻር ከዚህም የጠነከረ ቀስቃሽ “ብራቅ” ሳያስፈልገን ይቀራልን? ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ ለደረሰውና *እውነት ማለት የኔ ልጅ* የሚል ርእስ ለሰጠው የግጥም ስብስቡ ብርሃኑ ገበየሁ “እንደ መግቢያ” ሲጽፍ ካነሣቸው ሐሳቦች መኻል እንዲህ የሚለውን ልዋስ ይኾን? “... እኮ ለምን? ብሎ መጠየቅ ባልተለመደበት፤ ቸልታ፣ ግዴለሽነትና ዝንጋኤ በነገሠበት የድንቁርና ቤት ... ከብራቅ የፈጠኑ፣ ከብራቅ የገነኑ ድምፆች ... ከእንቅልፍ ያነቃሉ። አንዳንዱም “በስመ አብ” ብሎ፣ ከትውልድ ወደ ወረሰው የእንቅልፍ ታሪኩ ሊመለስ ይችላል። ግን መንቃት እስከ ፈለገ ድረስ ለእያንዳንዱ የዘመኑ ደወል — ብራቅ — ብርሃን ... አሉለት።”[17] ይላል።

[17] በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)፣ *እውነት ማለት የእኔ ልጅ፣ ሦስተኛ ዕትም* (ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተጠቀሰም፣ 2006 ዓ.ም.) 3።

አዎ፣ ጓዳ ጓዳውን እየተብሰለሰሉ በዝምታ ከመትከን አንገብጋቢ በኾኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ በግልጽ መነጋገሩ እንደሚበጅ ይታመናል። ደግሞም እኮ፣ በተነሡት ሐሳቦች ላይ ያለብን የተጠያቂነት ደረጃ ይለያይ እንደ ኾነ ነው እንጂ፣ “አይመለከተኝም” የሚል ሰው ይኖራል ተብሎ አይገመትም።

ይልቅስ ጽሑፉ በሚያጭረው የያገባኛል ስሜት ዐጋዥነት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን አሳሳቢ ዐውድ በመገንዘብ ፊታችንን ወደ ልዑል እግዚአብሔር እንድንመልስ፣ እንዲሁም ለቀናውና ለጸናው የቅዱሳት መጻሕፍት እውነትና ለድርድር ለማናቀርባቸው ክርስቲያናዊ አስተምህሮና የውርስ አሻራ ጥብ’ቅነት[18] “ደረታችንን የምንሰጥ” እንኾን ዘንድ የጸሐፊው ጸሎት ነው። በተነካ ጊዜ የማንቈጭለት እውነት የኛ ኾኗል ማለትስ ይቻላል እንዴ?

ይህ ሲባል ደግሞ በአስተምህሮ አክራሪነት ካባ ሥር ብቻ ተጠልለን ፍቅርና ርኅራኄ በጐደለው መንፈስ ኅብረትን የምንንድ ኾነን መገኘት ስለማይኖርብን እግዚአብሔር እንዲያግዘንና ጥበብን እንዲያበዛልንና እውነትን በፍቅር ለመያዝ አምላካችን እንዲያስችለን ጸሐፊው ይመኛል።

*“እግዚአብሔር ሆይ፥ መድኀኒትህን እጠብቃለሁ”* (ዘፍ. 49፥18)።

[18] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ ዐልፎ ዐልፎ፣ በአነባበብ መላላትና መጥበቅ ምክንያት የትርጕም ልዩነትና የአነባብ መደነቃቀፍን ለማስወገድ መጥበቅ ባለበት ቦታ/ሆሄ ዐናት ላይ «’» ይህን ጭረት/ምልክት ተጠቅሜአለሁ። በርግጥ ብዙውን ጊዜ ዐውዱ ይመራናል።



# ክፍል አንድ

# የእምነት ዐደራ፣ ክርስቲያናዊ አስተምህሮና የዘመናችን ገጽታው

# ክፍል

## 1. የእምነት ዐደራ፣ ክርስቲያናዊ አስተምህሮና የዘመናችን ገጽታው

ጽሑፉ የሚያተኩረው ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዐመታት በመታየት ላይ ባሉ አስተምህሯዊ ችግሮች ላይ እንደሚኾን አስቀድሞ ተገልጿል። ችግሮቹን ከማየታችን በፊት ግን የእምነት ዐደራን በአግባቡ ማስተላለፍን፣ የክርስቲያናዊ አስተምህሮን ምንነትና አስፈላጊነት፣ በመጠኑም ቢኾን፣ ጠቈም እናደርጋለን። እንዲሁም፣ የአስተምህሮ ችግሮች በታሪክ ውስጥ የነበራቸውን ከሥተት ለማጤን እንዲረዳን በማሰብ፣ ለምሳሌ ያህል፣ ከዐዲስ ኪዳኗ የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን በጨረፍታ እንመለከታለን። ይህን ማድረግ የሚያስፈልገን እንደ ችግር ያነሣናቸውን ነገሮች ለማጤን የሚያስችለን አጠቃላይ ማዕቀፍ (*frame*) ሊኖረን ስለሚገባ ነው። በመኾኑም የእምነት ዐደራን የማስተላለፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶችን በማየት እንጀምራለን።

## 1.1 የእምነት ዐደራን የማስተላለፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

*“እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ”* (2ጢሞ. 2፥2)።

ትውልድ እንደ ጅረት ነው፤ አንዱ ወደ ሌላው ይፈስሳል። ምንጩ ንጹሕ ከኾነ ወንዙም እንደዚያው የመኾኑ ዕድሉ ሰፊ ነው። ምንጩን በድፍርስ በክሎ ከወንዙ ንጹሑን ለመጠጣት መሞከር ተላላነት ነው። ትውልድ እንደ ሰንሰለት ነው። እርስ በርሱ መቈላለፉ ብቻ ሳይኾን አንዱ የጀመረው በጎም ኾነ ክፉ ነገር ወደ ተከታዩ ያደርሳል። አንድ ትውልድ ብቻውን ሁሉን ሊያጠናቅቅ አይችልም ይኾናል። አንዱ የጀመረውን ሌላው እየተረከበ፣ ከቀዳሚው ስሕተት ተከታዩ እየተማረና እያስተካከለ ይቀጥላል።

የአንድ ሰንሰለት ጥንካሬው ከቀለበቶቹ የደካማዋን ያህል ነውና፣ “አባት ያቈየውን ልጅ እንዳያፈርሰው” የሰንሰለቱን ዘለበቶች ሁሉ ማጥበቅ ያሻናል። የያዝነው እምነት እኛ የጀመርነው ሳይኾን በዐደራ የተቀበልነው መኾኑ ተወስቷል። የተቀበልነው እምነት ደግሞ ጤናማ አስተምህሮ የነበረው ነው። የተረከብነው ጤናማውን ትምህርት ከኾነ፣ ሳናበላሸው ለማስተላለፍ በእምነት ዐርበኞች መሥመር ላይ በምስክሮች ተከብበን ቆመናል (2ጢሞ. 2፥2፤ 4፥7-8፤ ዕብ. 12፥1-3)።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንደምናነብበው የእምነት መወራረስና እግዚአብሔርን ማወቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ቅዱሳን ሲጸልዩ ኖረዋል። ኀላፊነትን የሚረከብ ተተኪ እግዚአብሔር እንዲያስነሣላቸውም ሲናፍቁ ማየት የተለመደ ነው። የተወሰኑ ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል። አብርሃም የወራሽ ያለህ ጥያቄ ነበረውና እግዚአብሔር በተገለጠለት ጊዜ ጩኸቱን አሰምቷል (ዘፍ. 15፥1-4)። ሙሴ በመሪባ ውሃ “እግዚአብሔርን ባለመቀደሱ” ጌታ





ስላዘነበትና ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደማይገባ ስለ ወሰነበት፣ በታላቅ ናፍቆት ተተኪ መሪ ለማግኘት እንደ ጸለየ እናነባለን። ስለ ሙሴ ናፍቆት ቅዱስ ቃሉ ልብ በሚነካ መንገድ እንዲህ ይላል፤

> *ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- የእግዚአብሔር ማኅበር እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይኾን፥ በፊታቸው የሚወጣውን በፊታቸውም የሚገባውን የሚያስወጣቸውንም የሚያስገባቸውንም ሰው የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአ ብሔር በማኅበሩ ላይ ይሹመው* (ዘኍ. 27፥15-16)።

ከዐዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ሐሳቦችን መጥቀስ ይቻላል፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደ ተተኪ ማዘጋጀቱ ሳያንሰው፣ እሱ ራሱ ቀጣይ ባላደራዎችን እንዲያዘጋጅ መክሮታል (2ጢሞ. 2፥2)። በተከላቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሽማግሌዎችን (ተተኪ መሪዎችን) ማዘጋጀቱ ሳያንስ፣ የእግዚአብሔርን መንጋ በጥንቃቄ እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃቸው ነበር። ለምሳሌ፣ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከሰበሰበ በኋላ ያስተላለፈውን ማሳሰቢያ በሐዋርያት ሥራ 20፥28-30 ከተጻፈው ክፍል መመልከት እንችላለን፤

> *በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ ዐውቃለሁ።*

ባለዐደራነት ትልቅ ኀላፊነት አለበት። ጳውሎስም የሚለው ይህንን ነው፤ የተረከቡትን የጌታ መንጋ መንከባከብ፣ መጠበቅና በተራው ደግሞ ለታማኝ ባለዐደራ ማስተላለፍ ችላ የማይሉት ሰማያዊ ተልእኮ ነው። ይህ ኀላፊነት መነሻ የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ጥልቅ መሻት ነው። ከዚህ አኳያ እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል?

እግዚአብሔር በትውልዶች መካከል የእምነት መወራረስ እንዲኖር ይፈልጋል። በቀዳሚዎች ዘንድ የነበረ እግዚአብሔርን የመፈለግ፣ የመፍራት፣ የመከተልና የማገልገል ኹኔታ ሳይደበዝዝ ወደ ተከታዩ ትውልድ መተላለፉ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው (ዘዳ. 6፥4 ይመ.)። በኢያሱ አገልግሎት ጊዜ እግዚአብሔር ዮርዳኖስን ከፍሎ ሕዝቡን የማሻገሩ መታሰቢያ ይኾን ዘንድ በዮርዳኖስ መኻል የተተከሉት ሐውልቶች አገልግሎት፣ ቀጣዩ ትውልድ ምንነታቸውን በጠየቀ ጊዜ፣ ቀደም ብሎ አምላካቸው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥና በቀደመው ትውልድ ዘመን ያደረገውን እንዲያስተውሉበት ታስቦ የተደረገ አልነበረምን (ኢያ. 4፥6-7)?

እግዚአብሔር ከትውልድ ወደ ትውልድ ይታወቅ ዘንድ ይፈልጋል። ይህን ለማሳካት ደግሞ፣ ደካማውን ሰው በራሱ ጸጋ “ታማኝ አድርጎ የሚቈጥረው” (1ጢሞ. 1፥12) አምላክ በሚሰጠው ኀይልና ጥበብ መጠን (ኤፌ. 3፥20) የእምነት ዐደራን በታማኝነት መጠበቅ ይገባል። ተራችን ሲያበቃም ዐደራውን ለሌሎች የታመኑ ሰዎች ማስተላለፍ አለብን (ሉቃ. 16፥10፤ 1ቆሮ. 4፥2፤ ቈላ. 1፥7)። ይህ እውን እንዲኾን ታዲያ በማኅበሩ ውስጥ የምንሠራው ብዙ ተግባር ይኖራል።

አንዳንድ ወገኖች የምእመናን ቍጥር በመበራከቱና የአብያተ ክርስቲያናትም ተቋማዊ ጥንካሬ እየተሻሻለ በመሄድ ላይ በመኾኑ፣ ምንም ችግር ያልተፈጠረ ያህል፣ ሲጽናኑ ታይተዋል። ነገር ግን በተቋማዊ አደረጃጀትና ዐዳዲስ ቦታዎችን ለመድረስ በታቀደ ዐላማ ላይ ብቻ ከተገደበው የስብከተ ወንጌል ጥረታችን በተጓዳኝ ውስጣዊ ተሐድሶና መነቃቃትም ላይ ይበልጥ ማተኰር ይገባናል። ይህ ካልኾነ ግን አስከፊው ውጤት ልፋታችንን መና ሊያስቀረው ይችላል። የስብከተ ወንጌል መልእክተኛነት እና የሥነ ሰብ ጥናት ፕሮፌሰሩ ፖል ጂ. ሂበርት እንደሚሉት፤

> የአንዲት ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል መልእክተኛነት ራእይ ዐዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል ብቻ ሳይኾን ቀዳሚዎቹ ላይ ውስጣዊ ተሐድሶ በማምጣት ላይ ጭምር ማተኰር አለበት። የመጀመሪያው ዓላማ ያለሁለተኛው የተለፋበት እንደ ኾነ፣ የማታ





> ማታ የሞቱና በመሞት ላይ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በሞሏቸው ቦታዎች ወደ መጥለቅለቅ ያደርሳል። ዐዳዲስ ማኅበራን ምእመናን መወለዳቸው ብቻ በመንፈስ ንቁና ሕያው ኾነው ለመቈየታቸው ዋስትና አይኾንም።[19]

ዋስትናው “መትከል” ብቻ ሳይኾን በእግዚአብሔር ጸጋ ተደግፎ “ማጠጣት” ላይ መረባረብን ያካትታል ማለት ነው፤ ውስጣዊ ተሐድሶን ይጠይቃል። ይህ ዐደራ ቀላል አይደለም (ሉቃ. 12፥42፤ 1ቆሮ. 3፥6-10)፤ ቸላም አንለውም።

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ታሪክም እንደሚመሰክርልን ዐደራው በተዘነጋበት ጊዜና ቦታ ሁሉ አሳዛኝ ውጤት ተከሥቷል። የመጪው ዘመን ዕጣ በዛሬው ባለዐደራ እጅ ውስጥ መኖሩ አያጠያይቅም። ዐደራው ደግሞ ዋጋ የሚያስከፍል ነው፤ የሕይወት መስዋዕትነትን ጭምር። እኛም፣ “ወዝን ሳይኾን ደምን የሚጠይቅ መሥዋዕትነት የመከፈልን ውርስ ባለመከተላችን … ኀሊናችንን ካልጋረድን፣ አሊያም ከተደጋጋሚ ዝምታ የተነሣ መንፈሳችንን ካላደነዘዝነው በቀር የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ገጽታ ከወዲሁ ስናይ አስደንጋጭ ብርክ ውስጥ እንደ ወደቀ ሰው መንቀጥቀጣችን አይቀርም።”[20]

ከዚህ ድንጋጤ በመላቀቅ እውነትን የሚወርሰው ትውልድ በጸና መሠረት ላይ ተደላድሎ እንዲቆም የክርስትና እምነት ሳይበረዝና ሳይከለስ ሊተላለፍ ይገባዋል። ይህ ሊሳካ የሚችለው እምነቱ ከትክክለኛ አስተምህሮው ሳይነጠል የተገኘ ከኾነ ብቻ ነው። የአስተምህሮ አስፈላጊነቱም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ከቀዳሚዎቹ የተቀበልነውን የእምነት ዐደራ በታማኝነት ጠብቀን ለሌሎች ባለዐደራዎች ለማስረከብ የምንበቃው፣ እምነታችን ከአስተምህሮዎቹ ጋር በጥብቅ የተጋመደ መኾኑን ከተገነዘብን ነው።

---

[19] Paul G. Hiebert, *Anthropological Reflections on Missiological Issues* (Grand Rapids: Baker, 1994) 159.

[20] ፍቅረየሱስ ሁንዴሳ፣ *ደቀ መዝሙር ወይስ ደቂቀ መዝሙር* (ያልታተመ ጽሑፍ፣ 2005 ዓ.ም.) 5-6።

## 1.2 *የክርስቲያናዊ እምነትና አስተምህሮ ቍርኝት፣ ምንነትና አስፈላጊነት*

ክርእስ ጉዳያችን አኳያ ሊነሡ የሚችሉ በርካታ ጥያቄዎች መኖራቸው እሙን ነው። እምነትና አስተምህሮን ምን አገናኛቸው? ከነአካቴው፣ ትምህርት (ዶክትሪን) ለምን ያስፈልገናል? ክርስትና ያለ አስተምህሮ ሊኖር አይችልም እንዴ? ክርስቲያናዊ አስተምህሮ የተለየ ችግር ሊገጥመው የሚችለውስ ለምንድነው? በእኛስ ዘመን ምን ዓይነት ተግዳሮቶች ናቸው የገጠሙት? ጥያቄዎቹ ትክክለኛና መነሣትም ያለባቸው ናቸው።

ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ከመሞከራችን አስቀድሞ ግን “ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ስንል ምን ማለታችን ነው?” የተሰኘውን ሐሳብ በመጠኑ ማጤን ያስፈልጋል። በብዙዎች ዘንድ አስተምህሮን ለመግለጥ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ የዋለው “ዶክትሪን” የተሰኘ የእንግሊዝኛ ቃል ምልስ-ፍች (*transliteration*) ነው። *ዶክትሪን* እንደየዐውዱና ቤተ እምነታዊ አፈታቱ ልዩነት ቢኖረውም እንኳ፣ “ዶግማ”፣ “ቀኖና” ወይም በቀላሉ “ትምህርት” ማለት ይኾናል።

*ዶክትሪንን*/ትምህርትን በሚመለከት በዐጭሩ ብያኔ ለመስጠት እንሞክር። “መጽሐፍ ቅዱስ እናምነውና እንኖርበት ዘንድ የሰጠን መለኮታዊ ትምህርት” ነው ብንል ያስሄዳል። የስልታዊ ነገረ መለኮት ምሁሩና ጸሐፊው ዌይን ግሩደም ክርስቲያናዊ “*ዶክትሪን* ማለት ስለ አንድ ርእሰ ጉዳይ ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚያስተምረን ነገር ነው”[21] ይላሉ። ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ከቅዱሱ መንፈስ በቅዱስ መጽሐፍ በኩል የተሰጠን ሰማያዊ ትምህርት ነውና እንጠነቀቅለታለን። በዚህም መሠረት አስተምህሮ እውነትን ማስተላለፍንና ሊተላለፍ የሚገባውን እውነት ራሱን በአንድነት አጠቃልሎ ይይዛል።

---

[21] Wayne Grudem, *Systematic Theology: an Introduction to Biblical Doctrine* (Leisester: IVP, 1994) 25.





አንድን ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በአስተምህሮው እንለየዋለን። ጌታ ኢየሱስም በአስተምህሮው ተለይቶ ይታወቅ ነበር። “*ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤ እንደ ጻፎቻቸው ሳይኾን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና* ” (ማቴ. 7፥28)። ሕዝቡ ኢየሱስ ከሌሎች ቀደምት የአይሁድ መምህራን የተለየ መኾኑን ያረጋገጡበት አንዱ መንገድ በትምህርቱ ይዘትና በማስተማር ኹኔታው ነበር ማለት ይቻላል።

የ“ታላቁ ተልእኮ” ዐቢይ ትእዛዝና ግብ አማኞችን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ግን ይህ ተልእኮ በደፈናው ሰው እያሰባሰብን የምናሳካው ፕሮጀክት አይደለም። ዋጋ የሚያስከፍሉ ተግባራትን ማከናወን ይጠይቃል። ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ሂደት ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ “ያዘዘውን ሁሉ” ማስተማር ከተግባራቱ አንዱ እንደ ኾነ በግልጽ ተጠቅሷል።

> *ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።* (ማቴ. 28፥18-20 *አጽንዖት* የተጨመረ)።

ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው የታላቁ ተልእኮ ዐቢይ ግብ ግልጽ ነው። እሱም ከወገንና ቋንቋዎች ሁሉ መካከል የሚድኑትን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የማድረግ ዓላማ ነው። ደቀ መዛሙርት በማድረግ ሂደት ውስጥ ታዲያ *ማስተማር* በአማራጭነት የቀረበ ነገር አይደለም። ትምህርት ቡተለይ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በጥምረትና በመናበብ የሚከናወን ከኾነ ሕይወት ያላት ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች። በቃልና በሥራ የበረቱ እውነተኛ ደቀ መዛሙርትም ታፈራለች። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትምህርት ዋና ተግባር ነበር። የሚሰጠውም ለተወሰኑ ወገኖች ብቻ ሳይኾን ለምእመናን በሙሉ ነበር።

ሐዋርያቱና የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በትምህርታቸው ተለይተው ይታወቁ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በኢየሩሳሌም የነበሩት የመጀመሪያዎቹ ምእመናን *"በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር"* (ሐዋ. 2፥42)። እንግዲህ በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት የተመሠረተው (የተጠቀሱትን ሌሎቹን ቍልፍ ነገሮች ሳንዘነጋ) *"__በሐዋርያት ትምህርት__"*ላይ ነበር ማለት ነው። ይህም ማለት ኢየሱስ ለሐዋርያቱ "ያዘዝኋችሁን ሁሉ እያስተማራችሁ ደቀመዛሙርት አድርጉ" በማለት የሰጣቸው ትእዛዝ በተግባር ላይ ውሎ ይታይ ነበር ማለት ነው። ከጌታ በተሰጣቸው ጥሪ፣ ተልእኮና ሥልጣን መሠረት ሐዋርያቱ የክርስትናን ቍልፍ እውነቶች ለአብያተ ክርስቲያናቱ በሙሉ ያስተምሩ ነበር።

ከዚህ የተነሣ፣ እኒህ አገልጋዮች "መሠረት ጣይ" ሐዋርያት ሊባሉ ችለዋል። ቅዱስ ጳውሎስ *"በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው"* (ኤፌ. 2፥20) የሚለው ለዚህ ነው። የሐዋርያቱ "መሠረትነት" ከማንነታቸው የተገኘ ሳይኾን፣ በተገለጠላቸውና ባስተላለፉት ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የዐዲስ ኪዳን ምእመናን በዚህ ትምህርት የማመንና የመኖር ኀላፊነት ነበረባቸው (1ቆሮ. 11፥2፤ ቈላ. 1፥23፤ 2ጢሞ. 3፥14፤ 2ጴጥ. 3፥2)።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በእውነተኛው ትምህርት የመኖራቸውን ያህል፣ ከሐሰተኛ የሰውና የክፉ መናፍስት ትምህርት እንዲጠበቁም ጠንካራ ማስጠንቀቂያ እንደ ተሰጣቸው ደግመን ደጋግመን እናነባለን (ለምሳሌ፡- ማቴ. 15፥9፤ 16፥12፤ ቈላ. 2፥18፤ 1ጢሞ. 1፥4 ይመ.)። ማስጠንቀቂያው ያስፈለገበት ምክንያት ግልጽ ነው። *"በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ"* (1ጢሞ. 4፥1-2) የሚለው ቃል ስለሚፈጸም ነው።

ይህ "ኋለኞች ዘመናት" የተሰኘ ወቅት፣ በአንድ ቦታና በኾነ ውሱን ዓመት የሚከሠት ነገር ላይ የተንጠለጠለ ሳይኾን፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊተኛ





መገለጥ እና በዳግመኛ ምጽአቱ መካከል ያለውን ጊዜ በሙሉ የሚሸፍን ነው። ስለዚህም ማስጠንቀቂያው (የዛሬዎቹን እኛን ጨምሮ) በየትም ቦታና በየትኛውም ዘመን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ይመለከታታል ማለት ነው። ጳውሎስ መልእክቱን በጻፈበት ዘመን የነበረችው ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ያለች እንደ ነበረ ሁሉ፣ የዛሬዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያንም በዚሁ ሥፍረ ዘመን መጨረሻ ክፍል ውስጥ ትኖራለች። ስለዚህ ማስጠንቀቂያው እርሷንም በቀጥታ ይመለከታታል፤ ማለት ይመለከተናል።

ሌላው ጥያቄ፣ "በርግጥ አስተምህሮ የግድ ያሻናልን ወይ?" የሚለውን ሐሳብ ይነካካል። መልሱ ዐጭርና ግልጽ ነው። ይህ ምን ክርክር ያሻዋል! ያለ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ምን ልትኾን እንደምትችል ማሰቡ በራሱ ይዘገንናል፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አስፈላጊ ብቻ ሳይኾን እጅግ ወሳኝ ነው። ክርስቲያናዊ እምነትና ምግባር በክርስቲያናዊ አስተምህሮ/*ዶክትሪን* ላይ የተመሠረተ ነው። ጤናማ ነገረ መለኮት ጤናማ የኑሮ ጠባይ ይከተለዋል፤ አክብሮተ እግዚአብሔር ያልተለየው ርቱዕ ሕይወት (*orthopraxy*) እና ርቱዕ ጥልቅ ፍቅር (*orthopathy*) ከርቱዕ እምነት (*orthodoxy*) ጋር የተቈራኙና ከእርሱም የሚመነጩ ነውና።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክታቱ አዘውትሮ ያደርግ የነበረውን ለአብነት ያህል እዚህ ሥፍራ ማየቱ ይጠቅማል። ሐዋርያው ደብዳቤዎቹን ለአብያተ ክርስቲያናት በሚጽፍበት ጊዜ፣ ምእመናን ሊኖሩበት የሚገባውን ተግባራዊ የሕይወት ተዛምዶ፣ መመሪያዎችንና ትእዛዛትን ከማስተላለፉ አስቀድሞ፣ ለእምነታቸውና ምግባራቸው መሠረት የኾነውን ነገረ መለኮታዊ ትምህርት አስቀድሞ ማቅረብን ያዘወትር ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የላከውን መልእክት ውቅር ብቻ ብንመለከት ይህን በቀላሉ ማስተዋል እንችላለን። ሐዋርያው በኋለኞቹ ሦስት የኤፌሶን መጽሐፍ ምዕራፎች (ምዕራፍ 4-6) ቅዱሳኑ ሊኖሩበት የሚገባውን የሕይወትና ምግባር መመሪያዎች ይሰጣቸዋል። ነገር ግን፣ ለእነዚህ ተዛምዷዊ መመሪያዎች መሠረት የሚኾኑት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምእራፎች ውስጥ (ምእራፍ 1-3) የቀረቡት ዐበይት ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮዎች ናቸው።

*ዶክትሪን* የክርስቲያን እምነትና ሕይወት ያለመናወጥ የሚቆምበት ዐምድ ነው፤ እንደምታውም ቀላል አይደለም። አስተምህሮን መለወጥ፣ አንድ ሰው በዚህም ዓለም ይሁን በመጪው ዓለም የሚኖውን የመጨረሻ ውጤት ይወስነዋል።[22] ሰው ሐሰትን ቢያምን ጥፋት በእጁ፣ በደጁ ነው። በዐመፃ ደስ እያላቸው የሚቀጥሉ ሰዎች በእግዚአብሔር *ሲታዉ* ሐሰትን በማመን ፍርድን በላያቸው ያከማቻሉ (2ተሰ. 2፥11-12)። ይቀጡ ዘንድ ሐሰትን እንዲያምኑ የተተዉት ሐሰትን ማመን ስለሚያጠፋ እኮ ነው! ስሕተት በሕይወት አያኖርም።

ለማንኛውም፣ ክርስቲያናዊ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ መመሥረቱ ዐቢይ ዓላማው ሲኾን በሕይወት ተተርጒሞ ሊገለጥ ይገባዋል። መሠረታዊ ይዘቱም በመላው የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ ላይ ማረፍ አለበት። የተወሰኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ነገር ሊኾን አይገባውም። ይልቅስ በሕይወት ጭምር የሚገለጥ ሊኾን ይገባዋል።

> ጳውሎስ እውነትን በሕይወት የሚተገብርና በአስተማማኝ ኹኔታ በማንኛውም ዘመን ለክርስቲያናዊ ትምህርት መጽሐፈ ቅዱሳዊ መሠረት ኾኖ የሚያገለግል ቅንጅት (እምነት፣ ተስፋና ፍቅር) አቅርቦልናል። ይሁን እንጂ፣ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ያሉት ሐሳቦች … ከጥቂት ተወዳጅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወይም ከምርጥ ስልታዊ ሥነ-መለኮት … ያለፈ ሊኾን ይገባቸዋል። ለትምህርታዊ አገልግሎት ሥልጣን ያላቸው መመሪያዎች ይኾኑ ዘንድ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ኹነኛ በኾኑ በእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ከሚገኙ ልዩ የባሕርይ አቅጣጫዎች ጋር የተዛመዱ ሊኾኑ ይገባቸዋል።[23]

[22] አንድ ሰው “ክርስቲያን መኾኔ በቂ ነው፤ እውነተኛ የክርስቲያናዊ አስተምህሮ ሐሳቦች የትኞቹም የመኾናቸው ጉዳይ አያሳስበኝም” በማለት ሊዘናጋ አይችልም። ይህን ቢያደርግ ጥፋትን በራሱ ላይ እንደ መጋበዝ ይቈጠራል። ይህን በምሳሌ አጽንዖት ለመስጠት በአንድ ወቅት ከቤተ ክርስቲያን አበው መካከል አንዱ ስለ ትምህርተ ሥላሴ የተናገረውን እንመልከት፤ “ሰው ‘ምሥጢረ ሥላሴን በአዕምሮዬ ጠቅልዬ ልወቀው’ ቢል አዕምሮውን ያጣል፤ ‘ኧረ፣ ምን አስጨነቀኝ? ትምህርቱ ጭራሽ አያሻኝም’ ቢል ደግሞ ነፍሱን ያጣል” ብሏል። (Millard J. Erickson, *Christian Theology* [Grand Rapids: Baker, 1985] 342. ይመ.) ለማለት የፈለግሁት ሐሳብ ግልጽ ይመስለኛል፤ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች አዎንታዊ ፋይዳቸው (ለምሳሌ አምነን ስንጸናባቸው ማዳናቸው) ብቻ ሳይኾን ተያያዥ አንድምታቸው (ባናምንባቸው ወይም ብንስታቸው ፍርድ ማስከተላቸው) ጠሊቅ ነው ለማለት ነው።





መጽሐፍ ቅዱሳዊ *ዶክትሪን* የእምነታችን ዋነኛ መሠረት እንጂ ወደ ጠርዝ የሚገፋ ጉዳይ አይደለም። በመኾኑም ትምህርትን በሚመለከት የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነቷ ትልቅ ነው። ለዐዲስ ልደት በሚኾን መታጠብና በመንፈስ መታደስ ዳግም ልደትን ያገኙትን ቅዱሳን በሚገባ አንጾና አሳድጎ *“ለክርስቶስ የሚኾነውን ፍጹም ሰው ማቅረብ”* (ቆላ. 1፥28) የቤተ ክርስቲያን ታላቁ ጥሪዋ መኾኑ አያጠያይቅም። ይህ እንዲሳካ ደግሞ፣ ክርስቶስን ማእከል አድርጋ “እየሰበከች፣ እያስተማረችና እየገሠጸች” (ቈላ. 1፥28) *“የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ”* (ሐዋ 20፥27) ለመንጋው ማቅረብ ይጠበቅባታል። ይህ ምክረ-መለኮት በክርስቲያናዊ አስተምህሮዋ በኩል በአግባቡ ተዘጋጅቶና በጥራት ተዋቅሮ መቅረቡ የግድ መደረግ ያለበት ነው እንጂ አማራጭ የቅንጦት ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

ጳውሎስ *“የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና ”* (1ቆሮ. 3፥9) እንዳለው፣ ክርስቲያኖችን ማነጽ የመሰለ ክቡር ጥሪ አይገኝም። የ “ሕንጻዋ” ባለቤት ጌታ እግዚአብሔር ነው። ዋጋ የከፈለባት “ሕንጻው” ነችና (ኤፌ. 5፥25-27)። ክርስቶስ መምህራንን ከሌሎች “አገልጋይ ስጦታዎች”[24] ጋር ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበት ምክንያት “መታነጿን” ዓላማው በማድረግ ነበር፤

[23] ሚናስ ብሩክ (ተርጓሚ)፣ *የአገልግሎት መሠረቶች፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ* (ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ኢትዮጵያ፣ 2000 ዓ.ም.) 37።

[24] “አገልጋይ ስጦታዎች” ያልኳቸው በክፍሉ ውስጥ ተዘርዝረው የምናገኛቸውን *“ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪያን፣ መጋቢያንና መምህራንን”* ነው፤ ሰዎቹ ራሳቸው ስጦታዎች ናቸው። የንባብ ክፍሉን በአግባቡ ካየነው፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ድል በነሣበት ክብር፣ ከ“ቢሮዎቹ” ይልቅ “አገልጋዮቹን” ለአካሉ፣ ማለትም፣ ለቤተ ክርስቲያን ስጦታ አድርጎ የመስጠቱ ሐሳብ ያመዝን ይመስለኛል።

> *እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ* (ኤፌ. 4፥11-13) ይላል።

አዎ፣ የመምህራን ኀላፊነት ትልቅ ነው። እግዚአብሔር እንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ከሚባርክባቸው በርካታ ስጦታዎች መካከል አንዱ መምህራንን በመስጠት እንደ ነበር ተጽፏል (ሐዋ. 13፥1)።

እነዚህ መምህራን በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት አስተዋጽዖ ጕልህ እንደ ነበር ታሪክም ያስታውሰናል። ፓዝሚኖ የተባለ የክርስቲያን አስተምህሮ ጸሐፊ እንዳለው፣ "በጥላቻና በድብልቅልቅ አምልኮ በተከበበው ዓለም ውስጥ ይኖር የነበረው የክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ማንነቱን ወሳኝ የኾኑት ዐበይት የእምነት መሠረቶቹ ዘመን ተሻጋሪ ኾነው እንዲቀጥሉለት መምህራኑ ትልቅ ኀላፊነት ነበረባቸው።"[25]

ጳውሎስ በአንክሮ እንደ ተናገረው በቅዱሳን ቋሚ ጉባኤዎች ውስጥ ትምህርት ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር የማይነጠል ነበር፤ *"እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጐም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን"* (1 ቆሮ. 14፥26)።

ስለኾነም፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ የተዋቀረ አስተምህሮ እንደ ነበራት የዐዲስ ኪዳን ምንባባት ነግረውናል (ሐዋ. 2፥41-43)። አጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን እምነት፣ አመራር፣ አስተዳደር፣ አምልኮና

[25] Robert W. Pazmino, *Foundational Issues in Christian Education: an Introduction in Evangelical Perespective* (Grand Rapids: Baker, 1997) 135.





ሥነ ሥርዐት የሚመራው በዚሁ ወጥ አስተምህሮ እንደ ነበርም እናነብባለን (1ቆሮ. 14፥33-40፤ 1ጢሞ. 3፥14-16)።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የሚመሩ አገልጋዮች ጤናማውን ትምህርት እንዲያስተላልፉና እንዲጠብቁ እንዲሁም ሐሰተኛ ትምህርቶችን ነቅተው እንዲከላከሉና ስሕተት ተከሥቶም ሲገኝ እንዲያስወግዱ በጽኑ ተመክረዋል (1ጢሞ. 4፥1-5፤ ገላ. 2፥1-10)። ይህም ብቻ አይደለም። ለተቀበሉት ትክክለኛ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ጸንተው እንዲቆሙ፣ በሐሰተኛ ትምህርት አንጻር በመቆም ተግተው እንዲመክቱ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ተላልፎላቸው ነበር። ለማሳያ እንዲኾነን ያህል ከይሁዳ መልእክት የተወሰኑ ቍጥሮችን ብቻ ማየት እንችላለን።

> *ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ ላምክራችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ኾነብኝ። … እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ። አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፤ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ* (ይሁዳ 3፡ 20-22) ይላል።

እውነቱ ይህ ከኾነ የክርስቲያናዊ አስተምህሮ ፋይዳ በዘመናችን እንዲህ በቀላሉ የሚታይ ነገር መኾን የለበትም። ክርስቲያናዊ አስተምህሮ የእግዚአብሔር መገለጥና ፈቃድ የመኾኑን ያህል ተገዳዳሪዎቹም በርካታ መኾናቸው መታወቅ አለበት። ታሪክም የሚነግረን ጠላት (ቢሳካለት) በጤናማው እርሻ ውስጥ እንክርዳድ በመዝራት ትምህርቱን ለመለወጥ እንደሚፈወጥ፣ ካልኾነም ደግሞ ለመበረዝ ሲጣጣር መኖሩን ነው (ማቴ. 13፥25፤28)። ይህ ለመኾኑ ደግሞ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ማስረጃ ትኾነናለች። የወንጌለ መንግሥቱን ትምህርት በማጣመም ሐሰተኛ ትምህርትና ልምምዶችን በማዛመት ያቺን የጌታ ማኅበር የተለያዩ ሐሰተኞች እንዴት እንደተፈታተኗት የዐዲስ ኪዳን ምንባባት በደንብ ዘግበውልናል።

## 1.3 የአስተምህሮ ተግዳሮቶች “ያኔ” እና “ዛሬ”

ይህ ንዑስ ርእስ የተነሣው ክርስቲያናዊ አስተምህሮን እና የገጠሙትን ችግሮች በታሪክ ማዕቀፍ ውስጥ በሰፋት ለመዳሰስ አይደለም። የአስተምህሮ መፋለሶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን ሁሉ እንደ ነበሩና (ሁልጊዜም ባይኾን እንኳን) ተገቢ ምላሽ ሲሰጣቸው እንደ ኖረ ለማስታወስ ብቻ ነው። ዘወትር በምጸት ሲባል እንደምንሰማው “የነገረ መለኮት ታሪክ በአብዛኛው ጐኑ የኑፋቄ ታሪክ ነው።”[26] በሌላ አባባል፣ በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍለ ዘመናት ውስጥ በርትዓዊው የክርስትና እምነትና በኑፋቄዎች መካከል የማያቋርጥ ትግል ሲደረግ ነው የተኖረው።

ስለኾነም፣ በአስተምህሮ አኳያ ችግር የገጠመን የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እኛ አይደለንም፤ መፍትሔ ለመፈለግ ጥረት ውስጥ የምንገኘውም እኛ ብቻ አንኾንም። ከአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዛቢያ ላይ የተነቀለ መንገድ ስለማይኖረን፣ ትርፋም ኾነ ኪሳራው ያገኘናል። ይህን አስመልክቶ ወንድም ፍቅረየሱስ ሁንዴሳ በሚገባ እንዳስተዋሉት፦

> ያለንበትን መንፈሳዊ ዝቅጠት ድንገት የወረደብን መዓትና በተለየ ኹኔታ እየተጋትን ያለነው ፍርድ አድርገን መመልከት የለብንም። በተለያየ ዘመን፣ በተለያየ ስፍራና በተለያየ መንገድ ተመሳሳይ ክሥተቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ መድረክ ላይ ተከሥተዋል። በነዚያም ዘመን ... ክፋትን ያነገሡ አካሄዶች ታይተዋል። እኛም [ከዚያ የተገነጠለ ገጽ] የሌለንና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጋር የተቈራኘን እንደ መኾናችን [መጠን] ቤተ ክርስቲያን ሊገጥማት ከሚችለው ተመሳሳይ ረመጥ ላይ ወድቀን እንገኛለን።[27]

[26] Harold O. J. Brown, *Heresies: The Image of Christ in the Mirror of Heresy and Orthodoxy from the Apostles to the Present* (New York: Doubleday, 1984) xxiii.
[27] ፍቅረየሱስ፣ *ደቀ መዝሙር* ፣ 5።





እንግዲህ በዚህ ዘመን “የወደቅንበት ረመጥና” የገጠመን ተግዳሮት ቀደምት አባቶቻችን ያለፉበት ነበር። ታሪክ የሚናገረውም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ትግል ውስጥ እየወደቀችና እየተነሣች እዚህ መድረሷን ነው። በእነዚያ ትግሎች መካከል ታዲያ የመሪዎቿ ኀላፊነት ትልቅ እንደ ነበር መዘንጋት አይገባም።

አስቀድመን እንዳየነው፣ ቅዱሳን በጤናማው የክርስትና አስተምህሮ እንዲኖሩና እንዲመሩ በቅዱሳት መጻሕፍት ታዝዘው ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪ የኾነ ሰው *“ሌሎችን ትክክል በኾነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ እንደ ተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መኾን አለበት”* (ቲቶ 1፥9 *ዐመት*) የተባለው በዚሁ ኀላፊነት ምክንያት ሲኾን ምእመናኑም እንዲነቁ ከማስጠንቀቂያ ጋር መመከራቸው አልቀረም ነበር።

> *በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፥ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ* (2ቆሮ. 11፥2-4)።

ይኹን እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚነግረን፣ የአስተምህሮ ዐደራው ሳይጠበቅ በመቅረቱ፣ ውስጣዊና ውጪያዊ ተግዳሮቶች እንደ ተጋፈጡት መዝለቁን ነው። በዓለ ኀምሳን እንደ መነሻ አድርገን ወስደን ብናይና[28] የቤተ ክርስቲያን ዘመንን ብንቈጥር፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግማሽ ምእተ ዓመት እንኳን ሳይደፍን ሐሰተኛ አስተምህሮዎችና ኑፋቄዎች እንደ አሸን መፍላታቸው ታይቷል።

[28] ቤተ ክርስቲያን መቼ እንደ ተመሠረተች በክርስቲያኖች መካከል የተለያየ አገላለጥ መኖሩን ከግምት ከማስገባት የተነሣ ነው “እንደ መነሻ ወስደን ብናይ” ያልኩት።

የሐዋርያት መልእክቶች ዋነኛ ትኩረትም በየጊዜው የተነሡትን ኑፋቄዎች፣ የአስተምህሮ ግድፈቶችና የምግባር ዝንፈቶችን ማረምና ጤናማውን አስተምህሮ ማስተላለፍ ነበር። ኑፋቄ[29] ደግሞ እንደ ጭቃ ውስጥ እሾኽ ዐደገኛና ከውስጥም ጭምር የሚፈላና እውነትን ተመሳስሎ የሚመጣ በመኾኑ ምክንያት ጉዳቱን በጣም የከፋ ያደርገዋል።

ዲ. አር. ማ’ኮኔል የተባሉ ክርስቲያን አገልጋይና ጸሐፊ፣ ከመናፍቃን ጋር በመታገል ከታወቁት ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን አበው መካከል አንዱ የኾነውን አባት ኢራኒዎስን በመጥቀስ እንደ ጻፉት፣ ኑፋቄ ብዙውን ጊዜ የሚመጣው የለየለት “ነጭ ውሸት” ተከናንቦ ሳይኾን፣ “ከእውነት ከራሱ ይልቅ የበለጠ እውነት”[30] መስሎ በመቅረብ ነው። የሐሰት ትምህርት አባት የኾነው ሰይጣን “ዐይኑን አፍጥጦና ጥርሱን አግጥጦ” እንደማይመጣ ሁሉ፣ መናፍቃን አደናጋሪዎች፣ አስመሳዮች፣ ተንኮለኞችና ራሳቸውን በመለወጥ የተካኑ ናቸው፤ ጳውሎስ እንዲህ ይገልጻቸዋል፤

[29] “ኑፋቄ” ምንጩ “ነፈቅ” የሚለው የግእዝ ቃል ሲኾን፣ እንደ አገባቡ የተለያየ ትርጕም ይኖረዋል። ቃሉ (እዚህ በተጠቀምንበት ዐውዱ) የተተረጐመ እንደኾነ፣ “አንድን ነገር ለሁለት ከፍሎ ማመን፣ በጥርጣሬና በማመንታት የተሰናከለ እምነት መያዝ” እንደ ማለት ሲኾን፣ ከዚሁ የሚወጣው “መናፍቅ” የሚሰኘው ስም ደግሞ፣ “ሃይማኖቱ ሕጹጽ የኾነ፤ ምሉዕና ፍጹም ትክክል ያይደለ” ነው። (ኪዳነ ወልድ፣ *መጽሐፈ ሰዋሰው፣* 645-646)። ነገር ግን አንድን ትምህርት ወይም እምነት በኑፋቄነት የሚያስፈርጀው ምንድነው? በሚለው ሐሳብ ላይ የተለያየ አረዳድ ሊኖር ይችላል። ይህም ቢኾን ግን፣ ከክርስትና መሠረታዊ አስተምህሮዎች መካከል አንድና ከአንድ በላይ የኾኑትን የሚክዱትን ወይም የሚለውጡትን ሰዎች እና/ወይም ተቋማት በመናፍቅነት መፈረጅ ያለና የነበረ ነው። ስለ ጉዳዩ በስፋት የመረመሩትና የጻፉት ወንድም፣ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ፣ እንዳመለከቱት “መሠረታዊ ከኾኑት የክርስትና አስተምህሮዎች አንዱን እንኳ መካድ በመናፍቅነት ለመፈረጅ በቂ ነው” ይላሉ (*ዐበይት መናፍቃን* [ዐዲስ አበባ፡- የኢቃሕቤክሥጽአ፣ 2001] 15)። በተጨማሪ ዋልተር ማርቲን *Rise of the Cults* በሚል ርእስ ካዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ ጠቅሰው አቶ ተስፋዬ እንዳስቀመጡት፣ “በዐጭሩ ኑፋቄ ማለት፣ ርቱዕ ከኾነው የክርስትና አስተምህሮ ዐበይት ትምህርቶችን የሚክድ ማለት ነው” ብለዋል። *እዚያው፣* ገጽ 14።

[30] D. R. MacConnell, *A Different Gospel* (Peabody: Hendrickson, 1988) xiv.





*እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይኾናል* (2ቆሮ. 11፥13-15)።

የኑፋቄ ትምህርት በማር የተለወሰ መርዝ እንደ ማለት ነው። ወይም በረግረግ ላይ እንደ በቀለ ለምለም ሣር አማልሎ በማስጠም ብዙ ጥፋትም የሚያደርስ ዐዘቅት ነው። ዘነብ ኢትዮጵያዊ (ደብተራ) እንኳ እንደ ታዘባቸው፣ “ጕንዳን በደረሰበት እንደሚቈነጥጥ፣ መናፍቃንም በደረሱበት ጤና የላቸውም [ጤና አይሰጡም]።” እንግዲህ፣ በጥንቷ የጌታ ቤተ ክርስቲያን መካከል ተከሥቶ የነበረው ይኸንን መሳይ ችግር ነበር።

ሐዋርያቱ የተከሏቸውን አብያተ ክርስቲያናት አደራጅተው ዕልፍ ከማለታቸው እግር በእግር ተከትለው በእግዚአብሔር ጸጋ የተተከሉትን ቅዱሳን በትምህርት ነፋስ በማፍገምገም የሚነቅሉ ቢጸ ሐሳውያን (ሐሰተኛ ወንድሞች)፣ ሐሰተኞች ሐዋርያትና የዐመፃ ደመወዝን የወደዱ ክፉ ሠራተኞች ከውስጥ ይፈለፈሉ እንደ ነበር በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ ቀርቦልናል።

መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚያስተምረን፣ ለእያንዳንዱ እውነተኛ አካል፣ አጸፋ-ሐሰት (*Counterfiet*) ነበረው። ለምሳሌ ያህል ለእውነተኛው መሲሕ፣ ሐሳዊ መሲሕ [ሐሰተኛ ክርስቶስ] (ማቴ. 24፥24)፣ ለወንድሞች፣ ቢጸ-ሐሳውያን [ውሸተኞች ወንድሞች] (2ቆሮ. 11፥26)፣ ለክርስቶስ ወንጌል፣ ሌላ ወንጌል (ገላ. 1፥6)፣ ለሐዋርያት፣ ሐሰተኛ ሐዋርያት (2ቆሮ. 11፥13፤ ራእ. 2፥2)፣ ለነቢያት፣ ሐሰተኛ ነቢያት (2ጴጥ. 2፥1)፣ ለመምህራን፣ ሐሰተኛ መምህራን (2ጴጥ. 2፥1) ነበሩ፤ ዛሬም አሉ። መነሻቸውም፣ በአብዛኛው፣ ከውስጥ መኾኑ ሲታይ “ጤና የማጣቱን” ነገር አስከፊ ያደርገዋል።

ስለዚህም ነበር ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎችን እንዲህ ሲል ያስጠነቀቀው፤

> *በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኲላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ ዐውቃለሁ* (ሐዋ. 20፥28-29)።

ይህ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ሊመጣ ያለው አስፈሪ ዘመን በታየው ሐዋርያ ነበር። የተናገረውም አልቀረ ቤተ ክርስቲያን በሐሰተኛ ትምህርቶች ትታመስ ጀመር። ውሎ አድሮ ቅይጥነት እግሩን አስገባ፤ *ኖስቲካዊ ኑፋቄም*[31] ጥንስሱ መታየት ጀመረ፤ ይሁዲያዊ እርሾ[32] በሃይማኖት ቅናት እየተጀቦነ በየቦታው

[31] ኖስቲኮች (*Gnostics*) የልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ተከታይ ሲኾኑ፣ ድነት በዕውቀት እንደሚገኝ አጽንዖት የሚሰጡ ቡድኖች ነበሩ። በተጨማሪም፣ ኑባሬያዊ ምንታዌ (*Existential Dualism*) የትምህርታቸው መገለጫ ነበር። ምንም እንኳን ኖስቲካዊነት የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተገዳዳሪ የኑፋቄ ትምህርት በመኾን የወጣው ከ2ኛው ምእት ዓመት በኋላ ቢኾንም ቅሉ፣ የዚህ ግሪካዊ፣ ዕውቀት ቀመስና የአረማዊ ብሕትውና ቅይጥ ትምህርቱ ዳር ዳርታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ መግባት የጀመረው በጳውሎስ የአገልግሎት ዘመን እንደ ነበር የቆላስይስ መልእክትን ብቻ በማየት መረዳት ይቻላል።

[32] ለምሳሌ በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የተከሰተውን ልብ ይሏል። ጳውሎስ ከሰበከው የጸጋ ወንጌል ጋር የሚፃረር ኾኖ የተገኘውና በገላትያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተዛመተ የነበረው “ሌላ ወንጌል” (ገላ. 1፥6-7) ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሚደረግ ቃል ኪዳናዊ ኅብረት ለመግባት ግዝረትን እንደ አስፈላጊ እርምጃ የሚቈጥር እንግዳ አስተሳሰብ ነበረው (ሐዋ. 15፥24፤ ገላ. 5፥2፤ 6፥12)። የገላትያ ምእመናንን “እርነት ይሰልሉ ዘንድ” ሾልከው በስውር የገቡና (ገላ. 2፥4) “የሚያናውጡ” የተባሉት አዋኪዎች (ገላ. 1፥7)፣ በዚህ ማባበል በተሞላው አስተምህሮአቸው በመጠቀም የሰሟቸውን ከጸጋው በመለየት፣ ከክርስቶስ እንዲገነጠሉ ከጫፍ አድርሰዋቸው ነበር (ገላ. 3፥1፤ 4፥19፤ 5፥2፡4)። እነዚሁ አሳቾች፣ በአሕዛብ አማኞች መካከል የራሳቸውን የሕግ ጠባቂነት ተልእኮ በማስፋፋት ላይ የነበሩ አይሁድ ክርስቲያን አስተማሪዎች ሲኾኑ፣ ሐቁ ግን ሲመረመር “ሐሰተኛ ወንድሞች” (ገላ. 2፥4) ነበሩ። ጉዳዩ ጳውሎስን ምን ያህል እንዳስደነገጠውና እንዳስቈጣው በቀላሉ ከመጽሐፉ መረዳት ይቻላል። ስለዚህም፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ ቤተ ክርስቲያን የተነሣውን መሠረታዊ ችግር ለማስወገድ የሰጠው ምላሽ ሥር ነቀል ርምጃ መውሰድ ነበር።





ሾልከው በሚገቡ አቀንቃኞቹ አማካይነት ይዛመት ነበር። ይህም ብቻ ሳይኾን አረማዊ ቅይጥነት[33] እዚህም እዚያም እየተከሠተ፣ ዐዲሱ የእምነት ማኅበረ ሰብ በዙሪያው ካለውና ተለይቶት ከወጣው ኅብረተ ሰብ የተለየ ቅዱስ ሕዝብ መኾኑ እንዳይንጸባረቅ ሊታገለው ሞከሯል። በተጨማሪም “ዐይን ያወጡ” ሰይጣናዊ[34] ልምምዶችና ሌሎችም ችግሮች ቤተ ክርስቲያንን በጽኑ ፈትነዋል።

ይሁንና ሐዋርያቱና በጊዜው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በወሰዱት ጠበቅ እና ጠለቅ ያለ አስተምህሯዊ ተጋድሎ ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት ተከላክለዋል (ለምሳሌ፡- ሐዋ. 15፥1-29፤ ቆላ. 2፥4፤ ይሁዳ 1፥3)። ጳውሎስ ስለዚህ ተጋድሎው ሲናገር፣ *“የወንጌል እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም ”* (ገላ. 2፥5) ይላል፤ በጌታ ጸጋና በኀይሉ ችሎት በበዛላቸው ጥበብ፣ ወደ ኋላ ሳያፈገፍጉ፣ ችግሮቹን በጽናት ተጋፍጠዋቸዋልና!

ይህ *መጋፈጥ (confrontation) ታዲያ የሰውን ፊት አይቶ የሚታጠፍ ዐንገት* አልነበረውም። በራሳቸው በሐዋርያቱ መካከል እንኳን ከጸናው የእምነት ትምህርት ማፈግፈግና ፍንገጣ በታየ ጊዜ የመጋፈጡ *ሥራ* ተግባራዊ መኾኑ አልቀረም። ሐዋርያው ጴጥሮስና በርናባስ አይሁድ ክርስቲያኖችን ለማስደሰት ብለው *“እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ”* በተገኙበት ወቅት፣ ጳውሎስ ጴጥሮስን ያለማመንታት *“ፊት ለፊት”* ተቃወመው፤ ምክንያቱም ጴጥሮስ *“በግልጽ ስቶ ስለ ነበር”* (ገላ. 2፥11 *ዐመት*)፣ *“ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበር”* (ገላ. 2፥11፡14)።

[33] ለምሳሌ ያህል፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጻፈውን የመጀመሪያ መልእክት ይመለከቷል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተከሠቱት ችግሮች መካከል የአንዳንዶቹ ምንጭ በዙሪያቸው ካለውና ከወጡበት ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጐታ የተዘገነ አስተሳሰብና ልምምድ ሲኾን፣ ያንን አስተሳሰብና ልምምድ ደግሞ ከዐዲሱ እምነታቸው ጋር በማስባቀል የተገኘውን ነገር ቅይጥነት (*syncretism*) ልንለው እንችላለን ነው።

[34] ለምሳሌ፡- 1ጢሞ. 4፥1-2፤ 1ቆሮ. 10፥21፤ 2ቆሮ. 11፥3፤ ያዕ. 3፥15 ይመልከቷል።

ይህ ክፍል የሚያስተምረን ነገር ጥልቅ ነው። በሐዋርያቱ መካከል እንኳ ምን ያህል መተራረም እንደ ነበረ ስንመለከት ያስቀናናል። በእነሱ መካከል እንደ *“አዕማድ መስለው”* (ገላ. 2፥9) ከሚታዩት አንዱ ጴጥሮስ ነበር። ኾኖም ሰው ነበርና ተሳሳተ፤ ወይም ሳተ። ስሕተቱም ሌሎችን ጨምሮ የሚያበላሽ በመኾኑ *“እንደ ወንጌል እውነት እንዳልሄዱ”* ታዩ። በዚህ ጊዜ ግን ጳውሎስ የእውነት ልምጩን ይዞ ከተፍ አለ፤ አረማቸው። እንግዲህ ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ችግር ቢገጥማትም እንኳ መፍትሔ ለመውሰድ አታመነታም ነበር።

የሐዋርያቱም ዘመን ካለፈ በኋላ በነበረው የቤተ ክርስቲያን አበው የአገልግሎት ዘመን በአብዛኛው የሜድትራኒያን ዓለም ውስጥ ወንጌል መሰበኩና የክርስትና መስፋፋትን ተከትሎ አሥቃቂ የሐሰት ትምህርቶች እንደ አሸን ፈልተው ነበር።[35] አብዛኛዎቹ የስሕተት ትምህርቶች የሚያነጣጥሩት ደግሞ በመሠታዊ የክርስትና እምነቶች ላይ መኾኑ ሲታይ ምን ያህል አደገኛ እንደ ነበሩ መገንዘብ ይቻላል።[36] እነርሱን ለመመልከት መሞከር “ዐባይን በጭልፋ” ስለሚኾን አንሞክረውም። በርግጥ፣ የአስተምህሮ ችግሮች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን መኖራቸውን ለማሳየት ገና ሐዋርያቱ በሕይወት እያሉ የነበረውን በምሳሌነት ተመልክተናልና በቂ ማስረጃ ይኾነናል።

ስለዚህም፣ ይህንኑ አሳሳቢ ጉዳይ በገዛ ዘመናችን ምን እንደሚመስል ወደ ማየቱ መሻገር ይሻለናል። ቀጥታ የዘመናችንን የአስተምህሮ ድብልቅልቅ ማየት ከመጀመራችን አስቀድሞ ግን፣ ችግሮቹ እንደ ጅብ ጥላ በቅለው ለማደራቸው ምክንያት የኾነውን አስተሳሰባዊ ውቅር እንቃኛለን፤ እርሱም ድኅረ ዘመናይነት (*postmodernism*) ይባላል።

---

[35] W. H. C. Frend, *The Rise of Christianity* (Philadelphia: Fortess, 1984) 305-30.

[36] ቀደምት እና ደኅርት የቤተ ክርስቲያን አበው የተነሡበትን ዘመን ብቻ ለአብነት ያህል ብንወስድና ዋነኛዎቹን ጉባኤያት (ኒቂያ፣ ቍስጥንጥንያ፣ ኤፌሶንና ኬልቄዶን) ከግምት ብናስገባ፣ የጉባኤያቱ ዐበይት ነገረ መለኮታዊ ርእሰ ጉዳዮች የነበሩት *ትምህርተ ሥላሴ፣ ነገረ ክርስቶስና ነገረ መንፈስ ቅዱስ፣* መኾናቸውን እናስተውላለን። ጉባኤያቱ ያሳለፏቸው ውሳኔዎችም በነዚሁ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተነሡ ኑፋቄዎችን መንቀስ፣ ርቱዕ የኾነውን ትምህርት ማጽናትና ስሕተቱን ማውገዝ ላይ ያተኰሩ እንደ ነበሩ ይታወቃል።





## 1.4 *ዘመናችንና የአስተሳሰብ መዋቅሩ ምን ይመስላል?*

የእኔና[37] የእናንተ ዘመን ከሚታወቅበት በርካታ መገለጫዎቹ አንዱ በሐሳብ ትርምስ መጥለቅለቁ ነው። ዘመናችንን *ድኅረ ዘመናይ* ዓለም (*Postmodern World*) ይሉታል። የ*ዘመናዩ* (*Modernism*)[38] ሐሳበ ዘመን ማግስት መኾኑ ነው። የዚህን አስተሳሰብ ፍልስፍናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ውቅር ለማሳየት ቦታውም ኹኔታውም አይበቃንም። በዐጭሩ ለማሳየት የተፈለገው የዚህ አስተሳሰባዊ ጠገግ በዘመናችን የክርስትና አስተምህሮ ላይ ማጥላቱን ብቻ ነው።

*ድኅረ ዘመናይነት* በኀልዮ፣ በነቢብ ኾነ በገቢር (በሐሳብ፣ በቃልም ኾነ በተግባር) ማእከላዊ ቢጋርና ንድፍ የሌለው የተውተፈተፈ ብትን ዓለም ነው። ላዕላይ ሥልጣን ብሎ ነገር የማያውቀው፣ የእውነትን ፍጹምነት የማይቀበል፣ አንጻራዊነትን እየዘመረ፣ ወጥና ደርዝ ያለውን ታሪክና ትውፊት የሚያድፋፋ፣ “ክፍቱን ያደረ” ቤት ነው። በዚህ ነባራዊ (ቀደምት) እና ቅቡል ሐሳቦችን በመደምሰስ ልክፍት በተጠመደ ፍልስፍናዊም ኾነ ሃይማኖታዊ ዐውድ የጋራ ማእከል የሚባል ነገር የለም፤ አንድ ጠቅላይ የታሪክ መሥመር አይታወቅም።

---

[37] ይህ ጽሑፍ፣ በተለመደው የጥናታዊ ጽሑፍ አቀራረብ ድንጋጌ መሠረት፣ የመጀመሪያ መደብ ነጠላ ቍጥር አመላካቿን ተውላጠ ስም (“እኔ”)ን “አልጠመም”። ለምን የተባለ እንደኾን፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ራሱን ከዳር ያኖረ “የደላው ታዛቢ” ሳይኾን፣ ከናንተው ጋር በርእሰ ጉዳዩ ላይ “ዐብሮ ቃታች” ኾኖ ስለተገኘ ብቻ ነው።

[38] *ዘመናይነት* (*Modernism*) በዚህ አገባቡ ጥቅም ላይ የዋለው፣ “የጊዜውና ዘመን አመጣሽ” የኾነውን ነገር ለመወከል አይደለም። የመካከለኛውን ዘመን ማክተምና የዘመነ አብርሆት/አብራሄ (*Enlightenment*) መከሠትን ተከትሎ የመጣውን የአስተሳሰብ ንጽረት ለማመልከት ነው። በቅደም ተከተላዊ አሰላለፉም ብናስቀምጠው፣ ሰው ከ*አምላካዊነት* (*Theism*) ወደ *አምላከኛነት* (*Deism*) ተንሸራቶ በመጨረሻ ወደ አምላክ የለሽ *አላማኝነት* (*Atheism*) የሰረገበት ቅይድ ዐጥሩ ነበር—*ዘመናይነት*። *ድኅረ ዘመናይነት* የተባለው ንጽረተ ዓለም እንግዲህ *ዘመናይነትን* ተከትሎ ከ20ኛው ምእት ዓመት መግቢያ ጀምሮ መንሰራፋት የጀመረ የዘመናችን የአስተሳሰብና ንጽረተ ዓለማዊ መሥመር መኾኑ ነው።

ወንድማችን አቶ ምኒልክ አስፋው "ብጥቅጥቅ ዓለም"[39] ነው በማለት እንደ ጠሩት መኾኑ ነው።

*ድኅረ ዘመናይነት* ለ*ዘመናይነት* የተሰጠ ጥብቅ የዐጸፋ ተቃውሞ ነው። እነርሱ እንደሚሉት "በ*ዘመናይነት* ዓለም ሰዎች ሰብአዊ ዐቋማቸው በአመክንዮ፣ በቍሳዊ ተጨባጭነትና በሳይንሳዊ መርሖዎች እየተሸረሸረ ተናግቶ ነበር። በሰብአዊ ተፈጥሮአችን ውስጥ ያለ ግላዊ ደመነፍስ (*Instnict*) በምርታማነት ምኞትና ከተለየዩ ዶግማዎች በሚመጡ ውሱንነቶች ተገድቧል።"[40] ስለዚህ ለነዚህ ምቾት ማጣቶች *ዘመናይነትን* ዋነኛ ተጠያቂ ነው በማለት ይከስሳሉ።

በአንጻሩ የ*ድኅረ ዘመናዩ* አመለካከት "የኔ"ስሜት፣"የኔ" ምርጫዎችና "የኔ" ደመነፍሳዊ ፈቃድ ለሚባሉት ተገቢ ቦታ ያለው እንደመኾኑ፣ የተሻለው ግላዊ የሕይወት አተያይ ነው በማለት ይሟገቱለታል። በዚህም ምክንያት የ*ድኅረ ዘመናዩ* ዓለም ትውልድ "ሰዎች ከማሰብ ይልቅ ስሜትን የሚያስቀድሙበት፣ በደመነፍስ የተነቃቃ ትውልድ"[41] ነው። በዚህ ንጽረት ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ በትምህርታቸውም ኾነ በኑሯቸው በግልጽ እንደሚታየው፣ ውሳኔያቸውንና ጠባያቸውን የሚቈጣጠሩ ማንኛውም ዐይነት "ውጪያዊ"መርሖዎችና የሥልጣን ምንጮች ምቾት አይሰጧቸውም።

ይህ *ድኅረ ዘመናይነት* የተባለ የአስተሳሰብ ደመና ባጠላበት ዓለም የእውነትን ፍጹምነት የሚያስተባብሉ ዐቋሞች እንደ አሸን ፈልተዋል። መደበኛ መለኪያ የማይሻው ትውልድ በአንጻራዊነት ሐሳብ በመጠመዱ "የታየኝና የተረዳሁት እውነቴ ነው" ካለም ሰንብቷል። ይህ ዐይነት ውኅንብር መሠረታዊ መናጋት ከፈጠረባቸው ሥፍራዎች መካከል ይበልጡ የእምነት ቤቶች መኾናቸውም

[39] ምኒልክ አስፋው፣ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር* (ዐዲስ አበባ፦አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1999 ዓ.ም.) 169-180።

[40] Ajith Fernando, *Jesus Driven Ministry* (Wheaton: Crossway, 2002) 21.

[41] Laurence W. Wood, "Telling the Old, Old Story in the Post Modern Age," The Asbury Herald, Automn, 1996, 3.





አልቀረም። ስለዚህም ይኸው የአሰላስሎና አስተሳሰብ መሳከር በክርስትና አስተምህሮ አንጻር ለተከሠቱ በርካታ እንከኖች መፈልፈል በምክንያትነት ሲነሣ የምንሰማው ኾኗል።

እንግዲህ፣ *ድኅረ ዘመናይነትና* የአስተሳሰቡ ሸክም በተጫነው ዓለም የክርስትና እምነት አስተምህሯዊ ወጥነት ምን ያህል ፈተና እንደ ተጋረጠበት ለማናችንም ግልጽ ይመስለኛል። ይህን ለማብራራት አንድ ምሳሌ እንደሚከተለው ላቅርብ።

አንድ ክርስቲያን ጸሐፊ በ*ሮጀርዝቫይል* (አሜሪካ) በምትገኝ አንዲት[42] ቤተ ክርስቲያን መግቢያ ላይ "እግዚአብሔርን ውደድ፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አፍቅር፣ ከዚያ የተረፈው *የዶክትሪን* ጕዳይ ነው" የሚል ምልክት በሰሌዳ ላይ ተሰቅሎ ማየቱን ይናገራል። ይለጥቅናም፣ "መልእክቱ እኮ ግልጽ ነው፤ 'እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ *ዶክትሪን* ግን ያን ያህል በጣም አስፈላጊ በኾኑት ተርታ አይደመርም' እንደ ማለት ነው" ሲል ጥልቅ ኀዘኑን ይገልጣል። በዚች ቤተ ክርስቲያን መግቢያ ላይ ተሰቅሎ የታየው ይህ አባባል "የበርካታ አሜሪካውያንን ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የሚናገር" ስለ መኾኑም ጸሐፊው አስተያየቱን አስፍሯል።[43]

ይህ ዐይነት የተዛባ አስተሳሰብ በእኛም አገር ክርስቲያኖች ዘንድ ስለመኖሩ የተሠራው መጠነኛ ጥናት አመላክቶኛል። አሁን፣ አሁን እየተለመዱ ከመጡት አባባሎች መካከል የሚከተሉትን አስተሳሰቦች "አልሰምታችሁ" ይኾን?

[42] መረጃውን ባገኘሁበት ምንጭ ላይ የተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያኒቱ ስም በእኛም አገር ከምትገኝ አንዲት ቤተ እምነት ጋር የስም መመሳሰል ስላለውና ምሳሌው ያልተፈለገ ትርጓሜ እንዳይሰጠው ስለፈለግሁ፣ ስያሜውን ኾነ ብዬ አውጥቼዋለሁ። በሌላ በኩል፣ በአሜሪካን አገር የምትገኝን ቤተ ክርስቲያን በምሳሌነት መጠቀሙ ያስፈለገው በርካታ አስተምህሮአዊ ነፋስ ወደኛ አገር የሚነፍሰው ከወደዚያ የመኾኑን ሐቅ ለማመላከት ነው።

[43] ስቲቭ ክሌይን የተባለ ጸሐፊ እንዳተተው። Steve Klein, via *The Bulletin of the Church of Christ at New Georgia*, August 26, 2007.

"በዶክትሪን መነታረክ ምን ይፈይዳል? ዋናው ነገር ስብከተ ወንጌልና እግዚአብሔርን ማምለክ ነው"፤

"ዶክትሪን ላይ ማክረር የሚከፋፍል ስለኾነ አጽንዖት መስጠት አያስፈልግም"፤

"በነባር አስተምህሮዎች ላይ ችክ ማለት እግዚአብሔር በተቀቡ አገልጋዮቹ በኩል የሚያመጣቸውን ዐዳዲስ መገለጦች እንዳናገኝ ይጋርድብናል"፤

"የተማሩትስ የት ደረሱ? ምን ለውጥስ አመጡ?"

"የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት 'ያልተማሩ' (ሐዋ. 4፥13) አልነበሩምን? እኛን ምን አድርጉ ትሉናላችሁ?"

"ትምህርት፣ ትምህርት የሚባለው ጣጣ የመጣው ዐዳዲስ የተነሡልንን 'ባለ ራእዮቻችንን' ለማቀጨጭ ታስቦ ነው"፤ ወዘተ.

እንግዲህ እነዚህንና እነዚህን የሚመሳስሉ ሐሳቦችን የሚናገሩ፣ እንዲሁም ለአስተምህሮና አስፈላጊነቱ ጭምር ትኩረት የሚነፍጉ ክርስቲያን ወገኖች መኖራቸውን መታዘብ ተችሏል።

በጥናቱ ወቅት ማስተዋል እንደ ተቻለው፣ ዋነኛው ትኩረት፣ "ጌታን ማምለክ" (በዝማሬ መኾኑ ነው)፣ "ጠንካራ የጸሎት ሕይወት ያለው ሰው መኾን"፣ "እግዚአብሔር በምድራችን ሲከበር ማየት"፣ "የፈውስና ተአምራት መገለጥ" አስፈላጊነት፣ "የሕንጻ ግንባታና ልማት መቀላጠፍ"፣ ኢትዮጵያን እያጋጠማት ነው ስለሚባለው ወይም በቅርብ ዓመታት ልትደርስበት እንደምትበቃ ስለተተነበየው አጠቃላይ ምጣኔ ሀብታዊ ብልጽግናና ዕድገትን በመንተራስ የእግዚአብሔር ጕብኝት ማስረጃ መኾኑን አጽንዖት መስጠትና የመሳሰሉት ዋነኛ፣ ተፈላጊና ተቀዳሚ ነገሮች መኾናቸውን በተለያየ መንገድ ተናግረዋል።





በመሠረቱ እነዚህ የተዘረዘሩት ሁሉ (ምናልባት ከመጨረሻው በቀር) ቀጥተኛ የነገረ መለኮት ችግር የሌለባቸው፣ ክርስቲያናዊ አስተሳሰቦች ስለመኾናቸውና እንደ እውነተኛ ምእመናንም ልንለማመዳቸው እንደሚገባ ጸሐፊው ቅንጣት ጥርጥር የለውም። ነገር ግን የእነዚህ ተጠቃሾች መኖር ወይም አስፈላጊነት አስተምህሮን ችላ ለማለት የዋለ እንደ ኾነ ነው ቀውስ ተፈጠረ የሚባለው።

ዐልፎ ዐልፎ በተጐበኙ አጥቢያዎች ለማስተዋል እንደ ተቻለው፣ በአብዛኞቹ ማኅበራት ውስጥ ተመሳሳይ ጒድለት ይታያል። ይኸውም፣ በዕለተ እሑድ በሚካሄደው "የአምልኮ መርሐ ግብርና" በ"ፈውስ መርሐ ግብር" ወቅት የጠጠር መጣያ የማይገኝባቸው የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ "በትምህርት መርሐ ግብራቸው" ጊዜ "የተወረረ ከተማ" መምሰላቸው ተረጋግጧል። "ምዕመኑ ትምህርት ስለማይወድ ነው" የሚባለውን የተለመደ ወቀሳ ታክከን ወደ አንድ አቅጣጫ ያዘመመ ድምዳሜ ላይ መድረስ አግባብ አይኮንም። ምክንያቱም ልናያቸው በቻልነውና በሳልና ጠንካራ ተከታታይ ትምህርት ሲሰጥባቸው በነበሩ ጥቂት አጥቢያዎች ውስጥ ቦታ ለማግኘት ሲጋፉ የነበሩ ምእመናንን መመልከት ተችሏል።

ለማንኛውም፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን በርእሰ ጒዳያችን አኳያ የገባችበትን ውጥንቅጥ ለማሳየት በርካታ አስረጂዎችን ለማቅረብ ይቻል ነበር። ኾኖም ግን ይህ የዚህ መጽሐፍ የቤት ሥራ ባለመኾኑ አልተገባበትም። እዚህ ቦታ የአስተምህሮ ችግሮቹንና ተያያዥ ጒዳዮችን ብቻ በጥቂቱ ከነካካን ይበቃናል። እናም፣ እነርሱን ወደ ማየቱ መሻገር አግባብ ይኾናል።

## ክፍል ኹለት

# የክርስቲያናዊ አስተምህሮ ችግሮች

## ቅኝት

## በድጎረ "ነጻነት"

# ኹለት

## 2. የአስተምህሮ ችግሮች ቅኝት በድኅረ "ነጻነት"

ይህ ክፍል የጥናታችን የመጀመሪያ ዐቢይ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ወንጌላዊው ክርስትና ከአስተምህሮ አኳያ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በመዳሰስ ችግሮችን የምንነቅስበት ይኾናል። ችግሮች ለመሻሻል፣ ለዕድገና ለውጥ የሚከፈሉ ዋጋዎች ናቸው። "ችግሮችን መረዳት የመፍትሔው ግማሽ መንገድ ነው" ይባላልና ችግሮቻችንን በትክክል ከለየናቸው አትራፊዎች እንኾናለን። ሰው ችግሩን ካላወቀው እንዴት መፍትሔ ሊፈልግ ይችላል?

ርግጥ ሰው ሁሉ ችግሩ ሲነገረው ይወዳል ማለት አይቻልም። ምናልባት አንዳንድ ወገኖች "ስንት ሊወራ የሚገባው መልካም ነገር እያለ ችግር መዘርዘሩ ምን ይጠቅማል" በማለት ሲናገሩ ልንሰማ እንችላለን። በርግጥም ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የታዩና የተከናወኑ እግዚአብሔርን ለማመስገን ምክንያት የሚኾኑ ብዙ ነገሮች መኖራቸውን ማንም አያስተባብልም። ሊጠቀሱ የሚችሉና የሚገባቸውም የነጻነት ማግስት በረከቶች ቢኖሩም እንኳ፣ መነሻችን እነሱን መዘከር ባለመኾኑ አልተነሡም ይኾናል እንጂ ሳይኖሩ

ቀርተው አይደለም። ለነገሩማ መልካሞቹ ያሉን ከኾነ ማን ይወስድብናል? መጥፎው ካልታረመ አሉን የምንላቸው መልካም ነገሮችን ያበላሽብን የለምን?

ይልቅስ ተከማቹ በምንላቸው ፍሬዎች ላይ ብቻ አተኵረን ከመቦረቅ ይልቅ፣ የከበቡንን ችግሮች ለቅሞ በማውጣት ለመታረም መትጋቱ የተሻለ ይኾናል። ራሳችንን ለማታለል ካልሞከርን በቀር አሳሳቢ ችግሮች መኖራቸው ግልጽ ነው። ስከን ብለን ካሰብነው፣ አንድ አጥኚ እንደ ገለጹት፣ "በቍጥር ጥቂት ያልኾን መንገደኞች ተፈጥሯዊ ሂደቷን ተከትላ ከምትጓዝ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አፈንግጠን ልባችን ወደ ተሳበበት ኢ-መንፈሳዊ አቅጣጫ እያቀናንና መንፈሳዊውን ገበታ እያመሰን መኾኑን ማንም ሊነግረን አይገባም።"[44]

ስለዚህ ከአስተምህሯዊ ቀጥታኛነት በላይ ልማዳችን፣ ከምግባራችን ይልቅ ግርግራችን በጣሙን በናረበት በዚህ ዘመን ያጋጠሙንን ችግሮች አለማየትና አለማሳየት እንዴት ይቻለናል? ንጉሡ ሴዴቅያስ የሐሰት ትንቢት እየሰማ ያለእግዚአብሔር ጸጋና ቃል ከተሰበረለት የእንጨት ቀንበር ይልቅ የነቢዩ ኤርምያስን ድምፅ አድምጦ ቢኾን ኖሮ ከመጪው ጥፋት በተረፈ ነበር (ኤር. 28፥2-13፤ 2ነገ. 25)። እኛም *"ስለጭብጥ ገብስና ስለ ቍራሽ እንጀራ"* (ሕዝ. 13፥19) ከሚያዋክቡና "በጥርሳቸው መኻል ስለ ነከሱት" አንዳች ነገር (ሚኪ. 3፥5) የሕዝቡን መጠለያና የሕይወት ስንጥቅ "ያለ ገለባ ከሚመርጉ" (ሕዝ. 22፥28) ዘመነኞች ማባበያ ይልቅ ያለንበትን ችግሮች ፈልፍለን ብናወጣና ለማስተካከል ብንጥር እንጠቀማለን እንጂ አንጐዳም። እዚህ ለማድረግ የተሞከረውም ይኸው ብቻ ነው፤ እነሆ፣ እንግዲህ፣ ችግራችንን እንዳስስ ዘንድ እንራመዳለን።

ይህ ማለት ግን እያንዳንዱ ዝርዝር ተግዳሮት ምንጥር ተደርጎ እዚህ ቦታ በነቂስ ይሰደራል ማለት አይደለም፤ ኧረ፣ በፍጹም! ለአስረጂነት ይኾኑ ዘንድ፣ ጕልሃን ግድፈቶችን ብቻ በመለየት፣ ግንዛቤ ለመያዝ፣ ለጸሎት፣ ለውይይትና ርምጃ

[44] ፍቅረየሱስ፣ *ደቃ መዝሙር፣* 3።





ለመውሰድ እንድንበቃ የሚያስችሉ ነገሮችን ከማቅረቡ ላይ ትኵረት ካደረግን በቂ ይኾነናል።

### *"አሳሳቢ ኹኔታ ውስጥ ያለች ቤተ ክርስቲያን"*

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድሎችና በዕድሎች ብቻ የተከበበች መስላ ለምትታያቸው ወገኖች ይህ ጥረት ከንቱ ድካም ሊመስላቸው ይችላል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ልትጨነቅበት የሚገባ ኹኔታም ውስጥ እንዳለች መናገር ተገቢ የኾነበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

ይህን ለማድረግ የሚገፋፋን ነገር ምንድነው? ይህን የምናደርግበት ምክንያት ያለንበት ኹኔታ "አሳሳቢ" ስለ ኾነ ብቻ ነው። ይህንስ ለምን እንላለን? ይህን የምንለው በደፈናው አይደለም። ወይም የጸሐፊው የግል አመለካከት ስለ ተጫነው አለመኾኑ በሚገባ መታወቅ አለበት። ችላ ብለን የማናልፈው ችግር እንዳለ የተረዱ ወገኖች አሉ። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትና ሌሎች ተቋማት ተዘጋጅተው በነበሩ የተለያዩ ጉባኤዎችና ዐውደ ጥናቶች ላይ የቀረቡ ጽሑፎችን ስንመረምር የምናገኘው ይህንኑ ያጠናክርልናል። ለምሳሌ ሁለት ወረቀቶችን ብቻ ጠቅሰን የተወሰኑ ዐረፍተ ነገሮችን ብንመዝ የጉዳዩን አሳሳቢነት ቍልጭ አድርጎ ያሳየናል፤

> ... በየዘመናቱ ከስደት በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አደገኛና አሳሳቢ ኹኔታዎች ተፈጥረዋል። የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በተመሳሳይ ኹኔታ ውስጥ መኾንዋን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩ ያሉበት ዘመን ነው። ስለዚህ *አደገኛና አሳሳቢ ኹኔታ* ውስጥ ያለች ቤተ ክርስቲያን መኾኗን መገንዘብ መልካም ነው። (*አጽንዖት የተጨመረ*)[45]

[45] ከጳጒሜ 2-5 ቀን 1991 ዓ.ም. ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን መሪዎች በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ላይ "የመንፈሳዊ መሪነት ምንነት" በሚል ርእስ የቀረበ የጥናት ጽሑፍ፣ ገጽ 8 (እኔ ባገኘሁት ቅጂ ላይ የአቅራቢው ስም አልተገለጸም)።

> [የኢትዮጵያ] ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮች በበርካታ ውስጣዊ ችግሮች ተጠምደናል፤ ሁላችን የምንጋራቸው መሰናከሎች አሉ። ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ግፊቶችም በደጃችን ናቸው። ... የአገልግሎት በሮች ተከፍተዋል፤ የአገልጋዮች አዕምሮ ግን ተዘግቷል። የውጭ ምስክርነታችንን ለማሳመር ውስጣችንን ማጥራት የሚገባን ወቅት ላይ ነን።[46]

ክርስትና ራሱን መዛኝ፣ ኀያሲና ገምጋሚ እምነት ነው። በእግዚአብሔር ቃል መነጽር ሕይወታችን ይለካል። እምነታችን፣ ኑሯችን፣ ልምምዳችንና ሥርዐተ አምልኳችን ይመዘናል። ለዚህም ክርስቲያን ሁልጊዜ ለመማር ዝግጁ መኾን አለበት። እንዲሁም ለመታረምና ንስሐ ለመግባት ፈጣን ምላሽ እንድንሰጥ ጥሪያችን ያስገድደናል። መታረምና ንስሐ መግባትም ራስን ዝቅ ማድረግንና ትሕትናን ይጠይቃል። ለመልካም ሥራ ተነቃቅቶ ሌሎችን ወደ መልካም ጎዳና መመለስ የሚቻለው ካለንባቸው ችግሮችና ጥፋቶች ስንታረም መኾኑ ግልጽ ነው። ለራሱ ያልተመለሰ ሰው ሌላውን “ተመለስ”ለማለትስ እንዴት ይቻለዋል?

ይህንን ከግምት በማስገባት የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን በክርስቲያናዊ አስተምህሮና ተያያዥ ጉዳዮች አኳያ ያለችበትን ኹኔታ ለማሳየት የሚያስችሉ ተጨባጭ ነጥቦችን በማውጣትና የችግሩን መኖር ብቻ ሳይኾን አሳሳቢነቱንም ሊያመላክቱ በሚችሉ ክሥተቶችና ኹነቶችን ርስ በርስ በማገናዘብ እናያለን። የምናነሣቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የአስተምህሮ መናጋት ሊፈጥሩ ከሚችሉት መካከል ጥቂቱን እንጂ፣ ጥቃቅን መደነቃቀፎችን ሁሉ አይኾንም። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

[46] እንዳለ፣ *የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት*፣ 1።





## 2.1 *የሥልጣን ምንጭ መዘነፍ*

የቅዱስ መንፈሱና የቅዱስ መጽሐፉ ሥልጣን በእኛ ዘንድ ቸል እንደ ተባለ ልናይ ነው። ንፍኀ-መለኮት (የእግዚአብሔር መንፈስ/እስትንፋስ) ያለበት መጽሐፍ አለ፤ እሱም ሥልጣን ያለው ቃለ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፉ ስለ ራሱ ያለው ምስክርነት ይህንኑ ያረጋግጣል። ሥልጣን ያለው መጽሐፍ በእጃችን ውስጥ ተሰጥቶናል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ከላከው መልእክት የሚከተለውን ክፍል እናንብብና ሐሳባችንን እናጕልብት፤

> *ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ። አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፤ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና። ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን ዐውቀሃል። የእግዚአ ብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይኾን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል* (2ጢሞ. 3፥13-16)።

የሥልጣን ምንጭ ምንነት እንደየሚነገርበት ዐውድ ሊለያይ ይችላል። እውነት ፍጹም እንደ ኾነች ለሚታመነው የክርስትና እምነት ብቸኛው የሥልጣን ምንጭ ልዑል እግዚአብሔር ራሱ ነው። የእግዚአብሔር የሥልጣን ልዕልና ከመለኮታዊ ማንነቱ አኳያ ይታያል። አምላክ በመኾኑ ሥልጣን ባሕርይው ነው (1ቆሮ. 15፥24-28)።

የእግዚአብሔር ሥልጣን በማንነቱና በባሕርዩ ላይ የተመሠረተ ነው ስንል፣ ከዘላለማዊ ህላዌው (ዘዳ. 33፥27)፣ ከሁሉን ዐዋቂነቱ — ማለትም ገደብ ከሌለው ጥበቡና ዕውቀቱ (1ሳሙ. 2፥3፤ 1ዮሐ. 3፥20)፣ ከሁሉን ቻይነቱ (ራእይ 19፥6፤ ዕብ. 11፥3) እና ፍጹም ከኾነው ቅድስናና ጽድቁ (1ጴጥ. 1፥16፤ ቲቶ. 1፥2) ጋር የተቈራኘ ነው ማለታችን ነው።

እንግዲህ በመላለሙ (ዩኒቨርስ) ላይ ሉዓላዊ ታላቅነትና ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለሰው ልጆች ሰጠ፤ ተናገረ (ለምሳሌ ሕዝ. 16፥1፤ ሉቃ. 3፥2)። መንፈስ ቅዱስ የቃሉ ደራሲም ባለቤትም ነው (2ጢሞ. 3፥16፤ 2ጴጥ. 1፥21)። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ይመረምራልና የእርሱ የኾነውን ነገር እርሱ እንደ ፈቀደ ይገልጥልናል (1ቆሮ 2፥10-16)። *“መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና፣ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው”* (ቊ. 10) የሚለው ከዚህ የተነሣ ነው።

ስለዚህ፣ በእኛ እንዲያድር የመጣው እርሱ የእውነት መንፈስ የተሰጠን ስለ ክርስቶስ ሊመሰክር፣ ኢየሱስ የተናገረውን ሊያሳስበን፣ ወደ እውነት ሁሉ ሊመራንና የእግዚአብሔር የኾነውን ሊያስተምረን ነው (ዮሐ. 14፥17፡26፤ 15፥16፤ 16፥23)። መንፈሱ የሌለው ሰው የእግዚአብሔር ወገን አይደለምና የእውነት ዕድል ፈንታ የለውም። *“እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከኾነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም”* (ሮሜ 8፥9)።

መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ምእመናን ግን በመንፈሱ ሥልጣን ሥር ናቸው። “በመንፈሱ ሥልጣን ሥር ያሉቱ ደግሞ በመንፈሱ ለተጻፈው ቃሉ መገዛት አለባቸው።”[47] መንፈሱ ያደረባቸው እነዚህ ዐዲሱ የእምነት ማኅበረ ሰብ አስተምህሮአቸውን የሚመሠርቱበትና የሚመሩበት የእግዚአብሔርን ቃል የያዘው የእግዚአብሔር መጽሐፍ አላቸው ማለት ነው። ስለዚህ እውነተኛው ክርስትና ቅዱሳት መጻሕፍት ያሉት ብቻ ሳይኾን፣ እነዚሁኑ መጻሕፍት ብቸኛ የሥልጣን ማዕከል አድርጎ የሚቈጥር እምነት ነው (ለምሳሌ፡- 1ቆሮ. 14፥37፤ 2ጴጥ. 3፥16፤ 1ተሰ. 2፥13 ይመልከቱ)።

[47] J. I. Packer, *Keep In Step with the Spirit* (Leicester: IVP, 1984) 239.





በአስተርዕዮተ እግዚአብሔር (በእግዚአብሔር መገለጥ) ላይ የሚታመነው የክርስትና እምነት፣ የመለኮታዊ መገለጥ ግልጽ ማስረጃው ቃለ እግዚአብሔር ነው ሲል አጽንዖት ይሰጣል፡- አንድም፣ አካላዊ ቃሉ—እርሱም ክርስቶስ ነው፤ አንድም፣ የተጻፈው ቃሉ—ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እናም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር አስተርዕዮ የተሰጠበት (ግልጠተ መለኮት) ስለመኾኑ ጥርጣሬ የለውም፤ ምንጩና መለኮታዊ ደራሲው እግዚአብሔር ራሱ ነውና። ደግሞም፣ ሰብአዊ ደራሲዎቹን የመረጠውና የነዳው የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ኾነ ቃሉ ሥልጣናዊ ነው፤ ቃለ እግዚአብሔርም ይባላል።

*“ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጒም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ ”* (2ጴጥ. 1፥21) ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከራሳቸው ኀሊና አንቅተውና ከልባቸው አፍልቀው የጻፉት ድርሳን አይደለም፤ ይልቁኑም እግዚአብሔር ይጻፍ ዘንድ የፈለገው ሐሳብ የሰፈረበት መጽሐፍ እንጅ። በመኾኑም ንፍኀ-መለኮት (የአምላክ እስትንፋስ) ያለበት መጽሐፍ ነው ተብሏል (2ጢሞ. 3፥16)። ስለዚህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር ነው—የእግዚአብሔር ማንነት፣ ባሕርያቱና ፈቃዱ የተገለጠበት መጽሐፍ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ምንጩ መለኮት ስለ ኾነ የእውነት መለኪያ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ መለኮታዊ ደራሲው እግዚአብሔር እውነተኛና የማይዋሽ (ቲቶ. 1፥2፤ ዕብ. 6፥16-17) አምላክ ስለ ኾነ፣ ደግሞም መጽሐፉ ራሱ እውነትና የእውነት መለኪያ በመኾኑ (ሐዋ. 8፥43-45፤ 17፥3፤ 8፥17፤ መዝ. 119፥151)፣ እንዲሁም ቃሉ የእርስ በርስ ተቃርኖ የሌለው ሐቀኛ ነውና ከእርሱ የኾነው መልእክት እውነተኛ፣ ተአማኒና በቂ ነው። ስለዚህ መጽሐፉ የእውነት መለኪያ ብቸኛ ሚዛን ነው እንላለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ ማንኛውም ትምህርት፣ ሕይወት፣ ተመክሮ፣ ልምምድና ሥርዐት በሙሉ ውድቅ ነው።

ይህ መጽሐፍ ከብዙዎች እንደ አንዱ የሚወሰድ ሳይኾን ብቸኛ ነው። ይህን አስመልክቶ አቶ ንጉሤ ቡልቻ በአንድ ወቅት የተናገሩትን እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው። እንዲህ ብለው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ “‘አስተያይታችሁ ለኩኝ’ ሳይኾን የሚለን፣ ‘ሁሉንም በእኔ መለኪያ ተመልከቱ’ ነው። ‘ከሌሎች ሁሉ ጋር ተጠጋግተህ ተቀመጥ’ ስንለው ‘ምርጫው ኹለት ብቻ ነው’ ይለናል፤ ‘ቀዳሚ አድርጉኝ አለበለዚያ አላወቃችሁኝም’።”[48]

የክርስቲያናዊ እምነታችን አንዱ መገለጫ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ባለን ግንዛቤ ላይ የሚያጠነጥን ነው። ምክንያቱም፣ ዶ/ር ኀይሉ ቸርነት እንደ ጻፉት፣

> ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን ግንዛቤ በቀጥታ የሚወስደን ስለ እግዚአብሔር [ገብቶናልና] ተረድተነዋል ወዳልነው እውነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ልጆች ቋንቋ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስብከት ነው። እግዚአብሔር፣ ባሪያዎቹን በመጠቀም፣ አንድ መጽሐፍ [አስ]ጽፏል። ስሙም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ... ለዚህ ነው የዕብራውያን ጸሐፊ *“የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል* (ዕብ. 4፥12)” የሚለው።[49]

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ሲሰጠን ለኛ ያለውን ፍቅር ያስታወቀበት *መገለጥ* አድርጎ ነው። *መገለጥ* የሚለው ቃል በቀላሉ ሲተረጐም እግዚአብሔር ማን እንደ ኾነ፣ ባሕርይውን፣ ፈቃዱንና ሐሳቡን ያሳወቀበት መንገድ ማለት ነው። እኛ ከእርሱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዴት እንደምንፈጥር ለሰው ልጅ

[48] ንጉሤ ቡልቻ፣ “ዘጠኝ ወንጀሎች (በቃለ እግዚአብሔር ላይ የሚፈጸሙ)” *ቃሉ ይንገሥ፣* (ዐዲስ አበባ:-ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ባገኘሁት ቅጂ ላይ የኅትመት ቦታውንና ጊዜውን አመልካች ክፍሉ የተገነጠለ ነው) ገጽ 20።

[49] ኀይሉ ቸርነት፣ *ሕያው ቅብብል* (ዐዲስ አበባ:- አሳታሚ የለም፣ 1995 ዓ.ም.) 15።





ያስተላለፈበት መገለጥ ነው። ይህም እንግዲህ የእርሱ አንደኛው የመገለጥ ምርጫው ነው። እግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጡን በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ባያስታውቀን ኖሮ፣ እነዚህን ነገሮች ማወቅ አንችልም ነበር። ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ ቃሉን በሚመለከት ግልጽ የእምነት መግለጫ አለ። እርሱም ሁሉም ትምህርቶች የሚመዘኑበት መለኪያ ነበር።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ያስታወቀን መገለጥ ቀስ በቀስና (*progressively*) ዓመታትን በፈጀ ሂደት ውስጥ የተከናወነ ቢኾንም የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግንኙነት በውስጡ ጠንቅቆ የያዘ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከኾነ እምነትን፣ ልምምድን፣ ተመክሮን ምግባርንና ሥርዐትን በተመለከተ ላዕላይ ሥልጣን አለው ማለት ነው፤ ቃለ እግዚአብሔር ነው ብለናልና።

መጽሐፍ ቅዱስ ቃለ እግዚአብሔር በመኾኑ ክርስትና እምነቱን፣ ምግባሩንና ልምምዱን ሁሉ ከዚህ መጽሐፍ ሥልጣን ሥር ይቀዳል። “ምክንያቱም ሌሎች ምንጮች ውሃውን ሊያጨቀዩት ይችላሉ።”[50] ስለዚህ ትምህርታችንን በምንቀርጽበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ሚና አለው። የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንም አስተምህሮዋንና ሕይወቷን የምትለካበት ሌላ የሥልጣን ምንጭ ሊኖራት አይችልም፤ አይገባምም።[51]

በዘመናችን እየኾነ ያለው ግን ምንድነው? በአንድ በኩል በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስትና እምነት ውስጥ ሊታመኑ ይቅርና ከነጭራሹ ሊታሰቡ እንኳን የማይቻላቸውን እንግዳና ድቅል አስተምህሮዎችን ከየአቅጣጫው እየቃረሙ ማስተማር እዚህም፣ እዚያም ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፉን በመጠምዘዝና አላግባብ በመተርጐም ቅዱስ ቃሉ ሊናገር የፈለገውን ሳይኾን

[50] ምኒልክ፣ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣* 9።

[51] በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ሐሳብ ለማግኘት ካስፈለገ፣ አቶ ነቢዩ ዓለሙ የጻፉትን ማየት ጥሩ ነው። (“‘የወንጌላውያን’ የማንነት ቀውስ እና ማዕከላዊ የሥልጣን ዕጦት” *ማራናታ፣* ቅጥር 18፣ ግንቦት 2003 ዓ. ም.፣ ገጽ 30-31።)

እንዲናገርልን የምንፈልገውን ሐሳብ በውስጡ ደንጉረን የምናስጨንቅበት አተረጓጐም በየቦታው ሞልቷል። በዚህ ረገድ ጳውሎስ ራሱን ያማጠነበትና የተጸየፈው ሃይማኖታዊ ነጋዴነት (2ቆሮ. 2፥17)[52] እየተዛመተ ይመስላል።

ከቅንነት በራቀ መንፈስ እንደገዛ ፍላጐት ቃሉን ለመተርጐም መሞከር፣ ለግል ጥቅም በመጽሐፉ አሳብበ መነገድ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅሎ መሸቃቀጥ ዛሬ ብርቅ ነውን? በየዐውደ ምሕረቱ (መድረክ) ላይ ሳምንታዊ መርሐ ግብሮቻቸውን ጠብቀው በሚሰየሙ ሰባክያንና መምህራን አማካኝነት አንድ ምንባብ በተለያየ ብቻ ሳይኾን በተቃርኖ ሐሳቦች ተተርጉሞ ሲቀርብ አልገጠማችሁም? ለዓመታት የገነባችሁት ማኅበር በሁለት ቀን ዝግጅት ጉባኤ ላይ ብቅ ባለ አስተማሪ፣ ሰባኪ ወይም ነቢይ አማካኝነት በተላለፈ ዐዲስ ትምህርት ሲገለበጥስ አላያችሁም? ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ሌሎች ምንጮች ዋነኛ መመሪያዎች ተደርገው ሲወሰዱስ አልሰማችሁም?

የእግዚአብሔር ቃል ጥናት ላይ የተመሠረቱ መርሐ ግብሮች እንደ “ደረቅ” ስብሰባዎች መታየታቸው ሳያንስ፣ ኹነኛ ነገር የማይተላለፍባቸው የባከኑ ግር ግሮችን ማወደስ እየተለመደ መጥቷል።

እጃቸውን እያወዛወዙ በመምጣት መድረክ ላይ ከወጡ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ከምእመናን እጅ ተውሰው ለመስበክ የጠየቁ ሰባክያንና መምህራንን ደጋግመን ተመልክተናል። ሰዎች እንዳያኮርፉና ከአገልግሎታችን እንዳይቀሩ በሚል ዓላማ የቃሉ መልእክት “ቀጠን” ተደርጎ እንዲቀርብ እየተደረገ ያለበት ቦታና ኹኔታ ጥቂት አይደለም። በአንዳንድ ቦታዎች እንዲያውም በስብከትና በትምህርት ላይ በሥልጣን የሚጠቀሰው ቅዱስ ቃሉ መኾኑ ቀርቶ የቤተ ክርስቲያኑ “መሥራች” የተባለው ግለ ሰብ አባባሎችና “ትምህርታዊ ሐሳቦች” ሲኾኑ ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከኾነ ልንወደው፣

[52] *“የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደተላከን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ኾነን እንናገራለን ”* (2ቆሮ. 2፥17) የሚል ነው።





ልናጠናው፣ ልንታዘዘውና ልናምነው ይገባናል፤ የእግዚአብሔር ቃል ከኾነ እሱን ቻላ ማለት እግዚአብሐር ራሱን ቻላ ከማለት የተለየ አይደለም።

በቃለ ምልልስ ከተሳተፉትና የአንዲት ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ የነበሩ አባት እንዳሉት፣ “ጉዳዩ አሳሳቢ ነው፤ አሁን እየተነጋገርንበት ያለው እኮ ዐዲስ ወሬ አይደለም። ሁላችንም በየጓዳችን የምናብሰለስለውና የምናምጥበት ነገር ነው።”[53] አዎ፣ ከቃሉ መዘንጋትና ቸል መባል ጋር ተያይዞ እጅግ ብዙ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻል ነበር። ኾኖም ግን ቀጥሎ የቀረበውንና የዘመኑን ኹኔታ በማሳየት ሊወክል የሚችል አንድ ምሳሌ  ብቻ እስቲ እንመልከት፤

በ2006 ዓ.ም. በደብረ ዘይት ከተማ ለሰባክያን በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ወቅት በአንዱ ማለዳ የጋራ የጸሎት መርሐ ግብር ላይ የእግዚአብሔር ቃል ያካፍለን የነበረው ወንድም እንዳሻው ነጋሽ ስላጋጠመው ነገር በኀዘን የተናገረው ምሳሌ ይኾነናል። እንዳሻው ስሙን ያልጠቀሰው ሰባኪ በአንዲት አጥቢያ ተጋብዞ ለስብከት አገልግሎት በቆመበት ጊዜ፣ “*አሁን ቃሉን የምንሰብክበት ዘመን አይደለም፤* እስከ ዛሬ ተሰብከናል፤ አሁን የድርጊት ጊዜ ነው፤ ዛሬ ዝለሉ ካልኳችሁ ትዘላላችሁ፤ መጮኽ ካስፈለገንም በታላቅ ድምፅ ትጮኻላችሁ” በማለት ምእመናኑን ሲያንገላታ እንደ ነበር ተናግሯል፤ ያሳዝናል። ይህ ዐይን ያወጣ ድፍረት እኛን ከማሳዘን ዐልፎ ሰማያትንስ የሚያስቈጣ አይደለምን? እግዚአብሔር ፈውሱን ይላክልን እንጅ።

በሌላ በኩል፣ ቃሉ የምንናገረው ብቻ ሳይኾን የምንኖረውም መኾኑ መታወቅ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታችን ሥልጣናዊ የበላይነቱ የሚታወቀው ባጠናነውና በኑሯችን ላይ ባዛመድነው መጠን ነው። ከጊዜያችን ምን ያህሉን በቃለ እግዚአብሔር ጥናት እንደምናሳልፍ፣ እንዴት እየኖርነው እንዳለንም መጠየቅ ያለብን ወቅት ላይ እንገኛለን።

[53] በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ነገር ግን ስማቸው እነዲጠቀስ ያልፈቀዱ ዶ/ር “ለ” እንደ ተናገሩት።

ከቅዱስ ቃሉ ጋር እንደ ተኳረፍን ከሚያመላክቱ ተግባራት አንዱ፣ ክርስቲያን ወገኖች ወደ አምልኮና ጸሎት ስብሰባዎች ሲመጡ እንኳ፣ ቅዱሱ መጽሐፍ ከብዙዎች እጅ ጠፍቶና በሌሎች ነገሮች ተተክቶ መታየቱ ነው። የወንጌላዊ እንዳለ ጥናት ወረቀት ይህን ጉዳይ እንዲህ ይገልጸዋል፤

> ቃሉን በሙላት መስበክና ማስተማር ዐቢይ የመጋቢነት ዐደራ ኾኖ ሳለ ይህ በመዘንጋቱ ዛሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣው ሕዝብ “መጽሐፉ ለምኔ” ከማለቱ [የተነሣ ወንዱ] እጁን ኪሱ በመከተት [ሴቷም] ቦርሳዋን በእጇ አንጠልጥላ ነው። በአብያተ ክርስቲያናት ደጃፍ የደራው የመጽሐፍ ቅዱስ ገበያ ሳይኾን የወረቀት መሐረብ ገበያ ነው። ማልቀሱ እንደሁ ድሮ ቀርቷል፤ ምናልባት በጭፈራ ብዛት የሚፈጠረውን ላቦት ለመጥረግ ይኾናል።[54]

ይህ ብቻም አይደለም፤ ከነጭራሹ መጽሐፍ ቅዱስን የማያጣቅሱ ትምህርቶችና ፍልስፍናዎች በተለያዩ መድረኮችና ጽሑፎች[55] በቀጥታ እየቀረቡ ነው። ከዚህ ሲብስም ተራ የሰዎች ትምህርትና ተረታ ተረት የሚነገርባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸውን ልምምዶችን ሳይቀር “ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም” በሚልና *እምነት* በሚመስል ቀመር ሥር ለመደበቅ የሚሞከሩም ያጋጥማሉ። እርግጥ ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንዳችም ነገር የለም፤ እርሱ ሁሉን ይችላል። ሁሉን ቻይነቱ የሚታየው ግን እንደ ባሕርይውና ከቃሉ ጋር በማይቃረን መንገድ መኾኑ መነገር አለበት። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ሁሉን ቢችልም፣ መዋሸት አይችልም። ባሕርይው አይደለምና (ዘኁ. 23፥19፤ ቲቶ 1፥2)። በእኛ ዘመን ግን በየጓዳው፣ በየአብያተ ክርስቲያቱና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባዮች

[54] እንዳለ፣ *የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት*፣ 5።

[55] ይህን ለማረጋገጥ፣ ከብዙ አገልጋዮችና ምዕመናን እጅና የመጽሐፍት መደርደሪያ ላይ የማይለዩትን በአንዳንድ አስተማሪዎችም ሐሳቡ ተቀንጭቦ ሲነገር የምንሰማቸውን የማይልስ ሞንሮ መጻሕፍት ብቻ መመርመር በቂ ነው። እነዚህ መጻሕፍት፣ በከፍተኛ ቊጥርና ዐይነት በመተ'ርጐም ገበያውን ከሚመሩ መጽሐፍት ተርታ የተሰለፉና አብዛኞቹን የክርስቲያን መጻሕፍት መደብሮችን ያጣበቡ ናቸው።





ላይ በእግዚአብሔር ስም የተነገሩ ትንቢታዊ መልእክቶች “የውሃ ሽታ” ኾነው ሲቀሩ ሰምተናል፤ ተመልክተናል። ኾኖም ግን በቃለ እግዚአብሔር ፈትኖና መርምሮ ርምጃ የወሰደ ግን አለ? በየጓዳችን አጕተምትመን ነው የቀረነው።

ርግጥ ነው፣ ቃሉን የሚሰብኩ፣ የሚያስተምሩና በታማኝነት በሕይወታቸው የሚተገብሩ ወገኖች ይኖራሉ። ይህን አገልግሎታቸውን ለማከናወንም ትጋት የሚታያባቸውና በፍጹም የደስታ ስሜት (*enthusiasm*) ተመልተው ቃሉን ማገልገል የቻሉ መኖራቸውም እውነት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከመሰበኩ የተነሣ “የማይደፈሩ” ቦታዎች ጭምር የወንጌል መልእክት መድረስ ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ለመማር የተዘጋጀና ፈቃደኛ የኾነ ሕዝብ ቊጥሩ ቀላል አይደለም። የቃሉ አገልግሎት ቤተ እምነታዊ ዐጥር ባልገደበው መቀባበል ሲሰጥም ታይቷልና እግዚብሔርን ማመስገን ይገባል።

ኾኖም፣ መልካም ነገሮች ቢኖሩም እንኳ፣ ችግሩ እየተባባሰ ነው። የአብያተ ክርስቲያናት መድረኮች ሃይ ባይ ያላቸው እስከማይመስሉ ድረስ ውሸት በድፍረት ሲነገር የሚደመጥባቸው እየኾኑ ነው። መልእክት ያላቸው ምስባክ ተነፍገው መድረኩን ወደ ሕዝብ አጫዋችነት ለቀየሩት ሰፊ ሰዓትና ቦታ ሰጥተናል። ጤናማ ትምህርት በትሕትና ከማስተላለፍ ይልቅ እንግዳ ሐሳቦች የሞላባቸው ትምህርቶችና ልምምዶች በሚያስተናግዱ ተከብበናል። ጉዳዩን በአደባባይ አንሥተው እንድንታረም የሚወተውቱ ጥቂቶች ባይጠፉም ምላሹ አበረታች አይመስልም።

በአጠቃላይ፣ በአስተምህሮ አኳያ በዘመናችን ለተፈጠሩ በርካታ ውዥንብሮች መሠረታዊው ችግር የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣናዊ ማእከልነት መጣስ እንደ ኾነ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል፤ ወይም ግልጽ መኾን አለበት።

እንደሚታወቀው፣ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በአንቀጸ-ተአምኗቸው ፊተኛ መሥመር ላይ የሚያሰልፉት ነጥብ መጽሐፍ ቅዱስን በሚመለከት ያላቸውን ዐቋም ነው። አቀማመጡና አገላለጹ እንደየቤተ እምነቱ መጠነኛ ልዩነት ሊኖረው ቢችልም፣ ከሚከተለው ማጠቃለያ ብዙ የራቀ አይደለም።

> መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም የእግዚአብሔር ቃል ሲኾን፣ በመንፈስ ቅዱስ በተመሩ ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ፣ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበት፣ ስሕተት የማይገኝበት፣ እውነተኛና ተአማኒ፣ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ የመጨረሻ የእውነት መለኪያ እንደ መኾኑ መጠን በእምነታችን፣ በምግባራችንና ልምምዳችን ሁሉ ላይ ላዕላይ ባለ ሥልጣንና የመጨረሻ ዳኛ ነው።[56]

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ፊት ተደቅነው ካሉት ዐበይት ጥያቄዎች መካከል አንዱ ይኸው ነው፤ ይህ ከቡርና ዘመናትን ዘልቆ እኛ ዘንድ የደረሰው የእምነት መግለጫቸው እንዳልተሸራረፈ በዚህ ወቅት ደፍረው ለመናገር የእምነትና ምግባር ብቃቱ ይኖራቸው ይኾን? በርግጥ ዛሬ በእምነታችን፣ በምግባራችንና በሥርዐተ አምልኳችን ሁሉ ላይ የቅዱሱ መጽሐፍ ሥልጣን የተገለጠ ነውን?

በ2005 ዓ.ም. በናዝሬት ክልል መሠረተ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት “የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ አፈታት” የተባለ ኮርስ ይማሩ ለነበሩ 82 ተማሪዎች በዚህ ሐሳብ ላይ የተመረኰዘ መጠይቅ በትኜ ነበር። ተማሪዎቹ በልዩ ልዩ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚያገለግሉ ነበሩ። የጥናት ውጤቱ አስደንጋጭ ነበር የኾነብኝ። 92% የሚኾኑቱ ተጠያቂዎች “አስተምህሯችንና ኑሯችን ላይ የቃሉ ሥልጣናዊነት አጠያያቂ ኾኗል” ሲሉ መልሰዋልና።

በዚህ ዘመን፣ ምን ያህሎቻችን ነን፣ ሰዎች ትምህርታቸውና ኑሯቸው በግልጽ ከቃለ እግዚአብሔር ባፈነገጠ ጊዜ ትክክል አይደለም በማለት ለመጋፈጥ የምንደፍር? ዋጋ ቢያስከፍለንም እውነትን በፍቅር ለመናገር የማናመቻምች? ከስማችንና ዝናችን ይልቅ ቃሉ የበለጠብን እነማን ነን? የአብያተ ክርስቲያናት ዐውደ ምሕረት በስሜት ቀስቃሽ ንግግሮችና ተራ ሰብአዊ ሐሳቦች በደነዘዘበት በዚህ ወቅት ወደ ቅዱስ ቃሉ የሚመልሱን ተግሣጾች አያስፈልጉንምን?

[56] የአብዛኛዎቹን አብያተ ክርስቲያናት አንቀጸ-ተአምኖ (*Faith Statement*) እንደ ተመለከትኩት፣ ይህ አንቀጽ፣ ብዙውን ጊዜ፣ በአንቀጽ ተራ ቍጥር 1 ወይም 2 ላይ ሰፍሯል።





ይህ ዝምታችንስ የት ያደርሰናል? ዋናችንን ቸል ካልን ወይም ከተቀማን ምን ይተርፈናል? ያለዚህ መለኮታዊ መመሪያስ ማን ያስተዳድረናል? መጽሐፉን ከጣልን ማን ያነሣናል? ከቃለ እግዚአብሔርና ከመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ርቀን ብንቈስል ማን ያክመናል? የቃሉ ሥልጣን የበላይነት በዘመናችን ትምህርት፣ ምግባርና ልምምድ ላይ ጐልቶ ካልተተገበረ ትርምሳችንን ማን ያስቆመዋል? በየጓዳው ማጒተምተሙ ብቻ ምን ይፈይድልናል? እስከ መቼስ ዝም ይባላል? *“እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ”* (ዘካ. 8፥16) ተብለን የለም ወይ? አዎ፣ ያለንበትን አስመልክቶ እውነት ተነጋገሩ፤ እንነጋገር።

ከቡራንና ከቡራት “እንፋሎቶች” (ያዕ. 4፥14) ሆይ፣ *“ይህን እናገራለሁ፤ ዘመኑ ዐጭር ኾኖአል”* (1ቆሮ. 7፥29)። የምናመነታው ታዲያ ለምኑ ነው? *“ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና”* (1ጴጥ. 4፥17) የሚለው ኀይለ ቃል እኛን አይመለከተንም? ጌታስ አያዝንብንምን? የተሰጠንን ዐደራ በአግባቡ ሳንወጣ በቀረን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያዝንብናል።

በኢትዮጵያ የፊንላንድ *ጳንጠቈስጤ ሚሲዮን* አገልጋይ የነበሩት ሄይኪ ፔንቲንን፣ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በተገኙበት ሰሚናር ላይ ሲናገሩ፣ እንዲህ ብለው ነበር። “እንደ ክርስቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢራት ባለ ዐደራዎች ኀላፊነታችንን ሳናውቅ ስንቀር መንፈስ ቅዱስን ልናሳዝነው እንችላለን። እግዚአብሔር የሰጠን ታላቅ የኾነ ጥሪና ስፍራ ብቻ ሳይኾን እጅግ ታላቅ የኾነ ተጠያቂነትም ጭምር ነውና።”[57]

በእግዚአብሔር ፊት የተጠራን ዕድለኞች ብቻ ሳንኾን ተጠያቂዎችም ነን። ኀላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት ያስጠይቃል። ቤቱን የማይቈጣጠር ጌታ የለም። የዘገየ ወይም ዝም ያለ ቢመስልም፣ ጌታችን ኢየሱስ በምሳሌው እንዳስጠነቀቀው፣ *“ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቈጣጠራቸው”* (ማቴ. 25፥19) የሚለው ቃል እውን መኾኑ አይቀርም።

[57] ሄይኪ ፔንቲነን፣ *“የመግቢያ ንግግር፣” የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተቃቀም ሰሚናር*፣ (ዐዲስ አበባ፣ ኤገስት፣ 1997) 2።

## 2.2 *ካሪዝማዊ ግድፈት*

*"ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ... በብርቱ ፈልጉ"* (1ቆሮ. 14፥1)።

*ጰንጠቈስጣዊ*[58] *መነቃቃቶችና* *ካሪዝማዊ*[59] ተሐድሶዎች በተለያዩ ጊዜያት ሲከሠቱ መኖራቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል። እነዚህ ንቅናቄዎች በጌታ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚሰጡ የዐዲስ ኪዳን ስፍረ ዘመን የጸጋ ባርኮቶች አካልና የሰብከተ ወንጌሉ መስፋፋት መንስኢም ውጤትም ናቸው።

ከ20ኛው ምእት ዓመት በኋላ ባላቸው ኹኔታ፣ ከነገረ መለኮታዊ ትንታኔ አንጻር፣ *ጰንጠቈስጣዊ* እና *ካሪዝማዊ* አመለካከቶች የየራሳቸው ዐቋሞች እንዳላቸው ይታወቃል። ዐቋሞቹን በመጠኑ ልናያቸው እንችላለን።

---

[58] "ጰንጠቈስጤ" የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስ የወረደበትንና ቤተ ክርስቲያን የተወለደችበትን የ"በዓለ ኀምሳ" (ሐዋ. 2፥1) ታሪካዊ ቀንን ያመለክታል። አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ *"በዓለ ኀምሳ"* የሚል ፍች የሰጠው ዐዲስ ኪዳን በመጀመሪያ በተጻፈበት በጽርእ (ግሪክ) ቋንቋ "πεντηκοστή—ጴንጠቈስጤ" በማለት የተጠቀመበትን ስያሜ ነው። በቁሙ "ዐምሳኛ" እንደ ማለት ነው። ግእዙ፣ በበኩሉ፣ የጽርዑን ቃል እንዳለ በምልስ ፍች በመቅዳት አገልግሎት ላይ አውሎት እናገኘዋለን፤ "ወአመ ተፈጸመ መዋዕለ *ጰንጠቈስቴ* እንዘ ሀለዉ ከሎሙ ኅብረ አሐተኔ።" (ግብረ ሐዋርያት ፪፥፩ *አጽንዖት* የተጨመረ) ይላልና።

[59] *ካሪዝማዊ* እንቅስቃሴ፣ እንደ *ጰንጠቈስጤ*፣ ስየሜውን ያገኘበት ቃል የተወሰደው ከዚያው ዐዲስ ኪዳን ከተጻፈበት የጽርእ ቋንቋ ነው። χαρίζομαι — *ካሪዞማይ* ከተሰኘው የጽርዕ ግስ የሚመዘዘው ስም፣ χάρισμα — *ካሪዝማ* እንደየአገባቡ የተለያየ ትርጓሜ ያለው ነው። ለምሳሌ "በስጦታ የተገኘ ከፍ ያለ ዕድል" (ሮሜ. 11፥29)፣ "ከአደጋ መትረፍ" (2ቆሮ. 1፥11)፣ "የቤዝዎት ጸጋ/ስጦታ" (ሮሜ. 5፥15-16) እንዲሁም፣ በሥነ ጾታዊ ጉዳዮች ራስን ለመግዛት የሚያስችል "ዐቅም" (1ቆሮ. 7፥7) ማለት ይኾናል። እየተነጋገርንበት ባለው ዐውዱ ደግሞ፣ "ተጨባጭ የመለኮታዊ ጸጋ ልግስና መገለጫ ኾኖ ለግለ ሰቦች የሚሰጥ ከፍጥረታዊ ችሎታ በላይ የኾነ ኀይልና ስጦታ" (ሮሜ. 12፥6) ነው። በተጨማሪ፣ ለአገልግሎት በመለየት "ከእግዚአብሔር ከራሱ የሚሰጥ የጸጋ ስጦታ" እና "የተለየ ችሎታ" (1ጢሞ. 4፥14፤ 1ጴጥ. 4፥10) ነው። *ካሪዝማ*ን በአጠቃላይ፣ "መንፈሳዊ ስጦታ፣ ወይም ነጻ የመለኮት ጸጋና ኀይል" ልንለው እንችላለን። (Barbara Friberg, Timothy Friberg and Neva F. Miller, *Analytical Lexicon Of The Greek New Testament* [Grand Rapids: Baker, 2000]. Electronic Edition. ይመለከቷል)





*ጰንጠቈስጣዊ* እንቅስቃሴ ቀደምት[60] መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን ተከትለው በ20ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከተከሠቱ ልምምዶች በኋላ እየተስፋፋ የመጣና በአማኝ ሕይወት ውስጥ ከዳግም ልደት ቀጥሎ የሚከሠት "ዳግማዊ ባርኮት" መኖሩን አጽንዖት የሚሰጥ ነው። ይህ ባርኮትም "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ" ሲኾን፣ "ምልክቱ ደግሞ በልዩ ልሳናት መናገር ነው"ይላል።[61]

*ካሪዝማዊ* ተሐድሶ በበኩሉ በዐዲስ ኪዳን ምንባባት የምናገኛቸውና በመጀመሪያው ምእት ዓመት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተገኙት ስጦታዎች ሁሉ፣ በልሳናት መናገርን ጨምሮ፣ ዛሬም ይሠራሉ ብሎ ያምናል፤ ይለማመዳልም። ነገር ግን በልሳን መናገር ከሌሎቹ እንደ አንዱ እንጂ የግድ "ለእያንዳንዱ በመንፈስ የተጠመቀ አማኝ የሚታደል የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው" መባሉን አይቀበልም። እንቅስቃሴው ብዙ ጊዜ የራሱን ቤተ እምነታዊ ዐጥር ከልሎ ከመውጣት ይልቅ "ከጥንት ጀምሮ በተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መታየት"[62] ባሕርይው ነው።

እንግዲህ ከተጠቀሱት ልዩነቶች በስተቀር ከላይ ባየናቸው እንቅስቃሴዎች መኻል ሌላ መሠረታዊ ቅራኔ አይታይም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥም "ከሁለቱ አመለካከቶች የትኛው ትክክል ነው?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ አይገኝም። የተነሣንበት ዐላማ አይደለምና። ኾኖም ሁለቱም እንቅስቃሴዎች በመንፈሳዊ ስጦታዎች ቀጣይነት ላይ የሚስማሙና የሚለማመዱ ናቸው። ስለዚህም፣

---

[60] *ምንም እንኳ ጴንጠቈስጣዊ ባይኾንም*፣ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በጊዮርጊስ ዊትፊልድ (1714-1770) እና በዮሐንስ ዌስሊ (1703-1791) መሪነት በአውሮጳና አሜሪካ ውስጥ የተቀጣጠለው መንፈሳዊ የቅድስና መነቃቃት በኋላ ለተከሠተው የጰንጠቈስጤ እንቅስቃሴ እንደ ቀዳሚ አማማጭ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከቱ አልቀረም። ጄ. ዋርድም ይህን ሐሳብ የሚያወሳው በአንክሮ ነው፤ (J. W. Ward, "Pentecostalist Theology," in *New Dictionary of Theology.* Edited by Sinclair B. Ferguson and David F. Wright [Leisester: IVP, 1988] 502 ይመ.)

[61] Grudem, *Systematic,* 763.

[62] ኮሊን ማንሰል (ቄስ)፣ *ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ፣ 3ኛ መጽሐፍ* (ዐዲስ አበባ:- ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1999 ዓ.ም.) 185።

ከተነሣንበት ሐሳብ አኳያ፣ ሁለቱን ስያሜዎች በተለዋጭነት እስከ መጠቀም ያህል ያግባባናል። ስለኾነም *ካሪዝማዊ* እንቅስቃሴዎች በሚለው ስጠቀም በሁለቱም በኩል ያሉትን በሚያካትት መልኩ ወስጄው ነው ማለት ነው።

እውነተኛዎቹ *ካሪዝማዊ* እንቅስቃሴዎች በተከሠቱበት ዘመን ሁሉ ለቅዱሳን መታነጽ፣ ለአብያተ ክርስቲያናት መስፋፋትና ለእግዚአብሔርም መከበር ምክንያት የኾኑ በረከቶች ነበሯቸው፤ አሏቸውም። የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ለ*ካሪዝማዊ* ሞገዶች እንግዶች አይደሉም። በዚሁ በኛው ሀገር፣ *የካሪዝማዊ ጰንጠቈስጤ* ነፋስ ቤተ እምነታዊ ዐጥሮች ሳይገድበው ለአማኞች መታነጽ፣ ለወንጌል እውነት መስፋፋትና ለቅዱሳን ኅብረት መጠናከር አስተዋጽዖ ያበረከተ መኾኑን ማን ይጠራጠራል? የእውነተኛ *ካሪዝማ* ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነውና፣ ጌታችን ኢየሱስን እያስከበረ፣ ለእውነተኛ መንፈሳዊነትና እግዚአብሔርን መምሰል ለሚታይበት ሕያውና የተነቃቃ ክርስትና፣ ለስብከተ ወንጌል፣ እንዲሁም ለአምልኮተ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን አላተጋምን? መልሱ “አትግቷል እንጂ” የሚል ነው ሊኾን የሚችለው። ክብሩ የስጦታዎቹ ባለቤት፣ ለተቀባዮቹ ሰዎች ደግሞ ጌታቸው ለኾነው ለእግዚአብሔር ይኹን።

ነገር ግን፣ *ካሪዝማዊ* እንቅስቃሴዎች ሁልጊዜም ጤናማ ኾነው አልቀጠሉም። ዝንፈት ይገጥማቸዋል፤ ወይም የአስመሳይነት እርሾ “ዕቃውን” ይበክለውና “ቡኾውን”ያኮመጥጠዋል። ሲከፋም በመስኩ ላይ ባዕድ አረም ይበቅልበታል። እንግዲህ፣ እንደነዚህ ዐይነት ነገሮች ሲከሠቱ ነው *ካሪዝማዊ* ችግሮች ተፈጠሩ የሚባለው። አንዳንዶች ይህን መሳይ ችግሮችን “*ካሪዝማዊ ቀውሶች*” ብለው ይጠሯቸዋል። በካሪዝማዊነት ካባ ሥር አድፍጠው የሚፈጸሙ የማይገቡ ተግባራት ሞልተዋል ማለታቸው ሳይኾን አይቀርም።

ለነዚህ ችግሮች የመንሥኢ ዓይነቶቹ ልዩ ልዩ ናቸው። አንደኛው የአጠቃቀም ግድፈት ነው። እንደ ቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ድርጊት ማለት ነው። የዚያች ቤተ ክርስቲያን *ካሪዝማዊ* ችግሮች የተከሠቱት ስጦታው እውነተኛ ሳይኾን ቀርቶ አይደለም። ስጦታዎቹ በርግጥም ትክክል ነበሩ። ስጪው ሁሉን እንደ ፈቃዱ ምክር የሚሠራው ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደ ነበረ በ1ቆሮ. 12፥4-10 ላይ በግልጽ ተጽፎ እናገኘዋለን፤



“ሃያነበሬዙ በቅኮ”

*የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ ዕውቀ ትን መናገር ይሰጠዋል፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአን ዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጐም ይሰጠዋል፤ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።*

ይላል ቅዱስ ቃሉ። ስለ ውድ ስጦታዎቹ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ታዲያ ችግሩ ምን ነበር? ችግሩ በምእመናኑ ብስለት ማጣት፣ ስሜታዊነትና ተፎካካሪነት የተነሣ በጋራ አምልኮ ማዕቀፍ ውስጥ የተፈጠረ ሥርዐት አልበኛነት ነበር። ይህን መሳዩ ችግር ሲከሠት በአጠቃቀም መመሪያዎች ሊቃና ይችላል። ይህ ሊሳካ የሚችለው ግን በትሕትና መንፈስ ለመታረምና ጥፋትን ለማስተካከል የተዘጋጀ ልብ የተገኘ እንደ ኾነ ብቻ ነው።

ለ*ካሪዝማዊ* ዝንፈቶች መከሠት ሌሎቹ ምክንያቶቹ ደግሞ ሰይጣንና ሥጋዊነት ናቸው። ይኸኛው በርግጥ ያስፈራል፤ መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ማኅበራዊ ጥፋቶችን ሊያስከትል መቻሉ አይቀሬ ነውና። እንዲህ ዐይነቱ ችግር ሊመጣ የሚችለው አስመሳይና ሐሰተኛ የዐጸፋ እንቅስቃሴዎች (*Counterfiets*) ሲበራከቱ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በ2ቆሮ. 11፥3-4 ከእንዲህ መሰሉ አደጋ እንዲጠነቀቁ መከሯቸዋል።

*ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚኾን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።*

እኛ ባለንበት በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ዘንድ *ካሪዝማዊ ዝንፈቶች* (በየትኛውም ገጽታቸው) ስለ መኖራቸውና እየተስፋፉም ስለ መኾናቸው እየተነገረ ነው። ከሐሰተኛ ነቢያት መበራከት እስከ ምግባራዊ ዝቅጠት ድረስ ያሉ እንከኖች በመንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ሽፋን ሥር አድፍጠው እንደሚፈጸሙ የአደባባይ ምሥጢር ኾኗል።

ገበያ-መር መንፈሳዊነት በጓዳ ተሸሽጎና በአደባባይም ተፎክሮለት እየተዛመተ የሚገኘው በ*ካሪዝማዊነት* እያስመሰለ ነው። “ቅዱስ ዘይት” በብልቃጥ ከማደል ጀምሮ እስከ “ጠበል” ስጦታና የችርቻሮ ግብይት የሚካሄደው በእኛው ዘመን አይደለምን? ችግርና ድህነትን የሚያባርር ነው የተባለ “የተቀባ” የገንዘብ ወረቀት (የብር ኖት) ለጨረታ ቀርቦ እንደሚቸበቸብ አላየንም ወይም አልሰማንም ማለት እንችላለን? ከየአካባቢው መሪ/ዎች ጋር በመመሳጠርና በመሻረክ በየክፍላተ ሀገራቱ በሚዘጋጁ የጀማ ስብሰባዎች ላይ “መርገም ነቃይ” የተባለ ጧፍና ሻማ እንዲሁም የተበጣጠሰ የሸማ ቅዳጅ (መሐረብ) የሚቸረቸረው በዚሁ መንፈሳዊነት ስም በመታከክ እኮ ነው! የሩዝ ተባይ ያው ሩዙን ነው የሚመስለው።

ቃሉ *“አቤቱ አምላካችን ሆይ፥ ከአንተ በቀር ሌሎች ጌቶች ገዝተውናል። ነገር ግን በአንተ ብቻ ስምህን እናስባለን”* (ኢሳ. 26፥13) እንደሚል፣ በቸሩ ጌታ የወንጌል ብሥራት አማካይነት ሸሽተን አመለጥን የምንለው፣ “ይህን መጽሐፍ የጻፈ፣ ያጻፈ፣ ለሌሎች ያነበበ፣ የተሳለመ፣ እንደ ክታብ አንጠልጥሎ የዞረ፣ ‘ከቅዱስ’ ቦታ በተገኘ አመድ፣ ጭቃ፣ ትቢያ … የታሸ፣ የተቀባ፣ የጠጣ፣ የቀመሰ …” የሚለው የባልቲቶች ተረት ዛሬ መልኩንና ቦታውን ቀይሮ እየተስፋፋ ያለው የት ነው?

በሐምሌ 21 ቀን 2006 ዓ.ም. *በየኢትዮጵያ ሚሌኒየም 2000 ፐሬየር ቼይን* አማካይነት የተጠራና የዐዲስ አበባ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተሰባሰቡበት ሰሚናር ተዘጋጅቶ ነበር። በሰሚናሩ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ በመጋበዜ ምክንያት በቦታው ተገኝቻለሁ። ጽሑፌን አቅርቤ





ከመድረክ እንደ ወረድሁ የጸሎት አገልግሎቱ አስተባባሪ ወንድም ሳሙኤል ኀይሉ የዘመኑን ኹኔታ አስመልክተው አንዳንድ ሐሳቦች ይወረውሩ ጀመር። “አስደንጋጭ” ብለው ከጠቀሷቸው መካከል፣ በዚያው ሰሞን በዐዲስ አበባ ከተማ አንድ ሰፊ ጉባኤ ያዘጋጁ “ነቢይት” አስተላለፉ የተባለውን፣ “ዐዋጅ” አካትተዋል። ሴትዮዋ ዐወጁት ተብሎ የተነገረው እንዲህ የሚል ዘግናኝ ነገር ይዟል። “ጌታ ‘ከዚህ በኋላ በምታድዪው ዘይትና ውሃ ብቻ ሳይኾን፣ ገና በስምሽ እንኳ የሚጸለየውን ጸሎት እሰማልሻለሁ’ ብሎኛል።” እነሆ ዘመናዊዋ ክርስቶስ ሰምራ መጣች ማለትም አይደል? በጣም ያሳዝናል፤ ያስቈጣልም።

ሌሎች ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ወዛቸውን (ላባቸውን) የጠረጉበትን ለስላሳ ወረቀት ሳይቀር “በረከት አለውና ወስዳችሁ ተጠቀሙበት” የሚሉ ጨካኞች እንዳሻቸው የሚፈነጩት እኔና እናንተ ባለንበት ዘመንና መድረክ ላይ አይደለም ወይ? እነዚህ ሰዎች ለራሳቸው ያላቸው ግምት ከፍተኛ ከመኾኑ የተነሣ፣ እጃቸውን መጨበጥ መቻል የተለየ መንፈሳዊ ክብር እንደሚያስገኝ ሲያስተምሩ ምላሳቸው ትንሽ አይደናቀፍም። “እያንዳንዳችሁ ዐሥር ሺህ ብር የምትሰጡ ሃያ ሰዎች በዚህ ጉባኤ እንዳላችሁ ጌታ ይናገረኛል” እየተባለ “መንፈሳዊ” ማጅራት መቺነት ሲካሄድ አላየንም ወይም አልሰማንም ይኾን? “እንደ ሰጎን ዐንገታችንን ከአሸዋው ውስጥ ቀብረን”[63] ዐይንና ጆሯችንን ካልደፈንን በቀር፣ ያየነውም የሰማነውም መዓት (ጉድ) ሞልቷል። ማናችንም ደግሞ ከተጠያቂነት አናመልጥም፤ ለምን/እንዴት አናመልጥም? ባናደርገውም እንኳ በዝምታችን ዐግዘናቸዋልና እንዴት ልናመልጥ እንችላለን?

ማን እንደሾማቸው የማይታወቁና ለየትኛውም ተቋማዊ ሥልጣን ተጠያቂነት የሌላቸው “ነቢያት” ጓዳ ጐድጓዳውን እያጨናነቁ ነው። በእነሱም ምክንያት ስንት ቤት እንደ ፈረሰ፣ ስንት ሕይወት እንደ ከሸፈ እግዚአብሔር ይቍጠር። በየአጥቢያው መካከል በማስታመም ላይ ያሉትን “ቍስለኛ” ግን የሚያውቁ

[63] ይህ ታዋቂ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ *“hiding the head in the sand, like an ostrich”* ቍም ነገር አዘል መኾኑ ባይካድም፣ ሰጎን ዐንገቷን በዚህ መልክ የምትቀብርበት ልማድ ግን እንደሌላት የታወቀ ነው።

ያውቁታል። ያለ ምንም ተጠያቂነት የማስታወቂያ ሰሌዳ አሳትሞ መለጠፍ የቻለ ግለሰብ ኾነ ቡድን በሺህዎች የሚቈጠሩ ምእመናንን እያሰባሰበ ስንት በደል እንደሚፈጽም የታወቀ አይደለምን?

“የቡሽሪ ቀውስ” ተብሎ ወደ መጠራት የደረሰው የአንድ ሰሞን ግርግር ለዚህ አባባላችን ማስረጃ ይኾናል። የቡሽሪ የፎቶ ምስል ያለበት “ቡሽሪ ዘይት”፣ “ቡሽሪ ሳሙና”፣ “ቡሽሪ ቅባት” እና “ቡሽሪ ቅዱስ ውሃ”ን በገበያ ላይ በማቅረብ የሚዘገንን ጥፋት ሲፈጸም እንደ ነበር የዐይን እማኞችና ጥናት ያደረጉ ወገኖች አስታውቀዋል። ለምሳሌ ያህል ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በተዘጋጀ አስቸኳይ ሴሚናር ላይ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ቀጥሎ የቀረበውን ሐሳብ ይናገራል፤

> “ቡሽሪ ሳሙና” የንግድ ችግር ላጋጠማቸው ነጋዴዎች ገበያ ሳቢ፣ በትዳራቸው ችግር ላለባቸው ባለ ትዳሮች የችግራቸው መፍትሔ፣ በገንዘብ ዕጥረት ለሚቸገሩም የተትረፈረፈ ገንዝብ የሚያስገኝና ለሕሙማን ፈውስ የሚሰጥ [ነው ከመባሉ በተጨማሪ] … መንፈሳዊ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ነፍስ ከኀጢአት የሚያነጻ እንደ ኾነ፣ ዘይቱም ቢኾን ለነፍስ ድኅነትን እንደሚያስገኝ ነው ቡሽሪ የሚናገሩት። በነገራችን ላይ ሰውዬው የሚሸጡት ውሃ፣ ሳሙናና ቅባት የሰዎችን ሁለተናዊ ችግር ሊፈታ የሚችለው በግዥ ሲኾን ብቻ ነው። የሰው ልጆችን ኀጢአት የሚያነጻ ከኢየሱስ ደም ሌላ ተገኘ ማለት ነው? (ዕብ. 9፥7-13፡20፤ 1ዮሐ. 1፥7 ይመ.)[64]

ከዚህ የበዙና የገዘፉ ነገር ግን በአደባባይ ለመጻፍ የሚያሳፍሩና የሚያስፈሩ ጕዶች እንደሚደረጉ የታወቀ ነው። ለማለት የተፈለገው ምንድነው? ለማለት የተፈለገው፣ በመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ስም የሚፈጸሙ ግድፈቶች መኖራቸው ከአከራካሪነት ዐልፏል የሚል ነው። ለእነዚህ ግድፈቶች መንሥኤ የኾነውም

[64] የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ነገረ መለኮት ት/ቤቶች ኅብረት፣ *የሼፐርድ ቡሽሪ የዐዲስ አበባ አገልግሎት ግምገማና ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች* (ዐዲስ አበባ፡- ያልታተመ ጽሑፍ፣ ግንቦት 23 ቀን 2006 ዓ.ም.) 8።





የአስተምህሮ መዳደል ነው። በተዘዋዋሪም ካሪዝማዊ ግድፈቶቹ አስተምህሯዊ መመሰቃቀል ሊፈጥሩ መቻላቸው የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን አንደኛው ተግዳሮት ኾኗል እያልን ነው። እነሆ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስትና ዙሪያውን ከከበቡት ሌሎች ዘመነኛ ፈተናዎች በተጨማሪ ከዚህኛውም ጋ ተፋጦ ቆሟል።

ይህን አስመልክቶ ዕርማት እንዲደረግ የተለያዩ ትምህርቶች፣ ሥልጠናዎችና ዐውደ ጥናቶች በተለያዩ ቤተ እምነቶች ሲሰጡና የምልጃ ጸሎቶችም ሲካሄዱ ታይቷል።[65] የችግሩ መስፋፋት ያሳሰባቸው ወገኖችም የመፍትሔ ርምጃዎች እንዲወሰዱ እየጮኹ ይገኛሉ።

ለምሳሌ፣ *ማቴቴስ* መጽሔት በኅዳር 2003 ዓ.ም. ባወጣው የፊት ገጽ ሐተታው “ቤተ ክርስቲያን አደጋ ላይ ነች!” ብሎ ነበር። “አደጋዎቹን”ባሳየበት ርእሰ አንቀጹም ላይ በዚህ ዘመን የሚታዩ ውስጣዊ የቤተ ክርስቲያን ቀውሶች ምን እንደ ኾኑ አትቷል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ይኸው የካሪዝማዊ እንቅስቃሴ መዛባት መኾኑን ጠቍሞ ዐልፏል። ይቀጥልናም፣

> የክርስትና አስተምህሮን ማእከል ያደረገ የአመራር ችግር [መባስ]፣ የእውነተኛ እረኝነት አገልግሎት ዕጦት፣ የእርስ በርስ ግጭትና መከፋፈል፣ የስሕተት ትምህርት፣ የሐሰተኛ ነቢያት መበራከት፣ <u>*ካሪዝማዊ ቀውሱ በአሰፈሪ ኹኔታ መጨመሩና ስሜታዊነት ማየሉ*</u> … (<u>*አጽንዖት*</u> የተጨመረ) [66]

ዘመኑን መዋጀት በተቸገረችው የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው በማለት በቍጭት ያሳስባል። ይህ ቍጭት የጥቂት ወገኖች

[65] ምሳሌ ለመስጠት ያህል፣ “በኢትዮጵያ ኒው ሚሌኒየም 2000 ፕሬየር ቼይን” አማካይነት በተዘጋጀና በመቶዎች የሚቈጠሩ ተሳታፊዎች በመጋቢትና ሚያዚያ 2006 ዓ.ም. ለ21 ቀናት በተሳተፉበት የጾም ጸሎት መርሐ ግብር ላይ ይህ ርእሰ ጕዳይ ከዐበይት አጀንዳዎቹ አንዱ ኾኖ ቀርቦ ነበር።
[66] *ማቴቴስ*፣ ቍጥር 17፣ ኅዳር 2003 ዓ. ም.፣ ገጽ 2።

መብሰልሰል ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ቀጣዩ አንቀጽ ይህ ሥጋትና ቍጭት ዳርቻው ሰፊ መኾኑን ያወሳል።

የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና አገልጋዮች በተሳተፉበት አንድ ዐውደ ጥናት ላይ የውይይቱ ሊቀ መንበር የነበሩት ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ “ይህ አሳሳቢ ጒዳይ በአብዛኞዎቻችን የቈየ ሥጋትና ፍርሀት እንደ ነበረ እናውቃለን” ካሉ በኋላ፣ የጉባኤውን ማጠቃለያ ዐቋም እንደሚከተለው አቅርበዋል፤

> የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚታዩት የአምልኮና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ የሚሹ መኾናቸውን ሁላችንም አምነንበታል። ችግሩ ወቅታዊ ምላሽ ካላገኘ ዐዳዲስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚጨመሩ ምእመናን ዕንቅፋት ከመኾኑም በላይ በውስጥ ለሚገኙትም ክርስቲያኖች ቅሬታንና ራስን ማግለል የሚያስከትልና በአጠቃላይ ለወንጌል ሥራ መሰናክል እንደሚኾን ለማጤን ችለናል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የኾንን ሁሉ ምእመናችንን በድፍረትና በፍቅር እውነቱን ማሳየትና ማስተማር እንደሚገባንም ተገንዝበናል።[67]

ጥሩ ነው። ኾኖም ግን አብያተ ክርስቲያናቱ፣ በዚህ ዐቋም መግለጫቸው መሠረት፣ ባለፉት ዓመታት ምን ያህል “በድፍረትና በፍቅር እውነቱን” ማስተማር ችለው እንደ ነበር ብንጠይቅ ድፍረት ይኾናል?

እውነቱን የማሳየቱና የማስተማሩ ርብርብ መቀጠል አለበት። ይህን ንዑስ ርእስም ያነሣነው ያለ ምክንያት አይደለም። *ካሪዝማዊ ዝንፈቶች* ከአስተምህሮ ጋር ቀጥተኛ ቍርኝት አላቸውና ነው። ትክክለኛ አስተምህሮ በሌለበት ስሕተት ስለሚሰፍን አስመሳይነትና ስሜታዊነት የተጫኗቸው ልምምዶች በማኅበረ ምዕመኑ መካከል መንሰራፋታቸው አይቀርም። ሐሰተኛና ቀውስ የወረረው እንቅስቃሴ የተሳሳተ ትምህርት እንዲቀፈቀፍ በር ይከፍታል። ይህን ጥፋት የሚያባብሰው ደግሞ የአመራር ችግር በተጓዳኝነት ያጋጠመ እንደ ኾነ ነው፤ እኛ ደግሞ ከዚህ ተጓዳኝ ችግር ያመለጥንም አይመስልም።

[67] ንጉሤ ተፈራ፣ “የማጠቃለያ ሐሳብ፣” *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች*፣ 45።





## 2.3 “የነፍስ አባቶች”[68] አመራር ቅርቃር ሥር

አሁን፣ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ግለ ሰቦች የሥልጣን ማእከል እየኾኑ የመምጣታቸው ነገር የከፋ መዘዝ የሚያስከትል ያፈጠጠ ችግር ኾኗል። የአንድ ሰው ገደብ የለሽ አመራር ያለተጠያቂነት መስፈኑ ውሎ አድሮ የራሱን ችግሮች ይዞ መምጣቱ አይቀርም።

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ማንሣት ተገቢ ይኾናል። የአመራር መዋቅሩ “ቡድናዊ ወይስ ግለ ሰባዊ ይኹን?” የሚለውን ዘመን ያስቈጠረ ንትርክ በመቈስቈስ የአመራር ዐይነትን በችግር ምንጭነት መፈረጅ የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ የምልከታ ነጥብ አይደለም። አንዲት ማኅበር በየትኛውም መልክ የተዋቀረ የአመራር ሥርዐት ቢነደፍላትም፣ ትክክለኛው የሥልጣን ምንጭና ማእከል ተገቢውን ቦታ እስካላገኘና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኾኑ የክርስቲያን አመራር መሠረታውያን እስካልተተገበሩ ድረስ ትርምሱ መቀጠሉ አይቀርም።

ከእነዚህ የአመራር መሠረታውያን መካከል አንደኛው መሪዎች የጌታ ቤተ ክርስቲያን ባለዐደራና *አገልጋዮች (ሎሌዎች)* መኾናቸውን ካለመገንዘብና ይህንኑ በሚገልጥ መንገድ ካለመመላለሳቸው ጋር የተዛመደው ዋነኛው ነው። ይህ አገልግሎት “የፊተኛነትን” ክብር “ኋላ በመቅረት” ውስጥ የሚማጸን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት በፍቅር ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ሲኾን፣ መገለጫው ደግሞ ሎሌያዊ ርኅራኄና ምሳሌያዊ የሕይወት ንጽሕና ነው። የሚቀዳውም ከራሱ “የእረኞች አለቃ” ከተባለውና የመንጋው ባለቤት ከኾነው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ኑሮ ውስጥ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ያሳስባል፤

[68] “የነፍስ አባት” የሚለው ትርጓሜ የተወሰደው “አበ ነፍስ” ከሚለው የግእዝ ሥያሜ ሲኾን በልሙጥ የቃም ፍችው በላይ እንዲናገር ተፈልጎ የቀረበ ነው። ይኸም በታሪካዊ ሃይማኖታዊ ቀዳሚው የምእመናን “ባለዐደራዎችና የእግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢያን” (1ቆሮ. 4፥1) በዚያ የነበሩ ሰዎች (ከተፈቀደላቸው “እንደ ሎሌ” የመቈጠር ኀላፊነት ንረው) ወደ ባለቤትነት ደረጃ ሲመጥቁ የሚከሠተውን ጥፋት ለማሳየት እንዲችል ጥቅም ላይ ውሎ ስለ ተገኘ ነው።

*አኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የኾንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይኾን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይኾን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ኹኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኀይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ* (1ጴጥ. 5፥1-4)።

መሪዎች የመንጋው ባለዐደራዎች ኾነው የተሾሙ የክርስቶስ ሎሌዎች እንጂ ጌታዎችና አለቃዎች አይደሉም (1ቆሮ. 4፥1)። የከበሬታን ቦታ የሚፈልጉ፣ ወንበር የሚያፋጃቸውና መንጋውን የሚጠቀሙበት ሳይኾኑ፣ በእግዚአብሔር ልጅነታቸው ደስ ከመሰኘታቸው ጐን ለጐን ታማኝ አድርጎ በመቍጠር የሾማቸውን አምላክ የሚያከብሩ ትሑታን ሎሌዎችና የእግዚአብሔር የጸጋ ሠራተኞች ናቸው። ጐትፍሬድ አሴ-ሜንሳህ የተባሉ ጸሐፊ *ሎሌ መሪዎች ይፈለጋሉ* በተባለ መጽሐፋቸው የተከበረና በትሕትና የተሞላ መሪ ምን መምሰል እንዳለበት ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ምሳሌነት ጋር በማነጻጸር ይጽፋሉ፣ ይጠይቃሉም፤

> እኛ የሕያው እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን [እኮ]። የከበሬታን ስፍራ በተመለከተ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ከዚህ የበለጠ ምን እንሻለን? በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ወራሾች መኾንን የመሰለ ታላቅ ክብር ተጐናጽፈን ሳለ፣ ለምንድር ነው በሌላ መሠረት ላይ ቆመን ማንነታችንን ለማጕላት የምንጣጣረው? ጌታ ማን እንደ ነበረና የተሰጠውም ሥልጣን ምን እንደ ኾነ ያውቅ ስለ ነበረ የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ነጻ ነበረ።[69]

መሪዎች በፍቅራቸውና በመልካም ሥነ ምግባራዊ ኑሯቸው ለመንጋው ምሳሌ መኾን ይጠበቅባቸዋል። የመሪነት ጥሪ፣ ተሰጥዖና ሸክም የሌላቸው ሰዎች አገልግሎታቸው ፍሬ አልባና ለእግዚአብሔር ክብር የማያመጣ ከንቱ ሩጫ

[69] ጐትፍሬድ አሴይ-ሜንሳህ፣ (ተርጓሚ ሚናስ ብሩክ)*ይፈለጋሉ፦ አገልጋይ መሪዎች* (ዐዲስ አበባ፦ ኤስ. አይ. ኤም.፣ የኅትመት ዘመን ያልተገለጸ) 10-11።





ነው። ይህን ዐይነት ሰዎች ተከታዮቻቸውን በማወክ፣ በማበጣበጥና በማሳት ለጥፋት ሊዳርጓቸው ይችላሉ። “እንደነዚህ ዐይነቶቹ መሪዎች ሌሎችን ስለ ማገልገል ከልብ የኾነ አመለካከት የላቸውም። ራሳቸውን አጕልቶ ማሳየት እንጂ እግዚአብሔርን በመምሰል ምሳሌ የመኾን ሐሳቡም የላቸውም።”[70]

በዘመናችን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ከሎሌያዊ ባለዐደራነት ይልቅ የየማኅበራቱ ባለርስት የኾኑ ያህል የሚቃጣቸው መሪዎች ቍጥራቸው እየተበራከተ የመጣ ይመስላል። ዶ/ር ልደቱ ዓለሙ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያን መሪዎችን የአመራር ዘይቤ አስመልክተው ባዘጋጁት አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ያሰፈሩትን ማንበብ ብቻ ይህን አሳዛኝ ገጽታ አጕልቶ ያሳየናል፤ ከፊታችን የተደቀነ ፈተናችን መኾኑንም ይናገራል።

> “እጅግ ብዙ መሪዎች” ለማለት በሚያስደፍር ኹኔታ፣ አሁን ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሪነት ጥሪና ተሰጥዖ የሌላቸው ሲኾኑ “መሪና የመሪ ባሕር[ያት]” አልተገናኙም። ... “ክብርን ሥልጣንን ገንዘብን መውደድ” የሚታይባቸው እንዲሁም “ራሳቸውን ብቻ ለማገልገል የሚናፍቁ” ናቸው። ከዚህም በላይ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ራሳቸው የግል ድርጅት ወይም ኩባንያ የሚቈጥሩ ጥቂት የማይባሉ መሪዎች መኖራቸው ከአመራር ጋር የተያያዘና የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን ተግዳሮት ብቻ ሳይኾን ትልቁ ፈተናዋም ነው።[71]

የእግዚአብሔር መንግሥት አንዱ ሌላውን የሚያገለግልበት የእምነት ማኅበረ ሰብ እንጂ አንዱ በሌላው ላይ ጌታ ኾኖ የሚሠለጥንበት አለመኾኑን ክርስቶስ አስተምሯል። “*ከመካከላችሁ ታላቅ መኾን የሚፈልግ ሁሉ፣አገልጋይ ይኹን፤ ፊተኛ ለመኾን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይኹን*” (ማር. 10፥43-44 *በመት*) ብሏል። ጳውሎስም በዚሁ ሐሳብ መሠረት መኖር እንዲገባን ሲገልጽ፣

[70] አሴይ-ሜንሳህ፣ *አገልጋይ መሪዎች*፣ 28።
[71] ልደቱ ዓለሙ፣ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአመራር ገጽታ*፣ ያልታተመ፣ 2006 ዓ.ም.፣ 10።

“በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ኹኑ” (ገላ. 5፥13) በማለት መክሯል። የኛ ነገር ግን የተገላቢጦሽ እየኾነ የመጣ ይመስላል።

በግልጽ እንደሚታወቀው፣ ታሪካችንና ባህላችን በአመራር ጠቅላይነት ከፉኛ “ተጠምቆ የደቆነ” ከመኾኑ የተነሣ፣ ይህንኑ የአገዛዝ እርሾ ይዘን ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመምጣታችን፣ ያው ተመሳሳይ አባዜያችን “ሳያቀስ ላይለቀን” የዘመተብን ይመስላል። ስለ ኾነም፣ ቤተ ክርስቲያን “ኀላፊነቱ ያልተወሰነ የግል ማኀበር” ትመስል በግለ ሰቦች ቀጥተኛ ተጽዕኖ ሥር የተንበረከከችባቸው አያሌ አስረጅ ኹነቶች ሞልተዋል። በትንንሽ ኵርፊያና አለመግባባት የተነሣ አባላት ሲበተኑ፣ ሲታወኩና ሲከፋፈሉ የምንመለከትበት አስከፊ ጊዜ ላይ መድረሳችን ምስጢርነቱ አከትሟል።

ስንት ጊዜ ነው በመሪዎች ምርጫ ሥነ ሥርዐት ላይ በቡጢ እስከ መደባደብ የደረሱ ኹከቶች መፈጸማቸው የተሰማው? የአንድ ቤተሰብ አባላት ሳይቀር ተቧድነው አመራሩን የሚቈጣጠሩበት ኹኔታ መኖሩን ከጥቂት ዓመታት በፊት በጒዳዩ ላይ ጥናታቸውን ሠርተው ሲያበቁ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ላይ ጽሑፋቸውን ያቀረቡት ዶ/ር ሳምሶን እስጢፋኖስ ለጉባኤው ተሳታፊዎች ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው።

ወጥ አስተምህሮ የሌላቸው ማኅበራት ማእከልነቱን ማስጠበቅ በቻለው ግለ ሰብ ቀጥተኛ የአስተምህሮ መሥመር ተላሚነት ላይ መንጠልጠላቸውም በሰፊው ይታያል። በጥናቱ ከተካተቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በአንዷቱ የተከሠተውን ለምሳሌ እንጥቀስ። ይህች ማኅበር እንደ ቤተ ክርስቲያን ከመመዝገቧ አስቀድሞ በመጋቢው ስም በሚኒስትሪነት ብቻ ትታወቅ ነበር። መጋቢው በፈለጉ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለወጠች። መጋቢው ያስተምሩ የነበረው በዘመኑ አብዛኛው የአደባባይ ሰው የተጠመቀበትን “የእምነት ቃል” እና “የብልጽግና ወንጌል” ትምህርት ነበር። እኒህ መጋቢ ከዓመታት የቅዱሳት





መጻሕፍትና የነገረ መለኮት ጥናታቸው በኋላ የቀድሞ አስተምህሯቸውን ስሕተት ለይተው አረጋገጡ፤ አጠቃላይ የአስተምህሮ ለውጥም አደረጉ።[72]

እነዚህ እርምጃዎች ትክክል ቢኾኑም ውጤቱ ግን ለአንዳንዶች መራር እንደ ኾነባቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አንድ ሌላ የአመራር አባል ተናግረዋል፤ “ጥቂት በማይባሉ አባላት ላይ ያልተጠበቀ ዱብ ዕዳ ነው የወረደባቸው፤ በሕይወት የተፍገመገሙትም ጥቂት አልነበሩም። እንደገና ዐዲስ የነገረ መለኮታዊ አስተምህሮና የአስተሳሰብ ዘለበት ለማግኘትም ዋጋ አስከፍሏቸዋል”[73] በማለት ተናግረዋል።

ወደ ተነሣንበት ስንመለስ መሪነት ስለ ፈለግነው ብቻ የምናገኘው ወይም ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠው ዕድገት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። መሪዎችን የሚያስነሣ እግዚአብሔር ራሱ ነው። በዙሪያችን የምናየው ግን አሳሳቢ ነው። የአንድ ግለሰብ ገደብ የለሽ አመራር እዚህም እዚያም በስፋት ይታያል። ከዚህ በተጨማሪም “ባለ ራእይነቱን” ያረጋገጠው መሪ አስተምህሮን ጨምሮ በማንኛውም ጒዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጭ ይኾናል። በትምህርታቸው ላይ ግልጽ ስሕተት እንኳ ፈጽመው ሲገኙ ማስተካከያ ለማድረግ እንዲችሉ የሚያግዝም ኾነ የሚገሥጽ ጠያቂ የሌላቸው መሪዎች ጥቂት አለመኾናቸው። ይህ ያልተገደበ ሥልጣን፣ መዘዙ ብዙ የሚያማዝዝ እየኾነ ነው።

የዚህ ሁሉ ጣጣ መንሥኤ የግለ ሰባዊ ዝና አምልኮ መስፋፋቱ ይመስላል። በጥናታችን ወቅት የተመለከትናቸው በርካታ መምህራንና ሰባክያን መድረካቸውን ብቻ ሳይኾን፣ አሠራራቸውን ጭምር ራሳቸውን ለማጕላት በሚችሉበት መንገድ አመቻችተውታል። ገድላቸውን በመተረክና በማግነን ተግባር ከፉኛ ስለተጠመዱ በተከታዮቻቸው ዘንድ (በየትኛውም መስክ)

[72] እኒህ ወንድም ከተሰጣቸው ጸጋና ከእግዚአብሔር ቃል በመማር ከደረሱበት አስተውሎቶች የተነሣ፣ እግዚአብሔር ቢፈቅድ ለምድራችን በረከት ስለ መኾናቸው የጸሐፊው ጥልቅ ተስፋ ነው። በተመሳሳይ እንቅስቃሴ ውስጥ ለነበሩና ላሉት ሁሉ አርአያ የሚኾኑ ናቸው።

[73] ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ እንደ ተናገሩት። መጋቢ “መ”፣ ቃለ መጠይቅ፣ ታኅሳስ 2003 ዓ.ም. ዐዲስ አበባ፣ በጸሐፊው እጅ የሚገኝ ማስታወሻ።

የእነርሱ ሐሳብና ውሳኔ የመጨረሻው ቃል ተደርጎ እንዲወሰድላቸው ተግተው ሠርተዋል። አንዳንዶቹም አገልግሎታቸውና ሥልጣናቸው “ሐዋርያዊ” ስለኾነ፣ ማንም ሊዳፈራቸው እንደማይችል በአደባባይ ሲመሰከሩ ምላሳቸውን አያደናቅፈውም።[74] በአባሎቻቸው የግል ሕይወትና ዐበይት ምርጫዎች ላይ ሳይቀር የወሳኝነት ሥልጣን በቃል ኪዳን የተቀዳጁ ወገኖችም አሉ።

እነዚህ ሰዎች፣ የተናገሩት እንዳይመረመር ብቻ ሳይኾን፣ ትምህርታቸውና ልምምዳቸው እንዳይፈተን የምዕመናንን ኅሊናዊ ነጻነትና ዳኝነት በማይነቃነቅ ቃለ-ግዝት ወጥረው ቸንክረዋል። በእነርሱና ትምህርታቸው ላይ (ከመሥመር በወጡ ጊዜ እንኳን) ጥያቄ ማንሣት መንፈስ ቅዱስን እንደ መቃወም፣ የእግዚአብሔርን ቅቡዓን እንደ መተናኰስ፣ ሲብስም እንደ ሰይጣን ሐሳብ ተደርጎ እንዲቈጠር ያስጨበጡት አስተሳሰብ “በክረምት የተተከለ ችካል” ኾኗል። ማን ይነቅለዋል?

የዚህ አዛዥ ናዛዥነት አባዜ ሥር እየሰደደ ከመሄዱ የተነሣ በርካቶች ለራሳቸው በሚወስዱት የማዕረጋት ዐይነትና ላይ ከፉኛ እንዲንጠለጠሉና በሽሚያ መልክ እንዲራኮቱ ኾነዋል። ዛሬ “የእግዚአብሔር ሰው”፣ “ፓስተር”፣ “ሐዋርያ”፣ “ነቢይ”፣ “የመጨረሻው ዘመን መልአክ”፣[75] “የተቀባ” ወዘተ. ተብሎ የመጠራት ጥማት “የሞት ሽረት” ተጋድሎ የሚደረግበት አይደለምን? (ይህን ማዕረግ-ተኰርነት ለማሳየት ያህል “ፓስተር” ብለን ያልጠራናቸው እንደ ኾነ

[74] አንድ ትልቅ ስም ያላቸው “ሐዋርያ” በአደባባይ ሲናገሩ እንደ ተደመጠው፣ ሐዋርያ ተሳስቶ እንኳ የተገኘ እንደኾን፣ ሊያርመው የሚችለው እንደሱው “በሐዋርያዊ ሥልጣን የተቀባ” ሰው ብቻ የመኾኑን ግዴታ አጽንዖት ሰጥተዋል።

[75] ቢያንስ ሁለት “ሐዋርያ” እንደ ኾኑ ከስማቸው ፊት ማዕረጋቸውን የሚጠቅሱ ወንድሞች፣ “የመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር መልአክ” መኾናቸውንም በቅጥያነት ያኖሩባቸው ማስረጃዎች ተገኝተዋል። አንድ ሌላ ግለ ሰብ፣ እንዲያውም፣ ማዕረጉን ለፔፐት (APEPT) ብለው እንዲጠሩት በመድረክ ላይ ማዘዙ ተሰምቷል። ይኸውም፣ *Apostle, Prophet, Evangelist, Pastor-Teacher* (ሐዋርያ-ነቢይ-ወንጌላዊ-መጋቢ-መምህር) ነኝ የማለቱ ምኅጻረ ቃል መኾኑ ነው።





ፊታቸው ቅጭም የሚል አገልጋዮች መኖራቸውን ብንጠቅስ ሐቅ ለመኾኑ ከአንባቢያን በቀር ማን ምስክር እንጠራለን?[76])

በዚህ ግብግብ ጦስ፣ በአሳዛኝ መልኩ፣ አብያተ ክርስቲያናት እየተከፋፈሉ ነው። በነበሩበት አጥቢያ ወይም ቤተ እምነት ይህን የማዕረግ ጥማታቸውን ማርካት ያልቻሉ “ጕበዛዝት” የየራሳቸውን ድርሻ ከመንጋው ላይ “በጨቅ” አድርገውና ከፊታቸው በሚሄዱ ጥቂት “ሠረገላዎች”ታጅበው፣ “መለከት በመንፋት” በግልጽና በይፋ “የራሳቸውን ቸርች መከፈታቸውን” ያውጃሉ። “በመገለጥ ያገኘሁት ነው” የተሰኘ ሰበብ እየሰጡም አስተምህሯቸውን በወደዱት መንገድና ያለምንም ተጠያቂነት ያስሄዱታል።

“የአደባባይ ሰው” መኾንና ዝነኛነት (*popularity and celebrity*) ስር እየሰደደ መምጣቱ አስተምህሮን ለመበረዝ አስተዋጽኦ ማበርከቱ አልቀረም። ብዙ ጊዜ እንደታየው ከቀድሞ ቤተ ክርስቲያናቸው የወጡ አገልጋዮች ተከታዮቻቸውን ለማበራከትና የእነርሱን አገልግሎት ዐዲስና ትኩስነት ለማጽናት በመሻት ቀዳሚዎቹን ቤተ እምነቶቻቸውንና አስተምህሮዋቸውን በገሀድ ሲደበድቡና ሲያብጠለጥሉ ይታያል። በዚህም ሰበብ ለአስተምህሮ መሳከር በር ተከፍቷል። በአጠቃላይ መንግሥተ-እኔ እየተንሰራፋ የመንግሥተ እግዚአብሔርን ትምህርት እየጋረደው ነውና የክርስቲያናዊ አስተምህሮ በመንጋደድ ላይ ነው ብንል የተጋነነ አይኾንም። ይህ አደገኛ አዝማሚያ የመስቀሉ ሥራ ውጤት የኾነውን ቤዝዎታዊ ወንጌልና መስቀሉን መካከለኛ ያደረገውን ራስን የመካድ መሰጠት ችላ እንድንል እያደረገ መኾኑ በግልጽ የሚታይና የሚሰማ ነው። በዚህ ዘመን ጐልቶ ከሚታዩት ችግሮች መካከል ሌላው ችግር ይኸው ነው፤ በ “መስቀል አልባ ወንጌል” መከበብ።

[76] በዚህ ጥናት ወቅት በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ አገልጋይ እንደ ተናገሩት፣ በአንድ ወቅት እርሳቸው ወደሚያገለግሉባት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሰብከት የጋበዟቸው ሰው በዕለቱ መርሐ ግብር የመድረክ አስተናባሪ አማካይነት ስለማንነታቸው ለማኅበረ ምዕመኑ በተዋወቁ ጊዜ፣ “ወንድማችን ... ያገለግሉናል” ማለታቸውን ተከትሎ፣ ተጋባዡ አገልጋይ መድረኩን እንደያዙ፣ የመድረክ አስተናባሪውን በሚሠቀጥጥ ኹኔታ ከመዝለፋቸውም በተጨማሪ፣ “በስንት መከራ ያገኘነውን ፓስተርነት ልትገፍፉን ፈለጋችሁ ወይ?” ማለታቸው ተገልጿል።

## 2.4 *መስቀል አልባው "ወንጌል"*

*"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ"* (ገላ. 6፥14)።

ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የዓለም መድኅኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ (ማር. 15፥24፤ ዮሐ. 19፥18) ደሙን በማፍሰሱ ምክንያት፣ *"በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘተናል፤ እርሱም የበደላችን ስርየት"* (ኤፌ. 1፥7) ነው። *"ደም ሳይፈስ ስርየት የለም "* (ዕብ. 9፥22)። ስለዚህ ክርስቶስ ደሙን ሰጠ። ዐዲሱ ኪዳን ተመርቆ በተከፈተበትና (ዕብ. 9፥15፡18) የኀጢአታችን ማስተሰረያ ይኾን ዘንድ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ንጹሕ ደሙ (ቆላ. 1፥19) አማካይነት ታጥበን (ራእ. 1፥5) በመንጻት ወደ እግዚአብሔር መግባት ኾኖልናል (ሮሜ. 5፥2፤ ኤፌ. 2፥18፤ ዕብ. 10፥19-20)። ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን።

እንግዲህ ይህን እውን ለማድረግ መድኀኑ ጌታችን ኢየሱስ ስለ ኀጢአታችን የሞተው በመስቀል ላይ ነበር። *"ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ "* (1ጴጥ. 2፥24) ተብሎ እንደ ተጻፈ። ይህ የመስቀል ላይ ሞቱ የመከራና የሕማም ጣር የተሞላ ነበር። አዳኙ ጌታ በፈቃዱ ለአባቱ በመታዘዝ እንደ ሎሌ ነበር የኖረውና ያገለገለው (ፊል. 2፥6-9፤ ኢሳ. 42፥1-7፤ 49፥1-6፤ 50፤4-9፤ 53፥ 1-13)። ሊያውም የሕማም ጣርና ሥቃይ ያልተለየው "ሥቅዩው ሎሌ" (*The Suffering Servant*) ነበር። በመጨረሻም፣ ይኸው "ሥቅዩ ሎሌ"ድኅነትን ያስገኘልን ዘንድ በእንጨት ላይ ተሰቀለ። ስለዚህ *የተሰቀለው መሲሕ* ተብሎ ተጠራ (ማቴ. 26፥1-27፥56፤ 1ቆሮ. 1፥23)።

ከዚህም የተነሣ፣ ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ሁለት ሺ ዓመታት መስቀሉን ማእከል ያደረገውን ወንጌል ስታበሥር ኖራለች፤ *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን*





*እንሰብካለን"* (1ቆሮ. 1፥23) እያለች። የመንግሥቱ ወንጌል ቤዝዎታዊ እውነቱ የሚታየው ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ነውና። ያልተዋጁ ንጉሡንም ኾነ *መንግሥቱን አያዩትም።*

በአንጻሩ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ በኾነ ትምህርትና ኑሮ የመስቀሉን መልእክት አዛብታ የተገኘችበት ወቅትም ነበረ፤ ዛሬም አለ። ከእነዚህ ግድፈቶች መካከል የተወሰኑትን ማለትም ከሥቅዩው ሎሌ ይልቅ ማሠቃያውን፣ የመከራው ተካፋይነት ከሚገለጥበት የመስቀል ኑሮ ይልቅ ምልክታዊ ጌጥነቱን ማስቀደማችንን እንዲሁም መስቀሉን ማእከል ካደረገው ትምህርት ይልቅ ቅምጥልነትን የሚያስፋፋውን "ዘመነኛውን ወንጌል" ማስበለጣችንን በማንሣት እንታረምበት ዘንድ ዐጭር ሐሳብ ሰፍሯል። ከዚያ በፊት ግን የመስቀሉን ምንነት በጥቂቱ ማሳየት ተገቢ ነው። ዋነኛውን ጉዳይ ምን ያህል እየዘነጋነው መኾኑን ለማሳየትም ይጠቅማል።

ለመኾኑ መስቀል ምንድነው? ፋይዳውስ ምንድነው? እንግዲያስ ስለ ነገረ መስቀሉ ትንሽ ማየት ያስፈልግ ይመስለኛል— ምልክትነቱና ክብሩ የሚገባን ያን ጊዜ ነውና! ምልክቱ ከወከለው እውነት በላይ አይደለምና! ደግሞም የመስቀሉ በረከቶች ከመስቀሉ የመከራ ሕይወት ተነጥለው አይገኙምና!

ያለ መስቀሉ ክርስትናን ማሰብ መሞከር አይታሰብም።[77] የቃሉን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም ስናይ፣ መስቀል በሦስት መንገድ ይተረጐማል። አንደኛው ሰው ለቅጣት ይሰቀልበት የነበረ ቀጥ ያለ ወይም የተመሳቀለ እንጨት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስን ወጀአዊ ሥራ የሚያሳይ ትእምርታዊ

[77] ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት አምስት አንቀጾች፣ በቀጥታ የተወሰዱት፣ ጸሐፊው ከዚህ በፊት ካዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ተቀድቶ ነው። (ገብረ መሲሕ፣ *የመምሩ ምርቅና መረቅ፡- በ"የተኩላው ለምድ ሲገፈፍ ውስጥ"* [ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጠም፣ 2002 ዓ.ም.] 46-50)።

ትከ (*symbolic representation of redemption*) ነው። ሦስተኛው ስቅላትን (በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞትን) ያመለክታል።[78]

መስቀል የእግዚአብሔር ጥበብና ኀይል የተገለጠበት ነው። የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ቤዛዊ ሞት የድኅነታችን ምክንያት ከመኾኑም በተጨማሪ የደቀ መዝሙራዊና ምግባራዊ የኑሮ ጠባያችን መሠረት ነውና መሰበክ ያለበት እርሱ ነው (ሉቃ. 24፥46-47፤ 1ቆሮ. 1፥23፤ 2፥2)። ይህ ሰፊና ጥልቅ ርእስ ጉዳይ ነውና በጥቂት ገጾች የሚተረክ እንዳልኾነ ግልጽ ነው። ቢኾንም ነገረ መስቀሉን፣ በጨረፍታ፣ እንደሚከተለው እናየዋለን።

ሰው በእግዚአብሔር አምላክ የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በአጽናፈ ዓለሙ ካሉት ፍጥረታት በሙሉ የተለየና ክቡር አድርጎ ነው። እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮታልና፤ በምድር ያሉትን ፍጥረታት የማስተዳደር መጋቢያዊ ዐደራም ሰጥቶታል። (ዘፍ. 1፥26-28)። ሁሉን በቃሉ ሲፈጥር ሰውን *“ከምድር አፈር አበጀው”* (ዘፍ. 2፥7)። *“በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን ‘እፍ’ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ”* (ዘፍ.2፥7)።

*“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፥ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው”* (ዘፍ.1፥27)። ያዘጋጀለት መኖሪያውም ያማረና የተሟላ የአትክልት ስፍራ ነበረ። *“እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔድን ገነትን ተከለ፤ የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው”* (ዘፍ. 2፥8)። በምድርና በባሕር የሚኖሩትን በሰማይም የሚበሩትን እንዲገዛ እግዚአብሔር ለሰው ሥልጣን ሰጠው (ዘፍ. 1፥26-28)። ታላቁ አምላክ በማይነገር ጥበቡና ፍቅሩ ሰው በብርሃን የተሞላ የክብርና የጽድቅ ሕይወት ይጐናጸፍ ዘንድ ባለሟሉ አደረገው። ሊቁ ጎርጎርዮስ እንዳለው፣ “ከዚህ ክብር የሚበልጥ ምን

[78] J. D. Douglas and Merrill C. Tenney. (eds.), *New International Bible Dictionary* (Grand Rapids: Zondervan, 1987) 241.





ክብር አለ? ከዚህስ ትምክሕት የሚበልጥ ምን የሚያስመካ ነገር አለ? ... ሰውን አምላክ እንደ ፈጠረው እንዲመሰክር ከመኾን የበለጠ ምን ትምክሕት አለ?”[79]

ለሰው የተሰጠው ታላቁ በረከት ከፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት መኖሩ ነበር። የሕይወት ምንጭ ከኾነው አምላክ ጋር በሚኖር ኅብረት ብቻ ሕይወት በክብርና በሐሴት ትቀጥላለችና (መዝ. 36፥9፤ ዮሐ. 1፥4)። ይህን ለማረጋገጥም በመታዘዝ መኖር ይጠበቅበት ነበር። የመታዘዙ ምልክትም “ከፉና ደጉን ከሚያስታውቀው ዛፍ” አለመብላት ነበር። ከዚህ ዛፍ በበላ ቀን እንደሚሞት (ከእግዚአብሔር መለየትን የሚያካትተው መንፈሳዊ ሞትን ጨምሮ) እግዚአብሔር ለአዳም ነገረው (ዘፍ. 2፥15-17)።

ሰው የመረጠው የዐመፃ መንገድ ግን አስፈሪ ነበር። ከአምላኩ ይልቅ “እባቡ” የነገረውን በማመን እግዚአብሔርን “ሐሰተኛ” ለማድረግ ተጣደፈ። በራሱ፣ ያለእግዚአብሔር፣ መኖር እንደሚቻለውና እንዲያውም *“እንደ እግዚአብሔር”* ለመኾን ተመኘ (ዘፍ. 3፥5)። አዳምና ሚስቱ ሔዋንም የተከለከለውን ዛፍ ፍሬ በመብላት በእግዚአብሔር ላይ የተገዳዳሪነት ዐመፅ ፈጸሙ (ዘፍ. 3፥1-6፤ 1ጢሞ. 2፥14)። በዚህም ምክንያት ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ (ሮሜ 5፥12)። ውጤቱም ሞት፣ ኀዘን፣ ውርደትና ውድቀት ኾነ (ዘፍ. 3)። በመተላለፋችንና በኀጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተን ጠፋን (ኤፌ. 2፥1-3)።

አዳምና ሔዋን የሰው ዘር ሁሉ ወላጆች እንደ መኾናቸው፣ በሠሩት ኀጢአት ምክንያት ለመላው ልጆቻቸው ያወረሱት በኀጢአት የወደቀ ጠባይን ነው (ሮሜ 5፥12-14፤ ኤፌ. 2፥3)። አባቶች “ጥንተ አብሶ” (የውርስ ኀጢአት) ብለው የሰየሙት የኀጢአት ተፈጥሮ ሁሉንም የተጠናወተው በመኾኑ፤ በሐሳብ፣ በቃል፣ በሥራ ኀጢአተኛ አደርጎን ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በአካል ክፍሎቻችን ሁሉ ይሠራ ነበር (ሮሜ 7፥5)። የኀጢአት ውጤቱ ደግሞ ሞት

[79] ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. *ሃይማኖተ አበው፣ ዘጎርጎርዮስ* ፣ ም. 36፣ ቍ. 12 (ዐዲስ አበባ:- ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986) 124።

(ከእግዚአብሔር መለየት) በመኾኑ ከኰነኔ በታች ወድቀን ተከረቸምን (ሮሜ 6፥23)። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ አምላክ በመኾኑ፣ ኀጢአታችን ከእርሱ ለይቶን ነበርና (ኢሳ. 59፥2)። እሱው ካልታደገን ምን ተስፋ ነበረን?

ነገር ግን ጨለማው በነበረበት እንዲቀጥል የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምክር አልፈቀደም። ጌታ እግዚአብሔር፣ በመቤዠት ጥበቡ፣ የፈረሰውን ሊሠራው፣ የወደቀውን ሊያነሣው፣ የተበላሸውን ሊያድሰው ፍቅሩና ጥበቡ ቤዛችንን ገለጠው። የዚህ ሰማያዊ ድነት (ድኅነት) አጀንዳ መካከለኛው ደግሞ መስቀሉ (የክርስቶስ ቤዛዊ ሞት) ነበር። ከአብ ጋር በክብር የተካከለ ወልድ ወረደ፤ እስከ መስቀል ሞትም ድረስ ራሱን አዋረደ (ፊልጵ. 2፥5)። ትውፊት “ፍቅር፣ ኀያል ወልድን ከዙፋኑ ሳበው፤ እስከ ሞትም አደረሰው” እንዲል።

ጌታ ኢየሱስ ኀጢአታችንን ተሸክሞ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ (ማቴ. 27፥35፤ 1 ጴጥ. 2፥24) ። የኀጢአታችንን ቅጣትም ተቀበለ (ኢሳ. 53፥5-6)። እግዚአብሔር በመስቀል ላይ በሞተው በልጁ ሞት ምክንያት የእያንዳንዳችንን መከራ፣ ሞትና እርግማን አስወገዷል (ኢሳ. 53፥4፤ ገላ. 3፥13)። በዚህም አደራረጉ ጻድቅ ፈራጅነቱን አሳይቷል (ሮሜ 3፥25-26)። እንዲሁም፣ አንድ ልጁን በመስጠት እግዚአብሔር ፍቅሩን በመስቀሉ ላይ ገለጦልናል (ሮሜ. 5፥4)። ለአመን ለኛም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ዐዲስ በር ተከፈተ (ዕብ. 10፥19-20)። በመስቀሉ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ዐዲስ ኅብረት ለመመሥረትም በቃን። እርሱ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ኾኖልናልና።

በመስቀል ላይ በፈሰሰው በኢየሱስ ደም የኀጢአታችንን ስርየት ስለምንቀዳጅ (ቆላ. 1፥12-14፤ 1ዮሐ. 2፥1-2) በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አግኝተናል (2ቆሮ. 5፥21)። ስለኾነም፣ *“ምሕረትና እውነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ”* (መዝ. 85፥10) የሚለው ዐዋጅ በመስቀሉ ላይ ተፈጸመ።

እግዚአብሔር በጻድቅ ፈራጅነቱ በኀጢአታችን ላይ ከበየነው ፍርድ፣ በተራ ሰው ቤዛነት መዳን ስለማይቻለን፣ አንድያ ልጁን ነው የሰጠው (ዮሐ. 3፥16)።





ጌታ ኢየሱስም በፈቃዱ ስለ ኀጢአተኞች ነው የሞተው (ዕብ. 10፥9)። ይህ ተግባር ደግሞ የፍቅሩን ጥልቀት ያሳያል (ሮሜ. 5፥4)። ትክክለኛ ፍርዱንና ፍቅሩን በአንድነት እውን ያደረገው ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። ከመታወቅ የሚያልፈው ይህ ድንቅ ጥበቡ በክርስቶስ የመስቀል ሞት ተገለጠ—ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብና ኀይል ነውና (1ቆሮ. 1፥23-24)። ስለዚህም *“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነውና”* (1ቆሮ.1፥18) ተባለ። ክብር ለዘላለም ለእርሱ ይሁን፤ አሜን!

እውነቱ ይህ ከኾነ ታዲያ መስቀሉን ወደ ዳር (ጠርዝ) ገፍተን ማእከሉን ለማን ልንሰጠው ነው?! ደግሞም፣ “ከዘመናችን ስብከቶች፣ ትምህርቶችና ዝማሬዎች ውስጥ የመስቀሉን መልእክት ምን ሰወረው?” የሚለው ጥያቄ አንገብጋቢ ነው፤ ልንነጋገርበትም ልንቈጭበትም የተገባ ይመስለኛል።

በየጉባኤው የተዘሩት አንዳንድ ሰባክያን፣ መምህራንና ዘማርያን ሕግን ያለ ጸጋ፣ የሥነ ሥርዐት ርምጃን ከተሐድሶ ውጭ ይሰብካሉ። ግለሰባዊ ድነትን ከማኅበራዊ ርኅራኄ ነጥለው ያመነዥካሉ። ፍቅር በጐደለው ሃይማኖት መመሪያዎችን እንደዶፍ ያዘንባሉ። የመስቀሉን ጥበብ ሸፍነው ዕውቀታቸውን ይደሰኩራሉ። የመሲሑን ግርማ ገፍትረው የራሳቸውን ገድል ይዘምራሉ። ሌሎች “ዝነኞች” በፈንታቸው በ “ክርስቶስ ስም” ሰበብ ሌሎችን ተንከተሰውና ጐረቤቶቻቸውን ዘልፈው ሲያበቁ በመካከላችን እንደ ዐርበኛ በኵራት ይጀነናሉ። ተቃውሞ ከገጠማቸውም ራሳቸውን እንደ ሰማዕት መቍጠር ያምራቸዋል። ለመኾኑ የራሳችንን ስም ዝና ከፍ አድርገን የሰቀልነው መስቀሉን ወዴት ደብቀነው ነው? ምንነቱ የማይታወቅ ሐሳብ እያንበለበልን መንጋውን በማጯጯኽ ላይ የተመሠረተ “መንግሥተ እኔ”ን የማቆም የጥቅመ ሰናኦር መንፈስ እየከበበን ይኾን (ዘፍ. 11)?

ይህ ሐዋርያዊ ድምፅ እንዴት እንደማያቃጭልብን ግራ ነው፤ ጳውሎስ *“በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ ነገር*

*እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና”* (1 ቆሮ. 2፥2) ይላል እኮ። እኛስ ምን ለማወቅና ምን እንዳወቅን ለማሳወቅ ነው በጽኑ የዘመትነው? በሌላ መልኩ ደግሞ በትኩረት ስንታይ የመስቀሉን ክብር እንፈልጋለን፤ ውርደቱን ግን እንሸሸዋለን። ምነው? ባለግርማው መሲሕ *“ሥቅዩው ሎሌ”* አልነበርምን?

አንዳንዶቻችን ደግሞ በተገላቢጦሽ ይቅርታን ከመስቀሉ ውጭ እናውጃለን። ኅብረትን ያለጸጋና ተግሣጽ እናልማለን። ንጉሡን ገፍትረን መንግሥቱን ልንሰብክ እንቃጣለን። ምትክ የለሽ የኾነውን ወንጌል በአርቲ ቡርቲ ተክተን እየተጯጯኽን ሰዎችን ለንስሐ እንጋብዛለን። እግዚአብሔርን ማሳዘናችን ግድ ሳይሰጠን ሰዎች እንዳይከፋቸውና ከስብሰባችን ተለይተው እንዳይቀሩብን እንጠነቀቃለን። መንፈስና ኀይልን በመግለጥ የመስቀሉን ቃል ሥልጣን ማወጅ ስላቃተን፣ ሰሚዎቻችን እንዳያኮርፉ እናቈላምጣቸዋለን። ጆሮቻቸውን የሚያከክላቸውን መርጠን እንነግራቸዋል። የማያስኮርፉንን መምህራን እንደ ምኞቶቻችን ለራሳችን እናከማቻለን። ኧረ! መስቀሉ ወዴት ነው?

ወንጌሉ ትበለጽጋለህ የሚል መልእክት ብቻ ተሸከመ ይመስል ስሙን ሳይቀር ቀይረው “የብልጽግና ወንጌል” ይዘው የመጡ ወንጀል ሰባኪዎች “መስቀሉን ሰቀሉት”[80] ሊባሉ አይገባ ይኾን? እንጀራና ሆድ ይህን ያህል ክብር አግኝተው ዐውደ ምሕረቱን ሲወሩ፣ ወዛቸውን የጠረጉበትን ለስላሳ ወረቀት ሳይቀር በገንዘብ የሚሸጡ ነጋድያን በወንጌል አገልጋይነት ስም ሲወራጩ ባየን ጊዜ “መስቀሉን ሰቀሉት” ብለን እንጮኻለን፤ አዎ፣ መስቀሉን ሰሉት!

በ2006 ዓ.ም. “ዐቢይ ነቢይ ሼፐርድ ቡሽሪ” የተባሉ ግለሰብ ወደ ዐዲስ አበባ በመጡበት ወቅት የታየው ዕብደት ለአስረጂነት እዚህ መጠቀስ ይኖርበታል። በነጻ የተሰጠው የክርስቶስ ጸጋና የመስቀሉ ሥራ ገብቶኛል እያለ በሚመካ

[80] ይህ የተወሰደው “መስቀሉን ሰቀሉት” በሚል ርእስ በሰሎሞን አበበ ከተዘጋጀ ጽሑፍ ነው። ጽሑፉም ሚያዝያ 10 ቀን 2006 ዓ.ም. የክርስቶስን ስቅለትና ትንሣኤ ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ በአቧሬ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ ነው። (*ነገረ መስቀል፦ መስቀሉን ሰቀሉት* [ያልታተመ ጽሑፍ፣ ዐዲስ አበባ፣ 2006 ዓ.ም.])





ማኅበረ ሰብ መካከል አንድ ነጋዴ “የፈውስ ዘይት” እና “የበረከት ጸበል” በጠርሙስ እያሸገ ሲቸበችብ ዝም ከተባለ፣ “መስቀሉን ሰቀሉት” አይባልምን? *“ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉ የክርስቶስንም አይደለም”* (ፊል. 2፥21) እያለ ጳውሎስ ያለቀሰው[81] “የመስቀሉ ጠላቶች” ኾነው ስለሚመላለሱቱ “ውሾች” አይደለምን (ፊል. 3፥2)። መታወቂያቸውስ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው “መሸቃቀጥ” መኾኑስ አልተጻፈምን (2ቆሮ. 2፥17)? በአንድ ግለ ሰብ ስም የተዘጋጀና “የነፍስን ኀጢአት የሚያነጻ” የተባለ ሳሙና ለገበያ ቀርቦ ሲታይ ምን ያህል ሊያስቈጣን በተገባ ነበር። ነፍሳችንን የሚያነጻ ከኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ሌላ ምን አለ? ከዚህ የከፋ ነገር ምን ሊመጣብን ኖሯል።

በውኑ፣ በዚያ ተገኝቼ ሳለሁ “እጄ አብረቀረቀ” በማለት በደስታ ብዛት የሰከረ ሰው፣ የብርሃን መልአክ የመሰለ አንዳች ጋኔን (2ቆሮ. 11፥14-15)[82] ቢመለከት ምን ሊውጠው ነበር? ከእግዚአብሔር መኾናቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ “መላእከት ቢኾኑ፣ ልዩ ፍጥረት ቢኾን፣ ያለውና የሚመጣው ቢኾን፣ ኀይላት፣ ከፍታና ድንቆች” እንኳ ቢኾኑ ከክርስቶስ ፍቅር እንደማይለዩን አልተጻፈምን (ሮሜ 8፥37-39)? በውኑ ይህ *“እግዚአብሔር መምሰል ማትረፊያ በሚመስላቸው ሰዎች ዘንድ”* የማይጠፋ (1ጢሞ. 6፥4-5) ሰግብግብነት[83] በመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ስም ተመስሎ አደባባይ ሲወጣ ማየት ነውር አይደለምን? ኧረ፣ መስቀሉን ሰቀሉት!

[81] *“ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ኾነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ ላልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ”* (ፊል. 3፥18)።

[82] *“ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል”* (2 ቆሮ. 11፥14)።

[83] መጋቢ ጻድቁ አብዶ ከ *ሕንጸት መጽሔት* ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ፣ “ይህንን እምነት ‘የስግብግብነት ወንጌል’ እንጂ ‘የብልጽግና ወንጌል’ አልለውም፤ ትክክለኛውን ብልጽግናማ እኔም አምናለሁ …” በማለት ከተናገሩት የተወሰደ ነው። *ሕንጸት*፣ ቍጥር 2፣ ግንቦት 2006 ዓ.ም.፣ 29።

ወንጌል የሰዎችን ሐሳብ እያንኰታኰተ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያገንናል። ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኀይል ነውና ያድነናል (ሮሜ 1፥17)። የመስቀሉ ቃል ለአንዳንዶች "ሞኝነት" ነው፣ ለሌሎች ደግሞ "ማሰናከያ" ነው፣ ለሚያምኑ ግን *"የእግዚአብሔር ጥበብና ኀይል ነው"* (1 ቆሮ. 1፥18)። ይህን እንዴት እንዘነጋለን?

የክርስቶስ መስቀል ሥራ መካከለኛነት ትምህርታችንን እስካልተቈጣጠረው ድረስ የኢየሱስ ሁሉ በሁሉነት ችላ የማለት ወይም ሁሉን የሚሞላ እርሱ መኾኑን የመዘንጋት ከፍተኛ አደጋ ሊገጥመን ይችላል። ዶ/ር ኀይሉ ቸርነት ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የመድረክ አገልግሎቶች ባኄሱበት መጽሐፋቸው ውስጥ በቍጭት የሚጠቅሱት ነገር አላቸው፤

> አሁን አሁን ግን በእግዚአብሔር ስም ተሰብስበን [ባለንበት] አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ምስባኮች ጸጋን የሚሰጥ ሳይኾን ጸጋን የሚነጥቅ ነገር ሲከነወን እንመለከታለን። እንደውም አንዳንድ ሥፍራ መንፈሳዊው ነገር ሥርዐት አልበኛነት እየነገሠበት መጥቶ ከማነጽ ሥራው ይልቅ የማፍረሱና ግራ የማጋባቱ እንዲሁም የመከፋፈሉ ነገር እያየለ በመምጣቱ ጕዳዩ አነጋጋሪ ኾኗል።[84]

በርግጥ፣ ክርስቶስ መካከለኛ ባልኾነበት ምስባክ ማፍረስና ግራ ማጋባት ቢሠፍን ይደንቃል? በአጠቃላይ መስቀሉ ከተዘነጋ የሚተርፈን ይህን መሳይ ጥፋት መኾኑ ግልጽ ነው። በዚህ መልኩ ወንጌል ተሰበከስ ይባላል እንዴ? ጆን ስቶት ይህን ሐሳብ ሊያጠቃልል የሚችል አንድ አገላለጽ አላቸው። "ክርስቶስ ካልተሰበከ፣ ወንጌል ጨርሶውኑ አልተሰበከም፤ ሞቱና ትንሣኤው ማእከላዊ ካልተደረጉም፣ እውነተኛው ክርስቶስ አልታወጀም።"[85] እንዲያውም ኑፋቄ ባይኾን አይደል!

[84] ኀይሉ፣ *መድረኮቻችን*፣ 48።

[85] John Stott, *Evangelical Truth* (Leicester: IVP, 2003) 31.





## *2.5 ኑፋቄያዊ ትምህርቶች፦ የክርስቲያናዊ አስተምህሮ መሠረታውያን መናጋት፣ መለበጥና መለወጥ*

የሃይማኖት ነጻነቱን ታከው ያቈጠቈጡት የሐሰት ትምህርት አረሞች የዘመኑን ኹኔታ ያከፉና የቤተ ክርስቲያንን መልእክት ካደነቃቀፉ ጋሬጣዎች መካከል ይጠቀሳሉ። በስውርና በማስመሰል ከሚንቀሳቀሱት ጀምሮ በይፋ ወጥተው የሐሰት ትምህርታቸውን እስከሚለፍፉት ድረስ ብዛት ላላቸው የዋህ ሰዎች መሰናከል ምክንያት የኾኑት ግለ ሰቦችና ቡድኖች ጥቂት አይደሉም።

ዛሬ፣ ዛሬ በየመድረኩ፣ በየኅትመት ውጤቶች፣ በሳተላይት ቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችና ሌሎች ብዙኀን መገናኛዎች በኩል እየቀረቡ ያሉት "መያገርያ መጨበጫ" የሌላቸው ትምህርቶች የሰሚዎቻቸውን ኅሊናና ሕይወት ዐበሳ እያበሉ ይገኛሉ ብንል የተጋነነ አይኾንም። መጠነኛ መደነቃቀፍ መከሠቱ መቼም አይቀሬ ነው። ከሰው ፍጹምነት አንጠብቅምና፣ አንዳንድ ግርታዎች መፈጠራቸው ላያስገርም ይችላል። እዚህ የምናነሣቸው ግን አስከፊዎቹንና መሠረታዊ የአስተምህሮ ለውጥ የተካሄደባቸውን ዐቋሞች ነው። አሁን፣ አሁን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን የተወገዙ ሐሰተኛ ትምህርቶች ጭምር በየመድረኩና በየአጋጣሚው ያለምንም ማመንታት እየተነገሩ ነው ማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።[86]

ይህን ለማስረዳት ጥቂት ማስረጃዎችን ማንሣት ይቻላል። ለምሳሌ፣ "ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሥጋ ነች" ማለታቸው ሳያንስ "ክርስቲያን መኾን ማለት በቀላሉ ሲገለጥ ከእግዚአብሔር ጋር ተደባልቆ እግዚአብሔርም ሰውም መኾን ማለት ነው" የሚሰኘውን (የዋችማን ኒ ደቀ መዝሙር የነበረውን) የዊትነስ ሊ ትምህርቶች የሚያንበለብሉ ወገኖች በየከተሞቻችን እየተዛመቱ

[86] ለምሳሌ የሚከተለውን ይመለከቷል፤ "እንግዳ ትምህርት፣ እንግዳ እንቅስቃሴ፣" *ማኅቴሰ*፣ ቍጥር: 18 ግንቦት 2003 ዓ.ም፤ ገጽ 1-8።

መኾኑን አልሰማንም ይኾን?[87] “ሰው ካልፈቀደለት በቀር እግዚአብሔር በዚች ምድር ላይ ለመሥራት አይችልም፤ ልሥራ ቢልም ሕገ ወጥ ነው”[88] እያሉ የሚያላግጡ ደፋሮች እንደከበቡን አናውቅምን?

በሀገራችን ከተማ ገጠር ሳይል እየተዛመተ የሚገኘው “*የእምነት እንቅስቃሴ*” እና “*የብልጽግና ወንጌል*” ውስጥ የሚሰሙት ብዙዎቹ የሐሰት ትምህርቶች መኾናቸው ፀሐይ የሞቀው ነው። ከኬነት ሀገን ቀጥሎ በአስተምህሮው ታዋቂ ከኾኑት ኬኔት ኮፕላንድ፣ ቻርለስ ካፐስና ከሌሎችም ጋር በአቻ አስተማሪነት የሚታወቁት ፍሬዴሪክ ፕራይስ የሚሉትን ለምሳሌ እንጥቀስ፤

> አዎ፣ ይህ አስደንጋጭ ነው! እግዚአብሔር በዚህ ምድር ከበብ ስለ ሰው እንዲሠራ እግዚአብሔር *ፈቃድ* ማግኘት አለበት። … አዎ! *ተቈጣጣሪዎቹ እናንተ ናችሁ*! ተቈጣጣሪው ሰው ከኾነ ታዲያ ሊቈጣጠር የማይችለው ማን ሊኾን ነው? እግዚአብሔር ነው። … እግዚአብሔር ገዢነትን ለአዳም ሰጠው ማለት፣ እግዚአብሔር ያ *ሥልጣን* ከዚያ በኋላ የለውም ማለት ነው። እንግዲያስ፣ *እኛ ካልፈቀድንለት* በስተቀር እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ አንዳች ማድረግ አይችልም። ለእርሱ ፈቃድ የምንሰጠውም በጸሎታችን ነው።[89]

[87] *ድብቆቹ የቤተ ክርስቲያን አሳቾች፦ የሎካል ቸርች/ የሪከቨሪ ሙቭመንት በኢትዮጵያ* (ይህ መጽሐፍ ታትሞ በሥርጭት ላይ ቢኾንም ደራሲው ስማቸውን ጨምሮ አስፈላጊ መረጃዎችን አላካተቱም) 46።

[88] የማይልስ ሞንሮን *ጸሎት* የተሰኘውን መጽሐፍ በማንበብ፣ “ገዢው” ሰው በምድር ላይ ባለው “የማይቀለበስ *ሥልጣን*” መሠረት እግዚአብሔር በምድር ላይ እንዲሠራ በጸሎት ፈቃድ ይሰጠዋል በማለት የሚያስተምሩ በርካታ ሰዎች በመካከላችን ይገኛሉ።

[89] Frederick K. C. Price, “Prayer: Do You Know What Prayer is … and How to Pray” *The Word Study Bible* (Tullsa, OK.: Harrison House, 1990) 1178, as quoted in Hank Hanegraaff, *Christianity in Crisis* (Eugene: Harvest, 1993) 85.በዚህም ኾነ በሌሎች ቦታዎች የውጭ ሀገር ሰዎችን የጠቀስሁት ኾነ ብዬ ነው። የሀገር ቤቶቹ ሰዎቻችን የእነህ ሰዎች ትምህርት ተቀባይና አሠራጭ ስለ ኾኑ የትምህርታቸው ሥረ መሠረት ከየት እንደሚመመዘዝ ለማመልከት በሚል ነው።





እንዲህ ዐይነቱን አሠቃቂ ትምህርት በማስተላለፍ ሀገር ምድሩን የመረዙ ሰዎችን ነው እንግዲህ በኛው ሀገር የሚገኙ ደጋፊዎቻቸው “ዝንባቸው እሽ አይባል” እያሉ ሙሾ የሚያወርዱት። ይህን የሚያሰራጩ የሀገር ቤት ሰባኪያንና መምህራን እነማን እንደ ኾኑ ደግሞ ይታወቃል። በቂ በኾነ ምክንያት ግን የአብዛኛዎቹን ስሞቻቸውን እዚህ አልጠቀስኩም። ስማቸው ባይጠቀስም ትምህርታቸውን በማገናዘብ ካጤኑት ከአንባቢዎች የሚሰወሩ አይመስለኝም። እናም ሐሳባቸውን ከሚቀዱበት የውጭ ሀገር ሰዎቻቸው ትምህርት ውስጥ የተወሰኑትን ብንጠቅስ በቂ ነው በማለት ተቀንጭቦ የቀረበ ብቻ ነው። እንግዲያውስ ከዚሁ “የሰው ገዢነት” ርእሰ ነገር ሳንወጣ ሌላ ጨምረን እንጥቀስ፤

ፍሬዴሪክ ፕራይስ፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ አዳም ለእንስሳቱ ስም እንዲያወጣላቸው በእግዚአብሔር የታዘዘበትን ምንባብ መሠረት አድርገው በዘፍጥረት 1፥20 ላይ ትንታኔ ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ፤

> እኒያ እንስሳት የእግዚአብሔር ቢኾኑ ኖሮ፣ ለምን እግዚአብሔር ራሱ ስም አይሰጣቸውም ነበር? ለእንስሳቱ፣ ለዕፅዋቱና ለአትክልቱ ስም እንዲያወጣላቸው ለዚህ ደካማ ሰው የተወለት ለምንድነው? ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ገዢነት ሥር ሳይኾን ከሰው ገዢነት ሥር ስለ ኾኑ ነው። ለምን? ገዢው አዳም እንጂ እግዚአብሔር አይደለምና ነው።[90]

ይህን ባዩ ፍሬዴሪክ ፕራይስን አካትቶ ሌሎችም *የእምነት እንቅስቃሴ* ዋነኛ መምህራን (የሀገር ቤት መምህራንን ጨምሮ) እንደ መሠረት ጣይ የእምነት አባታቸው የሚቈጥሯቸውና “ዳድ ሀጌን” በማለት የሚያቈላምጧቸው ኬኔት ሀጊን የሚያስተምሩት የነበረውን ማክኮኔል ጠቅለል አድርገው እንዳስቀመጡት እነመልከት፤ በዚያውም በኛው ሰፈር ተመሳሳይ ሐሳቦችን አንዳንዶች በይፋ

[90] Frederick K. C. Price, “Ever Increasing Faith,” Television Program (3, May, 1992) as quoted in Hannegraaff, *Christianity*, 346.

ሌሎች ደግሞ ፈራ ተባ እያሉ ሲያቀነቅኑ ሰምተናልና ለማገናዘብ ይረዳናል፤ ጉዳዩ፣ በእነሱ ትምህርት መሠረት፣ የሰው ማንነትን የሚያስተነትን ነው።

> ሀጌን እንደሚሉት “በዐዲስ ልደት ውስጥ እውነተኛ ትሥጉታዊ አምላክነት አለ!” በዐዲስ ልደት ውስጥ፣ እግዚአብሔር “የራሱን ባሕርይ፣ ንጥረ ነገርና ኑባሬ ወደ መንፈሳችን” አካፍሏል። ስለዚህ፣ “እያንዳንዱ ዳግመኛ የተወለደ ሰው ትሥጉት ነው” እንዲሁም “አማኝ እንደ ናዝሬቱ ኢየሱስ ሁሉ ትሥጉት ነው።” አንባቢው ሀጌን ይህን የሚናገሩት በተምሳሌታዊ አገላለጽ ይኾናል ብሎ እንዳያስብ [ሰውየው የተናገሯቸውን] የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ አድርጉ፡- “እኛ ይህ ነን፤ እኛ ክርስቶሶች ነን” [ይላሉ። ይቀጥሉና] “በርግጥ በሐዋርያቱ ደብዳቤዎች ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ተብላለች። ክርስቶስ መኾናችን ቤተ ክርስቲያን ገና አልገባትም። ይህ ሲገባን እንድናደርገው የታሰበልንን ሥራ ማድረግ እንጀም ራለን” [ማለታቸው ሳያንስ]“ክርስቶስ ራስ እኛ ደግሞ አካሉ ነን፤ የክርስቶስ አካል ደግሞ ክርስቶስ ነው” ይላሉ።[91]

በዚህ ጥቂት ገጾች ብቻ ባሉት መጽሐፍ ውስጥ መረጃዎችን በስፋት መዘርዘር አስቸጋሪ ነው። ለማሳያ እንዲኾን በማለት በብድግ-ብድግ የተወሰዱትን ብቻ ነው እዚህ ማቅረብ የሚቻለው። ይህ ብቻ አይደለም፤ ሌላም ጉድ አለ፤ “ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ አምላክነቱን አልተጠቀመም” ብቻ ሳይኾን፣ “በድኅረ ትሥጉት አምላክ አልነበረም”[92] እስከሚለው ድረስ መስማትና

[91] MacConell, *A Different Gospel*, 122.

[92] “የንጋት ኮከብ” በሚባል ሚኒስትሪ እየተዘጋጀ በኤልሻዳይ የቴሌቪዥን ኔትዎርክ (ETN) ላይ የሚተላለፍ መርሐ ግብር ከመጋቢት እስከ ግንቦት 2006 ዓ.ም. ለተከታታይ እሑዶች በነገረ ክርስቶስ ላይ የሚያጠነጥን ዝግጅት አቅርቦ ነበር። በዚያ መርሐ ግብር፣ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ በተወያይነት ተጋብዞ በነበረበት ወቅት፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ለመናገር የተጋበዙ ሌሎች ሁለት ተወያዮች ይህን ትምህርት ያለ ማወላወል ሲያስተላልፉ ሰምተናል። እኒያ ወገኖች ያለምንም ማመንታት “ኢየሱስ በመዋዕለ ሥጋዌው (በሥጋው ወራት) ሰው ብቻ እንጂ አምላክ አልነበረም” የሚል ዐቋም ይዘው ሲከራከሩ በይፋ ተደምጠዋል።





ማንበብ ዛሬ ራስ የሚያስይዝ አልኾነም፤ ለምን? ያልን እንደኾነ፣ በርካቶች ሐሳቡን የተላመዱት መስሏልና። “ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰይጥኗል”[93] እያሉ ከሚሳደቡቱ ጀምሮ፣ “በሲዖል ውስጥ በሰይጣን ታስሮ በመንፈስ ሞቶ ነበር”[94] “ዳግም የተወለደውም በሲዖል ውስጥ ነው” እስከሚሉት አሠቃቂ ትምህርቶች ድረስ ያለአንዳች ማወላወል የሚያውጁ መናፍቃን “ወንጌላውያን ነን” በሚሉ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች እየተደመጡ እንዳለ የታወቀና ማስረጃ ለማቅረብ የማይከብድ ነው።

ለዚህ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ልጥቀስ፤ አንድ፡- አቶ ኀይሉ ዮሐንስ የተባሉ ሰው በታሕሳስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም ምሽት በሳተላይት ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ፋሲካ ከፍሌ የተባሉ (ጋዜጠኛ?) ቃለ ምልልስ ሲያደርጉላቸው ታይተዋል። ሰውየው ከተጠየቁት ጥያቄዎች አንደኛው “ኢየሱስ በሲዖል ሞቷል ብለህ ታስተምራለህ ይባላል፤ እውነት ነው ወይ?” የሚል ይገኝበታል። አቶ[95] ኀይሉ በስሜት ተሞልተው ሲመልሱ፣

> ኢየሱስ የተቀበለው መከራ ከመስቀል ያልፋል፤ ኀጢአትና እርግማን ኾኗል … ኀጢአት የእግዚአብሔርን ፊት አያይም። … ይህን የማያምን ክርስቲያን ደግሞ ክርስቲያን አይደለም፡- ይህን

[93] “እንግዳ ትምህርት”፣ ማቴቴስ፣ ገጽ 7።

[94] Joyce Mayer, *The Most Important Decision You Will Ever Make: A Complete And Thorough Understanding of What It Means to Be Born Again*, (Faithwords, 2008) 36።

[95] “አቶ” የሚለውን የክብር መጠሪያ ያስቀመጥኩት ሰውየው ሌላ ማዕረግ ከስማቸው ጋር ሲጠቀሙ ስላላየሁና ስላልሰማሁ መኾኑ ይታወቅ። እሳቸውን ለመጥቀስ የፈለኩትም ከሌሎቹ ተመሳሳይ መምህራን በተሻለ ሐሳባቸውን ሳይደባብቁ በይፋ ስለሚናገሩና በነኬኔት ሀጌን አስተምህሮ እንደሚያምኑ በይፋ ስለሚናገሩ ጭምር ነው። ውስጥ ውስጡን እየተሹለከለኩና በተድበሰበሰ ንግግራቸው ስሕተት እየረጩ ከሚጠማዘዙቱ ይልቅ የኚህን ሰው ዐቋም ለማግኘት የተሻለ ዕድል አለ።

> ሞት (ኢየሱስ) በመንፈስ ካልሞተው ክርስቲያን ይኖረዋል። ስለዚህ ኀጢአት በሲኦል መቀጣት ነበረበት...[96]

ብለው ነበር። እኚህ ሰው በተከታታይ ከሚያስተምሩት መካከል፣ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን፣ ተስፋዬ ሮበሌ ከጠቀሱት ላይ መቈንጠርም ይቻላል።

> እኔ የእምነት ቃል አስተማሪ ነኝ ... ክርስቶስ ያመጣውን በረከት ሁሉ የምናገኘው በእምነት ነው። ... *ፋክትና ሪያሊቲ* የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ኢየሱስ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ ከሞት ሲያስነሣ “ተኝታለች” ነው ያለው፤ ይህም ኢየሱስ “ሞታለች” የሚለውን ከዶታል። “ተኝታለች” ብሎ በመናገሩ *ሪያሊቲውን* ስለ ካደ ልጅቱ አልሞተችም፤ ነገር ግን ተኝታለች። ስለዚህ ኢየሱስ የሞተውን ሰው ሳይኾን ያስነሣው ያንቀላፋውን ሰው ነው ያስነሣው። ... ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ይኖራል ... አካል ነኝ የሚል ሰው ሥጋዊ ክርስቲያን ነው ... እኔ በጭቃ ቤት ውስጥ የምኖር እንጂ ጭቃ አይደለሁም፤ ... በጭቃ ቤት ውስጥ የምኖረው ኀይሉ ነኝ ... እኔ መንፈስ ነኝ ... አካሌ ደግሞ ድንኳን ነው ... የጭቃ ቤት ነው ... ቊርበት ነው ... ። ዳግም የተወለድነው በመንፈስ ነው፤ የሥጋ ቋንቋ ደግሞ የስሜት ሕዋሳት ናቸው።[97]

እንግዲህ ይህን አስተምህሮ የሚያራምዱ እኚህ ሰው በጥር 2004 ዓ.ም. ላይ በዐዲስ አበባ የስብሰባ ማዕከል ላዘጋጁት ኮንፈራንስ “የግቡልኝ” ጥሪ በትነው ነበር። በአደባባይ የጥሪ ፖስተሮቹ ላይ እንዳስተዋልኩት እኚህ ሰው በዐዲስ

[96] ስለ አቶ ኀይሉ ዮሐንስ አስተምህሮ የበለጠ ለማወቅ የፈለገ ሰው www.hyfm.org ማየት ይችላል። በEBS እና ETN ቴሌቪዥን ላይ ባላቸው መደበኛ መርሐ ግብራቸው ደግሞ እዚህ ከተጠቀሰው የባሱ ሌሎች ነገሮችን እንደሚናገሩ ያዳመጣቸው ሁሉ ያስታውሰዋል።

[97] ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ከ“እምነት እንቅስቃሴ” መምህራን ትምህርት ተጠበቁ* (ግራንድ ራፒድስ፦ ተዐከማ፣ 2011) 9 ላይ *ከ*Hailu Yohannes, *Birth Right* #1-#4 *http://www.hyfm.org/Videos.16.htm* ላይ ጠቅሶ እንዳሰፈረው።





አበባ የሚገኝ የትኛውም ቤተ እምነት ወይም አጥቢያ እንደ ጋበዛቸው የሚናገር መግለጫ አላኖሩም። ጉባኤውን የጠሩት በግላቸው ነው ማለት ነው። ነገር ግን በስብሰባቸው ላይ ምን ያህል ሰው እንደ ተሰበሰበ፣ የተሰብሳቢው ምንጮችም የትኞቹ ቤተ እምነቶች እንደ ኾኑ ስትመለከቱ መደንገጣችሁ ይቀራልን? በእነዚህ ዓይነት የአደባባይ ጉባኤዎች የአደባባይ ፖስተር እስካነበበ ድረስ ማን እየሄደ እንደሚታደም ግልጽ ነውና።[98]

*ሁለት፦* ማን እንደጋበዛቸው ለማጣራት ያደርግሁት ሙከራ ባይሳካም፣ በዐዲስ አበባ በምትገኝ አንድ ትልቅ አጥቢያ ጸሎት ቤት ውስጥ፣ በ2003 ዓ.ም.፣ አንድ ዠማ ስብሰባ ነበር። በዚያ ጉባኤ ላይ ጆይስ ሜየር የሚባሉ አሜሪካዊ ቴሌ ኢቫንጀሊስት በዋና ተናጋሪነት ቀርበው እንደ ነበር ይታወሳል።

ጉዳዩ ጆይስ ሜየር ለምን ተጋበዙ የሚል አይደለም፤ በየጉባኤው ላይ ማን መጋበዝ እንዳለበት የሚያውቀው የየአብያተ ክርስቲያናቱ አመራር አካል እንደኾነም ግልጽ ነው። ነገር ግን፣ ሴትዮዋ ከላይ የጠቀስኩትን የተሳሳተ ትምህርት፣ ለምሳሌ “ኢየሱስ በመንፈሱ ሞቶ ነበር” የሚሰኘውን ስሕተት፣ የሚያምኑና የሚያስተምሩ መኾናቸውን ከጠቀስኩ በቂ ነው።[99] እኒህ ሴት ይህን መሰል ዐቋም እንዳላቸው እየታወቀ እንዳልተጠሩ መገመት ይቻላል። ነገር ግን የመረጃ ክፍተቱን ለመጠቈም እንዲሁም ለአገልግሎት ወደ ሀገር ቤት የሚጠሩ የውጭ ሀገር ሰዎች የአደባባይ ዝናቸው ብቻ ሳይኾን አስተምህሯዊ ጤናማነታቸው ጠንቅቆ የመታወቁን አስፈላጊነት ለማሳየት ሲባል ያቀረብኩት ነው።

[98] በርግጥ ዛሬ ፖስተር መለጠፍ የቻለና ግብዣ የሰጣቸውን የተወሰኑ ሰባኪዎችና ዘማሪዎች ፎቶግራፍ ማባዛት የተሳካለት ግለ ሰብ ያለ ምንም ችግር ሺህዎችን ሰብስቦ የፈለገውን መልእክት ለመስተላለፍ ችግር እንደማይገጥመው ተደጋጋሚ ክዋኔዎች እያሳዩን ያሉት ነገር ነው። ባይኾንማ ኖሮ “ነቢይ” ቡሽሪ ባስጠሩት ዠማ ዝብሰባ ላይ በየቀኑ ከ35,000 በላይ ተሳታፊ እንዴት ሊሰበስቡ ይቻላቸው ነበር?

[99] ደራሲዋ ባዘጋጁትና ከስብከተ ወንጌል አገልግሎታቸው ማጠቃለያ ለዐዳዲስ አማኞች በሚታደለው መጽሐፋቸው ላይ የጻፉትን ብቻ ማየት ለዚህ በቂ ነው። Meyer, *Most Important*, Kindle Edition, 249-250።

በዘመናችን *"የእምነት እንቅስቃሴ"* በሚል ጭንብል በተሸፈነ አስተምህሮው የሚታወቀው ንቅናቄና *"የብልጽግና ወንጌል"* የተሰኘ አጓጉል መጐምዠት የተጠናወተው መጤ ሐሳብ በንቃት መመርመር እንዳለበት በዚህ ጽሑፍ አለማሳሰብ ዝንጉነት ይኾናል። ይህን ትምህርት በሚያሰራጩና ልምምዱን በሚያስፋፉ ግለ ሰቦችና ቡድኖች እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው አደገኛ ትምህርት አደባባይ እየወጣ ሕዝቡ እንዲያውቀው መደረግም ይኖርበታል። ይህ ነገር ትኩረት እንዲሰጠው ማስገንዘብ የዚህ መጽሐፍ ተረኛ ዕዳ ሳይኾን አይቀርምና ጠቋም ማድረጉ ተመርጧል።

ይህ ትምህርት ከነ ልምምዶቹ በሀገራችን በስፋት ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ወገኖች በግላቸው ከሚያሳዩት መፍጨርጨር በቀር በተቋማት ወይም በቤተ እምነት ደረጃ የሚወሰዱ የተጋፋጭነት ርምጃዎች ብዙም አይደሉም። የሉም አላልኩም፤ የአሳሳቢነቱን ያህል አልተሠራም አልሁ እንጅ።

በርግጥ በ1990 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት (ECFE) ደረጃ የተዘጋጀ ዐውደ ጥናት የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት አስገብቶና ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ተመሥርቶ ውይይት እንዳካሄደበት አቶ ተስፋዬ ሮበሌ በጽሑፋቸው ያኖሩትን ዋቢ አግኝቻለሁ።[100] ጥናታዊ ጽሑፎችን ካቀረቡት መካከልም አቶ ሰሎሞን ከበደ (መሠረተ ክርስቶስ)፣ አቶ ሰሎሞን ጥላሁን (መሠረተ ክርስቶስ)፣ አቶ (አሁን ዶ/ር) ሽመልስ አድማሴ (መካነ ኢየሱስ) እና ራሳቸው አቶ ተስፋዬ ሮበሌ (ቃለ ሕይወት) እንደሚገኙበትም ተጠቅሷል።

ሲደረጉ የነበሩ እነዚህ ጥረቶች የሚያበረታቱ ናቸው። ጥያቄው ግን ትምህርቱ እና እንቅስቃሴው በከፋ ኹኔታ እንደ ገና ባገረሸበት በዚህ ወቅት ምን ዐይነት ክትትል እየተደረገና ምንስ ዐይነት ምላሽ እየተሰጠ ይኾን የሚለው ነው። "የእምነት እንቅስቃሴ" ተብዬው ነገር ከምንገምተው በላይ በሀገራችን እየተስፋፋና እየተዛመተ ከመኾኑ አንጻር ምን እየሠራን ነው የሚለው ጥያቄ

[100] ተስፋዬ፣ *ከእምነት እንቅስቃሴ*፣ 2።





ምላሽ ማግኘት አለበት። በኢትዮጵያ ወንጌላውያን የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ኅብረት (AETIE) በኩል አበረታች እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ስለ ኾነ ጥረታቸውን እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ነው። የት ድረስ እንደሚዘልቅ ግን ገና የምናየው ይኾናል።

ርግጥ ይህን እንቅስቃሴ እንደ መንፈሳዊ የተሐድሶ ጉብኝትና መነቃቃት አድርገው የሚወስዱ ግለ ሰቦችና ቡድኖች አሉ። "ከእግዚአብሔር ጋር ስንጣላ እንዳንገኝ" መጠንቀቅ አለብን የሚሉም ተደምጠዋል። ነገር ግን፣ ለአንዳንድ የዋህ ወገኖች እንደሚመስላቸው፣ ይህ "የእምነት እንቅስቃሴና የብልጽግና ወንጌል" የተባለ ነገር፣ በመሠረታዊ ዐቋሞቹና ንጽረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ታሪካዊ መሠረቱም ፈጽሞ ስሕተት እንደ ነበር በርካታ ጥናቶች ይፋ አድርገዋል።[101]

አንዳንድ ቃላትና ሐሳቦችን ከክርስትና ትምህርት ቀንጭቦ በመውሰድና ከዲበ አካላዊ ፍልስፍና ጋር በመቀየጥ ዐዲስና እንግዳ ትምህርት በፈጠረው ኤሴክ ደብሊዉ ኬኒዮን ተወጥኖ የተጀመረው አስተሳሰብ የሌሎች ሰባኪያንና መምህራንን ትኩረት አልተነፈገውም። ኬኔት ሐጌንና ኬነት ኮፐላንድ የተባሉት አሜሪካውያን መምህራን ትምህርቱን በማስፋፋት መሠረታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና ትምህርቶችን በረዙ። እነሱን ተከትለው ታዋቂ የቴሌቪዥን ሰባኪያን በገፍ ተንደርድረው ወደ እንቅስቃሴው በመግባት ስፍር ቍጥር የሌላቸውን ወገኖች በአስተሳሰቡ ማጥመቃቸውን እንደ ቀጠሉ የታወቀ ኾነ።

[101] ለምሳሌ በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ይመ. Hanegraaff, *Christianity*; MacConnel, *A Different Gospel*; Robert M. Bowman, Jr., *The Word-Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel* (Baker: Grand Rapids, MI., 2000). ግርማዊ፣ *የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ መሠረቶችና መዘዞች* (ዐዲስ አበባ፡- ቤሪያ የኅትመት ኩባንያ፣ 1990 ዓ.ም.)፤ ተሾመ ነጋሽ፣ *እስከመጣ ድረስ* (ዐዲስ አበባ፡- ኤስ አይ ኤም፣ 1987 ዓ.ም.)

የእነዚህን ሰዎች አገልግሎትና ትምህርት በቀጥታ የቀዱት የእኛው ሀገር ሰዎችም ላለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት ያስከተሉት ነውጥና ጥፋት እንደ ቀጠለ ቢኾንም፣ ከጓዳ ማጉተምተምና ሹክሹክታ ከፍ ያለና የማያወላውል የመከላለከል ተግባር በጋራ የተወሰደ አይመስልም። ጉዳዩ እኮ ማንም ክርስቲያን ሊገጥመው እንደሚችል ቀላል መደነቃቀፍ በቸልታ የሚታይ አይደለም።

“ክርስትና በቀውስ ውስጥ” ተብሎ ሊተረጐም የሚችል ርእስ በያዘው መጽሐፋቸው ውስጥ *የክርስቲያን ሪሰርች ኢንስቲቲዩት* (CRI) ፕሬዘዳንት የነበሩትና ሀንክ ሀኔግራፍ የተባሉ የክርስትና ዐቃቤ እምነት እንደ ገለጹት፤

> የእምነት እንቅስቃሴ የክርስትናን ዐይነተኛ ባሕርያት በማጣመም የተደናገረ ክርስትና እና የተጨናበረ መሲሕ ያቀርብልናል። ስለኾነም፣ የእምነት አንቅስቃሴ ነገረ መለኮትን መቃወም ምእመናንን ከመከፋፈል ይልቅ አንድ የማድረግ ሚና አለው። በአሁኑ ወቅት ክርስቲያኖች በመጋፈጥ ላይ ያሉት የእምነት እንቅስቃሴ ቀውስ፣ በካሪዝማዊው ነገረ መለኮታውያን እና ካሪዝማዊ ባልኾኑት መካከል በሚደረግ የቃላት ጨዋታ የሚታለፍ አይደለም። ይልቁኑም የሞትና የሕይወት፣ የርቱዕ እምነትና የኑፋቄ፣ ብሎም ደግሞ የክርስቶስ መንግሥትና የመናፍቃን መንግሥት ጉዳይ ነው።[102]

ይህ አባባል ትልቅ መልእክት ያለው ነው። ግድ ደርሶብን እንጂ ስንት ሥራ በሞላበት በዚህ ወቅት ይህን መሰሉን ግብ ግብ ማድረግ ማን ይፈልግ ነበር? አንዳንዶች እንደሚያስቡት ስንት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ሞልቶ እያለ በትንንሽ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ፉከቻ አይደለም። የሕይወትና የእውነት ጉዳይ ነው።

[102] Hank Hanegraaff, *Christianity in Crisis* (Eugene, Oregon: Harvest House Pub., 1993) 47፣ ግርማዊ እንደጠቀሰው (*የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ*፣ 11)።





ሰዎቹም ኾነ ብለው ጉዳዩን ለማቃለል ጥረት አድርገዋል። በአንድ ፊት በቀደመው ትውልድና በዐዲሱ ትውልድ መካከል የተከሠተ አለመጣጣም እንዲመስል አድርገው ሐሳቡን ያዛምታሉ። በሌላ በኩል ቀጣይነት ያለው የተሐድሶ እንቅስቃሴን (*Progressive Reformation*) በተረዱና ባልተረዱ ሰዎች መካከል የሚታይ ውጥረት ነው ብለው ይለፍፋሉ። አሊያም የነገረ መለኮት ትምህርት ሥልጠና ባላቸውና በሌላቸው ወገኖች መካከል የተፈጠረ አለመግባባት ተደርጎ እንዲታይ ይጣጣራሉ። ወይም ደግሞ በ*ካሪዝማዊ* እና *ካሪዝማዊ* ባልኾኑ ክርስቲያናዊ ዐቋሞች መካከል የተፈጠረ የሐሳብ ልዩነት ነጥብ ተደርጎ እንዲወሰድላቸው በብልጠት ሲተጉ ታይቷል።

የክርስትና አዕማድ ትምህርቶችን እያወደሙ በ*ካሪዝማዊነት* ካባ ሥር መሸሸግ እንደማያዋጣ መሥራት ያለብን ጊዜ ላይ ደርሰናል ይመስለኛል። *ካሪዝማዊ ጳንጠቌስጠዊነትን* የዚህ ክፉ ዕዳ ተሸካሚ እንዲኾን የፈረደበት ማነው? ጄ. አይ. ፓከር “*ካሪዝማውያን* [ክርስቲያኖች]፣ ‘ቤተ ክርስቲያን ገና ታላላቅ የእግዚአብሔር ጉብኝቶች ይጠብቋታል’ ብለው በፍል ጉጉትና ጥበቃ በአውራ ጣታቸው ቆመዋል”[103] እንዳሉት፣ እኛ *ካሪዝማውያን* ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች “*ሥሡ*” መኾናችን እውነት ቢኾንም እንኳ፣ ምርቱን ከግርድ የማንለይ “ሞኞች” አለመኾናችንን ግን በይፋ ማሳየት ይኖርብናል። ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ የተነጠለ ካሪዝማዊነት እንደሌለ መናገርም አለብን።

ከወጣትና ተልእኮው (YWAM) እና ከጳንጠቌስጣውያን አብያተ ክርስቲያናት ወንድማማችነት (BPC) ጋር ይሠሩ የነበሩትና የተመሰከረላቸው *ካሪዝማዊ* አገልጋይ፣ እንዲሁም ጸሐፊ የኾኑት ዲ. አር. ማክኮኔል፣ በታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ *ዘመናዊውን የእምነት እንቅስቃሴ* ባበጠሩበት መጽሐፋቸው ውስጥ፣ ይህን ጉዳይ አስመልክተው ያስቀመጡትን እንመልከት፤ እንዲህ ይላሉ፤

[103] አቶ ንጉሤ ቡልቻ ለመጋቢ በቀለ መጽሐፍ ባሰፈሩት የቀዳሚ ቃል “መንደርደሪያ” ውስጥ ከጠቀሱት የተወሰደ ነው (በቀለ ወልደ ኪዳን፣ *ሪቫይቫል፣ ኢትዮጵያና የመጨረሻው መፈረካ* [ዐዲስ አበባ፡- እ.አ. ሙ.ወ.እ.ቤ.ክ.፣ 1994] 17) ይመ.።

> እኛ ራሳችንን ‘ካሪዝማውያን’ አድርገን የምንቈጥር ክርስቲያኖች በመስቀለኛ መንገድ ላይ ቈመናል፤ ... ካሪዝማዊ ተሐድሶ በታሪኩ መንፈሳዊ የቍርጥ ቀን ላይ ደርሷል። ... በካሪዝማዊ መሪዎች የሚወሰደው እርምጃም በቤተ ክርስቲያን የታሪክ ሰነዶች ውስጥ የሚኖረንን ስፍራ እንደሚወስነው አምናለሁ። አደጋ የተደቀነበት ነገር የእንቅስቃሴያችን አስተምህሯዊ ርቱዕነት ላይ ከማነጣጠር ያነሰ አይደለም። ... [ስለዚህ] በካሪዝማዊ መነቃቃት ውስጥ የሚገኝና ኀላፊነት የሚሰማው አመራር ... ተሐድሶውን ወደ ታሪካዊው የክርስትና ርቱዕ እምነት መምራት ይኖርበታል።[104]

አዎ፣ ይህ በትውልዳችን መካከል እግዚአብሔር ከፊታችን ያቀረበው ታሪካዊ ኀላፊነት ነው። ገና ለገና “መንፈሳዊ ነገር ባይገባቸው ነው” የሚሰኘውን ዘለፋ በመፍራት ብቻ ከጥሪያችን ያፈገፈግን ወገኖች ብንኖር መንቃት ያለብን ጊዜው አሁን ነው። ለአስተምህሮ ርቱዕነት መጽናት የካሪዝማዊ ዐቋም ልልነት ሊኾን የሚችለው እንዴት ነው? ርግጥ ልጁን ከታጠበበት ውሃ ጋር ወደ ቦይ አንደፋውም። አዎ፣ “ካሪዝማዊው ተሐድሶን የማልቃወመው ሰጪውን መንፈስ ቅዱስን የማልቃወመውን ያህል ነው”[105] ኾኖም ልጁን በታጠበበት ቆሻሻ ውስጥም እንደማንጥለው መታወቅ አለበት።

ይህን ንዑስ ርእስ ከመዝጋታችን በፊት አንድ ማሳያ ምሳሌ ልጨምር። ጸሐፊው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም. ያነጋገራቸውና የአንዲት ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ማኅበርን በሽማግሌነት የሚያገለግሉ ወንድም የነገሩትን አስደንጋጭ ነገር ይመለከታል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከአደባባይ የጠፋ (ነገር ግን ኅትመቱና ኅቡዕ ስርጭቱ እንዳልተቋረጠ የሚነገርለት) እንዲሁም ለበርካታ አስተምህሯዊ ብረዛዎች መንሥኤ የነበረ ጋዜጣን እኚሁ የቤተ ክርስቲያን መሪ ላለፉት ዐሥር ዓመታት በላይ ያለማቋረጥ እንደሚከታተሉ ተናግረዋል። ከዚሁም ጋዜጣ በቀዱት መሠረት በነባሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ትምህርት፣ ማለትም፣ ክርስቶስ በአካል፣ በግልጽ

[104] MacConell, *A Different Gospel*, xvi.

[105] *እዚያው*።



“ሃያነበቤሙ በቅሉ”

እየታየና በአጽናፈ ዓለማዊ ኩነት መመለሱን እንደማያምኑ ለጸሐፊው ያለማወላወል ነግረውታል፤ ሰውዬው በተማሩት መሠረት ጌታ “በእኛው መጥቷል፤ በእኛው ይመጣል” ነው የሚሉት።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከክርስትና ትምህርት ዋነኛ አዕማድ አንዱና የታሪክ-ድኅነት መደምደሚያ መኾኑ ግልጽ ነው። ጌታ ኢየሱስ ራሱ፣ “*እመጽእ ካዕበ—ሁለተኛ* እመጣለሁ” (ዮሐ. 14፥3) ብሎ ተናግሮአል። ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት ቆመው ወደ ሰማይ አንጋጥጠው ይመለከቱ ነበር። መላእክት[106] ተገልጠው፣ “*ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ይህ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል*” (ሐዋ. 1፥11 *አጽንዖት* የእኔ) እንዳሏቸው ተጽፎልናል።

ዳግም ምጽአትን የሚመለከት እምነት ከክርስትና አስተምህሮና መሠረታውያን አንዱ ነው። ምንም እንኳ የጌታን መመለስ ታክከው በሚፈጸሙ ኹነቶችና ዝርዝር ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አገላለጦችና አስተሳሰቦች ቢኖሩም፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ይስማማሉ። ይህም ማለት፣ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል ማለት ነው። ይህ ማለት፣ ክርስቶስ ጌታ በኑባሬ ህላዌው፣ በአካል፣ በግልጽ እየታየ፣ አጽናፈ ዓለማዊ በኾነ አንድ ዐቢይ የድርጊት ክዋኔና ትዕይንታዊ ኩነት ይመለሳል ማለት ነው። ይህን አስተባብሎ መገኘት መናፍቅነት መኾኑ አያጠያይቅም።

እኔ ይህን ያህል ማሳየት ከቻልኩ በቂ ይመስለኛል። በርካታ ሐሳቦችን በማንሣት ርእሱን ማጒልበት ይቻላል። ነገር ግን የቀረውን አንባቢዎች ከየገጠመኞቻቸው ሊጨምሩበት እንደሚችሉ ይታመናልና በዚሁ እናቁም። ከአስተምህሮ መናጋት ጋር የተያያዘ ሌላም ነጥብ አለንና ነው። እሱም ሥርዐተ አምልኮን ይመለከታል።

[106] መላእክቱ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎችን ተመስለው የተገለጡ ናቸው (ሐዋ. 1፥10)።

## 2.6 *የሥርዐተ አምልኮ ዝንፈት*

*“ጌታ ሆይ፣ ... የሰው ልጅ ሊወድስህ ይፈልጋል። ... አንተን በመወደስ ደስታውን እንዲፈልጋት የምትገፋፋውም አንተው ነህ። ለአንተ ለራስህ ፈጥረኸናልና፣ ልባችን በአንተ እስኪያርፍ ድረስ ዕረፍት አያገኝም። ጌታ ሆይ፣ በቅድምያ አንተን መጥራት ወይም መወደስ ይገባ እንደኾነ ... ማወቅንና መረዳትን ስጠኝ። ... ጌታ ሆይ፣ ጠርቼህ ምነው ባገኘሁህ፤ አምኜህ ምነው በጠራሁህ፤ አንተ ተሰብከህልናልና። ... በልጅህ ሥጋ መልበስ እንዲሁም በሰባኪህ አገልግሎት አንተ የሰጠኸኝ ይህች እምነት አንተን ትጣራለች።”*

— ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ *ኑዛዜ*፣ ክፍል 1፣ ምዕራፍ 1፣ ቍጥር 1።

እውነተኛው ሕያው ጌታ እግዚአብሔር ሊመለክ የተገባው አምላክ ነው። የሁሉ አስገኚ የኾነው የመላለም ፈጣሪ አምልኮትን መቀበል የባሕርይው ስለ ኾነ፣ “ክርስቲያናዊ አምልኮተ እግዚአብሔር በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ሊከናወን የሚችል እጅግ ቅጽበታዊ፣ በጣም አጣዳፊና ከሁሉ የበለጠ ክቡር ገቢር (ድርጊት) ነው።”[107]

*ሥነ* ፍጥረታዊ ኀላፊነታችን እግዚአብሔርን ብቻ እንድናመልክ ያደርገናል። ቤዝዎታዊ ጥሪያችንም ከአምልኮተ እግዚአብሔር ጋር በጥብቅ የተቈራኘ ነው። እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራው አምላክ የዘላለማዊ ዕቅዱ አካል የኾነውን የአድኅኖት *ሥራ* ያከናወነው፣ *“በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንኾን ዘንድ ነው”* (ኤፌ. 1፥12)። እግዚአብሔር በፈጠረን ጊዜ የአምልኮ መሻትን በውስጣችን አኑሯል፤ ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔርን ካላገኘ በቀር ሊረካ የማይችል ጥልቅ ጕጕት በማንነታችን ውስጥ ተፈጥሯል። ብሌይዝ ፓስካል እዳለው፣ “እግዚአብሔር

[107] Karl Barth, as quoted in J. J. von Allmen, *Worship: Its Theology and Practice* (Londen: Lutterworth, 1965) 13.





*ራሱ ካልሞላው በቀር ምንምና ማንም ሊሞላው የማይችል መካነ-ዕርቃን (ባዶ ኦና) በሰው ልብ ውስጥ አፉን ከፍቶ ይኖራል።”* ይህ የሕይወት ገደል የሚሞላበት አንድ ተስፋ ብቻ አለው። በዳግም ልደት ብርሃን “ዐዲስ ፍጥረት” ብቻ ሳይኾን “ዐዲስ አምላኪዎች” በመኾናችን ምክንያት ያ ጥልቅ መሻታችን ከፍ ያለ ትፍጽምቱን አግኝቷል።[108]

አምልኮተ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተግባሯ የኾነውም ከዚህ የተነሣ ነው። ቤተ ክርስቲያን የመንግሥቱ አገልጋይ ካህናት እንዲኾኑ የተዋጁ ምእመናን ማኅበር ናትና፣ ቅዱሱን አምላክ ትቀድሰዋለች፤ ትወድሰዋለች፤ ትገዛለትማለች። ቅዱስ ጴጥሮስ፣ *“እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ”* (1 ጴጥ. 2፥9) የሚለን በዚህ ምክንያት ነው።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ለመኖሯ፣ *አምልኮተ እግዚአብሔርን* ጨምሮ፣ አራት ዋነኛ ዓላማዎች አሏት። የተቀሩት ሦስቱ *ስብከተ ወንጌል*፣ *ደቀ መዝሙር ማድረግ* (ምእመናንን ማነጽ) እና *ማኅበራዊ ሱታፌ* ናቸው።[109] በዚህ ቦታ ለማየት የምንሞክረው አምልኮን ሲኾን፣ ትኵረታችን ግን በዘመናችን ያለው የሥርዐተ አምልኮ ገጽታ ላይ ይኾናል።

አምልኮ ከቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ተግባራቷ መካከል አንዱ ነው ብለናል። ምናልባትም ከላይ ካየናቸው ሌሎች ሦስት ተግባራቷ ጀርባ እንኳ አምልኮ አለ። አዎ፣ እውነተኛና ሕያው አምልኮተ እግዚአብሔርን “ያስቀደመች ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን መተናነጽና መልእክቷን ለዓለም ማድረስን ቻል አትልም።”[110] ለምሳሌ ያህል የስብከተ ወንጌል ሐዋርያዊ ተልእኮን

[108] Ron Owens, *Return to Worship: A God Centered Approach* (Nashvile: Broadman & Holman, 1999) 49.
[109] Erickson, *Christian theology*, 1060-1061.
[110] ኀይሉ ቸርነት፣ *መድረኮቻችን*፣ 27።

(*Missions*) እንመልከት። ጆን ፓይፐር ከዚህ መልእክተኛነት ዐደራ ተነሥተው ሲናገሩ፣ በታሪክ ውስጥና በቤተ ክርስቲያን መኻል የእግዚአብሔር ዐብይ ዓላማ አምልኮተ እግዚአብሔር መኾኑን ይገልጻሉ። በሌላ አባባል፣ እግዚአብሔር በሚሠራው ነገር ሁሉ ውስጥ የተቋጠረው ዐቢይና ዘላለማዊ ተልእኮ ለራሱ ክብርና ውዳሴ ማምጣት ነው ማለታቸው ነው፤

> የቤተ ክርስቲያን ዐቢይ ግቧ የስብከተ ወንጌል መልእክተኛነት አይደለም፤ አምልኮተ እግዚአብሔር ነው እንጂ። የስብከተ ወንጌል መልእክተኛነት ሊኖር የቻለው፣ አምልኮተ እግዚአብሔር ስላልኖረ እኮ ነው። ...
>
> ከመልእክተኛነት ይልቅ አምልኮተ እግዚአብሔር ዋነኛ የኾነበት ምክንያቱ ሰው ሳይኾን እግዚአብሔር ዋነኛው በመኾኑ ነው። ይህ ዓለምና ዘመን አብቅቶ ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል እልፍ አእላፋት የኾኑ የተዋጁ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በግንባራቸው ተደፍተው በሚያመልኩት ጊዜ፣ የስብከተ ወንጌል መልእክተኛነት ያበቃለታል። የወንጌል መልእክተኛነት ለተወሰኑ ዘመናት የሚቈይ አስፈላጊ ግዴታ ነው። አምልኮተ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ዘላቂ ነው። [111]

እንግዲህ አምልኮተ እግዚአብሔር ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተግባራት ሁሉ መካከል ዘላቂው እንደ መኾኑ፣ ከእርሱ ጋር ከማይደራረሱ ሌሎች ነገሮች ሁሉ በላይና በቀዳሚነት ቤተ ክርስቲያን በጸናችበት የከበረ መገለጥ ላይ ተመሥርቶ ሊታደስ፣ ሊታረምና ሊስተካከል ይገባዋል። ተሐድሶና መነቃቃት ግቡ ሕያውና ቅዱስ የኾነ የአምልኮተ እግዚአብሔር መስፈን ነው። ቤተ ክርስቲያን ትታደስ የምንለውስ ለምንድነው? እግዚአብሔርን በምልዓትና በትክክል ማምለክ እንድትችል አይደለምን?

[111] John Piper, *Let the Nations Be Glad: The Superemacy of God in Missions* (Grand Rapids: Baker, 1993) 11.





አምልኮ የቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ሕይወቷ መነቃቂያ ማእከል የኾነ ጕዳይና ለአምላኳ የምታቀርበው መገዛቷ ነጸብራቅ ነው። እኛና አምላካችን ኅብረታችን የተቋጠረበት ምስጢራዊና ቅዱስ ሰንሰለት ነው። ኅሊናችን በእግዚአብሔር ቅድስና እየተነቃቃ፣ ልቡናችን በክብሩ ውበት ነጸብራቅ እየነጻ የመንፈሳዊ ሕይወታችን ልክና ደርዙ የሚታወቀው ለእግዚአብሔር ባለን መገዛትና መሰጠት እንዲሁም እርሱ በኛ ላይ በወሰደው ሉዓላዊ ጌትነቱ መጠን መኾኑ አይታበልም። እሱ ራሱ መዝገባችን በኾነበት ዐውድ ውስጥ ለእግዚአብሔር መገዛታችን ጥልቅ ደስታችን ይኾንልናል።

ራልፍ ማርቲን የተባሉ ክርስቲያን ጸሐፊ ሰለ አምልኮተ እግዚአብሔር በጻፉት መጽሐፋቸው ለአምልኮ ብያኔ ሲሰጡ እንዲህ ብለው አስቀምጠውታል፤

> አምልኮ ማለት እግዚአብሔር በልዕልናው ምክንያት ከተጐናጸፈው ገናናነት የተነሣ ክብር የሚገባው አምላክ ስለኾነ እርሱን በድምቀት መወደስ ሲኾን፣ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ህላዌ ምንጭ እንዲሁም ለአምልኮ የሚያነሣሣው ነገር ይኸው የእግዚአብሔር ታላቅነትና ግርማዊ ክብሩን መረዳት የሚፈጥረው ግንዛቤ ነው። [112]

በክርስቲያናዊ አምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ መካከለኛው መለኮት ነው። ቀዳሚው ነገር የስሜት ፍንጠዛ አይደለም። በአምላኳ የተፈጠረችና በጸጋው የዳነች ነፍስ በመገዛትና በፍቅር ለእውነተኛውና ሕያው ለኾነው ታዳጊ አምላኳ ለጌታ እግዚአብሔር የምታቀርበው የቅድስና ምላሿ ነው እንጅ። ከዚህ እውነት የተነሣ ሁለንተናዊ የሰው ማንነት እግዚአብሔርን በመውደድ ላይ በተመሠረተ ፍቅር ለእርሱ ይሰጣል። ፊተኛይቱና ታላቋ ትእዛዝም በዚህ ሐሳብ ታስራለች፤ *“ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፦ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ዐሳብህ፥ በፍጹምም ኀይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፤ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት”* (ማር. 12፥30)። ይህች ታላቋ ትዕዛዝ

[112] Ralph P. Martin, *The Wroship of God: Some Theological, Pastoral and Practical Reflections* (Grand Rapids: Eardmans, 1982) 5.

ናት። እውነት ለመናገር፣ ታላቁን ትዕዛዝ ሳንፈጽም፣ ታላቁን ተልእኮ መፈጸም እንዴት ይቻለናል?

በአጠቃላይ አምልኮተ እግዚአብሔር ከውጪያዊ ድርጊቶች በላይ ጥልቅ በኾኑ ሐሳቦችና እውነታዎች ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው። ስለዚህም፣

> አምልኮን [እውነተኛ] አምልኮ የሚያደርገው አካላዊ መንዘፍዘፍ፣ የዝማሬ መድመቅ፣ የሙዚቃ መሣሪያ ድምፅ መዋብ፣ የከበሮና የጸናጽል፣ የእምቢልታና የመለከት በአማረ ኹኔታ መደርደር አይደለም፤ ወይም ሕዝቡ ጉባኤውን በዝማሬ ሲያቀልጠው መታየቱ ሳይኾን፣ በእውነት … እና በመንፈስ ኾነን በቅድስና፣ በቅዱስ ፍርሀትና በታዛዥነት ልብ አምላካችንን ማምለካችን ነው። በእውነት ላይ የተመሠረት አምልኮ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተና ማስመሰል የሌለበት ሲኾን፣ የሚቈጣጠረውም የሰዎች ኹኔታ ሳይኾን መንፈስ ቅዱስ ነው።[113]

በዘመናችን በተለያየ ቦታና ኹኔታ እየኾነ ያለው ግን እስካሁን ከተመለከትነው ጋር የማይጣጣም ይመስላል። በአንዳንድ ቦታዎች በምውት ሥርዐተ አምልኮ የመታሰር ኹኔታ ይታያል። የመንፈስ ነጻነት የማይታይበትና የዘልማድ ድብታ የተጫነው ሥርዐተ አምልኮ በተወሰኑ ወገኖች መዘውተሩም ይኖራል። በሌላ በኩል ደግሞ “የተፈታ” በሚሰኝ መንገድ ዐላማን የሳተ የስሜት መናጥ አለ። የሚያሳዝነው ደግሞ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከጭፈራ ጋር ብቻ የማቈራኘቱ አስተሳሰብ በስፋት ተቀባይነት ያገኘ መስሎ መገኘቱ ነው።

ዝማሬና መንፈሳዊ ቅኔ በአምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ ትልቅ ስፍራ መያዝ መቻላቸው እውነት ነው። *“በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ*

[113] ሙሉጌታ ከንፉ፣ *አምልኮና ቅድስና፣* ከጳጉሜ 2-6 ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሪዎች ስብሰባ ላይ የቀረበ፣ ያልታተመ ጽሑፍ ገጽ፣ 5።





*አመስግኑ”* (ኤፌ. 5፥19-20) ይላል ቅዱስ ቃሉ። ግና በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉ ክቡር አላባዎችን በዘነጋ መልኩ የሚቀርብ መዝሙርና ዜማ ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መዝሙር አምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የሚያጠነጥን፣ እግዚአብሔርን የሚያከብር፣ በውዳሴ አምላክ የተሞላ፣ በቅዱሳት መጽሐፍት በተገለጸው እውነት መሠረት የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚያውጅ ማሕሌት ነው። የእኛን እሱን የመፈለግ ጥማት የሚያሳይ፣ በእሱ ያገኘነውንም ድኅነትና እርካታ እንዲሁም የንስሓ መታደስን ሊያጐላ የሚችል ዜማዊ ነገረ መለኮት መያዝን ያውቃሉ። በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዝማሬ ደካማነታችንን የሚገልጥና ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ምህላና ምጥንታ (ተማጽኖ) ይኖረዋል። ይህም ብቻ ይደለም፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የገለጠውን የድኅነት መንገድ ማወጅም ይጠበቅበታል። ስለዚህ መስቀሉ መካከለኛ ይኾንበታል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛዊ ሞት የተቀበልነውን የኀጢአት ስርየትና በትንሣኤው የተቀዳጀነውን ድል ማብሠርም አለበት። በጌታ ዳግም መገለጥ ተስፋ የተሞሉና “ጌታ ቶሎ ና” ባይ ሐሳቦች የክርስቲያናዊ መዝሙሮች መታወቂያዎች ናቸው። እነዚህንና የመሳሰሉትን ያካተተ ነው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የዝማሬ መገለጫ።

የዛሬዎቹስ? የዛሬዎቹን ያየን እንደኾን “በአንክሮ ሰብ የተጠመዱ ናቸው” የሚል ወቀሳ እየተሰነዘረባቸው ይገኛል። መልእክታቸውንም ስናጤን ደካማ ኾነው ይታያሉ። “እኔ እንዲህና እንዲያ ኾነልኝ፤ እንዲህና እንዲያ ተደርጎልኛልና እግዚአብሔር እንዳደላልኝ ዕወቁ፤ እኔም እንዲህና እንደዚያ አደረግሁ ወዘተ.” የሚሉ ፋከራ ዐይነቶች ናቸው በመባል ይወቀሳሉ።

ይህ ማለት ግን ሁሉም የተበላሸ ነው ማለት አይደለም፤ በፍጹም። በተገቢው መንገድ የተሠሩና በመሠራትም ላይ የሚገኙ አሉና እግዚአብሔርን ስለ እነሱ ማመስገን አለብን። “የበላበንትን ወጪት እንዳንሰብርም” መጠንቀቅ ይኖርብናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚቀርብልንን ያየን እንደኾነ ግን “ገበያው የሚመራው ኾኗል” የሚለው ነቀፌታ ከእውነቱ ብዙ የራቀ አይመስልም።

ይህም ብቻ አይደለም፤ አምልኮን አስመልክቶ የሚነሡ ቅሬታዎች ሰፍተዋል። በአምልኮ መርሐ ግብሮች ላይ ሊካተቱ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች ወይ ይዘለላሉ፤ ወይም እንዳይቀሩ ያህል ይከወናሉ። ለምሳሌ አንዳንድ ማኅበራት ከዓመት እስከ ዓመት የጌታ ራት (ቅዱስ ቍርባን) ሳይካፈሉ እንደሚዘልቁ ይታወቃል።

አንድ ባለሙያ ሊያከናውነው የሚችል ተግባር ይመስል የመርሐ ግብሩ መሪዎች በፈለጉት ኹኔታ ሕዝቡን የሚያንገላቱበት ኹኔታም አለ። የመርሐ ግብሩ ጊዜ በዝማሬና በሌሎች ጉዳዮች ከመጠን በላይ እንዲባክን በማድረግ በአለቀ ሰዓት ለቃለ እግዚአብሔር የሚለቀቀው መድረክ አገልጋዩን ለጥድፊያና ለመሣቀቅ ሲዳርገው፣ ምእመናኑም በመቼ ያልቅልኝ ይኾን ችኮላ እንዲሞሉ ሲያደርጋቸው ይታያል።

አንዳንድ ጊዜማ፣ የመድረክ አስተባባሪው፣ መባ ለመሰብሰብ የቆመው ዲያቆን፣ ማስታወቂያ ተናጋሪው፣ ሰባኪውና ሌሎችም ተረኞች በሙሉ ካልዘመርሁ በማለት ሲያስቸግሩ የሚስተዋልባቸው ማኅበራት ሞልተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የአስተባባሪው የማያቋርጥ ትእዛዝና መመሪያ እንደ ዶፍ ከመድረክ ሲወርድ የሚውልበት ጊዜ አለ። ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት ትዕግሥት ያጡ ዘማሪያን የመኖራቸውን ያህል፣ ከጉባኤው ጋር የአምልኮ ጊዜን ማሳለፍ የማይኾንላቸው ሰባክያን ይኖራሉ። ሰባኪውና ዘማሪው ርስ በርሱ የተጣላ መልእክት አስተላልፈው ከመድረክ የሚወርዱበት ኹኔታም ስለሚያጋጥም ማኅበሩ በተከፋፈለ ሐሳብ ውስጥ እንዲገባ ሲገደድ መታዘብ ይቻላል።።

በአምልኮተ እግዚአብሔር ውስጥ ግድ ሊሰጠን የሚገባው ቴክኒክና ዘዴዎች ሳይኾኑ የእግዚአብሔር መገኘት ነው። አለበለዚያ ግን “የትኛውም ያህል በንግግራችን የተሳካልን እንኹን፣ ምንጩ እኛው ኾነን እኛው ከታየንበት፣ ጉዳዩ የፍጡር ተውኔት ይኾናል”[114] ማለት ነው። ከሌሎች ጉባኤዎች የተመለከትነውን ድርጊት ሁሉ እየኮረጅን ወረፋ በደረሰን ጊዜ ለመድገም መጣርም ከንቱነት ነው።

[114] ኀይሉ፣ *መድረኮቻችን፣* 49።





ክርስቲያኖች በአንድነት በሚሰበሰቡና ለአምልኮ በሚቀርቡበት ጊዜ ከውስጥ የመነጨ መገዛትና በመንፈስ የኾነ ተመስጦ ማድረግ እንዲችሉ መፈቀድ አለበት። ይህ የሚኾንበት አንደኛው መንገድ ደግሞ የኅብረት ጸሎት ነው። “ትርጕም ሊሰጥ የሚችልን ትክክለኛ አምልኮ ምንነት የሚገልጥልን ጸሎት ነው። በመለኮት መገኘት ውስጥ የሚመጣውን ኅብረት በጸሎት የሚለማመድ ሰው በዙሪያው የሚከናወነው ነገር ምን እንደ ኾነ ሳይረዳ ወደ አምልኮ መርሐ ግብር አይገባም።”[115] ይህ ዐይነቱ ክቡር ግንኙነት ግን በሰው ሠራሽ ግር ግር ሲተካ ይስተዋላል። ጸሎትም የዚህ ውክቢያ አካል ተደርጎ መወሰዱ አሳዛኙ ምጸት ነው። ጸሎትን ያህል ነገር ችላ ያለ አምልኮ ምን ዐይነት አምልኮ ሊኾን ነው?

በሌላ በኩል፣ ጸሎቱ አለ ከተባለ እንኳ “መሪው” ያለምንም ፋታ ትንፋሹ የሚቋረጥ እስከሚመስል ድረስ ስለሚለፈልፍ ማኅበረ ምእመናኑ የተመስጦና የጽሙና ዕድል ይነፈገዋል። ወይም አምልኮው በሰው ዐይን በሚገቡ ውጫዊ ትዕይንቶችና ሰው ሠራሽ ነገሮች ሲተካ ይስተዋላል። እውነቱ ግን “በሕይወት ውስጥ እጅግ የከበሩ ነገሮች፣ ነገሮች አይደሉም፤”[116] እግዚአብሔርን ማግኘት እንጂ። በአምልኮ ውስጥ እየፈለግን ያለነው እኮ ሰማይን ነው። በምድር ኾነን ሰማያዊውን የምንቀምስበትና ከፍ ያለውን ርካታችንንም በእግዚአብሔር መንግሥት ሐሳብ የምንለማመድበት አንዱ መንገድ ነው አምልኮ።

በተሰበረው ዓለም እየኖርን የመንግሥተ ሰማያትን ጥልቅ ሐሴት በክርስቶስ በኩል እንድንለማመድበት አምልኮ ከፍ ያለ እንክብካቤ ሊደረግለት ያሻዋል። በዚያን ጊዜ ነው ለሌሎችንም *“እግዚአብሔር ቸር እንደ ኾነ ቅመሱ፣ እዩም”* (መዝ. 34፥8) ማለት የሚቻለን። ተደጋግሞ እንደ ተነገረው፣ ፍስሐና ደስታ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው። ቅዱስ ቃሉም ይህን

[115] John Killinger as quoted in Jack Hayford, John Killinger and Howard Stevenson, *Mastering Worship* (Portland: Christianity Today, 1990) 17.
[116] “The greatest things in life are not things” የተሰኘውን የኬቪን ናቫሮ አባባል ተርጕሜው ነው። Kevin J. Navarro, *The Complete Worship Service* (Grand Rapids: Baker, 2005) 22-23.

እውነት ያረጋግጣል፤ *“የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፥ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ”* (መዝ. 16፥11)።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን ከተዘጋጁት በርካታ የእምነት መግለጫዎች አንዱ በኾነውና የዌስት ሚኒስትር የተአምኖ መግለጫ (*The Westminster Confession*) በሚሰኘው ውስጥ እንደ ሰፈረው፣ “የሰው ልጅ ከፍተኛውና ሁለንተናዊ መዳረሻ እግዚአብሔርን ማከበርና በእርሱም ደስ መሰኘት ነው።” አዎ፣ በፊቱ ብርሃን ጨለማችን ቦታ ያጣል፤ በመገኘቱ ውስጥ ርካታችን እውን ይኾናል፤ ደስም ያሰኘናል፤ *“የዘላለም በረከትን ሰጥተኸዋልና፤ በፊትህም ደስታ ደስ ታሰኘዋለህ”* (መዝ. 21፥6)። ለዚህ ጥልቅ ደስታ ለሚትረፈረፍበት ኅብረት ወደ ምንጩ መሄድ ያስፈልገናል። በእውነትና በመንፈስ የሚኾን አምልኮተ እግዚአብሔር ዕፎይታችንን ከምንጩ የምንቀዳበት መሥመራችን ነው። በአምልኳችንም ውስጥ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያደረገልንን በማውሳትና በማወጅ ደስ እንሰኛለን፤ በፊቱም ብርሃን እንመላለሳለን። ይህ እንዴት ድንቅ ነው!

ታዲያ የኛን ዘመን አምልኮ ስንመለከተው ይህ ተመክሮና ልምምድ በጥልቀት ይታይበታልን? ምላሹን ለአንባቢ ኅሊና ፍርድ እንተወዋለን።

የዘመናችንን የአምልኮ ኹኔታ በቅዱሳት መጻሕፍት በተገለጹ መመሪያዎችና ናሙናዎች መነጽር የተመለከቱት መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን ጠቅለል ባለ፣ ነገር ግን ጥንቃቄ ባልተለየው፣ አኳኋን የሰጡት ድምዳሜ ሊጠቀስ የሚገባው ነው፤

> የቀደሙት አባቶች እግዚአብሔርን ባመለኩባቸው መንገዶችና የሙዚቃ መሣሪያዎች ብዛት፣ ... እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚቀርብ ሰው ሊኖረው በሚገባው የመንፈሳዊ ሕይወት ይዘት፣ ... ለአምልኮ በተሰባሰቡ ሰዎች መካከል ሊኖር በሚገባው መሰጠት፣ የመንፈስ ነጻነትና እንዲሁም ሥርዐት፣ ... አንጻር





> ሲገመገም የዘመናችን አምልኮ ገና ብዙ እንደሚቀረው መገንዘብ እንችላለን።[117]

በዚህ “ብዙ መቅረት” ውስጥ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ቍም ነገሮች ቀላል አይደሉምና በቸልታ ሊታለፉ የሚችሉ አይኾንም።

ይህን ርእስ ከመዝጋታችን በፊት ከእውነተኛና ሕያው አምልኮ ጋር መነጠል የማይገባውን አንድ ተጨማሪ ጉዳይ ማንሣት አለብን። ይኸውም ጽድቅና ፍትሕ ማድረግን ይመለከታል። ጽድቅና ፍትሕ ሕይወታችን ወደ “ላይም” ወደ “ጐንም” ሊኖረው በሚገባ ኅብረት ንጽሕና ላይ የሚያጠነጥን ነው።

በአንድ በኩል ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና በመጠበቅ መኖር የአምልኮተ እግዚአብሔር ዋና ነገር መኾኑ መዘንጋት የለበትም። ቅዱሱ እግዚአብሔር በእድፋም ሕይወት አይመለክም። ይህ አንዱ ገጽታው ነው። *ጽድቅ* (*righteousness*) የተባለው እሱ ነው። ጳውሎስ እንዳለው፤ *“በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የኾነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የኾነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የኾነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢኾን ምስጋናም ቢኾን፥ እነዚህን ዐስቡ”* (ፊል. 4፥8) ተብለናል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የክርስቲያናዊ አምልኮ ሕይወት ማኅበራዊ ኀላፊነትም እንደ አለበት የታወቀ ነው። *ፍትሕ* (*justice*) ያልነው ይህን ነው። “ጎረቤት ጭንቀት ነው፤ እኛ ቤት ሰላም ነው” ይሉት ዳንኪራ ብቻ የሚያሸልለን ከኾነ ንፉጋን ኾነናል ማለት ነው። እኔ ቤት ተርፎ እየተደፋ፣ ወንድሜ ግን የሚቀምሰው ዐጥቶ ራሱ ከተደፋ አምልኮዬ የከንቱ ከንቱ ይኾናል። በሌሎች ላይ የሚደርሰው ግፍ የማይቈጨንና የማያስጨንቀን ከኾነ፣ ማኅበራዊ ፍትሐ ሲጓደልም ዝምታን ከመረጥን የአምልኮተ እግዚአብሔር ግንዛቤያችን “ግማሽ

---

[117] በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)፣ *“መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአምልኮ ልምምድ፣” የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፣* 5።

ልጩ" ይኾናል። ይህን አስመልክቶ ማርክ ሌበርተን በኀዘን የተናገረው ትክክል ነው፤

> በአምልኮ ላይ ያነጣጠረውን ትግል ማእከላዊ ነጥብ እንመልከት፡- የአምልኮ ልምምዳችን ፍትሕ ለማድረግ ከቀረበልን ጥሪ የተነጠለ ነው፤ ሲብስ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ራስን ከመካድ ሕይወታዊ ተመክሮ ይልቅ ራስን ማቀማጠል የተሞላውን ባህላዊ ዝንባሌያችን የሚያባብስ ኾኗል። ርግጥ ተኝተናል፤ እንግዲያውስ ከዕንቅልፋችን ነቅተን በመነሣት አደገኛ የኾነውን የአምልኮን ተግባር—እሱም ስለ ፍትሕ የቀረበልንን የእግዚአብሔርን ጥሪ — ከመለማመድ በላይ አስፈላጊ የኾነ ነገር እንደሌለ እንገንዘብ።[118]

ከላይ ያየናቸውን ሁለቱንም የአምልኮተ እግዚአብሔር የኀላፊነት ገጽታዎች ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ይሸመልላቸዋል። *"ንጹሕ የኾነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች፥ ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ ኢድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው"* (ያዕ. 1፥27)። "ስጡ" መባላችንን ወደ "ስጡኝ" በለወጥንበት በዚህ ዘመን ድሀ አደጎችንና መበለቶችን ማን ያስባቸዋል? እንዲያውም ይህን የሚያከፋፋ ትምህርት ሲተላለፍ ይሰማል እንጅ። ችግረኞች ሕሙማንና ኀዘንተኞች ያሉበት ቦታ መድረስም ጥሪያችን አይደለም ባዮች እየመጡ ነው።

በከተማችን የራሳቸው ማኅበር ያቋቋሙ አንድ መጋቢ በተሌቪዥን መስኮት በሚተላለፍ መርሐ ግብራቸው እንዲህ ብለው ነበር፤ "የእምነት አባቴ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ባገለገሏት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሰባና ሰማንያ ዓመት ዕድሜው በታች የሞተ አባል አልነበራቸውም፤ እኔም መመሥረት የምፈልጋት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዐይነት ነች፤ ለምን ቢባል በየሆስፒታሉና በየቀብር ሥፍራው መንከራተት አልፈልግምና ነው።"

[118] Mark Labberton, *The Dangereous act of Worship: Living God's Call to Justice* (Dowbers Grove: IVP, 2007) 22-23.





ይህ ምንኛ ማስተዋል የጐደለውና አሳዛኝ አባባል ነው! ንጉሡ በመጨረሻ፣ *"ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ኾኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና"* በማለት እንደሚባርክ በአንክሮ የተናገረው ሞጋች ሐሳብ በሕይወታችን የሚፈጸመው ከሆስፒታልና ከኀዘን ቦታ እየሸሸን ነውን? ኧረ፣ ለአነጋገራችን ትንሽ ለከት ይኑረን።

እንግዲህ አምልኮተ እግዚአብሔር ከቡር ትእዛዝ ቅዱስም ተልእኮ መኾኑ መዘንጋት የለበትም። በአምላኳ የተፈጠረችና በክቡር ደሙ ተዋጅታ በጸጋው የዳነች ነፍስ በመገዛትና በፍቅር ለእውነተኛውና ሕያው አምላክ በእውነትና በመንፈስ የምታቀርበው የቅድስና ምላሿ ነውም ብለናል። የኅብረት አምልኮ ማስተዋልና ብሥራት የተሞላ መኾን ይገባዋል። መጋቢው፣ ዘማሪው ወይም ሰባኪው ምእመናኑን በራሱ ማንነት የሚያስደንቅበት ትእይንት ሳይኾን፣ የከበሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገረ መለኮታዊ ሐሳቦችን በማስጨበጥና በመንፈስ በመመራት ማኅበሩ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲደነቅና እንዲደሰት መለቀቅ አለበት።

ዐላፊ ጠፊ ከኾነው ዓለም ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት የፈለስነው ንጹሕ የኾነ አምልኮ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነው። በወደቀው ዓለም ውስጥ እየኖርን ቢኾንም፣ እግዚአብሔርን በቅድስና የምናመልክ የእምነት ማኅበረ ሰብ ነን። ለተሰበረው ዓለም መልእክት አለን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን እንለምናለን። እንባ የምናብስ፣ ችጋረኞችን የምናጐርስ፣ መበለቶችን ጠያቂና ለድሀ ዐደጉ ተሚጋቾች መኾንም የጥሪያችን አካል ነው። እውነተኛና ሕያው አምልኮ ከዚህ ውጭ አይታሰብም። ጌታ እኛን የጠራን ዓለመኛነትን ከሚያባብሰው ሥሥት ተለይተን፣ መጻተኛ እንደ መኾናችን፣ የእምነት መናኝነት ጉዟችንን ጠበቅ አድርገን እንድንያያዘው ነውና። አሊያ ዐለመኛነት ይጠናወተናል።

## 2.7 ዓለመኛነት፦ "ሁሉ ዛሬ"ና "ሁሉ እዚሁ" ብቻ

በርእሱ "ዓለመኛ" ያልኩት ነገር መብራራት አለበት። እዚህ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ሐሳብን፣ ትኩረትን፣ የኑሮ ጠባይን እና የክርስትናችንን ሁለንተናዊ ግብ ወደ ምድራዊ ሥርዐት፣ ፖለቲካ፣ ሀብት፣ ብልጽግና፣ ወዘተ. ላይ <u>ብቻ</u> ቀርቅሮ በጽኑ መቸ'ከልን ለማመልከት ነው።

ጥያቄው እንግዲህ፣ "እንዲህ ዐይነቱ ሕመም በኛ ዘንድ አለ ወይ?" የሚል ነው። ሞልቶ እንጂ! ሕይወታችንና አኗኗራችንን ልብ ብሎ ለተመለከተ ሰው ከተወቃሽነቱ የምንርቅበት ኹኔታ ብዙም እንዳይደለ ሊያስተውል ይችላል። በራስ ታዘብና ተሐድሷውያን መጣጥፎቹ አማካይነት ትውልዳችንን፣ በጲጋ በተቀመመ የጥበብ ቃሎቹ፣ የሚገኅትለው ጋሽ ንጉሤ ካጣቀሰው ተሐዝቦት ትንሽ ብንቈርስ ሐሳባችንን ሳያጕለብትልን አይቀርም። ጋሽ ንጉሤ ከአሳሳቢነት ዐልፎ፣ ተርፎ "አስጨናቂና አስተካኝ" ኹኔታ አለ ነው የሚለው፤

> ይህን ያህል አሳሳቢ አነጋገሪ ሁኔታ አለወይ የተባለ እንደኾነስ? አሳሳቢና አነጋገሪ ብቻ ሳይኾን አስጨናቂ አስተካኝ ኹኔታ ላይ መኾናችንን መመልከት ይቻላል እላለሁ። ማዕድ ፊታችን ሲቀርብ ቡራኬ የምንሰጥ ቢኾንም፣ ሰላምታችን እልፍ ጊዜ "ጌታ ይባረክ" በሚል መፈክር ቢያስገመግምም፣ በጓዳ ጸሎታችን ግን "የወንድም ቀበኛዬን ዶግ ዐመድ አድርገህ አሳየኝ" እያልን የምንራገም ነን። ጸሎታችን አንዱ ታዛቢ እንዳለው የሚርት ጸሎት ኾኗ። "እሷ ዓለማዊት ናት ክርስቲያን?" እያልን የማኅበራችንን ወንበር የምንነፍግና የምንመጻደቅ ብንኾንም፣ "ዓለማውያን" ከኾኑት ይልቅ ዓለም በደንበኝነት የምታውቀን እኛኑ ኾነ። ምክንያቱም ዓለማዊነት በዓለም ውስጥ መኖር ሳይኾን በገዳምም ኾነን ዓለም በእኛ ውስጥ መኖሯ ነው። መዝሙሮቻችን ደጋግመው "አምላኬ ጌታዬ" እያሉ የታላቁን አምላክ ስም ቢጠሩም፣ ቊርጡን ስንጠየቅ ዕቃ አምላኪዎችና የገንዘብ ሎሌዎች መኾናችን እስከዚህም ድብቅ አልኾነም። ሟች ስንሸኝ ስለዘላለም ቤት፣ ስለ ሰማይ መንግሥት ብናወራም የየዕለት የሕይወት ዘይቤያችን ግን "ያላዩት ሀገር አይናፍቅም"፣ የሚያዋጣኝ የዛሬውንና የእዚሁን አጥብቄ መያዝ ነው፤ የሚመጣውን ሲመጣ እናያለን የሚል ይመስላል።[119]





እነሆ፣ እንግዲህ ይህን እንመስላለን። "ክርስቶስን በዚች ሕይወት ብቻ ተስፋ የማድረግ" (1ቆሮ. 15፥19) ድንጋሬ አልፈተነንም ማለት እንዴት ይቻለናል? *"በላይ ያለውን አሹ"* (ቆላ. 3፥1) ይሉት ወግ ዐልፎ ዐልፎ ስብከት ለማጣፈጥ ብቻ የሚነገር መሰለ፤ ሚዛን ተጓደለ። የጥቅም ፉክክሩ ጦፎ የአንድ አባት ልጆችን ሳይቀር እያካሰሰና እያካካደ ተገኘ። በአቋራጭ የበለጸገ ብልኅ ተባለ። የትልቅነት መለኪያው "የእንጀራ ዐይነትና" "የጕተራ" ብዛት/መጠን ኾነ። ምን ያልኾነ አለ? "ጌታን መጠበቅ ይሻለኛል" በማለት በንጽሕና ለመኖር መቊረጡ የሞኝነት መንገድ ተደርጎ አልተቈጠረምን? ይህንም ኾነ ሌላውን ዐይን አይታለች፤ ጆሮም ሰምታለች። በወንጌል ማመናችን የአሁኑን ዓለም ኑሯችንን መንካቱ ባይቀርም፣ ብቻውን መድረሻ ግባችን ተደርጎ ተወደሰ። በሽመታው የነሆለሉ ከክቡር የሕይወት ዓላማቸው የመፈናቀላቸው ነገር በሰፊው ሲነገር ሰማን፤ አነበብንም። ይህ የዋጤ (*consumerism*) ልክፍት ወደ ታች አስጎንብሶ የሚያስጕበድድ በመኾኑ የላይኛውን ከማሰብ ማዘናጋቱ ልብ የተባለም አይመስልም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና "በኾነና ሊኾን ባለ/በተፈጸመና ሊፈጸም ባለ" ድል መካከል ያለ ሕይወት ነው። እዚሁ ተጀምሮ እዚሁ የሚያልቅ ልቅላቂ አይደለም። የመንግሥቱ ሕይወት፣ ዐዲሱ ኪዳን፣ ድኅነታችን፣ ቤዛችን፣ የትንሣኤው ሕይወት፣ ዐዲስ ፍጥረት፣ የመጨረሻው ፍርድ፣ ወዘተ. ተመርቆ ቢከፈትም ተፍጻሜያዊ መጠናቀቁን ገና አላገኘምና በዚህ ድንኳን ያለን ከብዶን በመቃተትና በምጥ እየጠበቅን የምንኖር ሰዎች መኾናችን መዘንጋት የለበትም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ2ቆሮ. 5፥1-4 ላይ እንዲህ ይላል፤

---

[119] ንጉሤ ቡልቻ፣ "የከሐደት እምነት፣" *በመስተአየት* (ዐዲስ አበባ፦ ሊቪንግ ትሩዝ አገልግሎት፣ 2002 ዓ.ም.) 50።

> *ድንኳን የሚኾነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚኾን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፤ ከሰማይም የሚኾነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም። በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ኾነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን።*

አዎ፣ ከብዶን እንቃትታለን፤ ተስፋችን በዚሁ ዓለምና ዘመን ብቻ የተወሰነ አይደለም። *"በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከኾነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን"* (1ቆሮ. 15፥19)።

በዘመናችን የምንሰማቸው አንዳንድ ትምህርቶች ግን ነገራችንን እዚሁ ተጀምሮ እዚሁ የሚያልቅ አስመስለዉታል። እንጀራ ዋጋና ክብር አግኝቶ የሁለንተናችን መካከለኛ ተደርጓል። ቍሳዊ በኾነው ዓለም ሐሳብ ከፉኛ እንድንጠመድ የሚያተጉና የሚያነቁ ትምህርቶችም እየዘነቡብን ነው። ለዚህ ዓለም እንግዳና መጻተኛ መኾናችንን (ዕብ. 11፥13፤ 1ጴጥ. 1፥1-2) ማሰብም ኾነ ማወጅ ጕጭማ መረዳት ተደርጎ ይፈረጃል። ከዚህ ሲብስም ቀደም ባለው ዘመን ስለ ወንጌልና ስለ እውነት ብለው በከፈሉት ዋጋ የሚጸጸቱ አንዳንድ ሰዎችም ይገኛሉ። በአጠቃላይ ለዚህ ጊዜያዊ ድንኳን ኑሮ መገምገርት እየተስፋፋ ነው ብቻ ሳይኾን መንፈሳዊ ቋንቋ ተላብሶና ራሱን በቻለ የአስተምህሮ ኩታ ተሸፋፍኖ እየተስፋፋ ይመስላል። እስቲ በኤልሻዳይ *ቴሌቪዥን ኔት ወርክ* (ETN) ላይ በአንድ ሰባኪ ሲተላለፍ የነበረና በዕለቱ በማስታወሻዬ ያስቀረሁትን ይህን ስብከት፣ በምሳሌነት እንመልከተው፤

> እግዚአብሔር የሰጠኝ *ማንዴት* [ኃላፊነት] ይህን ሕዝብ ከድህነት ማላቀቅ ነው፤ የተጠራሁት ለዚሁ ነው። ... *School of Prosperity* — የብልጽግና ትምህርት ቤት — ይከፈታል። ባለጸጎች የሚሠለጥኑበት፤ *Future Billioners* የሚባሉ — የወደፊቱ *ቢሊየነርስ* — ተብለው ይገቡበታል ... በመንፈሳዊው ዓለም ላይ ባለሥልጣንነታችን መረጋገጥ አለበት።... የምትሠቃዩት ባለማወቅ ነው። ... በቤታችሁ ውስጥ የተቀመጡ ሰዎች አሉ፣ መኪናዎቻችሁን የያዙ አሉ፤ የማይገባቸው። አንዳንድ ጊዜ ይህን ሳይ ያስቈጨኛል። ... ባለፈው አንድ ቦታ ሄጄ የኾነ ነገር ተመለከትሁ፤ እናም "ይህ የኔ ነው" አልሁ። ... [120]





ጉድ በል ጳውሎስ! ዛሬ አንተ ብትኖር ኖሮ ይህን በመገምገርት የተሞላ ልፈፋ ምን ትለው ይኾን ነበር? "ምላጭ አበጠ፤ በምን ይበጣ" እንዲል የሀገሬ ሰው፣ መንፈሳዊ መሪዎቻችን የጽናት አርአያ ካልኾኑልን መንጋው ማን ይከተላል? አሳሳቢ ነገር ነው። ዓለመኛነት መንፈሳዊ ባንዲራውን እያውለበለበ በየቦታው እየተንሰራፋ በመጣበት በዚህ ዘመን ጥብቅ መሸሸጊያ ያሻናል።

"ባሕር ተሻግሮ" መሄድ መቻል፣ በተለይም አሜሪካና አውሮጳ መንጐድ፣ በጌታ የመከበርና የመገብኘት ምልክት ተደርጎ ይታመን ዘንድ፣ ቍጥራቸው ቀላል በማይባል ምእመናን አስተሳሰብ ውስጥ፣ በማይነቃነቁ ቅንዋት (ምስማሮች) እንደ ተቸነከረ ከምናየውና ከምንሰማው መረዳት ይቻላል። የሐሰት ምሥክርና ማስረጃ ሳይቀር እየተጠቀመ ወደ ውጭ ሀገር የተመመው ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ለምሳሌነት እዚህ መጠቀስ ይኖርበት ይኾናል።

የክርስቲያን ተስፋው የዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር ተሐድሶን የሚያመጣው ሁለንተናዊ ጕብኝት መኾኑ እውነት ነው (ኢሳ. 65፥17፤ 66፥22፤ ራእ. 21፥1)። ስለዚህም፣ *"ጽድቅ የሚኖርባትን ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን "* (2ጴጥ. 3፥13)። በዚህ ክቡር ተስፋ ተፍጻሜት ላይ ስንደርስ በምጥና በመቃተት የተሞላው ፍጥረት ከጥፋት ባርነቱ ይፈታል (ሮሜ. 8፥19-23)። *"እነሆ፣ ሁሉን ዐዲስ አደርጋለሁ"* (ራእ. 21፥5) ያለው ጌታ ተስፋውን ይፈጽማል። ስለ ኾነም ክርስቲያኖች *"ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ"* (ሉቃ. 21፥28) የተባሉ የእምነት መናንያን

[120] ኤልሻዳይ አበራ ("ዋና" መጋቢ)፤ *"ርእስ አልተጠቀሰም፤"* ስብከት፣ ታኅሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም. ከቀኑ 8:00 ሰዓት ጀምሮ በኤልሻዳይ ቴሌቭዥን ኔትዎርክ በኩል ሲተላለፍ ከነበረ ንግግር በከፊል የተወሰደ።

ናቸው። ይህ ሲባል በዚህ ሕይወት ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን የበጎነቱና የመግቦቱን ነገር ቸል በማለት አይደለም። ከመላለማዊ መግቦቱና ለሕዝቡ ካለው ርኅራኄ የተነሣ እግዚአብሔር በሚያስፈልገን ነገር ይባርከናል። ነገር ግን መንፈሳዊነትን ማትረፊያ ለማድረግ መባከን የወንጌሉን አድማስና ዳርቻ አለመገንዘብ ነው። ክርስቲያን "ተስፋ ለመያዝ የሸሸ" (ዕብ. 6፥18) የእምነት ተጓዥ እንደ መኾኑ፣ አማኞች ተፍጻሜትን (*Consummation*) ጠባቂዎች ናቸው።

በመኾኑም፣ ክርስቲያኖች ከግለ ሰባዊ ስኬት፣ ጤንነት፣ ርካታ፣ ብልጽግና በላይ የዓለም ብርሃንና ጨው የመኾን ማኅበረ ሰባዊ ፈያጅነት ላይ ያተኩራሉ። በፉለር ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የኾኑት የነገረ ሰብ ሳይንቲስቱ ፖል ሂበርት ይህን ርእሰ ጉዳይ አስመልክተው የጻፉት ለመጠቀስ የሚበቃ ነው፤

> እንዳለመታደል ኾኖ ብዙ ክርስቲያኖች የግለ ሰብ ጤንነትና ብልጽግናን እንደ ዋነኛ ግቡ አድርጎ የሚወስደውንና ይኽንኑ የሚያቀነቅነውን የምዕራባውያን ባህል እየሸመቱ ነው። ውጤቱም በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች በመላው ዓለም በድህነት፣ በጭቈናና በዐመፅ እያለቁ ባሉበት እኛ በራሳችን ጥቅም ብቻ እንድንጠመድ አድርጎናል። መጽሐፍ ቅዱሳዊው የጤንነት ብያኔ የሚያተኵረው በግለ ሰብ ደኅና መኾን ላይ ሳይኾን በፍቅር ላይ በተመሠረተ የርስ በርስ ግንኙነት ላይ በጸናው *ሻሎም* ላይ ነው። የሚጀምረውም ከእግዚአብሔር እና ከጠላቶቻችን ጋር ስንታረቅ ነው። መገለጫው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሳችንን መሥዋዕት በማድረግ ላይ በተመሠረተ የርስ በርስ መሰጣጠትና አገልግሎት የሌሎችን ጒድለት በማሟላት ነው። ፍሬውም አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጤንነት ነው። ከ*ሻሎም* ይልቅ በግለ ሰባዊ ደኅና መኾን እና ብልጽግና ላይ ብቻ ማተኰር ከበሽታው ይልቅ የሕመም ምልክቶቹን እንደማከም ይቈጠራል።[121]

ሂበርት በሚገባ አስተውለዋል። በሽታው ባልተወገደበት ጊዜያዊ የሕመም ምልክቶችን ብቻ ለማስወገድ መሞከር ከንቱ ድካም መኾኑን ያስተምራል።

[121] Hiebert, *Anthropological Reflections*, 244.





ሕመሙን የማስወገጃው መንገድ ራስን መስጠት የተሞላው የርስ በርስ መዋደድ ነው። ሞላሁ ማለት የማያቀውን የራስ ወዳድነት ጒድጓድ ለመድፈን መጣጣራችን በሕይወት ውስጥ ሊኖረን የሚገባውን ጥልቅ ዓላማና ዘላቂ ትርጒም ያባክንብናል። ይልቅስ ታላቅ ደስታ የሚያጐናጽፈንን ነገር መፈለግ አለብን። ይኽም ደስታ ትርጒም ባለው መንገድ ሌሎችን በማገልገል ላይ የተመሠረተው ጤናማ የርስ በርስ ኅብረታችን ታድሶ ሊባርከን ለሚቻለው አምላክ በመማረካችን የሚገኝ ፍስሐ ነው።

በአንድ ወቅት ለመንፈሳዊነት ጒጒት ያደረበት አንድ ወጣት ደቀ መዝሙር ገዳማውያን አበው (የምድረ በዳ አባቶች) ተብለው ከሚጠሩት መካከል ወደ አንደኛው ዘንድ ይመጣና፤ "አባ፣ እባክዎ ከቃለ እግዚአብሔር አንድ ኀይለ ቃል ይስጡኝ" በማለት ልመና ያቀርብላቸዋል።

ጥበበኛው መካሪ መነኵሴ ይህ ደቀ መዝሙር የሚሰጡትን የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ለሙሉ በሕይወቱ ኖሮት እስኪጠነቅቅ ድረስ ወደ እሳቸው ተመልሶ ላለመምጣት ቃል የሚገባ ከኾነ ቃሉን ሊሰጡት ይስማማሉ።

በጒጒት የተሞላው ወጣት ደቀ መዝሙርም፤ "በርግጥ፣ አባ፣ የሚሰጡኝን ቃል ሳልኖረው ወደስዎ ተመልሼ አልመጣም" በማለት አረጋገጠላቸው።

"እንግዲያውስ የኔ ልጅ፣ የጌታ ቃል ይኸውልህ፦ '*እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኀይልህ ውደድ*' የሚል ነው" አሉት። ያም ወጣት ቃሉን ተቀብሎ ተሰወረ፤ ዳግመኛም አልታየም፤ ምናልባትም እስከ ዘላለሙ የቀረ ይመስል ነበር።

ኾኖም፣ ከሃያ አምስት ዓመታት ቈይታ በኋላ፣ ያ ደቀ መዝሙር ወደ መካሪው አባት ለመመለስ ድፍረት አገኘ።

ወደ መነኵሴው እንደ ደረሰም፣ "ከዓመታት በፊት የሰጡኝን ቃል ኖሬዋለሁ፤ የሚሰጡኝ ሌላ ቃል አለዎት?" ሲል በአክብሮት ጠየቃቸው።

መካሪው መነኮሴም እንዲህ አሉት፤ “አዎን ልጄ አለኝ፤ ግን ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ ማሳሰቢያ ይኖረዋል፤ ይኸኛውንም ቃል የምሰጥህ በሕይወትህ እስክትተገብረው ድረስ ወደ እኔ ተመልሰህ የማትመጣ ከኾነ ነው” አሉት።

“እስማማለሁ አባቴ፣ ሳልኖረው ተመልሼ አልመጣም” አለ።

“በል እንግዲህ ተቀበል፤ ቃሉ ‘ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ’ የሚል ነው” አሉት።

ያ ደቀ መዝሙር ዳግመኛ ላይመለስ ላንዴም ለመጨረሻም እንደ ወጣ ቀረ።

መጠነኛ የደግነት አድራጎታችንም ይሁን የተትረፈረፈ ልግስና ማሳየታችን፣ በመንፈስ እየተመራን ሌሎችን ለማገልገል እስከ ፈጸምነው ድረስ፣ የውስጥ ርካታ እናገኛለን፤ እግዚአብሔርም ይከብርበታል። የምናገለግለው ለመታወቅ አይደለም፤ ምክንያቱም በተዘዋዋሪ የራስ ክብር የመፈለግ ሥሥት ይኾናልና። የምናገለግለው ከክርስቶስ ጋር እንዲሁም ርስ በርሳችን መቀራረባችን ጥልቅ ደስታ ስለሚሰጠን ነው። የፍቅራችን መግለጫ ይኸው ነው፤ ሌሎች ደስ እንዲሰኙ የሚገባንን ማድረግ ብቻ ሳይኾን፣ በእነርሱ ደስታ ምክንያት ደስታችን ከጨመረ፣ የክርስትና እውነተኛ ጠባይ በኛ ታየ ማለት ነው።

በመዋጀታችን ውስጥ ከመንግሥቱ ተስፋዎች በዚህ ሕይወት ሳለን የቀመስነው መኖሩ ትክክል ነው። በአሁኑ ዘመን ኑሯችን ውስጥ የምናገኛቸው መልካም ስጦታዎች ቢኖሩም እንኳ፣ ልክ ወደሌለው ሥሥትና መጕምጀት ሊወስደን ግን አይገባውም። ዓለመኛነት የወደቀውን ዓለም ፍርፋሪ በማሳየት በሥጋችን ድካም እየሰነከለ ንፍገታችንን የሚያጕለብት ጠንቅ ነው። ይህን የሚያባብሉ ትምህርቶች በመካከላችን መኖራቸውን ደግሞ ልናስተባብለው አይቻለንም።

በዚህ ርእስ ሥር በርካታ ነገሮችን ማንሣት ይቻል ነበር። ኾኖም ለአንባቢዎች በደንብ የሚታወቁ ናቸውና ዐልፌዋለሁ።በአጠቃላይ የአስተምህሯችን ወደ “ዛሬና እዚሁ ብቻ” አቅጣጫ ማዘንበል ሀይ ባይ ያጣ ችግር እየኾነ መምጣቱ ያሳስበናል። ይህን እያሰብንም አንድ ተጨማሪ ጕዳይ ወደማየቱ እንሻገራለን።





## 2.8 *የዝርወተ — ኢትዮጵያዊው (ዲያስጶራው) ነገር*

በልዩ ልዩ ምክንያት ከሀገር ወጥተው በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተበተኑ ኢትዮጵያውያን ቍጥር በጣም ከፍተኛ መኾኑ ከየአቅጣጫው የምንሰማውና የምናነብበው ነገር ነው። ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን መካከል የወንጌል አማኝ የኾኑ ክርስቲያኖች ቍጥርም ጥቂት የሚባል አይደለም። ምንም እንኳ እነዚህ ወገኖች ከሀገር ውጭ ቢኖሩም በሀገር ውስጡ ጕዳይ ላይ ያላቸው ጕልበት በቀላሉ የሚታይ አልኾነም። በማኅበራዊ፣ በምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ ጕዳዮች ብቻ ሳይኾን፣ በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ላይም ጠንካራና ረጅም እጅ እንዳላቸው የታወቀ ነው። ስለዚህም፣ በድኅረ “ነጻነት” በሀገር ቤቱ እምነትና አገልግሎት ላይ ያሳረፉት ተጽዕኖ ሣቅና እንባ የቀላቀለ ይመስላል።

አቶ ጌታቸው በለጠ ባዘጋጁት *ሌሎሄና ሃሌ ሉያ* በተባለ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ይህን ጕዳይ አስመልክተው እንዲህ ይገልጻሉ፤

> የዘመነ ደርግን ከፉ ዓመታት በሌሎች ሀገሮች በመጠለል ካሳለፉ በኋላ “የነጻነቱን ዘመን” ብሥራት ሰምተው ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት [የየራሳቸውን] “ሚኒስትሪና ቤተ ክርስቲያን” ለመክፈት የተሽቀዳደሙትም ሳይጠቀሱ አያልፉም። ... በባዕድ ሀገር የተማሩትን ዕውቀት፣ ያከማቹትንና በልመና ያገኙትን ሀብት እየያዙ በመምጣት ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በረከት የኾኑ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል፣ ባንጻሩ ደግሞ፣ አንዳንዶች በተቃራኒ ኹኔታ ስብራት መኾናቸው አልቀረም።
>
> ያለምክክር፣ በራስ ችሎታ፣ ድፍረት በተቀላቀለበት ኹኔታ፣ ከውጭ ሀገር በወረሷቸው ልምምዶችና ባህል መሠረት ራሳቸውን ገልጠው የተንቀሳቀሱ ወገኖቻችን የፈጸሟቸውና እየፈጸሟቸው ያሉት ስሕተቶች ካከናወኗቸው መልካም ተግባራት የበለጡባቸው ጊዜያትም በርካታ ናቸው።[122]

[122] ጌታቸው በለጠ፣ *ሌሎሄና ሃሌ ሉያ፡- የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ቅጽ ሦስት፣ ከ1966-1992* (ዐዲስ አበባ፡- የኢ.ቃሕቤክ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 1992 ዓ.ም.) 330።

ከሀገር ውጭ በተለይም በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ወገኖች የትምህርትና ሥልጠና ዕድላቸው ሰፊ ከመኾኑ የተነሣ፣ ሀገር ውስጥ ከሚኖሩ ወገኖች ይልቅ በተሻለ ደረጃ የተማሩ መኾናቸው አያጠያይቅም። በአንጻራዊነት ሲታይም የገንዘብ፣ የዕውቀትና የተጽዕኖ ፈጣሪነት ዐቅማቸው የተሻለ ነው። እኒህና ሌሎች መገለጫዎቻቸውን ከግምት ስናስገባ በሀገር ቤቱ ጉዳይ ላይ የእኒህ ወገኖች ተጽዕኖ የማሳረፍ ደረጃ በአዎንታዊም ኾነ በአሉታዊ ገጽታው በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በአገር ውስጥ ባለው ሕዝብ ዘንድ ደግሞ፣ ምክንያቱ መጠናት ያለበት አንድ ደካማ አስተሳሰብ መሠረቱን ጥሏል። ይኸውም፣ ከባሕር ማዶ የመጣን ሁሉ እንደ ምሁር፣ ሀብታም፣ ቅቡዕ፣ ሁሉን ለማድረግ የሚችል፣ ሊጠየቅ የማይችልና ሊወቀስ የማይገባው ልዩ ፍጡር አድርጎ የመቍጠር አባዜ አለ። እነዚህ ነባራዊ ኹኔታዎች ታዲያ በአስተምህሯችን አንጻር ያስከተሉትና ሊያስከትሉት የሚችሉት አንድምታ በአግባቡ የታየ አይመስልም።

እርግጥ ነው፤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በረከት የኾኑ ከባሕር ማዶ የሚኖሩ ቅዱሳን ሞልተዋል። በሕይወታቸው ንጽሕና የማይነቀፉ፣ በትምህርታቸውና ኑሯቸው ምሳሌ የሚኾኑ፣ በገንዘባቸውና ዕውቀታቸው የአገር ቤቱን የወንጌል ሥራ የሚደግፉ ወገኖች አሉ። ይህን መዘንጋት "ያጐረሰን እጅ መንከስ" ይኾናል። በሚኖሩበት የባዕድ ምድር ወንጌልን በመስበክ ብዙዎችን ወደ እውነት መንገድ የመለሱ፣ የተበተኑትን ምእመናንን በመሰብሰብ በጸጋቸው የሚጠቅሙ እንዳሉም የታወቀ ነው። ስለነዚህ ወገኖች እግዚአብሔርን ማመስገንና እነርሱንም መባረክ ተገቢ ነው።

በሌላ በኩል ግን፣ እዚህ ሀገር የሚደመጡ አንዳንድ ትምህርቶችና አሠራሮች ሥረ መሠረታቸው ባሕር ተሻግሮ ይገኛል። ሀገር ቤት ሳይመጡ በርቀት መቈጣጠሪያ ብቻ እዚህ ያለውን አጠቃላይ አደራረግ የሚዘውሩ መኖራቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው። አንዳንዶቹም ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው የራሳቸውን ሚኒስትሪና ቤተ ክርስቲያን መክፈት ችለዋል። ሌሎች ደግሞ እዚህ መጥተው ወይም ካሉበት ኾነው በሚያዘጋጁቻቸው ስብሰባዎች፣ የኅትመት፣





የኦዲዮ ቪዥዋልና የሳተላይት መገናኛ ዘዴዎች የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ እንግዳ ትምህርት ለማስራጨት በቅተዋል፤ እያሰራጩም ይገኛሉ።

የሎጂስቲክ ወጪዎችን መሸፈን እስከ ቻሉ ድረስ ከቤተ እምነቶች፣ ኅብረቶች፣ አጥቢያዎችና ግለ ሰቦች ጋር በመተባበር ትልልቅ ጉባኤዎችን መሰብሰብና ይዘው የመጡትን ትምህርት ያለጥያቄ ማስተላለፍ የቻሉ ነበሩ፤ አሉ። እነርሱ እጃቸው ሙሉ ነውና፣ ያገር ቤቱ አፍና ሆድ ሁሌ ሙሉ አይደለምና፣ "እጅ እጃቸውን" ማየታችን ላያስገርም ይችላል። ስለዚህ ያገኙትንና ያመጡትን ሁሉ በሀገር ቤት ወገናቸው "አፍ" ማጉረሳቸው አልቀረም። ያመጡልን የትምህርት ጉርሻ ሁሉ ግን ንጹሕ ነበር ወይ? ነው ጥያቄው፤ ምን ይዘውልን መጡ?

ተመልሰው ሲመጡ ይዘው የመጡትን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያካሄዱት አቶ ሸዋንግዛው ሉሌ እንዳሉት፡- እነዚህ ወገኖች፣

> የሀገር ቤቱን የእግዚአብሔር ሥራና ቤተ ክርስቲያንን ከማጠናከር ይልቅ *ሪሶርስ* በመሻማት አዳክመዋል የሚል ከፍተኛ ቅሬታ አለ። *ሪሶርስ* ሲባል ዕውቅ አገልጋዮችን በማባበል እንዲሁም በየቤተ ክርስቲያኑ ያሉ የታወቁ ሀብታሞችን በማባበል ማሰልቸት ጀምረዋል የሚል ቅሬታ አለ። ... በየጥቂት ምክንያት ያኮረፉትንና *ዲስፐሊን* የተደረጉትን በማሰባሰብ ከቦታ ቦታ ረጋጮችን አበራክተዋል።[123]

ይህች "ከቦታ ቦታ ረጋጮችን አበራክተዋል" ማለት ምንድነች? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። "መሬት መርገጥ ያልቻሉ" ተካላቢዎች በዙ ማለትም አይደል? በዚህ አካላቢነት ውስጥ ታዲያ የአስተምህሮ መደነጋገር የለም ወይ? ግራ ማጋባትና ማዋከብስ አልታየበትም? ከፍሬውስ ይልቅ እንከርዳዱን አላበዛም

[123] ሸዋንግዛው ሉሌ፣ *ቤተ ክርስቲያንና ዳያስፖራው (በውጭ ሀገር የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን አማኞች)*፣ ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና አገልጋዮች በተዘጋጀ ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ የጥናት ጽሑፍ፣ መስከረም 13 ቀን 1999 ዓ. ም. ዐዲስ አበባ፤ ያልታተመ።

ይኾን? ለምን አያበዛ! የጥናት ውጤቶች “ግራም አጋብተዋል፤ አዋከበዋልም” የሚል ይዘት ነው ያላቸው። አቶ ጌታቸው ይቀጥላሉ፤

> እነዚህ ቊጥራቸው ቀላል ያልኾኑ ወገኖቻችን፣ ከብዙ ነገር ተገልሎና በመከራና በስደት እየተሸማቀቀ ለኖረው ወጣትና በመከራ እየማቀቀ ላለፈው ምዕመን ጥቂትም ርኅራኄ ሳያደርጉና የማገገሚያ ጊዜ ሳይሰጡ፣ እየበረሩ እንደ መጡ፣ ድንገት በዱብ ዕዳ የአውሮጳን [እና የአሜሪካን] መንፈሳዊ ልምምድ፣ ባህልና ዘመን አመጣሽ ያልተለመደ የአምልኮ ሥርዐትን በማስተዋወቅ ግራ እያጋቡ አዋከበውታል።[124]

“ይህ ማዋከብና ግራ ማጋባት” ምን ያህል ሥር እንደ ሰደደ ራሱን የቻለ ጥናት ማካሄድን ይጠይቃል። የኾነ ኾኖ፣ በተጠቀሱትና በሌሎች ተጓዳኝ ኹኔታዎች ከዝርወተ ኢትዮጵያውያኑ መካከል የተወሰኑቱ ወገኖች የሀገር ቤቱን የክርስትና እንቅስቃሴ በአንድም ይኹን በሌላ መንገድ ተጽዕኖ እንዳሳደሩበት መገንዘብ ግን ይቻላል። በተለይ በአስተምህሮ አኳያ ያስከተሉት ውጤት መጤን ይኖርበታል።

በእነዚህ ወገኖች የተዘራው የትምህርት፣ ልምምድና ተመክሮ ዘር መከሩ ዛሬ ጐምርቷልና በመስኩ ላይ ምን ዐይነት ፍሬ እንደ በዛ ከየማሳቸው አዝመራ ላይ የተሰፋፋውን ፍሬ እየተመለከትን መገምገም እንችላለን። ባጠቃላይ ግን፣ የዝርወተ ኢትዮጵያውያኑን ተጽዕኖ ከግምት በማስገባት በአስተምህሮ አንጻር ሊያስከትል የቻለውን ውጤት ለማመልከት ይህን ያህል ከሞከርን ቀሪውን ተያያዥ ጥናት የማድረግ አስፈላጊነትን ለአንባቢዎች መተዉ ተመርጧል።

ቀጥሎ የምንሻገረው እነዚህ ችግሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጥፋቶች ወደ ማየቱ ይኾናል።

[124] ጌታቸው፣ ሌሎቹ፡ 331።





# ክፍል ሦስት

# የአስተምህሮ ዐደራ ክሽፈት የደቀናቸው ድርስ አደጋዎች

# ሦስት

## 3. የአስተምህሮ ዐደራ ከሸፈት የደቀናቸው ድርስ አደጋዎች

ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በመጣመር ለምእመናን መታነጽ አስፈላጊ መኾኑን አይተናል። በወንጌል በማመን በጌታችን በኢየሱስ አለኝታን የተቀበሉ ምእመናን ባጠቃላይ *"የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ"* (ሐዋ. 20፥27) ማግኘት እንደሚኖርባቸውም አውስተናል። ይህን የመወጣት ታላቅ ኀላፊነት፣ በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በቤተ ክርስቲያን ትከሻ ላይ መቀመጡንም ተመልክተናል። ይህ ኀላፊነት ቸል በተባለ ጊዜ ሊከተል የሚችለው ጥፋት ቀላል አይኾንም። በክርስቲያናዊ አስተምህሮ አኳያ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ያልናቸውን ችግሮች የሚያመለክቱን ነገር ቢኖር ነገሮችን ቸላ ብለን የምንቆምበት ጊዜ ላይ አለመኾናችንን ነው።

የጤናማ ትምህርት በአግባቡ አለመሰጠት የሰዎች እምነትና ምግባር በጭንገፋ እንዲመታ ምክንያት ይኾናል። የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን እንደ መኾኑ ታላላቅ ዕድሎችንና አደጋዎችን እንጋፈጣለን። የመጨረሻው ዘመን ወንጌል እስከ "ምድር ዳርቻዎች" ሁሉ የሚሰበክበት ዘመን ነው። ስለዚህም "የመጨረሻውን ዝናብና" መንፈሳዊ ተሐድሶ እንናፍቃለን። በአንድ በኩል የዚህ ታላቅ በረከት ተሳታፊዎች በመኾናችን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

ነገር ግን ዘመኑ ሌላ ገጽታም አለው። ይኸውም ክርስቲያኖችን የሚነካኩ መሰናከሎች የሚታዩበት ዘመንም መኾኑ ነው (ሉቃ. 7፥23፤ ማቴ. 24፥24፤ 2ጴጥ. 2፥1)። መሰናከል ከሚከሠትባቸው መንገዶች አንደኛው የክርስቲያናዊ አስተምህሮን ቸል ማለት፣ ማዛባት፣ መለወጥ ወይም ማጣመም ነው።

አሁን እየታዩ ያሉት፣ በክፍል ሁለት የጠቀስናቸውና ጭራሹኑም ያላነሣናቸው ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በዚሁ ከቀጠሉ በአንዳንዶች ዘንድ የአስተምህሮ ምክንያት መከሠቱ አይቀሬ ይኾናል። በውጤቱም በርካታ አደጋዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ፣ ለሐሰተኛ ትምህርት መቀፍቀፍ በር በመክፈት ሐሳዊ መምህራን በመስኩ ላይ ይበራከቱበታል ብሎ መሥጋት ጥፋት ናፋቂ አያሰኝም።

እንግዲህ፣ ከዚህ ቀጥሎ የምናያቸው ነገሮች ገና ወደ ፊት ይኾኑ ይኾናል በሚል ግምትና ንግር ላይ ተንተርሰው የተሰሉ ትንበያዎች ተደርገው መወሰድ የለባቸውም፤ ምክንያቱም አንዳንዶቹ አደጋዎች ቀድሞውኑ በደጃችን ያደፈጡ ሲኾኑ፣ የተቀሩቱ ደግሞ በየአደባባዮቻችን ላይ በይፋ ተንሰራፍተው የሚገኙ ናቸውና።

እነዚህን አደጋዎች አጒልቶ ለማሳየት በሚል ሐሳብ ብዙ ሐተታ በማካተት አንባቢን ለማድከም አልሞከርም። ሐሳቦቹን በነጥብነት ማስቀመጥ ብቻ በቂ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። ኾኖም፣ በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት "አደጋዎች" የተመረጡና ለውይይት ያግዙ ዘንድ የተለዩቱ ብቻ እንጂ ሁሉም አደጋዎች እነዚሁ ናቸው ማለት አይደለም። የተጠቀሱት ላይ በመጨመር መነጋገር ይቻላል። እውነቱን ለመነጋገር ግን ቀጠሮ አያስፈልገውም፤ ጊዜው አሁን ነው። አልበርት ሽዊዘር እንዳለው፣ "እውነት የራሷ የኾነ የተለየ ጊዜ የላትም፤ የርሷ ሰዓት አሁን ነው-ሁልጊዜም።"[125]

ለማንኛውም አደጋዎቹ የሚከተሉት ሊኾኑ ይችላሉ፤

[125] As quoted in David Littky with Samantha Grabelle, *Education is Everyone's Bussiness* (Alexandria, VA: ASCD, 2004) 195.





## 3.1 ቤት ሊፈርስ? የክርስትና አዕማድ መናጋት

የቤት ጥንካሬው በመሠረቱና በአዕማዱ (ምሰሶዎቹ) ጥንካሬ ይለካል። ጒጆ ምሰሶ ከሌለው የጣራው ክዳን መውደቁ አይቀርም። የክርስትና እምነት ጸንቶ የሚቆመው በመለኮታዊ መገለጥ ላይ በጸናው ትምህርቱ ጤናማነት እንደ ኾነ አያከራክርም። ትምህርቱ ችግር ከገጠመው ግን አሳዛኝ ውጤት ይከተለዋል። ባላው የፈረሰበት ዳስ በቀላሉ እንደሚወድቅ ሁሉ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ያልተገነባ ሕይወትም ይወድቃል። ጌታችን እንዲህ ብሎ አስጠንቅቋል፤ *"... ይህን ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጐርፍም መጣ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም"* (ማቴ. 7፥24-25)።

ክርስትና መሠረታዊ የሚባሉት አዕማድ አስተምህሮዎቹን ካጣቸው ወይም ከተበረዘበት እንደ ሞተ ይቈጠራል።ከጤናማ ትምህርቶቹ ውጭ ክርስትናን በሕይወት ማግኘት አይቻልም፤ ምውት ሃይማኖት ይኾናልና። ዐልፎ ተርፎም እምነቱ ከመሠረቱ ሊለወጥ ይችላል። ይህ ተራ ሟርት አይደለም፤ ታሪክ ያመለከተን ሐቅ እንጂ። የአውሮጳ እና መቅደሶች፣ የሰሜን አፍሪካ ጠፍ ምድረ በዳዎችና የጥንቱ ታናሹ ኤዥያ (የዛሬው ቱርክ) ዋሻዎች የሚነግሩን አንድ እውነት አለ፦ እውነቱ ከሌለ ሕይወቱ የለም! እውነቱ ከጠፋ እምነቱ በጽናት ይቈማልን? ሕይወትና ኀይል አልባ ስመ እምነት ቢተርፍስ ምን ይፈይዳል? ድርጅታዊ ቅርስና ሃይማኖታዊ ስም ብቻ ይዘው የቀሩ ተቋማትን ታሪክ ሲመዘግብ ኖሯል።

ምናልባት ይህ አባባል የተጋነነ መስሎ የሚታየን ወገኖች ያለን እንደ ኾነ፣ ጌታ ኢየሱስ በታናሹ ኤዥያ ለነበሩቱ ሰባቱ ጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናት የላከውን መልእክት ከራእይ መጽሐፍ ልንመለከት እንችላለን (ራእይ 1-3)። እኒያ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ የት ናቸው?

በአጠቃላይ የአስተምህሮ ችግር በአግባቡ ዕልባት ካልተሰጠው መዘዙ የከፋ መኾኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## 3.2 ጭምብል ለባሽ ኑፋቄዎች

ቀደም ባሉት ዓመታት የሐሰት ትምህርቶችን ለይቶ ማውጣት ብቻ ሳይኾን፣ እርምት በመውሰድ ረገድም አብያተ ክርስቲያናት (በአንጻራዊነት) ጠንካሮች እንደ ነበሩ ይነገራል። ከ1990ዎቹ በኋላ እየታየ ያለው ኹኔታ ግን በጣም አሳዛኝ መኾኑን የሚያወሱ አሉ። ከወንጌላውያን ክርስትና ጋር ተቀርነው የቆሙ ትምህርቶችን የሚያሰረጩ ግለ ሰቦችና ቡድኖች በወንጌላውያን መድረኮች ላይ በተጋባዥነት መገኘታቸውን የተመለከትን እንደ ኾነ፣ ወደፊት በሚመጡ ዘመናት የሐሰት ትምህርት ከሩቁ የሚጠቋቈሙበትና የእውነት "ወንጭፍ" የሚሰነዝሩበት ኢላማ መኾኑ ይቀር ይኾን? ያስብላል።

በአስተምህሯቸው ችግር እንዳለባቸው የሚታወቁ ግለ ሰቦችና ቡድኖች ከወንጌላውያን ክርስቲያኖች ጋር በመመሳሰል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው፣ ተመሳሳይ ሥርዐት እያከናወኑ፣ በዝማሬ ዓይነት ልዩነት ሳይኖር፣ ያለምንም ገደብ በፈለጉት ሰዓትና ቦታ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ምእመናን መሰብሰብ የቻሉና የሚችሉ ኾነው መገኘታቸው አነጋጋሪ እየኾነ ነው።

ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በማይወከሏቸው ግለ ሰቦችና ቡድኖች ትምህርት፣ ልምምድና ድርጊት አንድ ላይ ተጨፍልቀው ሲወቀሱ የምንሰማው በዚሁ ጭንብል አጥልቀው በሚመላለሱ ክፍሎች ምክንያት አይደለምን?

ይህን የምንናገረው ከተመክሮ ነው። ከዐመታት በፊት በሐሰተኛ ትምህርትነት ተፈርጀው የነበሩ አቋሞችን የያዙ ግለ ሰቦችና ማኅበራት ያለምንም ይፋዊ የማስተካከያ ርምጃ የቀደመ አስተምህሯቸውን እንደ ያዙ ቅበላ ሲደረግላቸው ይስተዋላል። ይባስ ብሎም እነዚያው ትምህርቶች በአብዛኛው ማህበረ ሰብ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ዘመቻ ሲደረግ ተመልከተናል። ወደፊትም ከዚህ እየከፋ ላለመሄዱ ዋስትናው ምንድነው?





## 3.3 "አሜባ አስተኔ"[126] የቤተ ክርስቲያን ክፈታ

ይህ ነጥብ የአብያተ ክርስቲያናት መከፋፍል፣ መበታተን፣ መለያየትና መዳከም የሚጠቍም ነው። በመታየት ላይ ያለው እንቅስቃሴ እንደሚያመለክተው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተ ክርስቲያን ተከላ ናሙና ቀርቶ "ቤተ ክርስቲያን ከፈታ" የተሰኘ ተግባር "እጅ አፍን አይስተውም" የሚባለውን ያህል ቀልሎ መጥቷል። ቀደም ብለን እንዳመለከትነው ይህ ነገር ወደ ፊት ይባባስ እንደኾን ለማለት ነው እንጂ ሆ! ብለን ከገባንበትማ ቈይተናል። "ዓሣውን ከባሕሩ ይልቅ ከመረቡ ማጥመድ" በቀለላቸው ዐዳዲስ "ባለ ራእዮች" ስንትና ስንት ቤት እንደ ፈረሰ፣ ምን ያህል ትርምስ እንደ ተፈጠረ መናገር "ለቀባሪው ማርዳት" ይኾናልና።

የቤተ ክርስቲያን መከፈቻ (ምርቃት?) ድግስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ማዘጋጀት የቻለ "ባለ ራእይ" ተጋባዦቹን በአደባባይ ጠርቶ ሲያበቃ፣ ድግሱን ሊካፈሉለት ከሄዱት ታዳሚዎቹ መካከል ምን ያህሉን ዘግኖ እንደሚያስቀር የታወቀ ነው። ለዚህም ይመስላል አንድ ተጠያቂ በምጸት "ዛሬ ጊዜ፣ ፓስተር ነኝ ለማለት ድፈር እንጂ ምእመን እንደ ኾነ የጋራ ነው"[127] ያለው። ይህ መራር እውነት ነው። መብዛታችን ባይከፋም፣ አበዛዛችን አስፈሪ ገጽታ እየተላበሰ ነው።

ይህ የመባዛት ስሌት ግር ከማሰኘት ዐልፎ ግራ የሚያጋባ ነው። ዕቅምና ዘዴውን "ያሳለጠ" ጐበዝ በቅነሳ፣ በአፈሳና በትርፈሳ ከቀዳሚዎቹ አጥቢያዎች ላይ ምዕመናንን ዝቆ "ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን" ከፈትሁ ሲል ማወጁ የተለመደ ኾኗል። ሌላ ተረኛ ቈንጣሪ "ባለራእይ" በተራው ከዚህኛው ላይ

---

[126] "የአሜባ ብጤ፣ አሜባን ይመስል" ለማለት ነው። አሜባ የሚባለው ባለ አንድ ሕዋስ ፍጥረት የሚራባበት መንገድ ራሱን ለሁለት በመጕመድ ነው።

[127] ሚካኤል ማሞ፣ ቃለ ምልልስ፣ ዐዲስ አበባ፣ የካቲት 2004 ዓ. ም. በጸሐፊው እጅ የሚገኝ ማስታወሻ።

ቀምጥሎ በመዝረፍ ሌላ "ኢንተርናሽናል ቤተ ክርስቲያን" ይከፍታል። በዘመናችን ለቤተ ክርስቲያን ከፊታ አስፈላጊው ነገር "በቂ ኰርፊያና ድፍረት" እየኾነ የመጣ ይመስላል።

ስለዚህም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በማኅበራትና በጐ አድራጐት ኤጀንሲ በኩል ፈቃድ አውጥተው እንደ ሃይማኖት የሚንቀሳቀሱ ቤተ እምነቶች ቍጥር ለሰሚው ግራ ነው። "ፕሮቴስታንታዊ" ትውፊቱን ተተግነው በሃይማኖት ስም የተመዘገቡት ቤተ እምነቶችና አጋር ማኅበራት ከነግሳንግሳቸው ከ 1500 በላይ መድረሳቸውን ሰምታችሁ ይኾናል። ዐምስት ሰው ኾኖ ሃይማኖት ማቋቋምና የምዝገባ ፈቃድ ማግኘት የሚፈቅደውን የሀገሪቱን የእምነት ነጻነት መመሪያ መሠረት በማድረግ፣ ባልና ሚስት ከልጆቻቸው ጋር ኾነው በመሥራችነት የተሰየሙበት ገጠመኝ እንደ ተደረሰበት በጕዳዩ ላይ ጥናት ባደረጉ ምሁር በአደባባይ አልተነገረንምን?[128]

በዐጭሩ ለማለት የተፈለገው ይህ ነው። ቤተ ክርስቲያን የመከፈት አባዜ የተጠናወታቸው ደፋሮች በዚሁ ከቀጠሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ማንነታዊ ትርጕም ደብዝዞ ከመጥፋቱም በላይ፣ የተበጣጠቁ መኅበራትና ቡድኖች በእምነት ስም ጓዳ ጐድጓዳውን ያጥለቀልቁታል። በፍጻሜውም እርስ በርስ የሚፎካከሩ፣ የሚጣሉና የሚወጋገዙ ቡድኖች ይፈጠራሉ። እስከ ዛሬ እንደታየው አንዱ ቡድን ከሌላው ዘንድ አባላትን ለማስኰብለል ሲባል "ዐዲስ" የሚላቸውን አሠራሮችና ትምህርቶች ማናፈሱ ስለማይቀር መሠረታዊ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ይወይባሉ፣ ይለወጣሉ፣ ወይም ይሻራሉ።

---

[128] ዶክተር ሳምሶን እስጢፋኖስ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጋር በመኾን በ2000 ዓ.ም. ባዘጋጁት ሲምፖዚየም ላይ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ። በተጨማሪ፣ ተመራማሪው እስከዚያን ወቅት ድረስ ብቻ የነበሩትን ወጌላውያን ክርስትና ማኅበራትን የሚያሳይ ማጣቀሚያ አውጥተው ነበር። ብዛታቸው ስድስት መቶ ያህል ነበር። ሳምሶን እስጢፋኖስ፣ *ብንጮኽ ይወድቃል፦ በሕዝቡ ዙሪያ እንጂ በሕዝቡ መኻል ቅጥር አይሠራም* (ዐዲስ አበባ፦ አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2000 ዓ.ም።) በርግጥ ይህ ዐምስት ሰዎችን ብቻ ለመሥራች አባልነት ይጠይቅ የነበረው መመሪያ ከ2006 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ኀምሳ አባላት ከፍ እንዲል ተደርጓል።





በጊዜው በየማኅበሩ የሚታዩት ውጥረቶች ይህን አመላካች ናቸው። ጥል፣ ውዝግብ፣ መካሰስ፣ ማፍረስና መዝጋት በየቦታው የሚታይ ብቻ ሳይኾን በየመገናኛ ብዙኀኑ ሳይቀር መፈ'ትፈት ከጀመረ ዓመታት ተቈጥረዋል። በፍርድ ቤት ከመካሰስ ዐልፎ ተርፎ የመንግሥትን ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት የጠየቁ ውዝግቦች በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጥላ ሥር በታቀፉ ቤተ እምነቶች መካከል መከሠታቸውን በኀዘን እናስታውሳለን።

የማኅበራትና በጎ አድራጎት ኤጀንሲ እንደ ዐዲስ ከተቋቋመ በኋላ በነበሩት ሁለት ዓመታት የነበረውን ተግባር አስመልክቶ በ2003 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ ላይ እንዳመለከተው በኹለት ዓመት ውስጥ ከቀረቡለት ጕዳዮች መካከል፣ እስልምናንና የኦርቶዶክስ ቤተ እምነቶችን የሚመለከቱ በጥቅሉ ከሰባት የማይበልጡ ሲኾን፣ ከወንጌላውያኑ ጋር የተገናኙት ግን ከ 200 በላይ እንደ ነበሩ ጠቅሷል።[129]

ዛሬ የኢትዮጵያ ክርስትና እንዲያብብ ከተፈለገ ከቍጥሩ ብዛት ጐን ለጐን ለጥራቱም ከፍ ያለ ቦታ መስጠት ሲገባው፣ ሩጫው ለድርጅታዊ ቡድኖች መበራከት የተለጠጠ ፍላጎት የተሸነፈ መስሏል። ወንጌል እንዲሰበክና ክርስትና እንዲስፋፋ ፍላጎት ካለን ሀይ ባይ ያልተገኘለት ቡድናዊ "የቤተ ክርስቲያን ከፈታው" መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል።

> የቍጥሩ ዕድገት ከብስለት ጋር መጣጣም አለበት። የበዛነውን ያህል መብሰል አለብን፤ የተመዘዝነውን ያህል መጥለቅ አለብን። አሊያ፣ አሁን እንኳ፣ በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚታየው ... የቍጥሩ ዕድገት እያሽቆለቈለ [መሄዱ አይቀሬ ነው]። አብያተ ክርስቲያናት ለመንፈሳዊ ብስለት መጨነቅና መታገል ካልጀመሩ ወደፊት ክርስቲያናዊ ዕድገት የሚታሰብ አይኾንም።[130]

---

[129] *ዐዲስ አድማስ*፣ 2003 ዓ.ም።

[130] ምኒልክ አስፋው፣ "ወንጌላውያን አማኞችና መጪው ሺህ ዓመት (ሚሌኒየም)፣" *ማቴቴስ*፣ ልዩ ዕትም፣ መስከረም 2000 ዓ.ም.፣ ገጽ 25።

## 3.4 "የወጣት አልወጣት"[131] ውጥረት

ለእግዚአብሔር ክብር የቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ ዕድገት መናፈቃችን እርግጥ ነው። ዛሬ ከምናየውና ከምንሰማው የተሻለ ነገር እውን እንዲኾንም እንጸልያለን፤ ይህም እውነት ነው። እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራን የፈቃዱን ሐሳብ አገልግለን እንድናጠናቅቅ አይደለምን? ለክብሩ ምስጋናና ለቅዱሳን መታነጽ የሚኾነው ሁሉ የልባችን ደስታና ናፍቆት ነው።

በክርስቶስ በማደግ ዐደራችንን እንድንፈጽም እግዚአብሔር ይጠብቅብናል (ቆላ. 4፥17፤ 2ጢሞ. 4፥5)። እኛ የተቀበልነውን የእምነት ዐደራ ደግሞ ለተተኪዎቻችን እንድናስተላልፍ ቅዱስ ቃሉ ግድ ይለናል (2ጢሞ. 2፥2)። የተሰጠንን ኀላፊነት ተወጥተን ለሚተኩን አገልጋዮች ቦታውን ማስረከብ አለብን። ቀኑ በደረሰ ጊዜ ዐደራችንን የምናስተላልፍላቸው ተረካቢዎችን ደግሞ ማዘጋጀት ያለብን "ቀን ሳለ" ዛሬ ነው። ስለ ኾነም በቂ ማስረጃን በመስጠት የክርስትናን እምነትና የክርስቲያንን የኑሮ ጠባይ ግልጽ አድርጎ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ለመጪው ትውልድ የምናወርሰው ምንድነው? ጭቅጭቅ፣ መካሰስ፣ የሥሥት "ወንጌል"፣ የተመሳቀለ ትምህርት፣ የፈንጠዝያ እምነት ወይስ እውነትና ተስፋ?

ይህ ተተኪዎችን የማዘጋጀትና ኀላፊነትን የማስተላለፍ ጕዳይ በዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚታይ ድካም መኾኑን ማስተዋል ቀላል ነው። ይህ ሲባል የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ ነገሮችን ለማሳነስ አይደለም። በርካታ ጥረቶች በመደረግ ላይ መኾናቸው እውነት ነው። በቤተ ክርስቲያንም ኾነ በተጓዳኝ ተቋማት በኩል የተከናወኑና እግዚአብሔርን እያመሰገንን ተስፋ የምንጥልባቸው ተግባራት ሞልተዋል። ኾኖም ጕዳዩ የተነሣው የተፈለገውን ያህል እየሠራንበት አይደለም ለማለት ታስቦ ነው። የተተኪ ጕዳይ አንገብጋቢ ርእስ ጕዳይ ነው።

[131] "ወጣት አልወጣት" የተሰኘችዋን የዕድሜ ተኮር ማኅበራዊ ቡድን መለያ የተዋስኩት ከጋሽ ንጉሤ ነው። *መስተአየት፣* 39።





በጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ እምነት፣ ሕይወትና አሠራር የሌለን ከኾነ፣ ተተኪ አይኖረንም። ያላዘጋጀነውን ለመተካት ማሰብ ካልዘራንበት ለማጨድ እንደ መሞከር ይቈጠራል። ይህ ዝንጋኤያችን እልባት ካልተበጀለት ለተለያዩ አተያዮችና እንደ አሸን ለፈሉት እንግዳ ትምህርቶች የተጋለጠ ወጣት በሚያመጣቸው ትምህርቶች ምክንያት ከቀዳሚው ትውልድ ጋር ወደ ፍጥጫ መድረሱ አይቀርም ብሎ መገመት ይቻላል።[132]

በሚገባ ኰትኵተን ያላሳደግነውን ትውልድ ሲያጠፋ ወይም ሲሳሳት ለማረምስ እንዴት እንችላለን? ስለዚህ፣ በጤናማው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በአግባቡ ያልተመሠረተ ምልልሳችን በዚሁ ከቀጠለ፣ በተደጋጋሚ እንደ ታየው፣ የትውልድ ክፍተት የሚፈጥረው ፍጥጫና ውጥረት ሲከፋም ዐመፃ ይከሠታል የሚል ሥጋት አለ።

አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ከግማሽ ምእት ዓመት በፊት ስለ ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መታደስ ሲጽፉ ያመለከቱት ነጥብ ይህን ኀላፊነት አጕልቶ ያሳያል፤ ሐሳባቸው ጠሊቅ ትምህርት ለመገብየት የምንችልበት ነው፤ እንዲህ ይላሉ፤ "ተከታዩ ትውልድ መውደቁ ወይም መነሣቱ አሁን ባሉት መምህራን እጅ በመኾኑ የኀላፊነታቸው ሸክም እጅግ ከባድ ነው።"[133] ይህ ተራ ሥጋት አይደለም። ጤናማ የትውልዶች ርክክብ የማይካሄድ ከኾነ የውርስ አሻራ የሌለን ላለመኾናችን ዋስትና የለንም። ቀጣዩ ነጥብም ይኸንን አጕልቶ ያሳየናል።

[132] ይህን ሐሳብ ለማጕልበት አንድ ምሳሌ ልጠቀስ። በ 1990ዎቹ መግቢያ ላይ በዐጭር ጊዜ እንደ ሰደድ እሳት በመዛመት ላይ የነበረ ሐዋርያዊና ትንቢታዊ ዘመቻ ("ኢምፓክት 2000" ን ያስታውሷል) ምን ያህል ወጣቶችን እንዳጋጋለና እንዳነሣሣ፣ ከየመሪዎቻቸው ጋርም ምን ያህል ውጥረት ውስጥ ዶሏቸው እንደ ነበር ይታወሳል። በወቅቱ የጕዳዩን አሳሳቢነት የተገነዘበው ኢቫሱ ባዘጋጀውና የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ራሱ በተካፈለበት አንድ ዐውደ ተዋሥኦ ላይ እንደ ታዘበው፣ ወጣቶቹ ከየቤተ እምነቱ በተጋበዙ መሪዎቻቸው ፊት ያሳዩት የነበረው "ጃሎ መገን" አስደንጋጭ ነበር።

[133] *መሠረት ስብሐት ለአብ* (አለቃ)፣ *ሰምዓ ጽድቅ ብሔራዊ* (ዐዲስ አበባ፦ አርቲስቲክ፣ 1951 ዓ.ም.) 10።

## 3.5 ቅርስና ውርስ አልባ እምነት

ትውልድ እንደ ጅረት ነው። አንዱ ወደ ሌላው ይፈስሳል። ምንጩ ንጹህ ከኾነ ወንዙም እንደዚያው የመኾኑ ዕድል ሰፊ ነው። ምንጩን በድፍርስ በክሎ ከታች ንጹሕ ለመጠጣት መሞከር ተላላነት ነው። ትውልድ እንደ ሰንሰለት ነው። እርስ በርሱ መቈላለፉ ብቻ ሳይኾን አንዱ የጀመረው በጎም ኾነ ክፉ ነገር ወደ ተከታዩ ይደርሳል። አንድ ትውልድ ብቻውን ሁሉንም ሊያጠናቅቅ አይችልም ይኾናል። ስለኾነም፤ "አባት ያቈየውን ልጅ እንዳያፈርሰው" የሰንሰለቱን ዘለበቶች ሁሉ ማጥበቅ ያሻናል፤ የአንድ ሰንሰለት ጥንካሬው ከቀለበቶቹ የደካማዋን ያህል ነውና። ደግሞም የዛሬው ትውልድ ብቻውን የጀመረው ተደርጎ መታሰብ የለበትም።

በርግጥ፤ አንዳንዴ፤ ሁሉን ነገር የዛሬው ትውልድ የጀመረው የምናስመስልበት ጊዜ አለ። ቀድሞ የነበረውን በጅምላ የሚያጣጥል አልጠፋምና። ከባህላችን የቀዳነው ይኾን? ብርሃኑ ድንቄ *አልቦ ዘመድ* ውስጥ የሳሉት ፀሐዩ የተባለ ባለ ታሪክ አለ። ባለ ታሪኩ የእሱ ዘመን ትውልድ የፈጸመውን "ትናንትን" የማጣጣል በሽታ እየነቀፈ ከፉኛ ሲጸጸት እንሰማዋለን፤ "[ትውልዱ] ባህሉን፣ ወጉን፣ ሥርዐቱን፣ ሥነ ጽሑፉንና ታሪኩን ጭምር ነቅፎ ከባዶ ቤት የሸፈተ ስለ ነበረ፣" ከትውልዱ ጋር ዐብሮ ሲያጨበጭብ መኖሩን በቍጭት ይተርካል። "ለካስ አባቶቻችንን አድኃሪያን እያልን የምንሰድበው የኛን ድንቊርና ለመሸፈን [ኖሯል]"[134] እያለ ይተከዛል፤ በርግጥ መተከዝ ሲያንሰው ነው።

ይህ ትልቅ ትምህርት የሚኾነን ነው። መደበኛ ትምህርት ቤት ካልሄዱት ቤተ ሰቦቻችን ስንቱን ክቡር ነገር ሸምተናል እኮ! በእምነትም ከቀዳሚዎቻችን ብዙ ተምረናል። ያስተላለፉልን የወንጌል ትምህርት አለ። የተረከብነው ጤናማውን ትምህርት ከኾነ፣ ሳናጐሸው ለማስተላለፍ በእምነት ዐርበኞች መስመር ፊት በምስክሮች ተከብበን ቆመናል (2ጢ.ሞ. 2፥2፤ 4፥7-8፤ ዕብ. 12፥1-3)።

---

[134] ብርሃኑ ድንቄ፣ *አልቦ ዘመድ* (የታተመበት ቦታና ዘመን እንዲሁም አሳታሚ አልተገለጸም) 7።





በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንደምናነብበው የእምነት መወራረስና እግዚአብሔርን ማወቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ቅዱሳን ሲጸልዩ ነበር። ኀላፊነትን የሚረከብ ተተኪ እግዚአብሔር እንዲያስነሣላቸውም ሲናፍቁ ማየት ይቻላል። የተወሰኑ ምሳሌዎችን መመልከት እንሞክር። አብርሃም የወራሽ ያለህ ጥያቄ ነበረው (ዘፍ. 15፥1-4)። እግዚአብሔርም ሰማው። ሙሴ በመሪባ ውሃ "እግዚአብሔርን ስላልቀደሰ"፣ ጌታ አዝኖበት ነበርና፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደማይገባ ከወሰነበት በኋላ በታላቅ ናፍቆት ተተኪ ለማግኘት ጸለየ።

> *ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ ብሎ ተናገረው። የእግዚአብሔር ማኅበር እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን፥ በፊታቸው የሚወጣውን በፊታቸውም የሚገባውን የሚያስወጣቸውንም የሚያስገባቸውንም ሰው የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአብሔር በማኅበሩ ላይ ይሾመው* (ዘኍ. 27፥15-16)።

በትውልዶች መካከል የእምነት መወራረስ ከሌለ ክፍተት ይፈጠራል። እንዲሁም፣ ያለፈውን የሚረሳ ዝንጉ ዜጋ ሊፈላ ይችላል። *"በግብጽም ዮሴፍን ያላወቀ ዐዲስ ንጉሥ ተነሣ"* (ዘጸ. 1፥8) እንደ ተባለ። በእስራኤል ታሪክ አሳዛኙ ታሪክ በትውልድ መካከል ሲከሠት ነው የኖረው። ለምሳሌ ያህል ብቻ ከመሣፍንት መጽሐፍ የሚከተለውን እንመልከት። *"...ትውልድ ሁሉ ደግሞ ወደ አባቶቻቸው ተከማቹ ከእነዚያም በኋላ እግዚአብሔርን ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ ያላወቀ ሌላ ትውልድ ተነሣ"* (መሳ. 2፥6-10)።

ይህን መሳይ ክሥተት በዓለማችን ዐዲስ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ተደጋግሞ ነው የታየው። ቀደም ብለን የጠቀስነውን እዚህ እንድገመው። የሰሜን አፍሪካ ምድረ ቡዳዎች የአውሮጳ እና መቅደሶች የሚጮኹት አንድ ነገር አላቸው። ታሪክ ብቻውን በቂ አይደለም!

የዘመናችን ወንጌላውያን ታሪክና ነገረ መለኮት ረጅም፣ ሰፊና ደማቅ ሥረ መሠረት ያለው እንደ ኾነ የታወቀ መኾን አለበት። አንዳንዶች ወንጌላዊውን ክርስትና ለለዘብተኛ ነገረ መለኮት የተሰጠ ዐጸፋዊ ምላሽ አድርገው

ቢቈጥሩትም እንኳ፣ (ግጭቱ ለወንጌላዊው ክርስትና መዳበር የራሱን አስተዋጽዖ ማድረጉ ባይካድም) ዐበይት ይዘቶቹና ቁም ነገሮቹ ከታሪካዊና ከርቱዕ ክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት የተወረሱ ናቸው። የወንጌላዊው ክርስትና አስተምህሮ፣ በዋናነት፣ በታላቁና ርቱዕ በኾነው የክርስቲያን ነገረ መለኮት ትውፊት መደብ ውስጥ የሚቆም ነው። ስለዚህ፣ ወንጌላዊው ነገረ መለኮት፣ በመጀመሪያው ምእት ዓመት የነበሩት ጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናት እምነታቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ጋር ለማቀናጀት፣ ከትርጒሙም ጋር ለመዋሐድና ከሐሰትም ለመጠበቅ ባደረጉት ጥረት ወደ አዘጋጇቸው ጥንታውያን የእምነት መግለጫዎች (*ክሪድ*) ድረስ ተዘርግቶ ይሄዳል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በ16ኛው ምእት ዓመት ከተነሣው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ጋር የተለየ ቊርኝት ያለው ወንጌላዊው ክርስትና፣ የአስተምህሮ ርቱዕነቱን አያስተባብልም፤ አይደራደርበትምም። ይህም ብቻ አይደለም፤ በቀጣይነት ለመጡት የወንጌላዊ መነቃቃቶችም ባለዕዳ ነው።[135] እንግዲያስ ወንጌላዊው ክርስትና ያለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረዶች ውስጥ የዘለቀውን እውነት እየጠበቀ የሚሄድ ነው። ይህ ነው ክቡር ውርሱ፤ ይህ ነው ታላቅ ቅርሱ።

ዛሬስ? ያለፈውን በመናድ ላይ ያተኰረ፣ ዐዲስ አመጣዋለሁ በሚሰኝ “አሠራር”፣ ወይም “መገለጥ” ወይም “አካሄድ” ላይ ተመሥርቶ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችና ልምምዶች መከተል፣ ማስፋፋትና ማዛመት ላይ የተጠመዱ አደራረጎች በአግባቡ ምላሽ ካላገኙ አደጋው አስፈሪ አይኾንምን? የሚታዩት ኹኔታዎች መፍትሔ ካልተሰጣቸው በቀር፣ ወንጌላዊው ክርስትና በቅዱሳት መጻሕፍት በተመሰከረለት እውነቱ፣ ደርዝ ባለው ታሪክ ላይ በተላለፈ ሐቀኛ ትውፊቶቹ እንዲሁም በተጨባጭና ኩልል ባለ ጤናማነቱ የመቀጠል ዐቅሙ ሊዳከም ይችላል በማለት የሚሠጉ በርካቶች ናቸው።

[135] በዚህ አንቀጽ የተጻፈውን በተዛማጅ ትርጒም ጠቅለል በማድረግ የወሰድኩት ቀጥሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ ነው። I. S. Rennie, “Evangelical Theology,” in *New Dictionary of Theology* (Downers Grove: IVP, 1988) 240-241.





ክርስትናን እኛ አልጀመርነውም። ቀዳሚዎቻችን ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል በሕይወታቸው ጭምር ውድ ዋጋ ከፍለውለታል። በመጥራቱና በጸጋ ስጦታው የማይጸጸተው አምላክ እኛንም በተራችን የዚህ እውነት ባለዐደራ እንድንኾን መረጠን። የኛም የምድር ላይ ዘመን ሲያበቃ ወይም ጒልበታችን ሲደክም ለባለተራዎች መልቀቃችን አይቀርም። ይህን ጠንቅቀን እናውቃለን። ይህን ማወቃችን ብቻ በቂ አይደለም።

> እንደማወቃችን መጠን ግን ቅብዓ ርኅራኄ ጨምረንበት በተከታዩ ጊዜ የሚሰማራውን ወገናችንን በወንጌል እውነት ብናጽናናውና ተከታትሎ ከሚደርስበትም ፈተና ብንታደገው ጽድቅን የሚያውቅ አስተዋይ ትውልድ ስለሚኾንልን የእኛ አበባነት ሲረግፍ በሚተካው ንጹሕ ፍሬያችን የበለጠ ደስታ ሊኖር ይችላል (ምሳ. 14፥34)።[136]

አዎ ውርስ የሌለው እምነት እንዳይመጣ መጠንቀቅ ይጠይቃል። ያለንበትን ኹኔታ ስናጤን አስፈሪ ነው። ይህን መሳይ ችግር እንዳንጋፈጥ በጸሎት ከመትጋት በተጓዳኝ የአስተምህሮ ጤናማነትን መፈተሽ ያስፈልጋል።

ወንጌላዊው ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥ ገና በአንድ ምእት ዓመት ዕድሜው እንዲህ ካነከሰ፣ (የጌታ ምጽአት ገና ቢኾን) መጪዎቹን ዘመናት እንዴት ሊኾን ነው? በርካቶች በጽሙና የሚያነሡት አሳሳቢ ጥያቄ ነው።

[136] *መሠረት (አለቃ)፣ ሰምና ጽድቅ፣* 10።

## 3.6 ለጥቃት የመጋለጥ ስንጥቃት

በትምህርት ነፋስ በመፍገምገምና ለጥቃቅን ልዩነቶች ሁሉ የከረረ ዐቋም በመውሰድ እየተበታተነ ያለው ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ቆም ብሎ ሊያስበው የሚገባ ሌላ ጉዳይ ከፊቱ ተደቅኗል። ይህ ኅብረትን በማላላት ላይ የተጠመደና ለወሳኝ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ተገቢውን ትኵረት የማይሰጥ አሠራር በተያዘው መልክ የሚቀጥል ከኾነ አደጋው ቀላል አይደለም። ይኸውም ለውጪያዊ ኀይላት ጥቃት መጋለጥ ነው። ጥቃቱም ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል።

በአንድ በኩል፣ አሁን ያለው ግርግር አንዱን ከሌላው ለመለየት በማያስችል መጥበርበር የሰዎችን ዐይን ስለ ከደነ፣ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በአግባቡ በማይወክሏቸው ግለ ሰቦችና ቡድኖች አስተምህሮና ድርጊት ምክንያት በጋራ ተጨፍልቀው የሚነቀፉበትና በውጪያዊ “ስሕተት አነፍናፊዎች” ዘንድ የሚሰደቡበትን ዕድል ያሰፋዋል፤ ይህም ለደካሞች መሰናከል በር ይከፍታል። ይህ ደግሞ ገና ይኾናል የሚባል ግምት አይደለም። በተደጋጋሚ ሲኾን ያየነውና ሲነገር የሰማነው አይደለምን? ለምሳሌ ያህል አዳራሽ መከራየት፣ የማስታወቂያ ስሌዳ መለጠፍና፣ ከውጭ ሀገር “ሰባኪ፣ አስተማሪና ነቢይ” መጋበዝ የቻለ ግለ ሰብ ወይም ቡድን ሁሉ በሚሠራው ያልተገባ ነገር ምክንያት ክርስቲያኑ ማኅረበረ ሰብ ዐንገቱን እስከሚደፋ ድረስ ዐብሮ አልተዘለፈም? ስሙ በአንድነት አልተሰደበም? ይህ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የታየና የተሰማ ነገር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በግለ ሰብ ዝና አምልኮ የመጠመድ መዘዝ ባስከተለው የአስተምህሮ ደርዝ ማጣት ምክንያት የሚታየው የአብያተ ክርስቲያናት መከፋፈልና መበታተን ለቀጥተኛ ጥቃት ሊዳርጋቸውም ይችላል። ይኸውም፣ በእግዚአብሔር ቃልና በክርስቶስ አማካኝነት ያገኙትን ኅብረት በማላላት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ለጋራ ጥቅሞቻቸውና መብቶቻቸው መከበር የሚያደርጉትን ጥረት ያዳክመዋል፤ ሲብስም መና ያስቀረዋል። በውጤቱም ውጪያዊ ጥቃቱ በቀላሉ ሊበረታባቸው ይችላል።





## 3.7 የደቀ መዝሙርነት መዳከምና የምግባር ብልሽት

ይህ ንዑስ ርእስ የዘመናችንን ቤተ ክርስቲያን ከደቀ መዝሙርነትንና ሥነ ምግባር አኳያ ለማየት ያለመ አይደለም፤ እርሱ ራሱን ችሎ ሊቀርብ የሚችል የጥናት ርእስ ጉዳይ ነው። ነገር ግን እዚህ ለመጥቀስ የምሞክረው የአስተምህሮ መዛነፍ ምግባራዊ ብልሽት ማሰስከተሉን ነው፤ የክርስቲያናዊ አስተምህሮን አስፈላጊነት አንሥቶ ከደቀ መዝሙርነትንና ሥነ ምግባር ጋር ያለውን ቊርኝት አለመመልከት ቸልተኛነት ይኾናል።

በተለያዩ ጊዜያት እንደ ተሰማው የወንጌላውያን ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ምግባር ጽናት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ ነው ይባላል። ግብረ ገባዊ መንሸራተት፣ ታማኝነትን ማጉደል፣ የጋብቻ ክብረት ማጣት፣ የትዳር መናጋት፣ የፍች መበራከት፣ ማኅበራዊ ቀውስ፣ መካሰስ፣ መጣላትና ለዕርቅ ፈቃደኝነትን መንፈግ እንዲሁም ሌሎች ጉድለቶች በተለያዩ ወገኖችና አብያተ ክርስቲያናት መካከል በመታየት ላይ ናቸው። ይህ ከደቀ መዝሙራዊ ሕይወት ተንሸራትቶ ከመውደቅ በቀር ምን ስያሜ ይኖረዋል።

ክርስቲያኖች ፍትሕ ፍለጋ በዓለማውያን ሸንጎ የቆሙት፣ ሊያስታርቃቸው የሚችል ሽማግሌ በመካከላቸው የለም ወይ ተብለው የተዘለፉት፣ ይቅርታን እንደ ውርደት የቈጠሩ፣ ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሠራር ፈንግጠው አንዳቸው የሌላውን አባላት ለመሻማት የዘመቱት፣ ምን ኾነው ነው? ይህ የሚያመላክተን የደቀ መዝሙራዊ ሕይወት መስተጓጎልን አይደለምን?

ደቀ መዝሙርነት የሕይወት ዘመን ጥሪ እንጂ የሦስት ወይም የስድስት ወራት የትምህርትና ሥልጠና መርሐ ግብር አይደለም። የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መኾን ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ ትምህርትና የኑሮ ጠባይ መኖርን መሠረት ያደረገ ነው (ማቴ. 28፥ 18-20)። በተለያየ መልክ እየታዩ ያሉት የሥነ ምግባር መጓደሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሯችን ምን ያህል ጠንካራ እንደ ኾነ እንድንመረምር የሚያደርግ ነው፤ ክርስቲያናዊ የምግባር መርሖዎች ምንጫቸው መለኮታዊ ስለ ኾነ፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደርጋሉና።

በቤተ ክርስቲያን ምእመናንን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች በስፋትና በጥልቀት ስለማይሠሩ ሰዎች ደቀ መዛሙርት ሳይኾን የሰንበት ተመላላሾች ብቻ እየኾኑ ይታያል። ለቃለ እግዚአብሔር ትምህርት የሚሰጠው ሥፍራ ማነስ ብቻ ሳይኾን ጊዜያዊ ፈንጠዝያና ግር ግር ለተሞላባቸው ስብሰባዎች የተጋነነ ቦታ መስጠት ይታያል። የቤተ ክርስቲያን ጉልበት፣ ገንዘብና ጊዜ የሚባክነው ቀዳሚና ዋነኛ ባልኾኑ ነገሮች ላይ እየኾነ ነው። ስለ ኾነም ውጤቱ ደቀ መዝሙርነት የመይታይበት የሃይማኖት ማኅበርተኛ መብዛት ይኾናል። ይህን መሳይ ችግር መኖሩን ያጠኑት አቶ ሽፈራው ወልደ ሚካኤል በአንድ ጽሑፋቸው እንዲህ ይላሉ፤

> የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ጉልህ ችግሯ ደቀ መዛሙርትን ከማፍራት አንጻር ነው። አብላጫው ምዕመን መንፈሳዊ ነገርን መረዳቱ በጣም ልል ነው። ተገቢና ተከታታይ ትምህርቶች ተሰጥተውት በቃሉ ላይ ሥር የሰደደ ሕይወት እንዲኖረው በሚገባ አላሰብንም፤ ተገቢውንም ትኩረት አልሰጠንም። ስለዚህም ያለፈ ያገደመ ሐሳብ ሕዝቡን ሲንጠው ይታያል። ይህ ተግዳሮት በሚገባ ዓላማችን ውስጥ ገብቶ የማስወገጃ ርምጃ መቀየስ ይኖርበታል።[137]

ልክ ብለዋል። ዛሬ የኢትዮጵያ ክርስትና እንዲጐመራ ከተፈለገ ደንበኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በስፋት መስጠት አለበት፤ በተያያዝነው መንገድ መቀጠልን ብንመርጥ ግን ጥፋት እንደሚገጥመን መገንዘብ አለብን።

የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በተቃና መንገድ ካልተሰጠና በሕይወት ካልተተገበረ እውነተኛ ደቀ መዝሙርነት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። ይህም ብቻ ሳይኾን፣ ምግባራዊ ክስረት በመፍጠር የእግዚአብሔር ስምና የእውነት መንገድ እንዲነቀፍ ያደርጋል። ይህም ደግሞ ማኅበራዊ ተአማኒነትን በጥያቄ ሥር ይጥለዋል።

[137] ሺፈራው ወልደ ሚካኤል፣ *ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተከፈቱ በሮች፡-* በተገኙ የወንጌል አገልግሎት ዕድሎችና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ የሚወይ ዐውደ ጥናት፤ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የተዘጋጀ፤ ዐዲስ አበባ፣ ዘመን አልተጠቀሰም፣ ገጽ 16።





## 3.8 *የስሙና ትምህርቱ መነቀፍ*

በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሐሳብ የመመረጣችንና የመጠራታችን ኹነኛ ግብና እኛም በክርስቶስ ተስፋ የማድረጋችን ዓላማው ለእግዚአብሔርና ለጸጋው ክብር ምስጋና እንድንኾንለት ነው (ኤፌ. 1፥12-14)። ጥቃቅኑ ድርጊታችን ጭምር ለእርሱ ክብር (1ቆሮ. 10፥31) ሊያመጣ ካልቻለ ከጥሪያችን ተልዕኮ ጐድለናል ማለት ነው። የእውነት ብርሃን የበራላቸው ምዕመናን በዓለም ቢኖሩም ከዓለም አይደሉምና ባሉበት ማኅበረ ሰብ ውስጥ በትምህርታቸው ጤናማነትና በኑሯቸው ቀጥተኛነት ምሳሌ መኾን አለባቸው። ስለዚህም፣ በእግዚአብሔር ስም የተጠሩ ቅዱሳን በኑሯቸውም ኾነ በትምህርታቸው እርሱን እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ ይገባቸዋል።

ጤናማ ኑሮአችን እንደሚያስመሰግነው፣ ጠማማ አካሄዳችን ስሙን ሊያሰድብ ይችላል። ስለኾነም የትምህርታችን መሳከር የምግባር መዛነፍ በማስከተል እግዚአብሔርን በአሕዛብ መካከል ያስነቅፈዋል። ሕዝበ እስራኤል የወደቀበት አንዱ ምክንያት ይህ አልነበረምን? ለአሕዛብ ብርሃን ለመኾን የተጠሩቱ እስራኤላውያን በትምህርታቸውና ኑሮአቸው ስለ ወደቁ፣ የእግዚአብሔር ስም ተነቀፈ፤ እግዚአብሔርም በኀዘን እንዲህ አለ፤ በእነርሱ ሰበብ በአሕዛብ መካከል *“ስሜም ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ይሰደባል”* (ኢሳ. 52፥5፤ ሮሜ 2፥24)።

ጴጥሮስ እንዳስጠነቀቀው፣ የዐመፃን መንገድ ከመከተልና ሐሰተኛ መምህራንን በመስማት ምክንያት ሊከሠት ስለሚችለው ድቀት ሲናገር፣ *“ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል፤ በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል”* (2ጴጥ. 2፥2) ይላል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ስምና እውነተኛው መንገድ ይነቀፋል ማለት ነው። የእኛም ትምህርትና ኑሮ እንደ እግዚአብሔር ቃል ጤናማ ካልኾነ፣ ይህን መሰል አሳዛኝ ውጤት ላለማስከተሉ ምን ማስተማመኛ ይኖራል?

ሐዋርያት ባስተላለፏቸው መልእክቶች ምዕመናንን አጥብቀው የወተወቱበት አንደኛው ምክንያት ይህ ነበር፡- በእነርሱ ኑሮና ምልልስ የጌታ ስምና ትምህርት

እንዳይነቀፍ። *“የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ”* (ቲቶ 2፥4-5) ቆነጃጅት የቤተ ሰብ ኀላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይመከራሉ። በቤት ውስጥ አገልጋይነት የተሰማሩ ወገኖች እንኳ፣ *“ስለ መድኀኒታችን ስለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ነገር ያስመሰግኑ ዘንድ”* (ቲቶ 2፥10) በታማኝነት አሠሪዎቻቸውን ቢያገለግሉ፣ *“የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ”* (1ጢሞ. 6፥1) ያደርጋሉ በማለት ተማጥነዋቸው ነበር።

በትምህርታችን፣ በአሠራራችን በኑሯችንና በአካሄዳችን ለብዙዎች ምሳሌ እንድንኾን ይጠበቅብናል። መልካም ነገር ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን እንደሚገኝ አድርገው ከውጭ ያሉት ትልቅ ስፍራ ሰጥተውናል። እኛ ዛሬ የተያያዝነው አደራረግ በውኑ እግዚአብሔርን በማያውቁት መካከል እያስከበረው ነው? ትምህርቱና ስሙ በመካከላችን ብቻ ሳይኾን በውጭ ባሉቱ ዘንድ እየተመሰገነ ይኾን? ምስክርነታችን የሚያሳየው ምንድነው? ማኅበራዊ ተአማኒነታችን ምን ያህል ነው? ትምህርታችንና ኑሯችን ለስብከተ ወንጌል አገልግሎታችን ዕንቅፋት እየኾነ ይኾን? ምላሽ መስጠቱ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ይኾናል።

ያነሣናቸው ነጥቦች ለማሳያነት እንዲያገለግሉ የተመረጡትን ብቻ እንደ ኾነ ቀደም ብለን ጠቅሰናል። ተጨማሪ ሐሳቦችን ማንሣት ይቻል እንደ ነበር ግልጽ ነው። ኾኖም ከዕንቅልፋችን ደንግጠን ለመነሣት ግን የተጠቀሱቱ ብቻ ከበቂ በላይ ናቸው ተብሎ ይታመናል። እንግዲህ ቀጥሎ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ መፍትሔው ምንድነው? የሚል ይመስለኛል። በቀጣዮቹ ጥቂት ገጾች ውስጥ ለማድረግ የተሞከረውም ይኸንኑ ነው።





# ሰነዶች

## 4. የመውጫ ፍኖት፦ ምን እናድርግ?

ሰማዩ ሲዳምን ተመልክቶ ዝናብ እንደሚመጣ መተንበይ ይቻላል። የዝናቡን መምጣት በመናገር ማስጠንቀቅም መልካም ሊኾን ይችላል። የተሻለው ግን ከዝናቡና እሱን ተከትሎ ከሚመጣው ማንኛውም ዓይነት ችግር መውጫውን ማዘጋጀት መቻል ነው። አንዳንድ ወገኖች ችግር መስማት እንደታከታቸው ይገባኛል። "*የዝናቡን መምጣት* ከመተንበይ *ጕን ለጕን መጠለያ* ስጡን፣ ወይ *ጀልባውን እንድንሥራ* ድጋፍ አድርጉልን" የሚሉ ይመስለኛል።

ይህ ጽሑፍ ሲዘጋጅና ጥናቱ ያሳያቸው ችግሮች ሲቀርቡ፣ ከአንባቢዎች ምልከታና በአንባቢዎች መካከል ሊፈጠር ይችላል ብዬ ከማምንበት ውይይት በርካታ የመፍትሔ ሐሳቦች እንደሚገኙ እምነት በማሳደር ነው። የችግሮቹ መኖር ብቻ ሳይኾን አሳሳቢነታቸው ላይ የጋራ መግባባት የሚኖረን ከኾነ፣ እያንዳንዱ አማኝ፣ ቤተ እምነት፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ተጓዳኝ ተቋማት መፍትሔ በመፈለጉ ሂደት ውስጥ የየራሳቸውን አስተዋጽዖ እንደሚያበረክቱ ይታመናል።

ይህ እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ ከዚህ በታች የዘረዘርኋቸው ሐሳቦች ካለንበት አስተምህሯዊ ቅርቃርና ተዛማጅ አደጋዎች ለመውጣትና ለመፍትሔው "እንደ መነሻ ሐሳቦች በመኾን ለማገልገል ሊጠቀሱ ይችሉ ይኾን?" በማለት ያቀረብኋቸው ናቸው፤ ምን መደረግ ነው ያለበት?

## 4.1 ለቅዱሱ መንፈስና መጽሐፍ ሥልጣን መገዛት

ይህ ቀላል መልስ ቢመስልም እንኳ፣ ዋነኛው መፍትሔ መኾኑ መታወቅ አለበት። ቅዱሱ መንፈስ በቅዱሱ መጽሐፍ በኩል ቅዱስ ቃሉን ሰጠን። ከዚህም በተጨማሪ ቃሉን እንድንረዳ አብርኾት እንደሚሰጠንና እንዲያውም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለመረዳት "የክርስቶስ ልብ" እንደሚኖረን በዚሁ ቃሉ በኩል ተስፋ ገብቶልናል (1ቆሮ. 2፥6-16)።

ስለዚህም ከቃሉና ከመንፈሱ ብንሰማ ኖሮ እንዲህ ዓይነት ድብልቅልቅ ውስጥ ባልገባን ነበር። ይህም  ሲባል በእያንዳንዱ ጥቃቅን ነገር ሁሉ የጋራ መግባባት ይኖረናል ማለት አይደለም። ይኹን እንጂ፣ በዐበይት አስተምህሮዎች ላይ የማይናወጥ ስምምነት ሊኖረን ይችላል፤ ይገባልም። ይህ እውን የሚኾንበትን አግባብ አስመልክተው ጆን ስቶት ሲናገሩ አምስት ነጥቦችን ጠቅሰዋል፤ እነርሱን በዚህ መድገሙ አስፈላጊ መስሎኛል፤ የአስተምህሮ ጤናማነትን ጠብቆ ለመዝለቅ ምን ማድረግ ነው የሚጠበቅብን?

1) የመጽሐፍ ቅዱስን ላዕላይ ሥልጣን መቀበል፤
2) የቅዱሳት መጻሕፍት ዐቢይ ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀጥአንን የሚታደግ ብቸኛው መድኅን እንደ ኾነ ምስክር መስጠት መኾኑን መገንዘብ፤
3) ጤናማ የኾነ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥነ አፈታት መርሖዎችን ማዳበርና ማበልጸግ፤
4) ቅዱሳት መጻሕፍትን በጋራ ማጥናት፤ እና
5) ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በትሑት፣ በተከፈተና ጌታ የሚናገረንን ሊቀበል በተዘጋጀ ቅን መንፈስ ወደርሱ መቅረብ ይኖርብናል።[138]

[138] John Stott, *Basic Christian Leadership* (Downers Groove: IVP, 2002) 71-72





በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ቀዳሚው የሥልጣን ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ከመኾኑ የተነሣ ለትምህርቱ፣ ለመመሪያዎቹና ትዕዛዛቱ የተለየ ትኵረት መስጠታችን ላያስገርም ይችላል። ሊያስገርምና ሊያሳዝን የሚችለው ግን የዚህን ታላቅ መጽሐፍ ሐሳብ ሳንረዳ ተሸከመነው ወይም እየተሳለምነው የተገኘን እንደ ኾነ ብቻ ነው።

ብዙ ሰዎች ይህን መጽሐፍ የማያነቡትና የማያጠኑት ስለማይገባቸው እንደ ኾነ ሲናገሩ ተሰምተዋል። በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስን ለተወሰኑ የሃይማኖት ሊቃውንት ጥናትና ትንተና የተሰጠ አድርገው በመቍጠር መጽሐፋቸውን ከራስጌያቸው ያኖሩ ወይም ከሰንዱቃቸው በክብር የሸሸጉ ወገኖች ብዙ ናቸው። መጽሐፉ የተሰጠን ግን በሕይወት መሥመር ላይ እንዲመራንና ሳንደነቃቀፍ እንድንሄድ ነበር።

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሷውያን አባቶች በሰው ትምህርትና ልማዳዊ ወግ ላይ ሲያምፁ ምክንያታቸው በእምነትና ሥርዐታዊ ጕዳዮች ላይ፣ የመጨረሻ ዳኛ በመኾን ረገድ፣ "ቃለ እግዚአብሔር የኾነው መጽሐፍ ቅዱስ ይከበር" የሚል ዐቋም ይዘው ነበር።[139] ለዚህም ሁለት ቀደምት ተሐድሷዊ የእምነት ዐርበኞችን ብቻ ለአብነት እጠቅሳለሁ። አንድም የእኛኑ መነኵሴ አባ እስጢፋኖስን[140] ሲኾን ሁለተኛው ደግሞ ጀርመናዊው መነኵሴ ማርቲን ሉተርን ነው።

[139] የወንጌላዊው ክርስትና ተሐድሷዊ ፈር ቀዳጆች የሚባሉትና ቤተ ክርስቲያን ከገባችበት የመካከለኛው ዘመን አስተምህሯዊ መቀመቅ እንድትወጣ ልዑል እግዚአብሔር በጸጋው ከተጠቀማቸው ሰዎች መካከል አንዱና ቀዳሚ የነበረው መነኵሴ ማርቲን ሉተር በዋናናት ካነሣቸው ሦስት "ብቻዎች" አንደኛው "መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ/*Sola Scriptura*" የእውነት መመሪያና ሥልጣን ምንጭ ነው የሚል ነበር። የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ እግዚአብሔር ኀጥአንን የተቤዠውና ድኅነትን የሚሰጣቸው "በጸጋ ብቻ/*Sola Gratia*" ሲኾን፣ ሰዎችም ይህን ድኅነት የሚቀበሉት "በእምነት ብቻ/ *Sola Fide*" ነው የሚል ነበር።

[140] በዚህ ላይ የበለጠ ለመረዳት ስለ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ እንዲሁም ሌሎች ገዳማውያን ገድሎች የተጻፈውንና በአማርኛ ቋንቋ ፕሮፌሰር ጌታቸው የተረጐሙትን መጽሐፍ ይመልከቱ። ጌታቸው ኀይሌ፣ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፦ "በሕግ አምላክ"* (ዐዲስ አበባ፦ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2002 ዓ.ም.)።

የአውሮጳ ተሐድሷውያን (*Reformers*) ሳይነሡ ብቻ ሳይኾን ገና ሳይወለዱ በፊት በኢትዮጵያችን የደመቀ የእውነት ምስክሮች ድምፅ ተሰምቶ ነበር። መጽሐፉ ከሚያስተምረው ውጭ አላምንም፣ አላስተምርምም የሚሉ መንፈሰ ጽኑዓን ተነሥተው ነበር፤ “*አነሰ ኢይሰግድ ለባዕድ ዘእንበለ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወከመዝ ውእቱ ሕገ እግዚአብሔር*— እኔስ ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ በቀር ለማንም ባዕድ አልሰግድም፤ የእግዚአብሔር ሕግ እንዲህ ነውና።” በማለት የጸና ሰማዕት ተወልዶ ያደገባት ሀገር ነበረችን። “ሐሰትን እምቢ” ያሉ ምስክሮች የተሠዉበት ክርስትና ነበረ። መጽሐፉ ካዘዘኝ ውጭ ለማንኛውም ፍጡርና ምስል አልሰግድም በማለት ሕይወታቸውን በግፍ የተነጠቁ የእምነት ዐርበኞችም ነበሩን፦ “ደቂቀ እስጢፋኖስ” (የእስጢፋኖስ ልጆች፣ ደቀ መዝሙሮች)።[141]

ይህ ዐቋማቸው ታዲያ ሕይወታቸውን በሰማዕትነት አሳልፈው እንዲሰጡ እንዳስገደዳቸው ታሪክ መዝግቧል። በዚህ ውሳኔአቸው ምክንያት በደቂቀ እስጢፋኖስ ላይ የደረሰባቸውን ለመተረክ ጊዜና ቦታ አይበቃውም። “የሰው ልጅ በአምሳሉ በሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ላይ ምን ያህል ቢከፋ ነው እንዲህ ሊፈጽም የሚችለው” አሰኝቶ ግራ የሚያጋባ ነውና። ከቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት በእኒህ ወገኖች ላይ የደረሰውን ጣምራ የሠቆቃ ውርጅብኝ ያነበቡትና አስተያየት የሰጡት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም “የደቂቀ እስጢፋኖስ ሠቆቃ ያስደነግጣል፤ ያሳዝናል፤ ያስቈጣል፤ የማናውቀውን ራሳችንን ዕርቃናችንን ያሳየናል ... ፈረንጆቹ *ቶርቸር* የሚሉትን ኰነኔ እኛ የፈጠርነው መስሎኛል፤” ነበር ያሉት። ለማንኛውም፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው የተረጐሙትን *ደቂቀ እስጢፋኖስ፦ “በሕግ አምላክ”* ማየት ውርጅብኙ ምን መልክ እንደ ነበረው ለማየት ያስችላልና እርሱን ከጠቈምን በቂ ነው።

እኒያ የእምነት ዐርበኞች የተቀበሉት መከራ ከባድነት ዋጋ አስከፍሏቸዋል። የጊዜው ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የወሰደው ርምጃ አሠቃቂ ነበር፤

[141] ግርማ ኤልያስ፣ *ደቂቀ እስጢፋኖስና የደብረ ብርሃን ሽንጐ* (ዐዲስ አበባ፦ አሳታሚ አልተጠቀሰም፣ 2000 ዓ. ም.) 79።





“ምላሳቸውን እየነቀለ፣ አፍንጫቸውን እየፎነነ (እየገመደ)፣ እጅ እግራቸውን እየከላ መነኰሳቱን ከነቆባቸው ተከታዮቻቸውንም ከነሳዱላቸው በደም ነክሮ ጨፍጭፏቸዋል።”[142] ነገር ግን ከእውነት መንገድ አላደናቀፋቸውም። ለእውነት የመቆም ቋንቋዋስ ይኸው አይደለምን? በኤ. ደብልዩ ቶዘር አባባል፣ “የእውነተኛ እምነት ቋንቋዋ ‘ሰው ሁሉ ውሸተኛ ቢኾን እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን’ የሚል ነውና።” ለመጽሐፉ ሥልጣን መገዛት ማለት እዚህ ድረስ ይወስዳል።

ማርቲን ሉተርም በአውሮጳ ፍጹም ሥልጣን በተቀዳጀችው የሮም ቤተ ክርስቲያን አንጻር ተመሳሳይ ፍጥጫ ገጥሞት ነበር። ውሳኔው ሊያስከትል በሚችለው ውጤትና ከቅዱሱ መጽሐፍ በተረዳው እውነት መካከል አጣብቂኝ ውስጥ የገባው መነኲሴ እምነቱን እንዲያስተባብልና ንስሐ እንዲገባ *ዳይት ኦፍ ዎርምስ* በተባለ ቦታ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲቀርብ ተገደደ።[143] ነገር ግን ሉተር “አላስተባብልም” ሲል በዐቋሙ ጸና። “ስሕተት ከመኾናቸው የተነሣ ልትተዋቸው ይገባሃል” ተብሎ እንዲያስተባብል የተገደደባቸውን የእምነት ዐቋሞች አስመልክቶ ምላሽ በሰጠበት ወሳኝ ቀን እንዲህ አለ፤ “በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነትና በጤናማ አመክንዮ ልታሳምኑኝ እስካልቻላችሁ ድረስ፣ አላስተባብልም” በማለት ቊርጠኛነቱን ገለጸ። እግዚአብሔርም ለዚህ ደካማ መነኲሴው የጽናትን ጸጋ በመስጠት የመጽሐፉን ሥልጣንና ትምህርት ከግለሰቦችና የሃይማኖት ተቋማት ጒልበትና መዳፍ ፈልቅቆ አስጣለ።

መፍትሔው ዛሬም አንድ ብቻ ነው፤ ከሰው ትምህርት ይልቅ ቃሉ ይቅደም! መናገር ስለቻልንና ከአትሮኖስ ፊት ስለቆምን ብቻ ያሻንን የማስተላለፍ መብት እንደሌለን ዳግመኛ ይታወጅ፤ የታማኝ መጋቢነት መገለጫው እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ በተሰጠን ጸጋ እንደ ቃሉ ማገልገል ነው።

[142] ገብረ መሲሕ፣ *የመምሩ ምርቅና መረቅ፦* በ“*የተከላው ለምድ ሲገፈፍ” ውስጥ* (ዐዲስ አበባ፦ አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2002 ዓ.ም.) 40።
[143] Richard Marius, *Matin Luther: The Christian between God and Death* (Massachusettes: Cambridge University Press, 1999) 246.

*ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መኾናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢኾን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኀይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚኾነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን* (1 ጴጥ 4፥11)።

በ"ተገለጠልኝ" ስም እንግዳ ትምህርቶችንና ልምምዶችን ከማሰራጨትና ብዙዎችን ከማሰናከል ይልቅ መሠረታችንን በደንብ እናጽና፤ *"ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት* (ዕብ. 6፥1)። ወደ ቅዱስ ቃሉ እንመለስ፤ እናንብበው፣ እናጥናው፣ በእርሱም እንመራ። እግዚአብሔር በእጃችን የሰጠን የእውነት መዝገብ ነው፤ የሕይወት መመሪያ ነው፤ ታላቅ ዕድል እኮ ነው። ቤንጃሚን ፍራንክሊን "ጕድጓዱ በደረቀ ጊዜ የውሃን ዋጋ ማስተዋል እንጀምራለን" እንዳለው መጽሐፍ ቅዱሳችን ምን ያህል ውድ እንደ ኾነ ለመገንዘብ እስከምናጣው አንጠብቅም።

ዛሬ ዛሬ በየቦታው የሚታየው መዋከብና መራወጥ የቃለ እግዚአብሔር ርኀብ የፈጠረው ይኾን ያሰኛል። ሕይወት ያለባቸውን ቃላት (ሐዋ. 7፥38፤ ፊል. 2፥16) ከእርሱ ተቀብለን፣ በመንፈስ ቅዱስ ለመንጋው ማቅረብ ከቻልን እግዚአብሔር ይከበራል፤ ሰዎችም ይለወጣሉ። ከዚህ የተለየ ተስፋና መፍትሔ ልናመጣ ግን አይቻለንም። አንድ ነገር ልብ ማድረግ አለብን፤ ሕዝባችንን ወደ ቅዱስ ቃሉ መምራት ከፊታችን የተደቀነ ኀላፊነታችን ኾኗል። ስለዚህ ይህን እንጮኻለን:- *"መጽሐፉን ስጡን!"*

የዌልስ መንፈሳዊ መነቃቃት (*ሪቫይቫል*) እንግሊዝን፣ አውሮጳንና አሜሪካን በናጠበት ወቅት እግዚአብሔር በጸጋው የተጠቀመበት ሰው ጆን ዌስሊ እንዲህ ብሎ ነበር፤





እኔ፣ ከቀስቱ እንደ ተለቀቀና በአየር ላይ ተወንጭፎ እንደሚያልፍ ፍላጻ በሕይወት መም ላይ የማልፍ የአንድ ቀን ፍጡር እንደ ኾንሁ አድርጌ ማሰብ ልማዴ ነው። ከእግዚአብሔር የመጣና ወደ እርሱም የሚመለስ መንፈስ አለኝ። በመጣሁበት ግዙፉ ሰርጥ ላይ ለጥቂት ቅጽበት ከንፌ ካለፍሁ በኋላ [በሥጋ] አልኖርም። በማይለወጠው ዘላለም አድማስ ውስጥ እንደ አንዲት ጠብታ ብቻ እጠልቃለሁ። ነገር ግን፣ አንድ ነገር ብቻ ላውቅ እፈልጋለሁ — የሰማዩን መንገድ! እንዴት አድርጌ ከዚያ ደስታ ከሰፈነበት የባሕሩ ዳርቻ (ከወደቡ) እንደምደርስ እናፍቃለሁ። እርግጥ ነው፣ ራሱ እግዚአብሔር ይህን መንገድ ለማሳየት ዝቅ ብሎ ወርዷል፤ አዎ፥ እርሱ ከሰማየ ሰማያት ወረደ፤ ያን መንገዱንም በመጽሐፍ በኩል ገለጠው። አቤቱ፥ ምንም ዋጋ ቢያስከፍል እንኳ ያንን መጽሐፍ ስጡኝ! የእግዚአብሔርን መጽሐፍ ስጡኝ![144]

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ይህን የምትጮኽ ይመስላል፤ ደግሞ እኛም እንጮኻለን:- የእግዚአብሔርን መጽሐፍ ስጡን! ከሰብአውያን ትምህርት ገላግሉን። የሰው ትምህርት እንዴት ያደክማል! እንግዳ ትምህርት ምንኛ ያፈዝዛል!

ከማናቸውም ግለ ሰቦች፣ ቡድኖች፣ ተቋማትና ቤተ እምነቶች በላይ የቅዱስ ቃሉ ሥልጣን መከበር አለበት። ያን ጊዜ እሱ ውሃ የማይቋጥሩ የሆይ ሆይታ ደመናዎችን ይበትናቸዋል። የመንፈስ ቅዱስን አብርሆት በመሻት መጠጋትም ይኖርብናል። በዚያን ጊዜ ቅዱሱ የጌታ መንፈስ እድፍ የሞላቸውን ጕድጓዶች ይጠርጋቸዋል፤ ያጠራቸውማል። ንጹሑ የሕይወት ውሃ ይፍሰስ፤ ነፍሳችን ትረስርስ፤ መንፈሳችንም እፎይታ ትመላ። ለእግዚአብሔር ክብር ይምጣ፤ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ትታነጽ። ለቅዱሱ መንፈስና ለቅዱሱ መጽሐፍ ቦታውን እናስረክብ። በቅዱስ ቃሉ ላይ የተመሠረተ የእግዚአብሔር ኀይል ይገለጥም ዘንድ መንፈስን እናጥፋ።

---

[144] John Wesley, *Sermons on Several Occasions,* (Longon: Originally published in 1771) Preface.

## 4.2 “መንፈስን አታጥፉ”

እማናዊ (እውነተኛ) መንፈሳዊ መነቃቃቶችን ላለማዳፈን መጠንቀቅ አለብን። ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ከገባው ተስፋዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው (ዮሐ. 14፥15-17፡ 26፤ 15፥26፤ ሐዋ. 1፥8)። የመንፈሱ መምጣት የዐዲስ ኪዳናዊው ዘመን መከፈት የምሥራችና እውናዊ ተጨባጭነት ማረጋገጫ፣ ዋስትናና ማኅተም ተደርጓል። እግዚአብሔር የጸጋው ክብር ይመስገን ዘንድ በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ እኛን የዋጀበትና በሕዝቡ መካከል በማደር ቅሩብ መገኘቱ እውን የኾነበት ኪዳን መጥቷል፤ በክቡር ደሙ ተመርቆም ተከፍቷል።

ከጠፊው ዓለም የተጠሩት ምእመናን የእምነት ተጓዦችና እግዚአብሔር የመረጣቸው የማስማሪያው በጎች ናቸው። ወደ ቤታችን በመሄድ ላይ ያለን የእምነት ተጓዦች ነን። “ዘላን ቤት የለውም፤ ሽፍታ ከቤቱ የሸሸ ነው፤ እንግዳ ከቤቱ የራቀ ሲኾን፣ የእምነት ተጓዥ ግን ወደ ቤቱ የሚሄድ ነው።”[145] እንግዲህ በእምነት በምንጓዝበት ጊዜ ብቻችንን አይደለንም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው። የዚህ ማረጋገጫው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ማደሩ ነው። አዎ፣ ጌታ እንደ ተስፋ ቃሉ *“ያን መንፈስም፥ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንኾን፥ በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው”* (ቲቶ 3፥6-7)። ክብር ለእርሱ ለዘላለም ይኹን።

የመንፈሱ መፍሰስ የእግዚአብሔርን የመገኘቱን ቅሩብነትና አሁንነት ያሳየ እውነት ነው። ይህም እውነታ አምላካችን እግዚአብሔር ዐልፎ፣ ዐልፎ ብቻ ሳይኾን ሁልጊዜ ያለማቋረጥ ከእኛ ጋር እንዳለ ያመለክተናል። ዐብሮነቱ በተስፋ የጸና ክብር ነበር። የእግዚአብሔር ዐብሮነት ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ዐዲሱ ኪዳን መምጣት ትንቢት ሲናገር ከተዘረዘሩት ዐበይት ተስፋዎች መካከል የሚገኝ መኾኑን እያነበብን ሐሴት እናደርጋለን።

[145] ቲም ፊሎስ፣ *የምታመልክ ሁን* (ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ፐብሊኬሽን፣ 2004) 342።





*እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር ዐዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር። ... ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይኾኑኛል። ኢያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ ኢያንዳንዱም ወንድሙን፡- እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፥ ይላል እግዚአብሔር* (ኤር. 31፥31-34)።

በዐዲሱ ኪዳን መግቦት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ኅብረት ወደ ዐዲስና የላቀ ደረጃ ከፍ እንደሚል መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል (ሮሜ 8፥9፡ 11፤ 1ቆሮ. 3፥16፤ 6፥19፤ 2ቆሮ. 13፥14፤ ፊል. 2፥1)። ይህ ከኾነባቸው ኪዳናዊ ባርኮቶች አንዱ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መቀበላችንና በመንፈስ መሞላታችን ነው (ዮሐ. 20፥22፤ ኤፌ. 5፥18)። የእግዚአብሔር ልጆች መኾናችንን ሳይቀር የሚመሰክርልን እርሱ የእውነት መንፈስ ነው (ሮሜ 8፥15-16)።

በአንዲት የክርስቶስ አካል ውስጥ እንድንኾን በአንድ መንፈስ ከመጠመቃችን የተነሣ አንዲቱን አካል ለማነጽ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን በሚያድላቸው ስጦታዎች አማካይነት በጥበብና በማስተዋል እግዚአብሔር ለሚከበርበት አገልግሎት መትጋት ያስፈልገናል። *“አይሁድ ብንኾን፣ የግሪክ ሰዎችም ብንኾን፣ ባሪያዎችም ብንኾን፣ ጨዋዎችም ብንኾን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንኾን ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል”* (1ቆሮ. 12፥13)።

እግዚአብሔርን በምልዓት በአዕምሯዊ ዕውቀታችን የምንቀርበው አይደለም። ተመክሯዊ ልምምድ ያካተተ ኅብረት ጭምር እናደርጋለን። ኀይሉንና ጸጋውን በዕለት-ተለት ኑሯችን ውስጥ ልንለማመድም እንችላለን (ሉቃ. 24፥49፤ ሐዋ. 1፥8)። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የምናነበውና የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የቀመሰችው “መንፈስን መቀበል” የዕውቀታዊ አብርሆት ጉዳይ ብቻ ሳይኾን፣ ምእመናን በግላቸው ተመክሮ ሳይቀር የተለማመዱት ባርኮት ነበር (ሐዋ. 8፥17-19፤ 19፥6)።

ምእመናን መንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲሰጣቸው ያውቁ ነበር (ሐዋ. 13፥24፤ 16፥6-7)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምሪቱ ለአካሉ መታነጽ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን በሰጣቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች አማካይነት ይመጣ እንደ ነበር (ለምሳሌ አጋቦስን ያስታውሷል) እናያለን (ሐዋ. 11፥27-28፤ 21፥10-11፤ 1ቆሮ. 12-14)።

ይህ የመንፈሱ ቅሩብነትና አሁንነት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን ሁሉ በተለያዩ የክርስቲያን ነገረ መለኮታዊ ትውፊት ውስጥ የነበሩ ምእመናን ጌታ እንደ ፈቀደ ሲለማመዱት ኖረዋል። ነገር ግን ታሪካችን የሚነግረን ይህን አዎንታዊ ጎን ብቻ አይደለም። ሃይማኖታዊ ድንዛዜ ያስከተለውንም መፋዘዝ እናስባለን። አጂት ፈርናንዶ በሚገባ እንዳስተዋለው፣

> ብዙውን ጊዜ ምውት ርቱዕነት (ደረቅ እውነተኛነት) የቤተ ክርስቲያንን አስተሳሰብ በመውረር፣ ይህን የመንፈሳዊ ልምምድ ነበልባል ለማዳፈን በውሃ እንደ ራሰ ኩታ አገልግሎ ያውቃል። ኾኖም በየዘመኑ በክርስቲያን ሕይወት ፊት መሥመር ላይ ተመላልሶ እንዲመጣ ለማድረግ ከመንፈስ ቅዱስ አሠራር በሚገኝ የክርስቲያኖች ልምምድ በኩል መንፈሳዊ መነቃቃቶች ሲከሠቱ ኖረዋል። ባለፉት ሦስት ምእት ዓመታት ውስጥ ብቻ የኾነውን ብናጤናቸው፣ በ*ዌስሊያዊው* እና በ*ካሪዝማዊው* እንቅስቃሴዎች ውስጥ የታዩት መነቃቃቶች ዋቢ ይኾኑልናል።[146]

በየዘመኑ እውነተኛ መንፈሳዊ ልምምዶችን ብቻ ሳይኾን አስመሳይና አሳሳች ድርጊቶችንም ታሪክ መመዝገቡ አልቀረም። በርግጥ የመንፈሱ ቅሩብነት በረከቶችን አላግባብ ከመጠቀም ጉድለቶች የተነሣ ችግር ይገጥማቸዋል። አንዳንዶች እግዚአብሔር ያላላቸውን በስሙ ሲናገሩ ታይተዋል። ምንጫቸው ከጌታ መንፈስ ቅዱስ ያልነበሩ አንዳንድ ልምምዶች ደግሞ፣ ከናካቴው አጥፊና አውዳሚዎች ነበሩ። እውነት ነው፤ ምንጫቸው የጌታ መንፈስ ያልኾኑት ላይ መጨከን ይኖርብናል። እውነተኛ የኾኑትን ስጦታዎች በተመለከተ “ግን፣ የስጦታዎች አላግባብ ጥቅም ላይ መዋል፣ ስጦታዎቹን ከነጭራሹኑ ጥቅም ላይ

[146] Fernando, *Jesus Driven*, 37.





ላለማዋል በር መክፈት የለበትም። ይልቅስ ችግሮች አግባብ ላለው አጠቃቀም የሚበጁ መመሪያዎችን እንድናዳብር ምክንያቶች ይኾኑናል። ጳውሎስም ያደረገው ይህንኑ ነበርና (1ቆሮ. 12-14)።”[147]

እኛም ልንከተለው የሚገባን የሐዋርያው ጳውሎስን አርአያነት ነው። “ልጁን ከታጠበበት ውሃ ጋር ወደ ውጭ የመድፋት” ርምጃ ለመውሰድ የሚሞክሩ ትልቅ ኪሳራ ያገኛቸዋል። መጋቤ ሐዲስ ዶ/ር ስቲቭ ብሪያን የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ኹኔታን ጳውሎስ በመልእክቱ ካስተነተነበት ዐውድ ተነሥተው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ባዘጋጁት ጽሑፍ እንዳመለከቱት፣

> አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ እየተፈጠረ ያለውን የአሠራር ብልሹነት አጋንንታዊ እንደ ኾነ ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ልምምዶቹን ሙሉ በሙሉ ማስወገድን እንደ አማራጭ ይወስዳሉ። ሐዋርያው ግን ይህን አላደረገም። ይልቁኑ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የተቀበሏቸው የጸጋ ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መኾናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ በቅጡ ካለመረዳታቸው የተነሣ እየተፈጠሩ ያሉትን ችግሮቻቸውን [ብቻ] ለማረም ሲጥር ይታያል።[148]

ከማንኛውም ክፉ ትምህርትና ተመክሮ ለመራቅ መፍትሔው እውነተኛውን አሠራር ማዳፈን አለመኾኑን መረዳት የተገባ ነው (1ቆሮ. 14፥39-40)። በመንፈስ ነጻነትና በድንጋጌ ሥርዐት መካከል ተገቢ ሚዛን መጠበቅ ያስፈልጋል። ትእዛዙም *“መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ”* (1ተሰ. 5፥20) የሚል ነውና።

[147] Fernando, *Jesus Driven*, 37.

[148] ስቲቭ ኤም. ብርያን፣ “መንፈሳዊ አስተርእዮትን (መገለጦችን) ክርስቲያናዊ ማድረግ፣” *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም ሴሚናር* (ዐዲስ አበባ፦ ኤገስት፣ 1997) 9-10።

## 4.3 ትኩረት ለስብከተ ወንጌልና ደቀ መዝሙርነት

ስብከተ ወንጌል ቸል ሊባል የማይችል የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋ ነው። የስብከተ ወንጌል ግብ በሰሚው ዘንድ ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ዋነኛ ርእስ ክርስቶስ ኢየሱስ ሲኾን፤ እርሱም ከዘላለም የእግዚአብሔር ልጅ የኾነው መድኅን ነው። ወንጌል ለሚታዘዙት ሁሉ የመዳን ደስታን ያጐናጽፋቸዋል።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በምድር ላይ ካስቀመጠበት ዓላማዎች መካከል አንደኛው ስብከተ ወንጌል ነው። ሁሉም አገልግሎቶች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ይህን ታላቅ ተልእኮ ማካተታቸው መዘንጋት የለበትም። ይህን ዓለማ ከመፈጸም የሚያስተጓጉሉ የትኞቹም ነገሮችን በጌታ ጸጋና ኀይል እንድንቃወማቸው ያስፈልገናል። የመሰብሰቢያ አዳራሾች ግንባታ፣ የመገልገያ ቍሳቍሶችና የሙዚቃ ዕቃዎችን ያስፈልጉናል። ኾኖም እነዚህ ነገሮችን የምንጠቀመው ዋነኛውን ተልእኳችንን ለማሳካት እንጂ ለማደናቀፍ ወይም የወንጌል ስርጭት ሥራን በማራቆት አለመኾኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለተመለከትናቸው ችግሮች በመንሥኢነት ከዋሉ ነገሮች አንደኛው የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን በማዳከም በሌሎች ተግባራት ላይ መጠመዳችን ሳይኾን አይቀርም። ስለ ኾነም አብያተ ክርስቲያናት ተልእኳዊ (*missional*) እንደ መኾናቸው በጥሪያቸው ላይ ቢያተኵሩ በርካታ ችግሮችን መቅረፍ በቻልን ነበር። ወንጌልን መስበክ ያቆመች ቤተ ክርስቲያን ሕያውነቷ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

ከወንጌል ስርጭትና መልእክተኛነት በተጨማሪ ደግሞ ከአስተምህሮ አኳያ ሊዘለል የማይችል መፍትሔም አለ። እርሱም የትምህርት አገልግሎትን ይመለከታል። የአስተምህሮ ችግሮች አሉ ብለን ስናበቃ፣ ለመፍትሔ ይኾን ዘንድ ጤናማ ትምህርትን በተገቢው መንገድ የመስጠቱን አስፈላጊነት አለማንሣት እንዴት ይቻላል? አይቻልም።





ግን "እንዴት ይሰጥ?" የሚለው ልንወያይበት የሚገባ ነው። ጸሐፊው እንደሚያስበውና ባብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች አጽንዖት እንደ ተሰጠው ከኾነ "ከደኅንነት"[149] ትምህርት ብቻ ያላለፈ ሥርዐተ ትምህርታችን መከለስ፣ መስተካከልና በተሻለ ኹኔታ ሊዘጋጅ የሚገባው ይመስላል።

አብዛኛው ምዕመን ከዝማሬ መልእክት፣ በየመድረኩ ከሚቃርመው የግለ ሰቦች ንግግር፣ ከየመጽሔቱ ላይ ከሚወጡ ሐሳቦች፣ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከሳተላይት ቴሌቪዥን በሚያገኛቸው አስተማሪዎች፣ እንዲሁም በቅንጭብጫቢና ተባራሪ የኦዲዮ ቪዥዋል መልእክቶች ላይ ተመሥርቶ ነገረ መለኮቱን በሚገነባበትና ሕይወቱን ደግፎ ለመምራት በሚፍጨረጨርበት ኹኔታ የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት በጣም ከፍተኛ መኾኑ አያጠራጥርም። ስለዚህ ከወዲያ ወዲህ የሚራወጠውን ምእመን መንፈሳዊ ረኀብ ለማስታገስ ጠንክረን በመሥራት ደቀ መዝሙራዊ ሕይወት ላይ ማተኰር ይኖርብናል።

ደቀ መዝሙርነት የእምነት መታዘዝ ነው። ድንበሩ ለጌታ የተሰጠ ሕይወት ነው። ደቀ መዝሙር የሚባለው ከጌታ የሚማር፣ እሱን የሚከተልና በሕይወቱ የሚያድግ አማኝ ነው።

> ደቀ መዝሙር ከጌታውና ከመምህሩ ብዙ የሚማር ነው። ጌታውን የሚወድና ፈለጉንም ለመከተል የሚፈልግ ነው። የሚማረው ትምህርት ሕይወቱን የሚለውጥ ስለ ኾነ ይበልጥ መምህሩን እየመሰለ ይመጣል። ስለጌታው ሁሉንም ነገር ለማወቅ የሚማር ብቻ አይደለም፤ ጌታውን እንዴት መታዘዝ እንዳለበት ይገነዘብ ዘንድ ይማራል እንጂ።[150]

---

[149] ይህ ዐዲስ ምዕመናንን ከመጀመሪያ የክርስትና ትምህርቶች ጋር ለማስተዋወቅ የሚሰጥ ትምህርት እንደየቤተ እምነቱ የተለያየ መጠሪያ እንደሚሰጠው ቢታወቅም (ለመግባባት ሲባል) በአብዛኞቹ ወንጌላውያን በተለምዶ የሚጠራበትን ሥያሜ —*የደኅንነት ትምህርት*— ተጠቅሜበታለሁ።

[150] ተስፋዬ መኰንን (ተርጓሚ)፣ *ደቀ መዝሙርነት* (ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 2002) 7።

## 4.4 ትኩረት ለቃለ እግዚአብሔር ጥናት

የቃለ እግዚአብሔር ጥናት እያንዳንዱ አጥቢያ የምር እንዲሠራበት ማሳሰብ አስፈላጊ ነው። አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖችን ማጠናከር፣ የቤት ለቤት መርሐ ግብሮችን ማበረታታት፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትምህረት መስጠትና የመሳሰሉትን ከሌሎች ጥረቶቻችን ጋር ማካተት ይኖርብናል። በርግጥ በየአጥቢያው የዐቅም ውስንነት መኖሩን እንገነዘባለን። ነገር ግን፣ በአግባቡ የተዘጋጀና ወጥነት ያለው ሥርዐተ ትምህርት በአንድ ቤተ እምነት ደረጃ ተዘጋጅቶ ለየአጥቢያዎቹ የሚዳረስበትን መንገድ ማመቻቸት ይቻላል።

በዚህ ላይ ለማከል ደግሞ፣ ዐቅማቸውን የገነቡ ጠንካራ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ አማራጮችን በመጠቀም ትምህርቶችን በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙኀን በኩል ማሰራጨት ይችላሉ። በተለይ የኅትመትና *ኤሌክትሮኒክ* መገናኛ ብዙኀንን መጠቀም አማራጭ ብቻ ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይመስለንም። በተለይ *የሳተላይት ሚዲያው* ወደ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ቤት ከዘለቀ ወዲህ ምን ያህሎቹ መምህራን ጤናማ እንደ ኾኑ የማጥናቱን ድርሻ ወደ ጐን ትተን፣ የተጽዕኗቸውን ኀያልነት ብቻ ለመጥቀስ እንወዳለን። ነገር ግን በዚህ የሚዲያ ዐይነት መሳተፍ ምን ያህል ዐቅም ፈታኝ እንደ ኾነ ብንረዳም፣ ቤተ እምነቶች አባሎቻቸው ከማን ገበታ እየቀረቡ እንደሚመገቡ የማስተዋል ግዴታቸውን ከግምት በማስገባት የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው።

የቃለ እግዚአብሔር ጥናት ጊዜን፣ ትጋትና ታማኝነትን የሚጠይቅ መኾኑን ችላ ማለት አይገባንም። አንድ የእግር ኳስ ግጥሚያን ለመከታተል በትንሹ ለሁለት ተከታታይ ሰዓታት ያለመታከት የሚቀመጥ ሰው የእግዚአብሔር ቃል ለማጥናት ግን ሲቍነጠነጥ መታየቱ አሳዛኝ ይኾናል።

በተጨማሪም፣ አገልጋዮችን እንደየጸጋቸው ማሰማራትም ትኵረት ማግኘት ይኖርበታል። አንድ ሰው ስለሚተነብይ ብቻ፣ ወይም የታምራትና ፈውስ ስጦታ ስላለው ብቻ ወይም አጋንንት ስለሚያስወጣ ብቻ አስተማሪ ላይኾን ይችላል (አንዳንዶች ሊኾኑ ይችላሉ)። ነገር ግን፣ ለሌሎች አገልግሎቶች “ሽር-ብትን” የምንለውን ያህል ለትምህርት አገልግሎት ብዙም ትኵረት እኛደማንሰጥ





ማሳያው የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር የማይበቁ ወገኖችን በማስተማር አገልግሎት ላይ አሰማርተን መገኘታችን ነው። ሕዝብ በሞላባቸው መድረኮች ላይ ለማስተማርና ለመስበክ ወረፋ የሚጠብቁ ነገር ግን በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ ቃለ እግዚአብሔርን ላማስተማርና ለማስጠናት የማይኾንላቸው ሰዎች አሉ። ይህ መስተካከል ይኖርበታል።

በተጨማሪም፣ ምእመናን መሠረት በሚጥሉበት የክርስትና የመጀመሪያ ዓመታት ዋነኛ የክርስትና ትምህርቶችን በበቂ ኹኔታ መስጠት እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ በቀጣይ ዘመናቸው የግልም ይሁን የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መንገዶችን እንዲቀስሙ ማሳየትና ማበረታት ጠቃሚ መኾኑ ከግንዛቤ ቢገባ መልካም ነው። ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የመረዳት ዐቅምን ባገናዘበ ኹኔታ የዐዋቂዎች የሰንበት ትምህርትን ማጠናከርም ይቻላል። የትምህርት ይዘቱም ኾነ አሰጣጡ ዐውዳዊና ሁሉን አቀፍ ሊኾንም ያስፈልገዋል።

አቶ ሚናስ ብሩክ በተረጐሙት አንድ የክርስቲያናዊ ትምህርት መጽሐፍ ላይ እንደ ተጠቈመው፣ “የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ትምህርት አገልግሎት ሁሉን አቀፍና ሚዛናዊ ሊኾን ይገባዋል። የኅብረተ ሰቡን የወንጌል ስርጭት ፍላጐት፣ እንዲሁም የአጥቢያ ምእመናኑን የዕድገት መሻት ከግምት ውስጥ ያስገባ መኾን ይኖርበታል።”[151]

[151]ሚናስ ብሩክ (ተርጓሚ)፣ *የአገልግሎት መሠረቶች፦ የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ* (ዐዲስ አበባ፦ ኤስ. አይ. ኤም ፐብሊኬሽን ኢትዮጵያ፣ 2000 ዓ.ም.) 23።

## 4.5 ትኩረት ለነገረ መለኮት ትምህርት

ይህ ማለት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ትልልቅ የነገረ መለኮት ተቋማት ያቋቁሙ ማለታችን አይደለም። ዐቅማቸው ቢችልና አስፈላጊም ኾኖ ከተገኘ ቢያደርጉት አይከፋም። ለማለት የተፈለገው ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጤናማ ለኾኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች እንደየደረጃውና ዐቅማችን በፈቀደ መጠን የነገረ መለኮት ትምህርትን እናጠናክር ለማለት ነው፤ በርግጥም ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ አማኝና እንደ ትውፊቱ “የመጽሐፉ ሕዝብ” የመኾኑን ማስረጃ በእምነቱ፣ በምግባሩና በኑሮው ሊገለጥ ይገባልና። ቃሉ፣ *“በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ”* (1ጴጥ. 3፥15) ይላል።

እዚህ ላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችም ሐሳብ መሰንዘር አስፈላጊ ይኾናል። የመጽሐፍ ቅዱስና የነገረ መለኮት ትምህርት ጥናቶቻችን ምን ያህል የእኛን ዐውድ ያማከሉ ይኾን? ከተመሠረቱ ረጅም ዓመታት የኾናቸው ተቋማት ካሠለጠኗቸው ተማሪዎቻቸው መካከል ምን ያህሎቹ በተገቢ ስፍራ ተሰማርተዋል? ለምዝገባ ከሚመጡት አመልካቾች መካከል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላይ የሚያተኵሩትን የመግቢያ ፈተናዎችን ባለማለፍ ከቅበላ መርሐ ግብር የሚመለሱ፣ ነገር ግን በአገልግሎታቸው ለእግዚአብሔር ክብርና ለአካሉ መታነጽ ምክንያት የኾኑ ተጽዕኖ ፈጣሪ ወገኖች ስንት ናቸው? ለእነሱ የሚኾን የሥልጠና መርሐ ግብር የማዘጋጀት ኀላፊነትስ የማን ነው?

ይህን አስመልክቶ ዶ/ር ሰብለ ወንጌል ዳንኤል እንደ ተናገሩት ከኾነ፣ ጉዳዩ “በጣም አሳዛኝና አሳሳቢ ነው። በቀጥታ በክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ላይ በትምህርት፣ ስብከትና አመራር ላይ የሚሳተፉትን በርካታ አገልጋዮች ለመድረስ፣ ያለው እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ እነሱ በሚረዷቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጭምር ማስተማርን ልናስብበት ይገባል”[152]

[152] ሰብለ ወንጌል ዳንኤል፣ ቃለ ምልልስ፣ ዐዲስ አበባ፣ መጋቢት 2004 ዓ.ም፣ በጸሐፊው እጅ የሚገኝ ማስታወሻ።





## 4.6 ትኩረት ለዕቅበተ እምነት

ዕቅበተ እምነትን (በቁሙ እምነትን መጠበቅ) እንደ አገልግሎታችን አካል እንጂ ለተወሰኑ ጥቂት ግለ ሰቦች የተሰጠ “ዕዳ” አድርገን መተው አይገባንም። በሌላ በኩል፣ ተግባራችን እሳት ለማጥፋት የመረባረብ ዓይነት ብቻ መኾን የለበትም። ችግሮች በተፈጠሩ ጊዜ ከመንጫጫት ያለፈ ተግባራዊና ዝግጁነትን ማዕከል ያደረገ ሥራን ማጠናከር ይኖርብናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ መከረው፣ መልካሙን ከክፉ ነጥለው የሚያዩ ዐይኖች በቤተ ክርስቲያን አሉ።

እምነት በመመከት አንጻር ያለብንን ድንክዬነት የሚያሳይ አንድ ነጥብ ማንሣት ይቻላል። እሱም የባህላችንን ዝግነት ይመለከታል። ጸሐፊው ከልጅነቱ ጀምሮ “አትመራመሩ” የተሰኘ ግዝት ሲሰማ ነው ያደገው። በርካታ ክርስቲያኖች የዚህ *መስፈራርቾ* ቀንበር ሥር እንደሚገኙም የታወቀ ነው። *“ወኵሉ አመክሩ፤ ወዘሠናይ አጽንዑ—ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ”* (1ተሰ. 5፥21)[153] የተሰኘው ኀይለ ቃል ከቤተ እግዚአብሔር ደጃፍና ከምእመናን ልቡና እንዴት ሊርቅ እንደ ቻለ ጸሐፊው ዘወትር ይጠይቃል። ይህ ምክር በቅዱሱ መጽሐፍ አይደለም ወይ የተጻፈው? ይህ ኀይለ ቃል መገኘት ያለበት የት ነበር? ጸሐፊው ይህን ጥቅስ በውብ ግርማው በአደባባይ ተቀርፆ ያገኘው በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም መግቢያ ደጃፍ ላይ ብቻ ነበር።

እምነትን መጠበቅ ዛሬ አስፈላጊ የኾነውን ያህል በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ አስፈላጊ ነበር። የወንጌል እምነትን አስመልክቶ ሐዋርያት ከማያምኑ ሰዎች ጋር ሳይቀር የተፋፋመ ክርክር ይገጥሙ እንደ ነበር የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በግልጽ ይነግረናል (የሐዋ. 17፥2-4፤ 19፥8-10)። በተጨማሪ “ደግሞ አብዛኛዎቹ የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተዘጋጁት በአንድ ወይም በሌላ የታወቀ ዕቅበተ እምነታዊ ሰበብ ነበር። የተጻፉትም የአንዱን ወይም የሌላውን

[153] በተጨማሪ በሐዋ. 17፥11፤ ኤፌ. 5፥10፤ ፊል. 1፥10፤ ራእ. 2፥2 የመሳሰሉትን ክፍሎች ይመለከቷል።

ክርስቲያን ማኅበር እምነት ለማጽናት ወይም ወንጌልን አስመልክቶ የተነሣ ማንኛውንም ዐይነት ጥያቄ ግልጽ ለማድረግ ሲባል ነበር።"[154] ዛሬም ይኸው ኀላፊነት ችላ ሊባል አይገባም።

ዕቅበተ እምነት የጥቂት ወገኖች ተግባር ሳይኾን የመላው ክርስቲያን ሕዝብ ኀላፊነት መኾኑ መታወቅ አለበት። ይህ ሊሳካ የሚችለው ምእመናን በክርስትና እምነታቸው የማይናወጡና እውነትን ጠንቅቀው የተገነዘቡ እንደ ኾነ ነው። የትኛውንም ትምህርትና ልምምድ በቃለ እግዚአብሔር አንጥረው ለመመልከት፣ እውነትን ለመቀበልና "ፍጹም የኾነውን ነገር ምን እንደኾነ" ፈትነው ለማወቅ በአዕምሯቸው መታደስ የተለወጡ (ሮሜ. 12፥2) ፈታሾችና አበጣሪዎች (*critical thinkers*) እንዲኾኑ ማዘጋጀትም የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ነው።

አዎ፣ ጠርጣራነት ዐመፃ ነው፣ መጠየቅና መመርመር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነጻነት አለው። የሚሰማውንና የሚያየውን ሁሉ ዘግኖ "አሜን፣ አሜን" እያለ ወደ ቤቱ የሚመለስ ሳይኾን፣ በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱሱ ቅባት ፈትኖ የሚማር ሕዝብ ነው—የእግዚአብሔር ሕዝብ። ይህን ዐይነት መኅበረ ሰብ ለማየት በቅዱስ ቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነገሮችን የሚፈትሽ፣ የሚፈትን አበጥሮ የሚያይና የሚሻለውን የሚመርጥ ምእመን ማዘጋጀትን ይጠይቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ይጸልያል፤ *"ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ምልቶባችሁ፥ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለነውር እንድትኾኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ፥ ፍቅራችሁ በዕውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ"* (ፊል. 1፥9-11)።

እምነታችን መሠረቱ ሰማይ ነው። *"ከሰማይ ከመጣው"* ፈቀቅ አንልም (ዕብ. 12፥25) የምንለው፣ እምነታችንን *"ከሰማይ የወረደው"* (ዮሐ. 3፥13) ስለ ተከለው ነው። *"ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው"* (ኤፌ. 4፥10)። ይህ የጠራ እውነት ነው፤ ነገር ግን ተፃራሪው በዝቷልና ለእኛ ለክርስቲያኖች የተሰጠን ማሳሰቢያ ብርቱ ነው። *"ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ኾነው እንደኾነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና"* (1ዮሐ. 4፥1) ተብለንስ የለም ወይ? ስለዚህ ዕቅበተ ወንጌል የክርስቲያኖች ሁሉ ኀላፊነት መኾኑን አጽንዖት እንሰጣለን።

[154] C. H. Pinnock, "Apolegetics," in *New Dictionary*, 36.





ነገር ግን ክርስቲያኖች ሁሉ እምነታቸውን የመጠበቅ ኀላፊነት ቢኖርባቸውም እንኳ፣ ይህን ኀላፊነት በተለየ መንገድ የሚወጡ መምህራንና ጸሐፊያን ደግሞ ያስፈልጉናል። ስለዚህ ያሉትን ማበረታታት ሌሎች እንዲነሡም መጸለይ አለብን። ለዚህ ሥራ ትኩረት መስጠት፣ ማበረተታትና ድጋፍ ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት መኾኑ መዘንጋት የለበትም።

ከዚህ አንጻር ዛሬ የሚታየው ነገር አሳዛኝ አይመስላችሁም? ስንትና ስንት እንቶ ፈንቶ በወንጌል ስም ጎዳናውን ሲያጥለቀልቅ ማን ምላሽ ሰጠ? ምን ያህልስ ተጋፈጥናቸው? ፈጽሞ ምላሽ አልተሰጠም ለማለት ሳይኾን፣ ከችግሩ ስፋት አንጻር መደረግ የነበረበትን ያህል አልተደረገም ለማለት ነው። በዝንጋኤያችን ምክንያት በተኩላዎች ተነድተው የተበሉብንስ በጎች ስንት ይኾኑ? የበግ ለምድ ለብሰው በመካከላችን የገቡት ተኩላዎችስ ምን ያህል ይኾኑ?

በአጠቃላይ ወንጌልን ከማመንና ከመስበክ ባልተናነሰ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያስተነትኑ ሐታትያን ያስፈልጉናል። ክርስቲያናዊ ዕድገትና የአገልግሎት ስኬት መለኪያ አለው ከተባለ፣ እውነት ሳይበላሽ፣ ሳይሸቀጥና ሳይበረዝ በዘላቂነት መቀጠል በመቻሉ መኾን አለበት። ይህን ለማስጠበቅ የክርስትና እውነትን በብቃት የሚያስተምሩ መምህራን የሚያስፈልጉንን ያህል፣ በወንጌል እውነት ላይ የሚቃጣውን ማንኛውንም ዐይነት ስሕተት የሚመክቱና የወንጌልን ሐሳብ በእኛው ዐውድ የሚያስተነትኑ የነገረ መለኮት ቀማርያን እንደሚያስፈልጉን ለአፍታም መዘንጋት አይገባም።

## 4.7 *ጉባኤያትና ፋይዳዎቻቸው ላይ ክለሳ ማድረግ*

ቤተ ክርስቲያን በተፈጥሮዋ ሕያው የጌታ ማኅበር እንደ መኾኗ *"በጉባኤም በየቤቱም"* (ሐዋ. 20፥20) የምትሰበሰብ ኅብረት (1ቆሮ. 11፥17፤ 14፥26) ኾና መታየቷ "የተፈጥሮዋ" ነው። ስለዚህ መሰብሰቧ የሚበረታታ እንጂ እንደ ችግር የሚቈጠር አይደለም። ታሪኳ የሚነግረንም በስደትና መከራ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ከሚገጥሟት ችግሮች መካከል አንዱ የመሰብሰብ ፍላጎቷ አለመሟላት ነው። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን የምትሰበሰብ የጌታ ማኅበር ናት። ነገር ግን ስብሰባዋ ዝም ብሎ መከማቸት አይደለም፤ የራሱን ዓላማና ፋይዳዎች የተሸከመ መኾኑ ይታወቃል። ስለዚህ ጉባኤያት መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚካሄዱ መጠየቅ አለበት።

በጉባኤ ልንጠመድባቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል አንዱ ለማኅበሩ መታነጽ የሚያገለግሉ መደበኛና ጠንካራ መንፈሳዊ ትምህርቶች መስጠት ነው። በዚህ ረገድ ጉድለት እንደሚታይ ደግሞ ግልጽ ነው። ወንድም ምኒልክ እንዳሉት፣ "በአብያተ ክርስቲያናት አከባቢ 'እንጭጭ መንፈሳዊነት' እንዲከሠት ካደረጉ አሉታዊ ምክንያቶች አንዱ መደበኛ ትምህርቶች አለመኖሩ ነው። ጠንካራ መንፈሳዊ ትምህርቶች እንደ ጦር በሚፈሩበት ሀገር መንፈሳዊ ዕድገትና ብስለት ሊኖር አይችልም።"[155]

ለመላው የእግዚአብሔር ቃልና አስተምህሮዎቹ ተገቢ ትኩረት መስጠት ብቻ ሳይኾን ለትምህርታችንም መሠረት መኾናቸውን ማወቅ ይኖርብናል። መላው የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ለትምህርት ለተግሣጽና በጽድቅ ላለው ምክር ጠቃሚ ነው (ማቴ. 4፥4፤ 2ጢሞ. 3፥16-17)።

በዚህ ረገድ ጉልህ ጥያቄዎች የሚያቃጭሉብን ይመስለኛል። እግዚአብሔርን የምንወድ ከኾነ አስተምህሮን በሚመለከት ምን ዐይነት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል? ባልንጀሮቻችንንም የምንወዳቸው ከኾነ፣ ትክክለኛና ጤናማ የኾነውን

[155] ምኒልክ፣ "ወንጌላውያን"፣ 21።





*ዶክትሪን* እናስተምራቸው ዘንድ ምን ያህል እንጠነቀቅ ይኾን? ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በሰጠው ምክር *"አንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እንዳያስተምሩና ወደ ተረት መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ ልታዝዛቸው በኤፌሶን ትቀመጥ ዘንድ ለመንሁህ"* (1ጢሞ 1፥3) ይለዋል። ይህ ማለት ከትክክለኛው አስተምህሮ ውጭ ሌላ ትምህርት እንዳይተላለፍ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እየሰጠው ነበር ማለት ነው።

በኛ ዘመን በየአጥቢያው የሚካሄዱት የተለመዱ መርሐ ግብሮች ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው የሚቀር አይመስልም። ለምሳሌ ያህል፣ ከሞቅታ *ኮንፈረንሶች* በተጨማሪ ትምህርታዊ ጉባኤያትን ማጠናከር ተገቢ ብቻ ሳይኾን ሳይውል ሳያድር ቤተ ክርስቲያን ልትረባረብበት የሚገባ ተግባሯ ነው። ዡማ ጉባኤ ከስደቱ ዘመን ማብቃት ጋር ተያይዞ ቤተ ክርስቲያን ወደ አደባባይ በመውጣት ደስ የተሰኘችበት፣ ወንጌልን የሰበከችበት፣ እርስ በርስ ለመጽናናትና ለምስጋና የተሰበሰበችበት እንደ ነበር ይታወቃል፤ እናም በጊዜው እነዚያ ስብሰባዎችዋ መልካም ብቻ ሳይኾኑ የግድ አስፈላጊም ነበሩ።

አሳዛኙ ነገር ግን፣ ቤተ ክርስቲያን በዚያ ጊዜ ወደ አደባባይ ስብሰባ እንደ ወጣች በዚያው ቀረች፤ ወደ ትምህርት ብዙም የተመለሰች አትመስልም። አንድ አገልጋይ በጥናታችን ጊዜ ከሌላ አገልጋይ እንደ ሰማው በማውሳት የተናገረው ምጸት ችግሩን በደንብ ይገልጸዋል፤

> ኮንፈረንስ የሚሉት ነገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመኑን ለቀጡበት የትምህርት ችጋር ማስታገሻ የሚያቀርቡት ድግስ ኾኗል። ዓመቱን ሙሉ ሕዝቡን በራብ አለንጋ ሲጠብሱ ይከርሙና 'ለድሀው ወይን ጠጅ ስጡት' እንደ ተባለው በሦስት ቀን የስብሰባ ድግስ ምእመኑን የሚያስከሩበት ፌሽታ ይመስላል፤ ብሏል።[156]

እንግዲያውስ ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ቃለ እግዚአብሔርን በሚገባ ለማጥናት እንዲችል ኹኔታውን ማመቻቸት ለነገ የሚባል ሥራ አይደለም። ወገኖች ሆይ?

[156] ኢዮብ ደምሴ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ዐዲስ አበባ፣ የካቲት 10 ቀን 2004 ዓ.ም፣ በጸሐፊው እጅ የሚገኝ ማስታወሻ።

ልዩ ትምህርት በዙሪያችን እየጋለበና በርካታ የምናውቃቸው ወገኖችም ገብተው ሲንቧቹ እያየንና እየሰማን ምን አገባኝ ማለት እንችላለንን? አይገባም። የኾነ ነገር መደረግ አለበት። ነገር ግን ፍላጎታችንና ጥረታችን በክርስቶስ ያሉ ወገኖቻችንን በጌታ ለማነጽና የሳቱትንም ለማቅናት መኾን እንደሚገባ መዘንጋት የለብንም (1ቆሮ. 14፥26፤ 8፥1)።

ከዓመት እስከ ዓመት በተጋባዥ አገልጋይ ብቻ መንጋውን ለመመገብ ማሰብ ተገቢ አይደለም። ማኅበረ ምእመኑ ያለበትን አጠቃላይ ኹኔታ በመመልከት ክብካቤና ምሪት [መሰጠት አለበት] … መላው ሰንበት በደርሶ ሂያጅ አገልጋይ ተጣቦስ እንዴት ይዘለቃል? አንዲት ሰብከት ይዞ ሀገር ካገር መዞርስ ለመንጋው ድርቆሽ ከሚመግብ እረኛ በምን ይለያል?

በጉባኤ ሊሰጡ ከሚገባቸው ትምህርቶች አኳያ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያነት ምእመናቸውንና ያሉበትን ማኅበረ ሰብ ፍላጎቶች ያማከሉ መርሐ ግብሮችን መንደፍና ማካተት ይኖርባቸዋል። ቀደም ሲል የጠቀስናቸው አንቶኒ ይህን አስመልክቶ ሰፋ ያለ ትንታኔ ያቀርባሉ፤ ትንታኔያቸውን በዚህ አንቀጽ መጠቅለል ይቻላል፤ የጀመርነውን ሐሳብም ያጠናክርልናል፤

> የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ክርስቲያናዊ የትምህርት አገልግሎት ሁሉን አቀፍና ሚዛናዊ ሊኾን ይገባዋል። የኅብረተ ሰቡን የወንጌል ስርጭት ፍላጎት እንዲሁም የአጥቢያ ምእመናኑን የእድገት መሻት ከግምት ውስጥ ያስገባ መኾን ይኖርበታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካኼዱ ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮች ማለትም እንደ መዝሙር፣ የወንጌል ተልእኮ፣ ወንጌል ስርጭት፣ የደቀ መዝሙር ሕይወት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የጸሎት ቡድኖች፣ የእርዳታ አገልግሎት፣ የቤት ኅብረት፣ የልጆች አገልግሎት፣ የወጣቶች አገልግሎት፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ለጐልማሳ አባላት የሚቀርቡ የአገልግሎት ዓይነቶች መካተታቸው ሊታወስ ይገባል።[157]

[157] አንቶኒ፣ *የአገልግሎት መሠረቶች*፣ 23።





## 4.8 *ኅብረቱ[158] ቢያብር ያሞጣ ይኾን?*

የአስተምህሮ መዛነፎችን እንዲያይ ተጨማሪ ኀላፊነት ለኅብረቱ መስጠት የሚቻልበት አግባብ ስለ መኖሩ በርግጠኛነት መናገር ባይቻልም፣ አማራጭ ሐሳብ ሳይኾን ግን አይቀርም።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት (ECFE) በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት በርካታ ቤተ እምነቶችን በሥሩ አካቷል። እነዚህ ቤተ እምነቶች በኅብረቱ ሲታቀፉ በዝርዝር አስተምህሯቸው ሙሉ በሙሉ ወጥ አንድነት ስላላቸው አለመኾኑ ግልጽ ነው። ይኹን እንጂ መሠረታዊ በኾኑ የክርስትና ዐበይት አስተምህሮዎቻቸው ላይ ግን የማይናወጥ አንድነት በመያዝ ነው ኅብረታቸው የተመሠረተው፤ ይህ መልካም፣ አስደሳችና በሌሎች ሀገሮች ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አርኣያ ሊኾን የሚችል ተመክሮ እንደ ኾነ ሲነገር ቈይቷል።[159] ኅብረቱ፣ የራሱ ውሱንነቶች እንዳሉበት ግልጽ ቢኾንም፣ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ክርስትና ታሪክ ውስጥ ሊፋቅ የማይችል ጕልሕ አሻራውን ማስቀመጥ እንደ ቻለም ይነገራል።

ነገር ግን፣ ኅብረቱ በወንጌላውያን አስተምህሮ አንጻር የሚከሠቱ የስሕተት ትምህርቶችና ኑፋቄዎችን አስመልክቶ ምን ሊያደርግ እንደሚችል የሚታወቅ አይመስልም። ኅብረቱ ካለው ከፍተኛ ተደማጭነት የተነሣ መሰል ተግባራትን እንዲያከናውን የሚጠብቁ ምእመናን ብዙ ናቸው። ይህን ጥናት በምሠራበት ወቅት ያነጋገርኋቸው ምእመናንና አገልጋዮች እንኳ፣ በአንድም ይሁን በሌላ

[158] የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትን (Evangelical Christian Fellowship of Ethiopia-ECFE) ለማለት ነው።

[159] በነገራችን ላይ፣ ይህ ጥናት በተጀመረ ሰሞን (ማለትም፣ 2003 ዓ.ም.)፣ ይህን ንዑስ ርእስ አስመልክቶ የነበሩን መረጃዎች፣ ይህ መጽሐፍ በዚህ መልኩ ሲሰናዳ (2006 ዓ.ም.) ለውጥ ገጥሟቸዋል። ይህም ማለት፣ ሁለት ታላላቅ ወንጌላውያን ቤተ እምነቶች ከኅብረቱ በይፋ መልቀቃቸውን ይመለከታል። እንግዲህ፣ በዚህ ንዑስ ርእስ ሥር የቀረበው ሐሳብ ሲሰነዘር እነርሱንም ባካተተ መልኩ የነበረ ቢኾንም ለውጡን ተከትሎ ሐሳቡ አልተቀየረም። ምክንያቱ ደግሞ፣ እየተመለከትነው ባለው ሐሳብ ላይ፣ እነዚህ ታላላቅ ቤተ እምነቶች ሊያበረክቱ ከሚችሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመነሣት ብቻ ሳይኾን፣ ወደ ኅብረቱ መመለሳቸው አይቀርም ከሚል ጽኑ ተስፋ ጭምር በመነሣት ማቅረቡን ከግንዛቤ እንዲገባለት ጸሐፊው ይጠይቃል።

መልክ፣ ይኸንን ሐሳብ አንጸባርቀዋል። ውይይታችን ጦፎ ባለበት ጊዜ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ቍጭት ከተሰማቸው መካከል፣ “ይህ ሁሉ ነገር ሲኾን ኅብረቱ ምን ይሠራል?” በማለት የጠየቁ ወገኖች ነበሩ። በኅብረቱ የአመራር አካል ውስጥ ካለለገሉ መሪዎች መካከል አንዱ መጋቢ ኅሩይ ጽጌ ይህንኑ ሐሳብ ይጋራሉ፤

> በከተማችንና በሀገሪቱ ስለሚታዩ በርካታ መንፈሳዊ ችግሮች፣ የአስተምህሮ ውኹንብሮች፣ በተለይም ምእመናንን በልዩ ልዩ ውሽት፣ ማታለል፣ ማስመሰል፣ መገለጥ የሚያናውጡትን እያየ ኅብረቱ ለምን ዝም ይላል? የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ምእመናን ኅብረቱን እንደ ትልቅ ባለ ዐደራና ተሰሚነት ያለው፣ ተጠያቂነት ያለበት አካል አድርገው ይመለከቱታል፤ እውነትም ነው[160] ይላሉ።

የመጋቢ ኅሩይ ጥናታዊ ወረቀት ኅብረቱ ባዘጋጀው ሴሚናር ላይ የቀረበ ነበር። ኅብረቱ ሊያደርገው ሲገባ አላደረገም በማለት የተወቀሰበትን ነገር “እውነት ነው” በማለት ተቀብለውታል። ኅብረቱ ይህን ወቀሳ ለማስወገድ ብቻ ሳይኾን ሊያደርገው የሚገባው ተግባሩ ከመኾኑም አንጻር እስከ አሁን ምን ሠርቶ ይኾን? ያሰኛል። ዛሬም “ኅብረቱ ለምን ዝም ይላል?” እየተባለ አይደለምን?

ስለዚህ ለኅብረቱ ተጨማሪ ኀላፊነት በመስጠት ራሱን የቻለ የነገረ መለኮትና አስተምህሮ አካል እንዲያደራጅ ማድረግ መፍትሔ ሊኾን ይችላል። አንድ የክርስቲያናዊ አስተምህሮ መማከርት ጉባኤ (ካውንስል) ማቋቋም አይቻልም ወይ?

ይህም የማይሳካ ከኾነ፣ ራሱን የቻለና ከየቤተ እምነቱ በውክልና የተውጣጡ ወገኖች የሚወከሉበት አካል ማቋቋም ይበጅ ይኾንን? ይህ የማይሠራ መስሎ የሚታይ ከኾነ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች የሚማሩባቸውና የሚሠለጥኑባቸው የነገረ መለኮት ትምህርት ተቋማት የመሠረቱትን ኅብረት የበለጠ በማጠናከር፣

[160] ኅሩይ ጽጌ፣ “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም እንዴት ሊጠናና ሊመረመር ይገባል?” በየመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፣ 29።





እንዲሁም ተቋማዊ ድጋፍ በመስጠት ይህን ተግባር እንዲወጣ ማስቻል አማራጭ ይኾናል። ይህ ሲባል አስተምህሯዊ ውሳኔዎችን ይስጡ ማለት አይደለም። ይልቅ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረቱ ሥራዎችን ውጤት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያቀርብ ለማስቻል ማለት ነው።

በአጠቃላይ በግለ ሰብ ደረጃ ወይም በየቤተ እምነቱ በኩል ብቻ ከሚደረጉ መፍጨርጨሮች በላይ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በጋራ የሚሠሩባቸው ጉዳዮች መኖራቸው የታመነ ነው። ከነዚህ መካከል የአስተምህሮ ነገር ትኵረት ባይነፈገው መልካም ነው።

መሪዎችና አገልጋዮችም የተጠራንበትን መጠራት፣ የተቀበልነውን ሰማያዊ ተልእኮ ያለንበትን የግንኙነት ኹኔታ የአስተምህሯችንን ጥራት የተመከሯችንን ነባራዊነት የዕድገታችንን ደረጃና የፍሬያማነታችንን ልክ በመፈተሽ መንፈሳዊ ተሐድሶን መሻት ይኖርብናል። መንፈሳዊ ተሐድሶን ከሕያው እግዚአብሔር ዘንድ የምንቀበልበትን ጊዜ ለማፋጠንም ኾነ ለማዘግየት ምክንያቱ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቢኾንም የመሪዎች ድርሻ ግን ላቅ ያለ ነው።

ከዚህ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረታቸውን ከምንጊዜውም የበለጠ አጠንክረው በተሐድሶ መንፈስ መንቀሳቀስ ለነገ የሚተላለፍ ተግባር አይደለም። የኅብረቱን አቅም ለማሳደግ መደረግ የሚገባው ሁሉ መደረግ ይገባዋል። የኅብረቱ መድረክ አብያተ ክርስቲያናት ችግሮቻቸውን በውስጥ የሚፈቱበትና የሚተራረሙበት እንዲሁም በቅንነትና በየውሃት መንፈስ የሚተናነጹበት እንዲኾን ተገቢው ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

አንድ ነገር ግን ፈጽሞ መዘንጋት የለበትም። ኅብረታችንን ማጠናከር አለብን ሲባል፣ ኅብረታችን በክርስቶስ መካከለኛነት ላይ የጠነከረ መኾን እንዳለበት አጽንዖት በመስጠት ነው፤ ነገር ግን የእውነትን “በግ” በመሠዊያ ላይ አቅርበን ልናቆመው የምንሞክረው ኅብረትና አንድነት ሊኖረን እንደማይችል መገንዘብ ይኖርብናል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንድነቷን ጠብቃ በጤናማነት የቈየችው በአስተምህሮዋ ትክክለኛነትና ይህንኑ ትምህርትም ለምእመናኑ በሙሉ

በማስተላለፏ ነበር (ሐዋ. 2፥42)። ከዚህ አንጻር የእኛም ዘመን ክርስቲያኖች ተመሳሳይ ዐቋም ልንይዝ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረቱ፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥሪና ምግባሯን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ የሚችሉ ትምህርቶች፣ ልምምዶችና አካሄዶችን ለማጥራትና ከመሥመር እንዳትወጣ ለማድረግ እንዲቻል እንዳስፈላጊነቱ መሪዎቿንና አገልጋዮቿን እያሰባሰበ፣ የጸሎት፣ የሥልጠና፣ የምክክርና የመተናነጽ መድረኮች ማዘጋጀትና መተግበር ቢችል የተሻለ ነገር ማስገኘት ይቻላል። ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አንድነትና ለተገልጋዩ ሕዝብ ሕይወት ጤንነት ሲባል በምክክርና በልበ ሰፊነት በእውነት ላይ የተመሠረተ የመቻቻል መርሕ መከተሉም ጠቃሚ ነው።



# ክፍል ዐምስት

## መጠቃለያ፣ ጥቆማና ተስፋ

# ሀሃሣት

# 5. ማጠቃለያ፣ ቍጭትና ተስፋ

## 5.1 *ማጠቃለያ*

እስከ አሁን በተመለከትናቸው በነዚህ ጥቂት ገጾች ውስጥ፣ በዘመናችን ያለችውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን (ከአስተምህሮና ተያያዥ ጉዳዮች አኳያ) በመጠኑ ለመቃኘት ሞክረናል፤ ለጸሎት ለውይይት፣ ቀጣይ ጥናት ለማድረግና ርምጃ ለመውሰድ ሊያግዙ የሚችሉ ሐሳቦች እንዲሁም ጥቂት መፍትሔዎች ቀርበዋል ብለንም እናስባለን።

ለማጠቃለል ግን ይህን አንድ ነገር አጽንዖት እንሰጥበታለን፤ መንፈሳዊ ትምህርትና ክርስቲያናዊ አስተንትኖት ቸል ሊባል አይገባውም። ትክክለኛውን ትምህርት መከተል ከኀጢአት አርነት የሚያወጣን ሲኾን፣ (ዐውቀንም ኾነ ሳናውቅ) የተሳሳተ ትምህርት መያዝ በበኩሉ አምልኳችንን ከንቱ ከማድረግም ዐልፎ ተርፎ ከእምነት እንድንወድቅና ከእግዚአብሔር እንድንለይ ሊያደርገን ይችላል።

በተስፋ ቃል እንደ ተጠሩ የዐዲስ ኪዳን ምእመናን ኀላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት ይኖርብናል። ክርስቲያኖች በእምነት ሊያንጹ በማይችሉ ይልቁንም ውዝግብና ንትርክን ሊያባብሱ በሚችሉ የማይረቡ ጥያቄዎችና ሙግቶች ላይ

በመረባረብ ሕይወታችንን ስናባክን መገኘት አይገባንም (1ጢሞ. 1፥4፤ 6፥3-4፤ 2ጢሞ. 2፥23፤ ቲቶ 3፥9፤ ፊል. 2፥14)። የከበረ ሥራ አለብን።

በሌላ በኩል ጥሪያችን ለሰዎች ንቃተ ኅሊና ለመስጠት ወይም የቃላት ትንንቅ ለመፍጠር አይደለም። መሻታችን በጌታ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የኾኑትን ለማነጽና ለማሳደግ መኾኑን ማስተዋል ይኖርብናል (1ቆሮ. 14፥26፤ 8፥1)። ይህን ማለታችን ለጸናው እውነት "መጋደል ይገባናል" (ይሁዳ 3) መባላችንን ለማስተባበል አይደለም። በአስፈላጊው ቦታና ጊዜ ይህን ማድረግም የጥሪው አካል መኾኑን አንዘነጋም።

የዚህ ጥረታችን ግብ የመንግሥቱ ናፍቆትና የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ነው። ከክርስቶስ ኢየሱስ መንግሥት የበለጠ ራእይ የለንምና፣ ስለ እርሱ ክብር እንድንኾንለት የሚሻውን ያደርገን ዘንድ መትጋት አማራጭ አይደለም።

"የመንፈሳዊ ራእይ ማእከል የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። የፈረሰው እንዲጠገን፣ ያልተያዘው መሬት እንዲያዝ ባንዲራው ባልተተከለበት እንዲተከል፣ ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክ፣ ምላስ ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ኾነ እንዲመሰክር ነው።"[161]

መንግሥተ እግዚአብሔር ማእከል ያልኾነበት ራእይ የጥቅመ ሰናዖር መንፈስ ያረብብበታል። *"ስማችንን እናስጠራ"* (ዘፍ. 11) የሚባልበት ትንንቅና ትጋት ይደራበታል። ሰብአዊ ትዕቢት ደርቡን እያሳመረ ወደ ላይ ቢወጣም፣ መለኮት ተቈጥቶ "ይወርድበታል"። ማእከሉ እግዚአብሔር የኾነበት መንፈሳዊ ራእይ ግን ለእግዚአብሔር ክብርን ለክርስቶስ አካልም መታነጽን ያመጣል። በክብር የተቀበልነው እምነታችን ይህን በአንክሮ ያስገነዝበናል። እምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ አለው፤ እርሱም ባለቤቱ መድኅን ዓለም ክርስቶስ ነው (ዕብ. 12፥2)።

---

[161] ንጉሤ ቡልቻ፣ "እስር ቤቱን ስበር፣ ከንፍ ስጠኝ ልብረር፣" በ *መስተአየት* ውስጥ (ዐዲስ አበባ፡- ሊሺንግ ትሩዝ አገልግሎት፣ 2002 ዓ.ም.) 37።





ይህን ዐደራ ተወጥተው የሄዱ "እንደ ደመና" የከበቡን (ዕብ. 12፥1) "ብዙ ምስክሮች" (1ጢሞ. 6፥12) ቀድመውን ዐልፈዋል (ዕብ. 2፥3)።

የተመረጥነውና የተጠራነው በእግዚአብሔር በመኾኑ ጉዳይ ባንከራከርም፣ የወንጌል እምነት ወደ እኛ ዘመን የደረሰው በዐደራም ጭምር እንደ ኾነ መታሰብ አለበት። ከጌታ የተቀበሉትን "ያስተላለፉን" (ሉቃ. 1፥1-2) ቀዳሚዎች ነበሩን። *"እኔ ደግሞ የተቀበልኩትን ... አሳልፌ ሰጠኋችሁ"* (1ቆሮ. 15፥3) ይሉት ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። "ዐደራ ጥብቅ፤ ሰማይ ሩቅ" እንዲሉ፣ የተቀበሉትን ጠብቆ ለተከታዩ አማኝ ትውልድ ማስረከብም ከእኛ የሚጠበቅ ታላቅ ኀላፊነት የመኾኑ ጉዳይ ተወስቷል። ይህ ኀላፊነት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የተባረከ ተግባር ነውና እንረባረብበት።

የኾነ ኾኖ፣ ዛሬ ያለንበት ኹኔታ "አይበርደኝ፣ አይሞቀኝ" የምንለው ዐይነት አይመስልም። ወዳጆች ሆይ፣ የኾነ "ክፉ ወበቅ" አይሰማችሁም? የኾኑ የትምህርት ብናኞች "ሊያስነጥሱን" አልጀመሩን ይኾን? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለችበት ኹኔታ አንዳንድ ወገኖች ከበሮ እንደሚደልቁለት "የታላቅ ጉብኝት ጊዜ" ይኾን? የምሩን እንነጋገር ከተባለ፣ በውጪያዊና አማላይ ገጽታዎቻችን ራሳችንን መሸንገል ያለብን ጊዜ አይመስልም።

ይህን የምታነብቡ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምእመናን እንደምትገነዘቡት መራር በኾኑ ውድቀቶችና ዝብርቅርቅ መካከል መገኘታችን "ሳይታለም የተፈታ" ነው። ይህ ኹኔታችንም ከበርካታ ወገኖች አንደበት የሚደመጥ ከብርዓቸውም የሚነበብ ጉዳይ ኾኗል። ለዚህም ይመስላል በየቦታውና በየኹኔታው የንስሐና የተሐድሶ ጥሪዎች ሲደረጉ የምንሰማው። ለማንኛውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለውጥና ተሐድሶ ያስፈልጋታል የሚለውን ጥሪና ሐሳብ ሊገዳደር የሚችል ማሳያ አልተገኘም። ቢያስፈልግ በርካታ ዋቢ መጥቀስ ይቻላል። ያለንበትን ኹኔታ አስመልክተው፣ አቶ ሽፈራው ወልደ ሚካኤል በአንድ ወቅት፣ "እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ክርስቲያን መሪዎች ምን ይላል?" በሚል መሪ ሐሳብ በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ የመግቢያ ንግግር አድርገው ነበር። በጊዜው ካቀረቡት ንግግር ውስጥ እስከ

አሁን ከልቦናዬ ተቀርፆ የቀረውን አንድ ነገር እዚህ መጥቀሱ አግባብ ይመስለኛል። እንዲህ ነበር ያሉት፡-

> የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ቅጥሮቿ ፈራርሰው እጅግ በሚያሳዝን፣ ነፍስን በሚያስቈዝም፣ ጆሮን ጭው በሚያደርግ፣ ግራ በሚያጋባ አሠቃቂ ኹኔታ ውስጥ ትገኛለች። ዕድገት አለ፤ ግን ቡፍታ ነው። ድምቀት አለ፤ ግን በብዙ መልኩ ውጫዊ ነው። መሳሳም አለ ግን ልባዊ ያይደለ አፋዊ ነው። ለእግዚአብሔር መገዛት አለ፤ ግን እኔ ያልኩት እስካልተነካ ብቻ ነው። አምልኮ አለ፤ ግን ያለ እግዚአብሔር መፍራት ነው። እምነት አለ፤ ግን በሕይወት ያልታጀበ ነው።[162]

በርግጥ አባባላቸው አሳዛኝ አገላለጥ ነው። የበለጠ የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ ሰውዬው ይህን ከተናገሩ ዐሥር ዓመታት በኋላ ያለው እውነታ ከእርሳቸው አባባል ወደ ከፋ ኹኔታ መድረሱ ይመስለኛል። ታዲያ በእንዲህ ዐይነት ኹኔታ ውስጥ ተሸጉጠን ያለን ክርስቲያኖች ምን ማድረግ ነው ያለብን? አንዳንድ ወገኖች እንዳደረጉት ተስፋ ቈርጠን እንቀመጥ? ዝም ብለን በአርምሞ ጥላ ሥር እናድፍጥ? ነገሮች ስለተበለሻሹ ከአምላካችን እንሽሽ? ኧረ፣ በፍጹም!

በርግጥ መልካም ነገሮች የሉም ማለት አይደለም፤ ሞልተዋል። ኾኖም ግን በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ታሪክ “ድኅረ ነጻነት” በተሰኘው ዘመን በርካታ አዎንታዊ ተግባራት የተከወኑበትን ያህል፣ ቀላል የማይባሉ አሳሳቢ ችግሮችም ተከሥተውበታል። የሚያሳስበንም ይኸው ነው፤ ያሳለፍናቸው እነዚህ ሁለት ዐሠርት ዓመታት ከነበረው የተሻሉ ውጤቶች ይመዘገብባቸው አልነበረም? ወይስ የኾነው ሁሉ ይኾን ዘንድ ይገባው የነበረው ነው? የነበሩት ዕድሎች ከዚህስ በኋላ ይቀጥላሉን? ጸጸት ባይኾንም ከቅን ልቡና የመነጨ ቍጭት አላደረብንም? ያመለጠ ነገር ቢኖርስ?

[162] ሽፈራው ወ/ሚካኤል፣ *“የመግቢያ ንግግር፣” እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ክርስቲያን መሪዎች ምን ይላል?* ግንቦት 1991 ዓ. ም. ዐዲስ አበባ።





## 5.2 ያመለጡ ዕድሎች?

የክርስትና መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ መኾኑ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና የደቀ መዛሙርቱን አርኣያ መከተሉ አልቀርም። ይህ ዓለም ጌታችን ኢየሱስንም ኾነ ሐዋርያቱን እንዳሳደደ ሁሉ በየዘመኑ ክርስቲያኖችን ያሳድዳል። ክርስትና ስለ ወንጌል የሚሰደዱለት እምነት ነው። *“በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ”* (2ጢሞ. 3፥12)።

በክርስቶስ የተመሠረተውና ከዘመናችን የደረሰው ወንጌል በኢትዮጵያችንም ውስጥ የተሰበከው ከብዙ መከራና ስደት ጋር መኾኑ በታሪክ ማኅደር የሰፈረ እውነት ነው። ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እንደ መሰከሩት፣ “የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ታሪክ በስደት ተጀምሮና በስደት ተጕዞ ወደ 21ኛ ክፍለ ዘመን ተሻግሯል።”[163]

በአንጻሩ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ባለፉት ሁለት ዐሥርታት ውስጥ ያገኙት ዕድል በብዙ መንገድ ሲወደስና ሲሞካሽ ኖሯል። እውነት ነው፤ በአሠቃቂ ዕመቃ ተመትቶ ጓዳ ለጓዳ ሲሽሎከሎክ የኖረው የጎዳጣን (አናሳዎች) እምነት በረድኤተ እግዚአብሔር ታግዞ የአደባባይ ዝክርና ክብር ስለ ተሰጠው ዘመኑ ቢመሰገን ላይገርም ይችላል።

ክብር ለእግዚአብሔር ይኹንና፣ ወንጌላዊው ክርስትና በጐዳናዎች፣ በታላላቅ አዳራሾች፣ በየሰፈሩና አካባቢው ወንጌልን የሚሰብክበት ዕድል አግኝቶ ቈይቷል፤ የራሱን የጸሎትና አምልኮ ቦታዎች ማግኘትም ችሏል። እንደሌለ ከመፈረጅ ዐልፎ በሚሊዮኖች የሚቈጠሩ ምእመናን የሚከተሉት መንገድ ለመኾን በቅቷል። ታዲያ ደስታን ማብዛት ይብዛበት!

[163] ተስፋዬ ያዕቆብ፣ “ቀዳሚ ቃል፣”ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)፣ *በዚያን ጊዜ* (ዐዲስ አበባ፣ ኢ.ሙ.ወ.አ.ቤ.ክ.፣ 2002 ዓ.ም.) 3።

በነዚህ ዓመታት፣ ዝማሬው አደባባዩን ሞልቶት፣ ስብከተ ወንጌሉ ጎዳናውን አጥለቅልቆት ተመልክተናል። እልፍ፣ አእላፋት በክርስቶስ በማመን የድኅነት ብርሃን ለማየት በቅተዋል። አብያተ ክርስቲያናት በጌታ ጸጋ እየታነጹ በዝተው ታይተዋል። ስለዚህ፣ በየከተሞችና በየገጠሩ በሺህዎች የሚቈጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ተተክለዋል። እጅግ ብዙ አገልጋዮች በእግዚአብሔር ተጠርተው ራሳቸውን ለወንጌል አገልግሎት ሰጥተዋል። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ተከፍተው በመቶዎች የሚቈጠሩ አገልገዮችን አሠልጥነዋል።

"እግዚአብሔር ምድሪቱን በቅኔና በዜማ አብዝቶ ባርኳል። እጅግ ብዙ የቡድንና የግል ዘማርያን አሉን። ቅኔው ይፈልቃል፤ ዜማው ይጎርፍል። ይህ የበረከት ዐይነተኛ ምልክት ነው።"[164] ከመከራው የተረፉ አባቶችም በትንንሽ ልጆቻቸው አፍ ቃለ እግዚአብሔር ሲነገር የዝማሬና ቅኔ ሀብት ሲፈስስ ለማየት በመብቃታቸው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ታይተዋል። ለምሳሌ ከመጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ መጽሐፍ ውስጥ ይህን አንቀጽ እንመልከት፤

> በመላ ሀገራችን፣ በአንጻራዊነትም ቢኾን፣ ታላቅ የኾነ መንፈሳዊ ተሐድሶና መነቃቃት አይተናል። ወንጌልን በትጋትና በታማኝነት በመስከሩ ምእመናንና አገልጋዮች አማካይነት በክርስቶስ እያመኑ ከዘላለም ሞት የሚያመልጡትን አያሌ ሰዎች ለማየት አምላካችን አድሎናል። በገጠር በከተማ ምድራችን እንደ ገና የምስጋናና የዝማሬ ድምፅ የሚሰማባት ኾናለች። በዚህ መነቃቃት ውስጥ ሕዝቡን ያገለግሉ ዘንድ ጸጋውን አልብሶ ጌታ ለክብሩ ባስነሣቸው የወንጌል አገልጋዮችና ዘማርያን በእጅጉ ተባርከናል። ...[165]

ከዚህም በላይ ሌሎች በርካታ ባርኮቶችን መዘርዘር ይቻላል። ስለዚህ ሁሉ አምላካችንን ማመስገን ይገባናል፤ የዚህ ሁሉ መልካም ስጦታ ባለቤት እግዚአብሔር ነውና፤ ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን!

---

[164] ሺፈራው፣ *የተከፈቱ በሮች*፣ 6።
[165] ተስፋዬ፣ *በዚያን ጊዜ*፣ 132።





ይህ ሁሉ እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች የተሰጣቸውን ብርቅ ዕድል ምን ያህል ተጠቅመውበት እንደ ኾነ መጠየቅ ድፍረት ይኾናልን? ከላይ እንደ ተጠቀሰው፣ የተሠሩትን መልካም ነገሮች መዘርዘር እንደሚቻል ጸሐፊው በሚገባ ይገነዘባል፤ በጣም በርካታ ድሎች ተፈጽመዋል። ሚሊዮኖች የወንጌልን ብሥራት ሰምተው የድኅነትን ብርሃን ማየታቸውንም እያሰበ፣ እንደ እናንተው ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብራል። ግን ዐልፎ፣ ዐልፎ በኅሊናው የሚያቃጭልበት ሙግት ይገጥመዋል። ከእግዚአብሔር ልዕልና አኳያ ሳይኾን፣ ከሰው ኀላፊነት አንጻር ሲያሰላስል፣ "ከዚህ በላይ ሊኾን አይችልም ነበርን?" ሲል ይጠይቃል። ያው ቍጭት መኾኑ ነው። የባከነ ነገር አልነበረም?

ይህን ሳስብ ሳለሁ፣ ባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን የዐፄ ቴዎድሮስን የመቅደላ ስንብት ባሰላሰሉበት የምናብ እይታቸው ካሰፈሩት ስንኞች "እነሆ ሁለቱን በእኛ ዐውድ ለማጠየቅ ይቻል ይኾን?" እልማለሁ።

ቅኔውን ቀደም ብላችሁ ላላነበባችሁት ዐውዱን በመጠኑ ማሳየት ይቻላል። በጀነራል ናፒር የሚመራው የእንግሊዝ ጦር በዐፄ ቴዎድሮስ የታገቱትን እንግሊዛውያን እስረኞች ለማስለቀቅና የታላቋ ብሪታኒያን ክንድ ለቴዎድሮስ ለማሳየት፣ ንጉሡ ወደ ሰፈሩበት መቅደላ ያለ የሌለ ኀይሉን ታጥቆ፣ መጣ።

ከሠራዊቱ የሞተው ወድቆ፣ የቈሰለው ዝሎ፣ የደከመው ሸሽቶ ነበርና ቴዎድሮስ በመጨረሻዋ ሰዓት ከባዕድ ጭፍራ ጋር የተፋጠጡበት ጊዜ ነበር። ለቀውጢ ቀን እንዲኾን ተብሎ የተሠራውና *ሰባስቶፖል* የተባለው መድፍ ወደ ኋላው ተኵሶ ሲያበቃ ራሱም ፈነዳ። ዝነኛው የጦር አዝማች ፊታውራሪ ገብርዬም በእንግሊዝ ጠብ መንጃ አረር ተመትተው የመውደቃቸው መርዶ በንጉሡ ድንኳን ተሰማ። ይባስ ብሎ፣ ናፒር ንጉሡን ማርኮ ለመውሰድ ስለቋመጠ "እጅህን ስጥ" ብሎ ለዐፄው ደብዳቤ ላከባቸው።

ቅኔው የሚያጠነጥነው፣ በዚህ ነገር ሁሉ በፈራረሰባቸው ወቅት፣ ንጉሡ በነበራቸው የስሜት ሕማማትና የቍጭት ንዝረት ላይ ነው። ቴዎድሮስ ዘውድ ከመጫናቸው በፊትም ኾነ በዙፋን ላይ ከወጡ በኋላ ያደረጉት ውጣ ውረድ ቀላል አልነበረም። የከሸፈ ነገር ቢገጥማቸውም እንኳ፣ የተሳካላቸውም ነበር።

ነገር ግን፣ ባለቅኔው፣ በምናቡ ተሳኩ በተባሉት ነገሮች ከመመሰጥ ይልቅ ይኾኑ ዘንድ ይገባቸው በነበሩ ግን ሳይኾኑ በቀሩ ነገሮች እየተቈጨ የተብሰለሰሉበት ቅኔ መኾኑ ነው።

ለማንኛውም፣ ስንኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

*ያለፈ ጥረታችንን ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ፣*
*ከሞከርነው ነገር ይልቅ ያልሞከርነው ነው የሚቈጨኝ።*[166]

የሚል ነው። ንጉሡ የተነሡለት ምድራዊ ኀላፊነት ያለሙለትን ያህል ከዳር ሳይደርስ በመከሸፉ ምክንያት የተቈጩት እንዲህ ባለ መልክ ሊኾን ይችላል በሚል ዕሳቤ ባለቅኔው ጸጋዬ በምናባቸው ተቈጨላቸው ማለት ነው። “ያልሞከርነው ነው የሚቈጨኝ” እያሉ።

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ባርያዎች ሆይ፣ የእኛስ ጉዳይ? የታላቁ ዐደራስ ነገር? ባለፉት ሁለት ደርዘን ዓመታት ውስጥ ይደረግ ዘንድ ይገባው የነበረው ይህ ብቻ ነበር? የሚያስቈጭ ነገር የለም?

ብዙ የተለፋለት ነገር ሲነካ ማስቈጨቱ አይቀርም። አዎ ያስቈጫል። *የትሩፋን ናፍቆት* በተባለው መጽሐፍ ላይ እንደ ሰፈረው፣ “ሕልም ሲከስም ቍጭት እንደ እግር እሳት ያንገበግባል፤ እየዋለ እያደረ ጸጸት ወደ ልቡና ይዘልቃል። ሕልምም ኾነ ቅዠት በሌላቸው ሰዎች ዘንድ የማይገኝ ውስጣዊ ነዲድ ኀሊናን ይሞሽልቃል።”[167]

[166] ጸጋዬ ገብረ መድኅን፣ *“የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ፣” እሳት ወይ አበባ* (ዐዲስ አበባ፡- የጸ.ገ.መ. ቤተ ሰቦች፣ 1999 ዓ.ም.) 214።

[167] ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን፣ *የትሩፋን ናፍቆት* (ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2006 ዓ.ም.) 223።





ኾኖም ግን መጽናት አለብን። የአንድ ሰው ዋነኛ መለኪያው በምቾትና መደላደል ውስጥ በርትቶ ማለፉ አይደለም፤ በችግርና ውጥረት ውስጥ ጸንቶ መቆም መቻሉም ነው። በዙሪያችን ከከበበን ነገር ይልቅ የተበላሸውን እንደ ገና ዐድሶ በሚሠራው በእግዚአብሔር እንታመናለን። ለውጥና ተሐድሶ የእግዚአብሔር አምላካችን ሥራ ነውና።

ክርስትና በኢትዮጵያ በመድኅነ ዓለም ክቡር ደም በጸናው ወንጌል መመሥረቱ እሙን ነው። የምሥራቹ ሲታወጅም የሰማዕታትን ደም በምስክርነት መስጠቱ አይታበልም፤ በስደት፣ ዕመቃና እንግልት የደመቀ ታሪክም እንደ ነበረው እንገነዘባለን። ነገር ግን ይህ ክቡር ትናንት ውድ ዋጋው እንደ ተጠበቀ ወደ ነገ እንዲዘልቅ ዛሬን ይሞግተን ዘንድ ከፊታችን ቆሟል፤ እኛስ እንሞገትምን? ብንሞገትና የተሻለውን ብንቀይስ አይሻለንም? አለዚያ ኪሳራ ይገጥመናል። ራሱን የማይመረምር ሕይወት ከኪሳራ ሌላ ምን ሊመጣበት ኖሯል? መጽሐፍስ ይህን እያስተምርምን? *“በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ”* (2ቆሮ. 13፥5) የምትሰኘዋ ጥበብ ሰማያዊ ናት።

ትናንትን ብቻ እያሞካሸን መዝለቅ አንችልም። በትናንት ትዝታ ተውጠን በዛሬው ክፋት ጠውልገን መጓዝስ አይበቃንም? ታሪክ ብቻውን መተማመኛ አይኾንም። ወንጌላዊ እንዳለ ገብረ መስቀል በአንድ ወቅት እንዳሉት ነው፤ *“ምሥረታ ታሪክ ነው፤ መከራ መቀበል ምልክት ነው፤ ማገልገል የፍቅር ዕዳ ነው፤ መጽናት ግን ብድራት ነው።”* ባልጸና አስተምህሮ የምንጸናው ግን እንዴት ነው? የጸና ትምህርት ያስፈልገናል ብቻ ሳይኾን በእውነት መጽናትም ያሻናል።

ይህን የምንለው ዘመኑ ከፉ ትውልዱም አስቸጋሪ ነው መባሉን በመዘንጋት አይደለም። አዎ፣ የሚታየውና የሚሰማው ቀላል አለመኾኑ እውነት ነው። ልንወጣው የሚገባን ተራራና አቀበት ከፍ ያለ ይመስላል። “ዳገት” አለ፤ ቢኾንም ግን ተስፋ ገና የቀረልን ሕዝብ ነን።

## 5.3 *ዳገትና ተስፋ*[168]

ልጆች ሳለን በሚነገሩን ጣፋጭ ተረቶች በኩል አጮልቀን የምናያቸው የሕልም ዓለማት ነበሩን። (ርግጥ፣ በነ "እያ ጅቦ" ታሪክ ብቻ ላደገ ልጅ ይህ አባባል አይሠራም።) እኒያ ተረቶች የሚያነጫንጩ የልጅነት ችግሮቻችንን በማስረሳት በሐሳብ ሰመመን ውስጥ አስገብተው እንደሚያፍነከንኩን ትዝ ይለናል። ነገር ሁሉ "አልጋ በአልጋ" በኾነበት የተረት ዓለም፣ የፈጠራ ታሪኮቹ፣ ከደስታ ባሕር ላይ ያንሳፍፉን ነበር።

በዕድሜያችን ከፍ ብለን ከእውነታው ጋር መገናኘት ስንጀምር ግን፣ በልጅነት ልቡናችን የገነባናቸው ረቂቅ የሐሳብ ዓለማት መናድ ይጀምራሉ። የእውናዊውና የገሀዱ ዓለም "ጣጣ ፈንጣጣ" ይቀበለናል። እኛም ከእናቶቻችን ጀርባና ከአባቶቻችን ዕቅፍ "ሳናንከሻኩሽ" ወርደን ወደምንውተረተርበት ሥፍራችን "ዝቅ" እንላለን።

የአጽናፈ ዓለሙ ማእከል የኾንን ያህል እንዲሰማን የሚያደርጉን እኒያ የተረት ዓለም ጣፋጭ ነገሮች እየተነኑ ይለዩናል። ከብዙዎች እንደ አንዱ የመኾናችን ሐቅ ፊታችን ይገሸራል። ከሕይወት ጋር ፊት ለፊት እንጋፈጣለን። ዓለማችንን ከነቡጉሯ ጭምር እናያለን። የእሳት ዳር ተረኮች ቀስ በቀስ ትርጒማቸው ይወይብና፣ ከሕይወት ጋር የሚኖረን ጥምረት አስተውሎት ተጨምሮበት፣ አካባቢያችንን ከውጣ-ውረዱ፣ ከደስታና ኀዘኑ፣ ከጥያቄው፣ ከሩጫው ... ጋር እንረከባለን። እየወደቅንና እየተነሣን የምናዘግምበት ወይም የምንከተፈተፍበት መንገድ ይኖረናል። ሩጫ በተሞላው የኑሮ ጎዳና ላይ ማዝገሙ አይቀሬው ዕጣ ፈንታችን ይኾናል፤ እንሮጣለን። የክርስትና ሕይወት ጒዞም በሩጫ ተመስሏል (1ቆሮ. 9፥24፤ ዕብ. 12፥1-3)።

[168] የዚህን ሐሳብ አብዛኛውን ክፍል በግንቦት 2006 ዓ.ም. በታተመችው *ሕንጸት መጽሔት* ላይ አስነብቤው ነበር።





እናም፣ ሕይወት እንደ መንገድ፣ ሕይወት እንደ ጒዞ፣ ሕይወት እንደ አቀበት፣ ሕይወት እንደ ዳገት፣ ሕይወት እንደ ሩጫ ... ትመጣበናለች። እኛም የሕይወት ግብ ግቡን እንያያዘዋለን። አንድ ነገር ግልጽ ይኾንልናል፤ በተሰጠን ዘመን "ሯጮች" መኾናችን።

*በሕይወት መንገድ ላይ፣ ሁላችን ሯጮች ነን*

*ቀዝፈን የምንዋኝ፣ በዕድሜ ጅረት ሰፍረን።*

የዚህ ምድር ሩጫና ግብግብ ብርቱ ሰልፍ የተሞላ ነው (ኢዮ. 7፥1)። ለእኛ ለክርስቲያኖችም የዚህ ዓለም ኑሮ መከራና ተግዳሮት የሞላው መኾኑ ተነግሮናል። ሐዋርያቱ፣ *"ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል"* (ሐዋ. 14፥22) በማለት እንደ ተናገሩት ብጤ ነው። ዳገት እንወጣለን፤ ቍልቍለት እንወርዳለን፤ ሸለቆም እንሻገራለን ።

የልባችን ዐይኖች ሲከፈቱልን፣ ለከበረ እውነትና ለዘላቂ ዓለማ መሰለፍ አለ። አለዚያ ይህ "እንጀራ" ይሉት ነገር ወዛችንን እየመጠጠና ሐሳባችንን እየሰነከለ ያንከላውሰናል። ዘመናችንን የምንደኛ ወራት ሊያደርግብን ይዳዳዋል። ደረጀ በላይነህ በ*የዕድሜ መንገድ* ውስጥ ባሰፈራት "ሯጮች" በተሰኘችው ግጥሙ እንዳለው እናንጐራጒራለን፤

*ሁላችን ሯጮች ነን፣ ሁሌ እንሮጣለን*

*ከእንጀራችን ኋላ፣*

*ምንም አሸንፈን ዋንጫውን ባንበላ።*[169]

[169] ደረጀ በላይነህ፣ "ሯጮች፣" *የዕድሜ መንገድ* (ዐዲስ አበባ፦ አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1997 ዓ.ም.) 30።

ብታንስም ብታድግ የራሳችን ሩጫ አለችን። የልደታችን ፀሐይ ከሠረቀችበት ቅጽበት ፊትም ኾነ ኋላ ሩጫውና ትግሉ እንዳለ ነው። "ከልደታችን በፊት" ያልኩት፣ ባይታወቀን እንጂ፣ በማሕፀንም ውስጥ ኾነን ስንትና ስንት "ሩጫ" ማሳለፋችን አልቀረምና ነው። በዚች ምድርም ላይ፣ የተሰጠንን ዘመን ያህል፣ መፏደዱ ይኖራል። ቀን ሳይል ሌሊት መብከንከኑ ይቀጥላል። የባሰበት ተኝቶስ መች ያርፋል? በስሜት እየባከነ ጣራ ሲቈጥር፣ ሲያስርና ሲፈታ፣ ሲወጣና ሲወርድ ሌሊቱን ማጋመሱና ሲብሰም ማንጋቱ አለ። እንዲህ ዐይነቱ መማሰን ከብዙዎች አንደበት ሲነገር የምንሰማው ሕማም ነውና እናውቀዋለን።

ይህ ሩጫ ታዲያ "ዐልጋ በዐልጋ" ዓይነት የምቾትና የተድላ መንገድ ብቻ አይከተልም። አድካሚና "የዳገት ላይ ጉዞ" የሚኾንበት ወቅት ሞልቷል። በግልም ኾነ በጋራ ዳገቱን መቧጠጥ ይኖራል። የአንዳንዱ ጥረት እንደ ሸረሪት ነው፤ ድሩን እያደራ እያውተበተበ ይነጉዳል። የሌላው እንደ በረሮ ነው፤ በዘፈቀደ የመርመስመስ። የገብረ ጉንዳን ዓይነት ጥሮ-አደር ብርቱም አለ። በጥምዝምዙ ሳይበገር በኅብረት እየተረዳዳና እየተጋገዘ የሥልጣኔ "ዡይሳውን" የሚገነባ።

ቤተ ሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ማኅበረ ሰብ፣ ኅብረተ ሰብና ሀገር ማለት እንደ ዡይሳው ይመስለኛል። "እኔው የሠራሁት" እና "የእኔው ነው" አይባልምና። "የእኔ፣ በእኔ፣ ለእኔ" ብቻ የማለት መገደር (ትምክሕት፣ ትዕቢት) የመጣብን እንደ ኾነ ግን፣ አፈር ድቤ የምታስግጠውን የናቡከደነፆርን ጽዋ መጨለጥን ያስከትላል (ዳን. 4፥30-33)።

ግርማ ተስፋው የተባለ ገጣሚ፣ *የጠፋችውን ከተማ ኅሠሣ* በምትል መድበሉ መግቢያ ላይ፣ "ሁላችንም የየራሳችንን ዳገት በየቀኑ እንወጣለን"[170] ይላል። እውነት ነው። በግልም በኅብረትም የሚወጣ አቀበት ይኖራል።

---

[170] ግርማ ተስፋው፣ *የጠፋችውን ከተማ ኅሠሣ* (ቦታና አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2005 ዓ.ም.) 1።





የአንድ ትውልድ ጉዞ፣ የአንድ ማኅበረ ሰብ የዕድገት፣ የለውጥና የተሐድሶ ተስፋ የሚጠይቀው ጥረት እጅግ ታላቅ ነው። ዛሬ ጠዋት ተጀምሮ ምሽት ላይ የሚጠናቀቅ ስኬት የለም። በአንዲት ጀንበር የተጠናቀቀ ሥልጣኔም ኾነ ተሐድሶ አይታወቅም። በውጣ-ውረድ የተሞላ መፍጨርጨርን ይጠይቃል፤ ትጋትን ይፈልጋል። የዳገት ላይ ሩጫ ነዋ።

እኛማ፣ በመልክአ ምድራዊ አቀማመጧ ጭምር በተራራና በዳገት የተሞላች ሀገር ውስጥ የምንኖርም አይደለን? *The Ethiopian Highlands* ማለትን ማን ያጣዋል? በአጠቃላዩ ማኅበራዊ ጥምዝምዛችን ውስጥ እንደ ሕዝብም፣ እንደ እምነት ማኅበረ ሰብም፣ እንደ ሀገርም የራሳችን "ዳገት" ያለን መስሎ ይታየኛል። ልንወጣው የምንፍጨረጨርበት "አቀበት"ይሣልብኛል። ከሀገሪቱ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ምሁራን፣ ጸሐፍትና ከያኒያን አንደበትና ብርዕም ይህንን ሐቅ መልቀም ይቻላል።

ለምሳሌ፣ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ በረከት ስምዖን *የሁለት ምርጫዎች ወግ* በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ ሐሳባቸውን የሸበለሉት "ናዳን የገታ ሀገራዊ ሩጫ" በሚል ሐረግ ነው።[171] ናዳ ከዳገትና ገደል በቀር ወደየት አለ? ያለ ዳገት ናዳ አይኖርም።

*ዘመን* መጽሔት በኅዳር 2005 ዓ.ም. በድጋሚ ታትሞ ለንባብ በበቃው ልዩ ዕትሙ ላይ ክቡር ጠ/ሚ ኀይለማርያም ደሳለኝ በቀድሞው ጠ/ሚ አቶ መለስ ዜናዊ የቀብር ሥነ ሥርዐት ላይ ያደረጉትን ንግግር አስፈሯል። ከዚያ ውስጥ ስለ "ዳገቱ" ከተናገሩት ውስጥ የሚከተለውን መቀንጨብ ይቻላል። አቶ ኀይለ ማርያም ሲናገሩ፣ "... የዳገቱን ጉዞ አጋምሰናል። ... ዳገቱ መኻል ላይ መቀመጥ ወይም ማረፍ አይፈቀድልንም። ካረፍን ይደክመንና ዳገቱን መውጣት

---

[171] በረከት ስምዖን (ሚ/ር)፣ *የሁለት ምርጫዎች ወግ፦ ናዳን የገታ ሀገራዊ ሩጫ* (ናይሮቢ፦ 2004 ዓ.ም.)

ይሳነናል"[172] ይላሉ። ልብ በሉ፤ ሀገራዊውን ጉዞና ጥረት የመሰሉት በዚያው በተለመደ "ዳገት" ነው።

ለማለት የፈለግሁት፣ ማኀበረ ሰባዊና ሀገራዊ "የዳገት ላይ ጉዞ" የመኖሩ ነገር ሰፋ ያለ ቅቡልነት እንደ አለው ነው። "ዳገቱ" የማኀበረ ሰብ ከመኾን በላይ የግል ሕይወት ጉዳይ መኾኑም ግልጽ ነው። ርግጥ፣ አንድ ሰው በሰሎሞን ደሬሳ የአሰላሰሎ ንጽረት ላይ በመመሥረት "የዳገቱ ነገር" እንደ አተያዩ ነው ብሎ ሊከራከረን ይሞክር ይኾናል።

*ዳገት፣ ሽቅብ የታየ ቍልቍለት*

*ቍልቍለት፣ ቍልቍል የታየ ዳገት፤*[173] በማለት።

የኾነ ኾኖ፣ ወደድንም ጠላን "ዳገትማ" አለ። በግልም በጋራም የምንወጣው "አቀበት" አለ። "ዳገቱ" ብቻ ሳይኾን እሱን ለመሻገር የሚደረገው ጥረት ሳይቀር እንዳለ አለ። እንደሚታወቀው፣ "አቀበቱን" ለመውጣት የሚከፈል ውድ ወዝ ከየዜጋው ተመጥጦ መፍሰሱ አልቀረም። በየዘመኑ ዳገት መቧጠጡ እንደ ነበር ማን ሊያስተባብል ይችላል። በየሥርዐቱ ልዩ ልዩ የዳገት ላይ መንገዶችን ተጋፍጠናል። በየልማዱና ወጉ ውስጥ የተመደበልንን "አቀበት" ለመውጣት ተውተርትረናል። በየአግባቡ ያጋጠሙንን "ፈፋዎች" ለመሻገር ሞክረናል። የተሳካልን ያለውን ያህል፣ ያልተሳካልንም ይኖራል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በአንድ ግጥማቸው ውስጥ ያኖሩት ሐረግ "ዳገት ላይ ሰው ጠፋ፣ አቀበት ከበደ"[174] ይላል። በዳገት ሩጫው ያጋጠመ "ጥፋትን" የገለጹበት የቍጭት መግለጫ ይመስላል።

---

[172] *ዘመን መጽሔት*፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ ቍጥር 48፣ ልዩ ዕትም፣ መስከረም 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 53።

[173] ሰሎሞን ዴሬሳ፣ *ዘበት ዕልፈት* (ዐዲስ አበባ፡- ተዋነይ ስቱዲዮ፣ 1991 ዓ.ም.) ሽፋን ገጽ።

[174] መስፍን ወልደ ማርያም (ፕሮ.)፣ *ዛሬም እንጉርጉሮ፡- እንነሣለን* (ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2005 ዓ.ም) 21።





እንደ ማንኛውም ሕዝብ፣ የእኛም ጥረትና መፍገምገም ያለና የነበረ ነው። ከስሕተታችን ተምረን፣ በስኬታችንም ተበረታትተን ከመቀጠል ሌላ ምን አማራጭ ይኖረናል?

በዚህ መፍገምገም ውስጥ እንደ ወጣ የቀረ እልፍ አእላፍ ዜጋ አለ። ገሚሱ ታሪክ ሠርቶ፣ ለተከታዩ የመሸጋገሪያ መደላድል አበጅቶና "መሰላሉን" ኾኖ ተተኪው ትውልድ ወደ ደርቡ ይወጣ ዘንድ ዐግዟል። መሪው፣ ተመሪው፣ ገበሬው፣ ነጋዴው፣ ወታደሩ፣ ምሁሩ፣ የእጅ ባለሞያው፣ ካህኑ፣ ወዘተ... ሀገራዊ ዋጋውን ታሪክ ይሰጠዋል ብለን ተስፋ እናድርግ። ወሮታውን የሚያጣጥል ትውልድ ካልተነሣበት ዐላፊው ወገን የቈፈረው ምንጭ ላይ አሸዋ አይሞጀርበትም፤ ጉድፍ አይጣልበትም።

እንግዲህ፣ በዚህ የዳገት ላይ ጉዞ፣ በክርስቶስ ወንጌል የተለወጡ ክርስቲያኖች አበርክቶት ታላቅ ተስፋ ተሸክሟል። ምክንያቱም፣ "የተለወጡ ሰዎች የማያሳፍሩ የወንጌል ምስክሮች፣ የሕዝብና የሀገርንም ሁለንተና በጽድቅ የሚያገለግሉ ይኾናሉና።"[175]

ለማንኛውም ዳገቱን የመውጣት መፍጨርጨሩ አለ። በነዚህ ሁሉ ትግሎቻችን ምን ያህል ተሳካልን? ወይም ምን ያህል ጊዜ ተንሸራትተን ወደ ታች ተመለስን? ትልቅ ጥያቄ ነው። በዚህ የዳገት ላይ ጉዞ ተሸንፈው ወደ ዐዘቅቱ የሰረጉ እንደ ነበሩ ስንሰማ ኖረናል፤ አንብበንማል። ሌሎች ደግሞ በአቀበቱ መኻል ሲፍገመገሙ በሌሎች ተጓዦች ተገፍትረው ተሰውረዋል። ይህ በዓለማዊውም በቤተ እግዚአብሔርም ታይቷል። ጥቂቶች በጽናት ተጉዘው ከአፋፉ ላይ ደምቀው እንደሚያበሩ ግልጽ ነው።

ክርስትናም ውድ ዋጋ ባስከፈለውና ውጣ ውረድ በተሞላው የዳገት ላይ ጉዞው ተፈትኗል። ትውልዱ ከቀዳሚዎቹ የወረሰው ዐደራ ክቡር የኾነውን ያህል ከፊቱ ሊወጣው የተገባው ዳገትም ቀለል አይደለም። በዚህ መጽሐፍም ለማሳየት እንደተሞከረው ገና ብዙ የምንወጣው ዳገት አለ።

---

[175] ተስፋዬ፣ *በዚያን ጊዜ*፣ 134።

ዋናው ነገር፣ የዳገት ላይ ሩጫው ምሬትና ሥቃይ እንዳይበረታበት ምን ማድረግ አለብን የሚል ነው። አንድም “ነጻነታችንን ኀላፊነት በተሞላ መንገድ እንጠቀምበት። ዘመኑን ከአሁን የበለጠ በማስተዋል እንዋጅ፤ በጥቃቅን መናኛ ጉዳዮችና ያለ ልክ በመዝናናት የምናጠፋው ጊዜ የለንም።”[176]

በጥርጣሬና በመካሰስ የምናተርፈው ነገር አይገኝም። አቀበቱን በእሾኽ መሙላትስ ምን ይጠቅመናል? በበደሉን ላይ የምንበትነው ጠጠር እኛኑ መልሶ እንዳያውከን ማሰብ ይኖርብናል። የዳገቱን ጉዞ በመያያዝ እንጂ በመጓተት አንዘልቀውም። ወንድሞቻችን ከፈፋው ሰጥመው ከቀሩ በኋላ ብቻችንን ከተራራው አናት ብንደርስስ ሐሴት ይሞላናልን? የአጥቢያችን ስኬት ብቻውን ያስፈነድቀናል? *“በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ”* (1ጴጥ. 5፥9) መባሉን ስናውቅ ዐብሮ በጸሎት ከመትጋት ጋር አጋርነትን ማሳየት እንዳለብን መጽሐፍ አስተምሮናል።

ልብ መባል ያለበት ሌላም ቍም ነገር አለ። እርስ በርሳችን እየተካሰስን ብንካለብ እንጠፋፋለን። በዙሪያችንም ኾነ በመካከላችን እየኾነ ያለው ግን ምንድነው? የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ድካም የምንደግም ይመስላል። *“ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፥ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?”* (1ቆሮ. 6፥6)። የአቀበቱ ጉዞ መተማመን ይሻል። ገጣሚ አበባው መላኩ “ዳገት የከፈላቸው” ወንድሞችን በአቤልና ቃየል የውረድ-እንውረድ ሽመቃና ነፍስ ነጠቃ ምሳሌነት በሣለበት “እሰከ ማእዜኑ” በተባለ ግጥም ስንኞች ውስጥ የመጠራጠርን ፍዳና የመተማመንን ፋይዳ ልብ በሚነዝር ቋንቋ ያወሳል፤

*“ከዚህ የቀን ጐደሎ ነው ከዚህ ክሕደት በኋላ፣*

*በተራራው አናትና ከግርጌ በቆመው መኻል መተማመኑ የላላ።”*[177]

[176] ተስፋዬ፣ *በዚያን ጊዜ*፣ 134።
[177] አበባው መላኩ፣ “እስከ ማእዜኑ” *ከራድዮን* (ቦታና አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1999 ዓ.ም.) 69።





እዎ፣ የማይተማመኑ ወዳጆች ዐብረው መጓዝ አይኾንላቸውም። የጋራ ራእይ አይኖራቸውም። ምናልባትም ባይጠፋፉ አይደል። መጽሐፍም፣ *“ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ”* (ገላ. 5፥15) በማለት ያስጠነቅቃል።

በዚህ አነስታኛ መጽሐፍ ውስጥ ከበድበድ ያሉ ርእሰ ጉዳዮች ተነሥተዋል። የተጋፈጥናቸውና ገናም የምንጋፈጣቸው አቀበቶች እንዳሉብን ተጠቅሷል። ታዲያ ተስፋው ምንድነው? ተስፋው ተስፋ ነው። እንደ ተራራ የተገተረውን አቀበት በጽናት መውጣት እንደሚኖርብን ይሰማኛል። ወገባችንን በፍቅርና ተስፋ ጠበቅ አድርገን በማሸነፊጥ እንወጣዋለን።

ራሳችንን ለመሸንገል ካልፈለግን በቀር፣ ያለንበት ኹኔታ የሚያስጨበጭብ አይመስልም። ሀገረኛው ብሂል “ሆድን በጎመን ቢደልሉት፣ ጉልበት በዳገት ይለግማል” ይላል። ርግጥ የሚያስቈጩ ነገሮች ሞልተዋል። ነገር ግን በቍጭት፣ በብሶትና ቍዘማ ብቻ የትም አይደረስም። “ቍጭትና መረቅ ለጊዜው ይጣፍጣል።” ነገር ግን ተስፋ ከሌለበት ዐጥንት ያነቅዛል።

ተስፋ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ነው። አንዳንዶች የተስፋን አስፈላጊነት *ኦክስጂን* ለሳንባችን ከሚያፈልግበት ውድነት ጋር ያመሳስሉታል። ያለ*ኦክስጅን* ታፍኖ መሞት እንደሚከሠት ሁሉ፣ ያለተስፋ ደግሞ የሰው ሕይወት በተስፋ መቍረጥ ዐዘቅት ውስጥ ይዘፈቃል፤ በዓላማ ቢስነትና ትርጉም የለሽነት ዐውሎ ይመታል። ተስፋ የሰውን ልጅ አዕምሯዊም ኾነ መንፈሳዊ ጥረት የሚያንቀሳቅስ የኀይል ምንጭ ነው፤ ለግለ ሰብ የሚያስፈልገውን ያህል ለማኀበረ ሰብም ያሻዋል። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የእምነት፣ የፍቅርና የተስፋ ማኀበረ ሰብ ናት።

ከማኀበራዊ መነጽር ከተመለከትነው፣ ተስፋ የአንድ ማኀበረ ሰብ ሕዝባዊ ንቃተ ኀሊና (*civic consciousness*) መጐልበት ምንጭ ይኾናል። ምክንያቱም ተስፋ የመጪውን ጊዜ ኅብረተ ሰብ፣ ከተማ ይሁን ሀገር መድረሻ

ብሩኅና አጓጊ ያደርጋልና።[178] ያለተስፋ ሰው ወደየራሱ የብቸኝነት ጥግ ተስፈንጥሮ በመስጠም ከማኅበራዊ ተግባቦቱ ይነጠላል። በሌላ በኩል፣ ተስፋ መቍረጥ የመታው ሰው፣ ሽሽትን እንደ ብቸኛ አማራጭ ስለሚወስድ፣ ኅብረት ይወድቃል። እንዲህ ዐይነት ሰው ከፊቱ ያለውን ዕንቅፋት ሁሉ ለማንሣት በሚያደርገው የሞት ሽረት መንፈራገጥ የተነሣ በጭካኔና ደመነፍሳዊ መወራጨት ሊሞላ ይችላል።

ተስፋ ከዚህም በላይ ነው። ትዕግሥትን ያስተምራል፤ በሐሳብ ከማይስማማን ሰው ጋር እንኳን በፍቅር እንድንደማመጥና በማስተዋል እንድመላለስ ዐቅም ይሰጠናል። ሮናልድ ቺያ እንዳለው፣ “ተስፋ ቢስነት የሞት ዐይነት ነው። ምክንያቱም የፍርሀትን በር ይከፍታልና፤ ፍርሀት ደግሞ ያደክማል፤ ያሽመደምዳልም።”[179]

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት ካነጋገርኋቸው ወገኖች መካከል በአንዳንዶቹ ላይ ግልጽ የኾነ የተስፋ መቍረጥ ስሜት ተመልክቼአለሁ። ተመሳሳይ ስሜት የሚጋሩ ወገኖች መኖራቸውን ሰምተናል፤ አንብበናልም።[180] ነገር ግን፣ ተስፋ የመቍረጥ ደመና ቢከበንም እንኳ ተስፋ ራሱ ብርታትን እንደሚያጐናጽፈን የታወቀ ነው።

የተስፋን ባሕርይ አስመልክቶ፣ ከግማሽ ምእት ዓመት በፊት፣ ጋብርየል ማርሰል እነዚህን ቃላት ጻፈ፤ “እውነቱ ይህ ነው። የተስፋ መቍረጥ ፈተና በሌለበት ጊዜ፣ ተስፋ ሊኖር አይችልም፤ ተስፋ እኮ ይህን ፈተና በንቃት፣ በቅልጥፍና፣ ያለዳተኝነትና በድል አድራጊነት የምንቋቋምበት ከዋኔ (ተግባር) ነው።”[181]

አሜሪካዊቱ ክርስቲያን *ኖቨሊስት* አኔ ላሞትም ለዚህ አተያይ የቀረበ ሐሳብ አላት። “ተስፋ የሚጀምረው በጨለማ ውስጥ ነው፤ ትክክለኛውን ነገር

[178] Ronald Chia, *Hope for the World* (Leicester: IVP, 2006) 11.
[179] Chia, *Hope*, 11
[180] ነቢዩ፣ *“የወንጌላውያን” ማቴቴሶ*፣ 30።
[181] Gabriel Marcel, as quoted by Ronald Chia, *Hope*, 12.





በማድረግ የምትቆምበት ጽኑ ተስፋ ካለህ የማለዳው ንጋት ይመጣል። በንቃት ትጠብቃለህ፣ መሥራትህንም አታቆምም፤ ተስፋም አትቈርጥም” ትላለች። ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይመክረናል፤ *“ቍጣው ለጥቂት ጊዜ ነው፥ ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን። ልቅሶ ማታ ይመጣል፥ ጥዋት ግን ደስታ ይኾናል”* (*መዝ.* 30፥5)።

የጊዜው መከራችን የክብርን የዘለለም ብዛት እንዲያደርግ እናውቃለን (2ቆሮ. 4፥17)። ጸሎታችን ሳይመለስ የዘገየ ቢመስለንም እንኳ ተስፋ ገና አለ። በግራ መጋባታችን፣ በመቍሰላችንና በሕማማችን ውስጥ ዐልፎ የሚሠራ ነገር ይኖራል። አኔ ግርሃም ሎዝ እንዳለችው፣ “እግዚአብሔር በመከራ ከተቈረሰው የኢየሱስ አካል በረከት ማውጣት ከቻለ፣ መስቀልን ከመሰለ ዘግናኝ የሥቃይ ቦታም ክብርን ማውጣት ከቻለ፣ ከእኔም ችግር፣ ሕማምና ያልተመለሰ ጸሎት ውስጥ ባርኮትን ሊያወጣ ይችላል። እኔ እሱን መታመን ብቻ ነው ያለብኝ።” አዎ፣ በስብራታችን ውስጥ የሚሠራ ነገር አለ።

አንድ ነገር ግልጽ መኾን አለበት። የክርስቲያን ተስፋ ከልማዳዊው ተስፈኛነት (*optimism*) የተለየ ነው። “ነገ ይህ መኾኑን አላውቅም፣ ምናልባት ሊኾን እንደሚችል ግን ተስፋ አደርጋለሁ” ማለት ፍጥረታዊ ነው። ክርስቲያናዊ ተስፋ እግዚአብሔር አምላክ ከሰጠው አስተማማኝ የተስፋ ቃል የተነሣ አንድ ነገር እንደሚኾን ርግጠኛ የምንኾንበት በጌታ ያለን የመተማመን ደረጃ ነው።

ነጋችን በእግዚአብሔር ዋስትና እንደ ተጠበቀ ርግጠኞች ካልኾንን ከልክ በላይ በመጨነቅ ሕይወታችንን እናባክናለን። ይህ ዐይነቱ መፋዘዝ በበኩሉ ኢደንዛዥ ሥጋትና ፍርሀት ይለቅብናል፤ አለዚያም በስግብግብነት መንፈስ ይሞላናል። በመጨረሻም ንፉግነት ይጠናወተንና “ስለ ራሴ ብቻ፣ ስለ እኔ መጪ ጊዜ ብቻ፣ ስለ እኔ ችግር ብቻና ስለ እኔው ብርታት ብቻ” በሚብከነከን የሥሥት ዐጥር ውስጥ ይቀይደናል። በመጨረሻም ሌሎችን ከማፍቀርና ከተቈርቋሪነት ጥሪ ተመልሰን በማይገባ ቦታ ስንቈዝም እንገኛለን።

በሌላ አባባል ተስፋ ራስን መስጠት የተሞላው የክርስቲያናዊ ፍቅር መገለጫ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲጠብቀን በመፍቀድ በራሳችን ምቾትና ብርታት ከመተማመን ጣዖት ያርቀናልና ነው። ርካታችን በግል ገበታችን ላይ በቀረበው ማዕድ ልክ መኾኑ ያበቃለታል። ስለ ሌሎችም ግድ ይለናል፤ ሕመማቸው ይሰማናል። የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ይከብድብናል (2ቆሮ. 11፥28)። በዚህም አኗኗራችን እግዚአብሔር የበለጠ ይታያልና ለክብሩ ምስጋና ይኾናል። ምክንያቱም የክርስቲያን ተስፋ የሚጀምረው በመስቀሉና በትንሣኤው ኀይል ነው። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነሣ ከዓለም በተለየ መንገድ መኖር እንችላለን።

ሀገራዊ አበርክቶዎቻችን ከዜግነት ኀላፊነታችን እንደሚመነጩ ግልጽ ነው። ግን ደግሞ ክርስቲያናዊ ምግባራችንም ይህን ያስገድደናል። ለሰላም ለዕርቅና ለመግባባት መሠረት የኾነውን የክርስቶስ ወንጌል ተስፋ ለጠፋበት ትውልድ ማቅረብ የተልእኳችን ማእከል ነው። የተሰበረው ዓለም የፍቅር አስታማሚና ፈዋሽ ይፈልጋል። የወንጌል መልእክተኞች አስለቃሾች ሳነኾን ዕንባ አባሾች ነን። ዐመፅን መሸሽ ብቻ ሳይኾን ማውገዝም አለብን። ሰይፍ የሚያነሡ በሰይፍ ይወድቃሉ ያለው ጌታ ትምህርት ብርሃን በእኛ ሕይወት በኩል ለዓለም መታየት አለበት። አለበለዚያ የዳገቱን መንገድ የበለጠ እናከብደዋለን። *“በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከኾነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ”* (ማቴ. 6፥23)!

ጌታ ኢየሱስ ዓለምን ስለ መለወጥ አስተምሮናል። ግን ዓለምን የምንለውጥበት መንገድ ከፍ በማለት ሳይኾን፣ በዝቅታ ነው፤ ጥቅማችንን በማሳደድ ሳይኾን መብታችንን ጭምር በመተው ነው። በባልንጀሮቻችን ላይ ጉልበት በመፈተሽ ሳይኾን፣ እግራቸውን በማጠብ ነው። የሚያሳዝነው ግን፣ “ከፍ ለማለት” የሚደረግ ግብ ግብ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ከመስፋፋቱ የተነሣ የጌታ ማኅበር እየተከፋፈለች ዘልቃለች። ይህ ከንቱ ምኞትና ትንንቅ የዳገት ላይ ጉዞውን አስንካክሎታል። ነገር ግን፣ እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም (መዝ. 25፥3)። ጌታን ተስፋ እናደርጋለን።





በሌላ በኩል፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለተመለከትናቸው ችግሮች መንሥኤ ከኾኑ ነገሮች መካከል አንደኛው በማናገኘው፣ ብናገኘውም እንኳ ለክርስቶስ ክብር በማያመጣው ጉዳይ የበለጠ መጠመዳችን መኾኑን አይተናል።

የማይገኘውን ከመፈለግና ከእኔነትን ርኵሰት ራሳችንን ካልገታን የሕይወት ጉዞ አይሳካም። ታላቁ እስክንድር ፈላስፋው ዲዮጌነስ፣ አንዳች ነገር እንደሚፈልግ ሰው፣ የዐፅም ክምር ላይ አፍጥጦ ያያዋል። ምን እየፈለገ እንደ ኾነም ይጠይቀዋል። ፈላስፋውም ሲመልስለት፣ “ፈጽሞ ላገኘው የማልችለውን ነገር እየፈለግሁ ነው። ያም ምን መሰለህ? በአባትህ (ዳግማዊ ፊሊጶስ) ዐጥንትና በባሪያዎቹ ዐጥንቶች መካከል ያለውን አንዳች ልዩነት እያሰስሁ ነበር፤ ኾኖም ምንም ልዩነት አላገኘሁባቸውም”[182] አለው። የማይገኘውን የመፈለግ ከንቱ ልከፍትን ያሳየበት ምሳሌ መኾኑ ነው።

በምድር ላይ ሕይወታችን መጨረሻ ላይ በጣም ልዩት (*unique*) ወይም በጣም አስፈላጊ የኾነው ነገር ከቅሪተ አካላችን ጋር የተያያዘ አይደለም። ከኋላችን ትተን የምንሄደው ምልክት ወይም የውርስ አሻራችን በክርስቶስ የኖርነው ሕይወት ነጸብራቅ ብቻ ነው። በተለይም በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተውነው ቋሚና ምግባራዊ ሀብት ነው ዋጋ የሚኖረው። ይህን እስቲ እንጠይቅ፤ ሕይወቴ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ከሠራው የተነሣ በተቀበልኩት ፍቅር የሚታወቅ ነውን? ከዚህ ፍቅር በሚመነጭ ተስፋ የተሞላና የዳገት ላይ ጉዞውን የሚያግዝስ ነውን? ለከበረው ክርስቶስና ለማይናወጠው መንግሥቱ የሚያቃጥል ፍቅር በልቤ አለብኝን? ፍቅር የለውጥ ኀይል ነው።

---

[182] ከ16ኛው እስከ 19ኛው ምእት ዓመት የተጻፉ በርካታ መጻሕፍት ይህ አባባል የዲዮጌነስ እንደ ኾነ እያወሱ ሐሳቡን ሲጠቀሙበት ቢኖሩም፣ ብዙዎች ግን አባባሉ የእሱ መኾኑን ይጠራጠራሉ። ለማስረጃ ምንጭነት ግን የሚከተሉትን በዋቢነት ማየት ይቻላል፤ Philip Graham Ryken, *Ecclesiastes: Why Everything Matters* (Wheaton: Crossway, 2010) 4; Raj Arumugam, *Alexander: Son of Olympias* (Np: Truth and Thought Systems Pty Ltd, 2006) 15.

ፍቅርን የምንማረውና የምናስተምረው ለራሳችን ፈቃድና ምኞት በመሞት ነው። በዚህ ፍቅር የተሞላ ተስፋ ያለው ሰው የሕይወትን ዳገት በአግባቡ ይወጣል። የዳገት ላይ ጉዞ ያለተስፋ ቢሞከሩት የመፍገምገም ጣር ይሞላዋል። ተስፋም ያለፍቅር ባዶ ምኞት ኾኖ ይቀራል። ኾኖም አንድ ዐቢይ ጉዳይ ግን አለ። ተስፋችን ዘላለማዊ እንጂ እዚሁ ተጀምሮ እዚሁ የሚያልቅ ምናምን አይደለም። ምክንያቱም፣ እኛ ምእመናን *"ጽድቅ የሚኖርባትን ዐዲስ ሰማይና ዐዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን"* (2ጴጥ. 3፥13)። በመንግሥቱ መከፈት ወደ ውስጥ ያስገባንና በተፍጻሜያዊ የመገለጥ ተስፋው ሁሉን ዐዲስ የሚያደርገው አምላካችን ይመጣልናል። የዚህች ተስፋ እስረኛ የኾነችው ቤተ ክርስቲያንም በእውነተኛ ደቀ መዝሙርነት ሕይወት የምትዘጋጅ የፍጻሜ ዘመን መሲሐዊ የእምነት ማኅበረ ሰብ ናትና በመቃተት መኖራችን እውነት ነው። *"የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የኾነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን"*(ሮሜ. 8፥23)። በመቃተት ምጥ እየተጠባበቀች ለክርስቶስ የሚኾን ፍጹም ሰው የምታዘጋጅ ማኅበረ ሰብ ናት ቤተ ክርስቲያን (ቈላ. 1፥28)።

በዚህ መዘጋጀት ውስጥ አስተምህሮ ትልቅ ቦታ አለው፤ ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል። ለዐደራ የተዘጋጁ፣ በሚመችና በማይመች ጊዜና ስፍራ የጌታን ፍቅር በማወጅ የሚተጉ አገልጋዮች ያስፈልጉናል። የእግዚአብሔርን መንጋ በጊዜውም አለጊዜውም ነቅተው የሚጠብቁ መሪዎችን ወቅቱ ይጣራል። የዘመኑ መንፈስ ሳይኾን ፈቃደ እግዚአብሔር የሚመራቸው የእውነት ወዳጆች ናፍቀናል። ደግሞስ ጽኑዓን የእምነት ምስክሮች ወዴት ናቸው? የሰው ፊት አይተው የማያመቻምቹ እውነትን ለድርድር የማያቀርቡ ቈራጦች ወደ አደባባዩ ይውጡ። ለእውነት የሚሟገቱ፥ የቀናውን መንገድ የሚያሳዩን ዐርበኞች ይነሡልን እንጂ! እያሉ ያረመሙቱም (ዝምታ የዋጣቸው) ተነሥተው በጽናት ይናገሩልን። እነርሱን ማሠሣችንም ይቀጥላል።





## 5.4 *ያላረመሙ ዝይዎችን*[183] *ፍለጋ*

ስለ ቅዱስ አውግስጢኖስ ከሚነገሩ ታሪኮች መካከል በአንደኛው ላይ እንዲህ ይተረካል። ይህ ተረክ የሚያጠነጥነው ለረጅም ዓመታት በዘለቀው የቅዱስ አውግስጢኖስ የወንጌል አገልግሎቱ መደምደሚያ አካባቢ በተደረገ ጉዳይ ላይ ነው። አውግስጢኖስ በረጅሙ አገልግሎቱ ጤናማውን የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮና ሐዋርያዊ ትውፊት በመጠበቅ ከመትጋት ባለፈ፣ ከልዩ ልዩ መናፍቃን ጋር በመታገል የቅዱስ ወንጌል እውነት እንዳይበረዝ ሲጮኽ ኖረ። እውነተኛው ክርስቲያናዊ ትምህርት ሳይበረዝ እንዲሰበክ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ከነበሩት ሌሎች ቀዳሚ አባቶች ጋር ሰማይም ታሪክም የማይረሳውን ተግባር ሲያከናውን ነበር። ነገር ግን፣ በ326 ዓ.እ. በሰሜን አፍሪቃዋ ሒጶ በነበረችው ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይዞ የቈየውን ሊቀ ጳጳሳዊ ኀላፊነቱን ለምትኩ የሚያስተላልፍበት ቀን ደረሰ።

በዚያም ቀን፣ ትሑቱ ተተኪው፣ ኢራቅሊዮስ፣ ከተቀመጠበት ተነሥቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ እንደ አሸን የፈሉት *ዋዝንቢቶች*(ፌንጣ አስተኔዎች)[184] ዙሪያችንን እየተጯጯኹ ባሉበት በዚህ ወቅት፣ ታላቁ *ዝዪ* ግን ሊያረምም (ዝም ሊል) ነው።" ልብ የሚነካ አነጋገር ነበር። የኢራቅሊዮስ ሥጋት የነበረው፣ እነዚያ ነፍስን የሚያንገደግዱ የኑፋቄ ማዕበሎች ከየአቅጣቻው በነፈሱ ቍጥር ያለማወላወል በጽናት ይመከት የነበረው ታላቅ ድምፅ "ጸጥ ሊል ይኾን?" በማለት ነበር። የዚህ ጽሑፍ ርእስም የተወሰደው የእርሱን አባባል በአዎንታዊ ጐኑ ቀልብሶ በማየት ነው። *ዝዪዎቹ* አላረመሙም!!

---

[183] ይህ ክፍል በቀጥታ የተወሰደው በጸሐፊው እየተዘጋጀ ካለና ካልታተመ መጽሐፍ ሲኾን፣ ርእሱም ኾነ ቀጣዮቹ ሦስት አንቀጾች በቀጥታ የተተረጐሙት መጋቢ ጆን ፓይፐር "ስለ ሁለንተናችን መሟገት" ሲሉ ከጻፉት መጽሐፍ መቅድም ላይ ነው። John Piper, *Contending for Our All* (Wheaton Cross Way Books, 2006) 9.

[184] ዋዝንቢት/ ዋኽንቢት የሚባለው እኽል የሚያጠፋ ጥቍር ትል ነው። የፌንጣ ዝርያ የሚመስልና የሚዘልል፣ በየስርቻው ውስጥ በተለይ በጨለማ ውስጥ ኾኖ የሚንሳጠጥ ድምፁን የሚያሰማ ፍጥረት ነው።

እንደ ቅዱስ አውግስጢኖስ ያሉ በርካታ ታላላቅ ድምፆች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን ሁሉ ሲናገሩ ኖረዋል፤ እኛም በአግባቡ እናዳምጣቸዋለን። የእግዚአብሔር ባለዐደራዎች ለቅዱሳን አንድ ጊዜ የተሰጠውን እምነት ለመጠበቅ ሲጋደሉ (ይሁዳ 3) ኖረው ዐልፈዋል። እነዚህ የእምነት ዐርበኞች ታሪክና ተረት ብቻ አይደሉም፤ ሞተውም እንኳን ገና ይናገራሉ (ዕብ. 11፥4)።

የእኛስ ዘመን ተስፋ ይኖረዋል? ይኖረዋል ብለን እናምናለን። አንዳንድ ዝቢዎች በኛም ዘመን “እየዘመሩ” ነው፤ ግና ብዙ አይደሉም። ዝማሬያቸውም ገና ዘመናትን ተሻግሮ ይዘልቅ እንደ ኾነ መጪው ጊዜ ይነግረናል። በርግጥ ታሪክ በመቶዎች ለሚቈጠሩ ዝቢዎች ያን ፍርዱን ቀደም ብሎ ሰጥቷል። እነርሱ ቢሞቱም እንኳን ሥራቸው የዘመን ሚዛንን ተሻግሮ ቆሟል። ስለዚህ፣ የእነሱን ዜማ እኛ እናደምጠው ዘንድ ዛሬም ከዋጋው ጋር አለ። ዜማቸውን ግን የት ነው የምናገኘውና የምናደምጠው? በበርካታ ድል በታጀበው ተጋድሏቸው እናደምጣቸዋለን። የገናናው ጌታችን ዳግም ምጽአት እስከዚያ የሚቈይ ከኾነና የታሪክ ሀዲድ ካልታጠፈ፣ ቀጣዩ ትውልድስ እኛን ያዳምጠን ይኾን?

ዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስን ተተግነው ለሚገነፍሉና ነፍስን በሚያጥወለውል ሕጸጾች ለተሞሉት ትምህርቶች ሰፊ ሜዳ ያዋሰ መስሏል። ስለኾነም እጅግ ብዙ እንቶ ፈንቶዎች በእምነት ትምህርት ተመስለው በየቤተ ክርስቲያኑ ሲንቧቹ ተስተውለዋል። ታዲያ በዚህ መካከል እንደ ሻማ ቀልጠው እንደ ከዋክብት የሚንተገተጉ ፋናዎች አያስፈልጉንም? በጫጫታ ድምፅ በተሞላው አድማስ መካከል ጐልተው የሚደመጡ ዝቢዎች በብርቱ ይፈለጋሉ።

ሕዝበ እግዚአብሔር በቃለ እግዚአብሔርና በጤናማ ትምህርት ታንጾ በደቀ መዝሙርነት እንዲያድግ መምህራን እንዲበዙልን እንሻለን። የእውነተኛ መጋቢያንን መነሣት እንመኛለን። እውነቱን ከስሕተት ለይተው የሚያመላክቱ፣ የእግዚአብሔር መንጋ ከስሕተት አረንቋ የሚጠብቁ እረኞች ወዴት ናቸው? በየዘመኑ የሚነሡ የስሕተት ትምህርቶች ዐይነትና ብዛት ተቈጥሮ የሚዘለቅ ባይኾንም፣ ስለ እውነትና ዕቅበተ እምነት ግድ የሚላቸው ወገኖች እንዲነሡ እንናፍቃለን። እንደ ጋን ውስጥ መብራት ያልተዳፈነ ወጋገን ለሁላችን የሚያሳዩ





“ተወርዋሪ ከዋክብት” ናፍቀውናል። የክርስትና ትምህርት ጤናማና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኾኖ እንዲቀጥል የመረባረብ ኀላፊነታችን ከፊታችን ተደቅኗልና በታላቁ ተልእኮ ሐቀኛነትና በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ተደግፈን ልናጸናው ይገባናል።

> በአጠቃላይ ስንመለከተው፣ ወንጌላዊ ክርስቲያናዊ ትምህርት ለቀደመው ቅርስ ታማኝ እስከ ኾነ ድረስ እያደገና እየጠነከረ ይቀጥላል። … በወንጌላዊነቱ ጸንቶ የሚቈየውም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ታላቁ ተልዕኮ (ማቴ. 28፥18-20) ማዕከል የያዘውን ሰፍራ አጽንቶ የጠበቀ እንደ ኾነ ብቻ ነው። የወንጌላዊ ክርስቲያናዊ ትምህርት አሰጣጥ ውጤታማ ኾኖ የሚቆየው፣ በትምህርት አሰጣጡ አገልግሎት የሕይወት ምንጭ በኾነው የተስፋው መንፈስ (ሐዋ. 1፥8) የተደገፈ እንደ ኾነ ብቻ ነው።[185]

ታሪካዊው ክርስቲያናዊ ትምህርት ርትዕዊነቱን ጠብቆ ይዘልቅ ዘንድ ከቡር ዕሴቶቹን እንጠብቅለት። ችግር በተከሠተ ጊዜም እንጩኽለት። ዝምታውም አላዋጣም። ይህና እንዲህ ከኾነ ምን እናድርግ? የሚለውን ጥያቄ ራሳችንን መጠየቅና ግላዊና ቡድናዊ ርምጃዎችን መውሰድ አማራጭ የለውም። መደበኛ በኾነ ኹኔታና አስፈላጊ ኾኖ ሲገኝ ተልእኳችን የሚያስከፍለውን ዋጋ ጭምር መክፈል ይጠበቅብናል።

ትኵረታችን ማረፍ ያለበትና እኛና የእኛ የኾነው ነገር ሁሉ ሊረባረብበት የሚገባው ነገር በወደደንና ስለ ኀጢአታችን ራሱን በሰጠ በትንሣኤውም ክብር ከሙታን በተነሣው ጌታ ዐደራ ላይ ነው። ጌታ የሚያየውን እንድናይና እርሱ የሚያከብረውን ነገር እንድናከብር ማስተዋሉን ይስጠን። በየትኛውም ዘመን ማንኛውም የክብር ከፍታና የኑሮ ደረጃ ጋሬጣ ሳይኾንባቸው የእውነት ሸቃጮችን በተፋለሙ፣ የጽድቅን ሰንደቅ ባነገቡና ዋጋቸውን እንደ ተገኙበት ዐውድ ባልቀያየሩ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አማካይነት ቤት ክርስቲያን ጌታዋን እያሳየች ቀጥላለች፤ ትቀጥላለችም።

---

[185] ሚናስ፣ *ክርስቲያናዊ ትምህርት*፣ 71።

## 5.5 ማሳረጊያ

መልካሙን ማድረግ ለሌሎች ብቻ ብለን የምንፈጽመው አይደለም። ለራስም ይጠቅማል። ንጹሕና የተከበረ ነገር መሥራት ትዝታችንን ከመቈሸሽና ጸጸት ይጠብቀዋል። የርስ በርስ መደጋገፋችን ያበረታታናል። ብቻችንን የቀረን ሲመስለን፣ ሌሎች አጋሮች እንዳሉን ባወቅን ጊዜ ተስፋችን ይለመልማል። ጉዳዩ ከበደ ሚካኤል “በቅኔ አዝመራ” ውስጥ እንዳቀለሙት ነው፤

*“በሥራ በዕውቀት ግሎ ለመነሣት፣*
*ቈሰቋሽ ይፈልጋል የሰው ልጅ እንደ እሳት።”*

በዚህ ጽሑፍ በርካታ ነገሮችን ነካክተናል። ልናደርግ የሚገባንንም አይተናል። ለመጠየቅ፣ ለመማርና ለመመርመር የማያመነታ ትውልድ ማዘጋጀት የዘመኑ መሪዎች ኀላፊነት መኾኑን አጽንዖት ሰጥተናል። መማርን እንደ መድረቅ የሚመለከተው ባህላችን ጤናማ አይመስልምና ሊታረም እንደሚገባው አጢነናል። ትውልዱም ጊዜውም እየተለወጠ መምጣቱን መዘንጋት ተገቢ አለመኾኑን ተመልክተናል። “በድሮ በሬ እያረስን” መቀጠል እንደምንችል የምናስብ ብንኖር ዘመኑን በአግባቡ አልዋጀነውም። በጸሎትና በጥሞና ሕይወት “ትኩስነቱ” ያልበረደ ክርስቲያን፣ በጤናማ አስተምህሮ ላይ እስከ ተመሠረተ ድረስ፣ ሕይወቱ የቀና ውርሱም የጸና ይኾናል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ አገልግሎታችን ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣና የጌታን ማኅበር ለማነጽ መኾን አለመኾኑን መፈተሽ አለብን። ለማነጽ የኾነ ስኬታማ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፣ በቃለ እግዚአብሔር እውነትና በክርስቶስ መሠረት ላይ የሚገነባ ነው። ከዚህ የወጣ አገልግሎት የማፍረስ ይኾናል። መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን ስለ አገልግሎት ስኬታማነት የጻፉት አንቀጽ ለዘመኑ እንደ መርዝ-አርክስ (*antidote*) የሚታይ ነው፤





> ስኬታማው አገልጋይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈርስ ሳይኾን የሚያንጽ ነው። በማን ላይ ነው የሚያንጸው? ... የክርስትና እምነት የተመሠረተው በክርስቶስ ላይ ነው። ... ከክርስቶስ በስተቀር ሌሎች መሠረቶች መሥርተዋል በማለት ወንጌላዊው የክርስትና ዘርፍ ካቶሊካዊውንና ኦርቶዶክሳዊውን የክርስትና ዘርፎች ሲከስሳቸው ብዙ መቶ ዓመታት ኖሯል። ኾኖም በማወቅም ይኹን ባለማወቅ፣ በዘመናት ውስጥ፣ ክርስትናን በክርስቶስ ሳይኾን በሌሎች የተለያዩ ነገሮች ላይ ለመመሥረት ሙከራ ያደረጉ ወንጌላውያን ክርስቲያኖችም ነበሩ፤ ዛሬም አሉ። ከእነዚህ ሌሎች መሠረቶች መካከል እንደ እምነት፣ እንደ ብልጽግና፣ እንደ ተአምራት ያሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።[186]

አሁን የሚታዩትን አንዳንድ ትምህርታዊና ልምምዳዊ ችግሮች ስንመለከት ወንጌላዊወው ክርስትና በሌሎች ላይ ጣቱን ከመቀሰር ዐልፎ ራሱን መፈተሽ እንዳለበት ያስገነዝበናል። ጓዳን ሳያጸዱ በአደባባይ መጓደድ ግብዝ ከመኾን አያድንም።

በመጨረሻ ያለንበትን ኹኔታ በግልጽ በመነጋገር መፍትሔ እንድንፈልግ ይህ ጽሑፍ ጥሪውን ያቀርባል። አንዳንድ ሰዎች ችግሮችን ግልጽ በማድረግ መወያየት ሌሎች በእኛ ላይ እንዲዘባበቱ ያደርጋል በማለት ዝምታ መርጠው ተሸሽገዋል። ነገር ግን የአስመሳይ መዓት ዙሪያችንን ከብቦ ባለበት ምን ዝምታ ይኖራል? “ያባትህ ቤት ሲወረር፣ ዐብረህ ውረር” ዐይነት ልግምና ዳተኝነት እንደ መርግ ካልተጫነን በቀር ስለ እውነት መሟገቱማ አይቀሬ ነው። የዚህ ጽሑፍ ተስፋ (ሁላችንም ባንኾን እንኳ) ከመካከላችን የተወሰኑቱ ጨዋነት ያልራቃቸው “ተናጋሪዎች” ይኾናሉ የሚል ነው።

በርግጥ፣ መናገር መልካም ቢኾንም፣ ማዳመጥ የሚበልጥበት ብዙ ምክንያት መኖሩ ሲነገር የኖረና ከሕይወትም የተማርነው ነው። ያገሬ ሰው “ባፍ ይጠፉ፣ በለፈለፉ” የሚለው በከንቱ አይደለም። ጥበብ በጕደለው መንገድ ምላስን

[186] በቀለ፣ ሪቫይቫል፣ 232።

መጕልጕል የሚያሳጭደው አሳር መኖሩን ለማመልከት የተነገረ ነው። ስለ ኾነም አበው “ዝም አይነቅዝም፤” እንዲሁም፣ “ዝምታ ወርቅ ነው” አሉ፤ ዝምብን ከአፋችን ሲገላግሉ። አለቅጥ ሲለጠጥ ደግሞ፣ “ዝም ባለ አፍ፣ ዝምብ አይገባበትም፤” እያለ የዝምታን ውበት እያበረታታ የሚተክዝ ባህልና ማኅበረ ሰብ ሳናጠናከር አልቀረንም፤ መልካም ነው። የሚያሳዝነው ግን፣ መናገር በተገባበት ጉዳይ ላይ ሳይቀር፣ ወደ “ዛጎላችን” ተከትተን የምናሳየው አስፈሪ ጸጥታ ነው። ዳዊት ጸጋዬ *አርነት የወጡ ሐሳቦች* በተሰኘችው የግጥም መድበሉ ውስጥ አጕል ዝምታን በምጸት ሲሸነቍጥ እንዲህ ይላል፤

*“ ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም፣*
*ንብም ስለሚያልፈው ማር አይኖርበትም።”*[187]

ርግጥ ነው፣ መጽሐፉ ዝምታን ያበረታታል (ምሳ. 10፥19፤ 13፥3፤ 15፥2፤ 17፥27፤ 18፥21፤ ያዕ. 3፥26፤ 3፥1-2)። ግን “ጊዜ አለው” በሚለው መርሕ የሚገዛ ነው። *“ለመናገርም ጊዜ አለው”*ና (መክ. 3፥7)። ነቢዩ ኤርምያስ መናገር በሚገባው ጊዜ ዝምታን ሞክሮት ነበር፤ ያተረፈው ግን በውስጣዊ ነዲድ መቃጠል ነበር፤ *“የእግዚአብሔርን ስም አላነሣም፥ ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም ብል፥ በዐጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ኾነብኝ፤ ደከምሁ፤ መሸከምም አልቻልሁም”* (ኤር. 20፥9) ይላል።

ዙሪያችንን ስንመለከት፣ መናገር በሚገባ ጊዜ በዝምታ የመትከን ሕመምን እንዴት ማራቅ እንደሚገባን መነጋገር ሳይኖርብን አይቀርም። ያገሬ ሰው “ዝምታ ለበግም አልበጃት፤ ዐሥራ ሁለት ኾና አንድ ነብር ፈጃት” ማለቱ መች በዋዛ ነው? እኛም በዝምታችን ስንት ነገር እየተበላሸብን እንደ ኾነ ያጤንነው አይመስልም። ዝምታችንን ተመልክቶና አሽናፊነት እየተሰማው “ኧረ! እሰይ ስለቴ ሠመረ” ባይም ሞልቷል እኮ። ዝምታ መልእክት ሊኖረው እንደሚችል አልገባቸውም። ዝምታችን ሁሉ መሸነፍ ነውን? ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ፡-

---

[187] ዳዊት ጸጋዬ፣ “አል-ዝም” *አርነት የወጡ ሐሳቦች* (ዐዲስ አበባ፡- 2003 ዓ.ም.) 34።





*“ ዝም ብዬ ቢያየኝ፣ ዝም ያልሁ መስሎታል፣*
*ሲታሰብ ነው እንጂ፣ ዝም ማለት የታል?”*

እንዳለው ቢኾንስ? ከዛሬ ነገ “ነገሮች ይሻሻሉ ይኾናል” ከሚል ተስፋ የተነሣ ዝም ብለን ይኾናል። አሁን ግን ነገሮች እየተለወጡ ነውና መናገርም ይገባናል። ዝምታማ የለም። ስንት የሚነገር ባለበት ዝምታ ዕርም ነው። ማርቲን ሉተር ኪንግ “ስለ አስፈላጊው ነገር መናገር ባቆምን ዕለት፣ ሕይወታችን ማለቅ ጀምሯል” ሲል ትርጕም አልባ ዝምታን ይጸየፋል።

ይህም ሲባል ታዲያ፣ በኾነ ባልኾነው እየተነሣን መቀባጠር አለብን ማለት አይደለም። የመለፍለፍ ዐመል የተጠናወተው ሰው የተገኘውንና አፉ ላይ የመጣውን ሁሉ እየዘረገፈ መኖሩ የተለመደ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ሰው፣ በዙሪያው ያለውን አቧራ ዘግኖ በዐላፊ አግዳሚው ላይ እየበተነ እንደሚዛብር ዕብድ፣ የወንድሙን ስም ሲያጠፋም ሊውል ይችላል። አፍ ከጕርሻ፣ ምላስም ከመቅመስ በተጨማሪ ያላቸውን ተግባርና ጕልበት አሚጦ የሚጠቀም ለፍላፊ በየቦታው ሞልቷል። ይህን መሰሉን ሕይወት እግዚአብሔር ከእኛ ያርቀው።

ነገር ግን፣ ዙሪያ ገባው የበግ ለምድ በለበሰ ተኵላ ተመልቶ እያየን ዝምታችን የጤንነት ነው? የእምነት ቈራጥነት እግዚአብሔር እንዲያድለን እንለምን እንጅ። ትናንት ከሩቅ የምንሰማው ከንቱ ልማድና ልምምድ ከደጃፋችን ሲንሰራፋ እጃችንን ባፋችን ላይ ብንጭን ይበቃል? በ2006 ዓ.ም. አጋማሽ ማኅበራዊ ሚዲያውን አጨናንቆ የከረመውና ተከታዮቹን (ለምንም ዓላማ ቢኾን) ሣር ያስጋጠው “ፓስተር” ተብዬ የሠራው ግፍ ነገ በእኛው መካከል ላለመፈጸሙ ዋስትና የለም። ዳሩን ካልጠበቁት ማኸሉ ዳር መኾኑን ደጋግመን አይተናል፤ እንዴት ዝም እንላለን?

“ትላልቆቹ ሳይቀር ዝም ባሉበት፣ ብዙኀኑም ባደፈጡበት፣ እኔ ምን ቤት ነኝ” የሚሉ ወገኖች ሞልተዋል። እኒህን ወገኖች በፍቅር “ኧረ፣ እንዲህ አይባልም” እንላቸዋለን። ታሪክ እንዳስተማረን ብዙዎች ዝም ባሉበት ጥቂቶች ብቻ

እየተጋፈጡ እውነትን ጠብቀዋልና። ቅዱስ አትናቴዎስ አፋሽ አጎንባሹ ጊዜ ለሰጠው ሐሰተኛ ሲያረግድ “ዞር በል” ብሎ እንደ ኖረ ታሪክ አስተምሮናል። ይህ ሰው “ዓለም እውነትን ተፃር የቆመ እንደኾን፣ አትናቴዎስ ዓለምን ተፃር ይቆማል” በማለት ዐውጆ ነበር፤ እንደ ዐዋጁ መንፈስም ተመላለሰ። “እውነትና ንጋት እያደር ይጠራልና፣” ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ “*Attanasious Contra Mundom — አትናቴዎስ የዓለሙ ተቃናቃኝ*” እየተባለ ለመጠራት በቃ።

ይህ ሲባል፣ ፍቅር በጐደለው እውነት መጨካከን አለብን ማለት አይደለም። ተሠገዎአዊ ፈያጅነታችን (*incarnational relevance*) እንዳይዘነጋ መጣርና መትጋት አለብን። ተግባራዊ የደቀ መዝሙርነት ሕይወትን፣ የቅዱሳን ኅብረትንና ፍቅርን ችላ በማለት ለአደባባይ ጩኸት ብቻ ያጋደለ ትኩረት መስጠት አይገባም። እውነትን በአደባባይ አስጩኸን ስናበቃ፣ ያችኑ እውነት በፍቅር የሚያንሾካሹክ ልከኛ ሕይወት ከሌለን ቀልጠን አቅልጠናል ማለት ነው።

የከፋው ቢመጣ እንኳ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ እውነት ለመሞት መዘጋጀት አለብን እንጂ ስለ እውነት ልንገድል አልተጠራንም። ስለ እውነት መዘመር ያለብንን ያህል ስለ እውነት ማልቀስ ይኖርብናል። ስለ እውነት መከራከር የሚያስፈልገውን ያህል ስለ እውነት ዝም ማለትን መለማመድ ይገባል። አስተምህሯዊ ርቱዕነት (*doctrinal orthodoxy*) እንደሚያሳስበን ሁሉ ነቢያዊ ተጋፋጭነትን (*prophetic confrontation*) መዘንጋት ከእኛ አይጠበቅም።

መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ በቁጥብ ቃለት እንደሚመከሩት፣ “እንግዲያውስ ሙሉ በኾነ መስጠትና አስፈላጊውን ዋጋ ጨክኖ በመክፈል፣ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ የመኖር ጥሪው አሁንም ይከበር። ዋጋ በመክፈል ማገልገል የክርስቶስና የሐዋርያቱ ፈለግ ነው፤ እንከተለው።”[188]

[188] ተስፋዬ፣ *በዚያን ጊዜ*፣ 134።





የተለየ ዓላማ የለንም። ቢኾንልን ከሐዋርያው ጋር የምንለው ይህን ነው፦ *“እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚኾን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው”* (ቆላ. 1፥28)። ክርስቶስ ኢየሱስ መካከለኛ በኾነበት ትምህርት፣ ስብከትና ተግሣጽ የጌታ ማኅበር እንድትታነጽ እንተጋለን። ይህን ለማድረግ አምላካችን ባሰማራን የአገልግሎት ቦታ ሁሉ *“በቅጥሩ ላይ ተበታትነናል”* (ነህ. 4፥19)። ጌታም ይረዳናል።

ይህ በክርስትና መልእክተኛነትና ተልእኮ ውስጥ ልብ ሊባል የሚገባው ሐቅ ነው። የወንጌል ብሥራት አገልግሎት የክርስቶስን ብርሃን በቅብብሎሽ ለሌሎች ማድረስ አለበት። ዐደራን ተቀብሎ “የማይጠቅም ባሪያነትን” ከተወጡ በኋላ (ሉቃ. 17፥10) ለተከታይ ባለተራ ማስረከብ ያስፈልጋል (2ጢሞ. 2፥2)። እኛ የቀዳሚ ባለዐደራዎች ዕዳ ያለብን ሰዎች ነን። እነርሱ በእንባ በዘሩበት መከር ገብተን በደስታ ያጨድነውን ነዶ ለጌታ ክብር እንድናውለው እርሱ ሊጋሱ ጌታ ትሕትናና ቅንነት ያብዛልን። አሜን።

በዚህ ወሳኝ ታሪካዊ ወቅት ላይ የቆምን እኛ በጽኑ እንሞገታለን። ክርስቲያናዊ ትምህርት በኛ ዘመን እየጠነከረ ይሄድ ይኾን? ለትውልዱ ምን እናስረክባለን? ምንጩን ላገኘው ባልችልም፣ በማስታወሻ ደብተሬ ውስጥ አርኔል ሞትዝ የተባሉ ሚስዮናዊ ስም ጠቅሼ ያሰፈርሁት አንድ ሐሳብ ይገኛል፤ “ታሪክ በትክክለኛነት ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ማለት ይቻለዋል፤ በስብከታችሁ [እና በትምህርታችሁ] የኢትዮጵያ ክርስትና ይቆማል፣ አልያም ይወድቃል”። ኾኖም ቅዱስ ጳውሎስ *“ስለዚህ ጌታ ለማፍረስ ያይደለ ለማነጽ እንደ ሰጠኝ ሥልጣን”* (2ቆሮ. 13፥10) በሚለው የአገልግሎት መንፈስ እንመላለስ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን።

**ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ዘአፈጸመኒ በደኅና።**

# ዋቢ መጻሕፍት


Arumugam, Raj. *Alexander: Son of Olympias*. Np: Truth and Thought Systems Pty Ltd, 2006.

Bowman, Robert M. Jr. *The Word-Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel.* Grand Rapids: Baker, 2000.

Brown, Harold O. J. *Heresies: The Image of Christ in the Mirror of Heresy and Orthodoxy from the Apostles to the Present.* New York: Doubleday, 1984.

Chia, Ronald. *Hope for the World*. Leicester: IVP, 2006.

Douglas, J. D, and Merrill C. Tenney (eds.). *New International Bible Dictionary.* Grand Rapids: Zondervan, 1987.

Erickson, Millard J. *Christian Theology.* Grand Rapids: Baker, 1985.

Fee, Gordon D. *The Disease of the Health and Wealth Gospels.* Costa Mesa, California: The Word for Today, 1979.

Fernando, Ajith. *Jesus Driven Ministry.* Wheaton, Ill: Crossway, 2002.

Foster, John. *Church History I: The First Advance AD 29-500*. London: SPCK, 1991.

Frend, W. H. C. *The Rise of Christianity.* Philadelphia: Fortess, 1984.

Friberg, Barbara, Timothy Friberg, and Neva F. Miller. *Analytical Lexicon Of The Greek New Testament.* Grand Rapids: Baker, 2000: Electronic Edition.

Grudem, Wayne. *Systematic Theology: an Introduction to Biblical Doctrine.* IVP: Leisester, 1994.

Hanegraaff, Hank. *Christianity in Crisis.* Eugene, Oregon: Harvest House Publishers, 1993.

Hayford, Jack, John Killinger, and Howard Stevenson. *Mastering Worship.* Portland: Christianity Today, 1990.

Hiebert, Paul G. *Anthropological Reflections on Missiological Issuess.* Grand Rapid: Baker, 1994.

Klein, Steve. *The Bulletin of the Church of Christ at New Georgia*, August 26, 2007.

Labberton, Mark. *The Dangereous act of Worship: Living God's Call to Justice.* Dowbers Grove: IVP, 2007.

Littky, David, Samantha Grabelle. *Education is Everyone's Bussiness.* Alexandria, VA: ASCD, 2004.

MacConnell, D. R. *A Different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement.* Peabody, Masachusetts: Hendrickson, 1988.



Marius, Richard. *Martin Luther: The Christian between God and Death.* Massachusettes: Cambridge University Press, 1999.

Martin, Ralph P. *The Wroship of God: Some Theological, Pastoral and Practical Reflections.* Grand Rapids: Eardmans, 1982.

Mayer, Joyce *The Most Important Decision You Will Ever Make: A Complete And Thorough Understanding of What It Means to Be Born Again*. Faithwords, 2008.

Navarro, Kevin J. *The Complete Worship Service: Creating a Taste of Heaven on Earth.* Grand Rapids: Baker, 2005.

Owens, Ron. *Return to Worship: A God Centered Approach.* Nashvile: Broadman & Holman, 1999.

Packer, J. I. *Keep In Step with the Spirit.* Leicester: Inter Varcity Press, 1984.

Pazmino, Robert W. *Foundational Issues in Christian Education: an Introduction in Evangelical Perespective.* Grand Rapids: Baker, 1997.

Piper, John. *Contending for Our All.* Wheaton: Cross Way Books, 2006.

—. *Let the Nations Be Glad: The Superemacy of God in Missions.* Grand Rapids: Baker, 1993.

Rennie, I. S. "Evangelical Theology," in *New Dictionary of Theology*, Edited by Sinclair Ferguson and David F. Wright, 240-241. Downers Grove: IVP, 1988.

Ryken, Philip Graham. *Ecclesiastes: Why Everything Matters*. Wheaton: Crossway, 2010.

Sergew, Hable Selassie. "The Establishnment of the Ethiopian Church," in *The Church of Ethiopia: A Panoroma of Histoy and Spritual Life, 2nd Print*, by EOTC, 1-8. Addis Ababa: EOTC, 1997.

Stott, John. *Basic Christian Leadership.* Downers Groove: Inter Varcity Press, 2002.

—. *Evangelical Truth: A Personal Plea For Unity, Integrity and Faithfulness.* Leicester: IVP, 2003.

Von Allmen, J. J. *Worship: Its Theology and Practice.* Londen: Lutterworth, 1965.

Ward, J. W. "Pentecostalist Theology," In *New Dictionary of Theology*, Edited by Sinclair B. Ferguson and David F. Wright. 502-505. Leisester: IVP, 1988.

Wesley, John. *Sermons on Several Occasions.* London: n.pub., Originally published in 1771.

Wood, Laurence W. "Telling the Old, Old Story in the Post Modern Age," *The Asbury Herald*, Automn 1996: 3.





ልደቱ ዓለሙ፤ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአመራር ገጽታ።* ዐዲስ አበባ:- ያልታተመ፣ 2006 ዓ.ም.።

መሠረት ስብሐት ለአብ (አለቃ)፤ *ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ።* ሀዲስ አበባ:- አርቲስቲክ፣ 1951 ዓ.ም.።

—፤ *ትውፊታዊ ኀሳበ ዘመንና ታሪኩ:- በኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን ዐቋም።* ዐዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም.።

—፤ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋጽኦ።* ዐዲስ አበባ:- ያልታተመ ጽሑፍ፣ ዘመኑ አልተጠቀሰም።

መስፍን ወልደ ማርያም (ፕሮፌ.)፤ *ዛሬም እንጕርጕሮ:- እንነሣለን።* ዐዲስ አበባ:- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2005 ዓ.ም.።

ሙሉጌታ ክንፉ፤ *አምልኮና ቅድስና፣ ከጳጉሜ 2-6 ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሪዎች ስብሰባ ላይ የቀረበ።* ዐዲስ አበባ:- ያልታተመ ጽሑፍ፣ ዘመኑ አልተጠቀሰም።

ሚናስ ብሩክ (ተርጓሚ)። *የአገልግሎት መሠረቶች:- የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ።* ዐዲስ አበባ:- ኤስ. አይ. ኤም. ኢትዮጵያ ፐብሊኬሽን፣ 2000 ዓ.ም.።

ሚኪያስ በላይ፤ "ቃለ መጠይቅ፣" *ሕንጸት፣* ቍጥር 2፣ ግንቦት 2006 ዓ.ም. ገጽ 19፣ 40።

—፤ "ቤተ ክርስቲያን አደጋ ላይ ነች!" *ማኅቴስ፣* ቍጥር 17፣ ኅዳር 2003 ዓ.ም. ገጽ 2።

ማንሰል፣ ኮሊን፤ *ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ፣ 3ኛ መጽሐፍ።* ዐዲስ አበባ:- ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1999 ዓ.ም.።

ምኒልክ አስፋው፤ *ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1999 ዓ.ም.።

—፤ "ወንጌላውያን አማኞችና መጪው ሺህ ዓመት (ሚሌኒየም)" *ማቴቴስ፡ ልዩ ዕትም*፣ መስከረም 2000 ዓ.ም.፤ ገጽ 25።

ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን፤ *ነገረ መስቀል፡- መስቀሉን ሰቀሉት።* ዐዲስ አበባ፡- ያልታተመ ጽሑፍ፣ 2006 ዓ.ም.።

—፤ *የትሩፋን ናፍቆት።* ዐዲስ አበባ፡- ርኆቦት አታሚዎች፣ 2006 ዓ.ም.።

ሰሎሞን ዴሬሳ፤ *ዘበት ዕልፊቱ።* ዐዲስ አበባ፡- ተዋነይ ስቱዲዮ ፒ. ኤል. ሲ.፣ 1991 ዓ.ም.።

ሳምሶን እስጢፋኖስ፤ *ብንጮኽ ይወድቃል፡- በሕዝቡ ዙሪያ እንጂ በሕዝቡ መኻል ቅጥር አይሠራም።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2000 ዓ.ም.።

ሸዋንግዘው ሉሌ፤ *ቤተ ክርስቲያንና ዲያስጶራው (በውጭ ሀገር የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን አማኞች)፣ ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና አገልጋዮች በተዘጋጀ ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ የጥናት ጽሑፍ።* ዐዲስ አበባ፡- ያልታተመ፣ መስከረም 13 ቀን 1999 ዓ.ም.።

በረከት ስምዖን (ሚ/ር)፤ *የሁለት ምርጫዎች ወግ፡- ናዳን የገታ ሀገራዊ ሩጫ።* ናይሮቢ፣ 2004 ዓ.ም.።

በቀለ ወልደ ኪዳን፤ *ሪቫይቫል፡- ኢትዮጵያና የመጨረሻው መጨረሻ።* ዐዲስ አበባ፡- ዐዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን፣ 1994 ዓ.ም.።





በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)፣ *እውነት ማለት የእኔ ልጅ፣ ሦስተኛ ዕትም* (ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተጠቀሰም፣ 2006 ዓ.ም.።

ብርሃኑ ድንቄ፤ *አልቦ ዘመድ።* ቦታ፣ አሳታሚና የኅትመት ዘመን አልተገለጸም።

ብርያን፣ ስቲቭ ኤም. "መንፈሳዊ አስተርእዮትን (መገለጦችን) ክርስቲያናዊ ማድረግ፣" *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀም ሴሚናር።* ዐዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ 1997 ዓ.ም.፤ 3-7።

ተስፋዬ መኰንን (ተርጓሚ)፤ *ደቀ መዝሙርነት ።* ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 2002።

ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ከ"እምነት እንቅስቃሴ" መምህራን ትምህርት ተጠበቁ.* ግራንድ ራፒድስ፡- ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፡- 2011፤ ኤሌክትሮኒክ ቅጅ።

—፤ *ዐበይት መናፍቃን።* ዐዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት፣ 2001 ዓ.ም.።

ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)፤ *በዚያን ጊዜ።* ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን፣ 2002 ዓ.ም.።

ተሾመ ነጋሽ፤ *እስከመጣ ድረስ።* ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ፕሬስ፤ 1987 ዓ.ም.።

ኀይሉ ቸርነት፤ *ሕያው ቅብብል፡- የአሰባበክ ጥበብና ተግዳሮቱ።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተጠቀሰም፣ 1995 ዓ.ም.።

—፤ *መድረኮቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ።* ዐዲስ አበባ፡- ራእይ፣ 1997 ዓ.ም.።

ጎሩይ ጽጌ፤ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም እንዴት ሊጠና ሊመረመር ይገባል?" *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱሳ አጠቃቀም ሴሚናር።* ዐዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሥነ መለኮት ድኅ. ምረቃ ትምህርት ቤት፣ 1997 ዓ.ም. 28-29።

ነቢዩ ዓለሙ፤ "'የወንጌላውያን' የማንነት ቀውስ እና ማዕከላዊ የሥልጣ ዕጦት፣" *ማቴቴስ፣* ቁጥር 18፣ ግንቦት 2003 ዓ. ም፡- ገጽ 30-31።

ንጉሤ ቡልቻ፤ *መስተአየት።* ዐዲስ አበባ፡- ሊቪንግ ትሩዝ አገልግሎት፣ 2002 ዓ.ም.።

—፤ "ዘጠኝ ወንጀሎች (በቃለ እግዚአብሔር ላይ የሚፈጸሙ)" *ቃሉ ይንገሥ፣ ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣* በተገነው ቅጅ የኅትመት ቦታውንና ጊዜውን አመልካች ክፍሉ የተገነጠለ ነው፣ ገጽ 20።

አርኔል ሞትዝ፤ *ሕይወት ለዋጭ ስብከት።* ዐዲስ አበባ፡- አይ. ኢ. ሲ. ፐብ., 1999።

አበባው መላኩ፤ *ከራድዮን።* የኅትመት ቦታና አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1999 ዓ.ም.።

አንቶኒ፣ ሚካኤል፣ (ሚናስ ብሩክ [ተርጓሚ])፤ *የአገልግሎት መሠረቶች፡- የክርስቲያናዊ ትምህርት መግቢያ።* ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ፐብሊኬሽን፣ 2000 ዓ.ም.።

ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ፤ *ሃይማኖተ አበው።* ዐዲስ አበባ፡- ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986 ዓ.ም.።

ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፤ *አማርኛ መዝገበ ቃላት።* ዐዲስ አበባ፡- ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም.።





ኢትዮጵያ ወንጌላውያን ነገረ መለኮት ት/ቤቶች ኅብረት (AETIE) ኀላፊነት የሰጣቸው አጥኚዎች በቡድን፤ "የሼፐርድ ቡሽሪ የዐዲስ አበባ አገልግሎት ግምገማና ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣" ዐዲስ አበባ፡- ያልታተመ ጽሑፍ፣ ግንቦት 23 ቀን 2006 ዓ.ም. 1-19።

እንዳለ ገብረ መስቀል፤ *የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙበት ወቅታዊ ኹኔታ፡- መንፈሳዊ ችግሮች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖዎችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች።* ዐዲስ አበባ፡- ያልታተመ ጽሑፍ፣ 1999 ዓ.ም.።

አሴይ-ሜንሳህ፣ ጐትፍሬድ (ተርጓሚ ሚናስ ብሩክ)፤ *ይፈለጋሉ፡- አገሊጋይ መሪዎች።* ዐዲስ አበባ፡- ኤስ. አይ. ኤም. ፐብሊኬሽን፣ የኅትመት ዘመን አልተገለጸም።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።* ዐዲስ አበባ፡- ደስታ ተክለ ወልድ በአርትስቲክ ማተሚያ ቤት እንዳሳተሙት፣ 1948 ዓ.ም.።

ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* ዐዲስ አበባ፡- አርቲስቲክ፣ 1962 ዓ.ም.።

ደረጀ በላይነህ፤ *የዕድሜ መንገድ።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 1997 ዓ.ም.።

ዳዊት ጸጋዬ፤ *አርነት የወጡ ሐሳቦች ።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2003 ዓ.ም.።

ገብረ መሲሕ፤ *የመምሩ ምርቅና መረቅ፡- በ"የተኩላው ለምድ ሲገፋ ውስጥ"።* ዐዲስ አበባ፡- አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2002 ዓ.ም.።

ጌታቸው ኃይሌ፤ *ደቂቀ እስጢፋኖስ፡- "በሕግ አምላክ"።* ዐዲስ አበባ፡- ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2002 ዓ.ም.።

ጌታቸው በለጠ፤ *ኤሎሄና ሃሌ ሉያ፦ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ቅጽ ሦስት፣ ከ1966-1992።* ዐዲስ አበባ፦ የኢትየጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 1992 ዓ.ም.።

ግርማ ተስፋው፤ *የጠፋችውን ከተማ ኀሠሣ።* የኅትመት ቦታና አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2005 ዓ.ም.።

ግርማ ኤልያስ፤ *ደቂቀ እስጢፋኖስና የደብረ ብርሃን ሸንጎ።* ዐዲስ አበባ፦ አሳታሚ አልተገለጸም፣ 2000 ዓ. ም.።

ግርማዊ፤ *የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ መሠረቶችና መዘዞች።* ዐዲስ አበባ፦ ቤሪያ የኅትመት ኩባንያ፣ 1990 ዓ.ም.።

ጸጋዬ ገብረ መድኅን፤ *እሳት ወይ አበባ።* ዐዲስ አበባ፦ የጸ.ገ.መ. ቤተ ሰቦች፣ 1999 ዓ.ም.።

ፊሎስ፣ ቲም፤ *የምታመልከ ሁን።* ዐዲስ አበባ፦ ኤስ. አይ. ኤም. ፐብሊኬሽን፣ 2004።

ፍቅረየሱስ ሁንዴሳ፤ *ደቀመዝሙር ወይስ ደቂቀ መዝሙር።* ዐዲስ አበባ፦ ያልታተመ ጽሑፍ፣ 2005 ዓ.ም.።



# መፍትሔ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀላዌ | *ትርጓሜው ሰፊ ነው። አካል ገጽ፣ ቁመት፣ ባሕርይ፣ ጠባይ* |
| "ለመሬት የከበደ" | *ትልቅ ሰው፣ የሚታፈር፣ የሚከበር* |
| ልግም | *ከፋት፣ ጥመት፣ ማልመጥ* |
| ሐተተ | *መረመረ፣ ፈተነ፣ መላልሶ ጠየቀ* |
| ሕጸጽ | *እንከን፣ ጉድለት፣ ቅሬታ* |
| መቀፍቀፍ | *በብዛት መውለድ፣ ማበራከት* |
| መቅ / ዕመቅ | *መቃመቅ፣ ጥልቅ ጉድጓድ፣ አንጦርጦስ* |
| መብከንከን | *በሐሳብ መያዝ፣ መብሰልሰል፣ መቈጨት፣ መጸጸት* |
| መትከን | *በኀዘን፣ በብስጭት፣ በንዴት መብሰልሰል* |
| መወራጨት | *መንፈራገጥ፣ መቅበጥበጥ፣ የጭንቅ እንቅስቃሴ ማሳየት* |
| መዘዝ | *(1)ጦስ፣ ሰበብ፤ (2) በአንድ ነገር ምክንያት ተያይዞ የሚመጣ ችግር* |
| መዘበር | *መቀላመድ፣ መለፍለፍ፣ መቃዠት* |
| መፏደድ | *መገስገስ፣ መሮጥ* |
| ማርገድ | *መጨፈር፣ መዝለል፣ ዳንኪራ መምታት፣ ማሽብሸብ* |
| መርግ | *ትልቅ ናዳ* |
| ማሰባቀል | *ማመሳቀል* |
| ማበጥ | *ማወከ፣ መረበሽ፣ መበጥበጥ* |
| ማዘንቅ | *ማደባለቅ፣ መቀየጥ* |
| ምህላ | *ልመና፣ ምልጃ፣ የማኅበር ጸሎት፣ እግዚኦታ* |
| ምስባክ | *በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የዚህ ቃል ግልጋሎቱ "አትሮኖስ" ለማለት ነው። በባዕዱ ቋንቋ* Pulpit *ወይም* Podium *የሚሉት ነገር ነው።* |
| ምኅጻር | *መጠንን ማሳነሻ፣ መቍረጫ ሲኾን፣ "ምኅጻረ ቃል" ቃልን ሐረግን አሳጥሮ ማቅረቢያ ነው።* |
| ምጥንታ | *ተማጽኖ፣ ልመና፣* |
| ሠረቀ | *ወጣ፣ ታዬ፣ በራ፣ ተገለጠ፣ ብቅ አለ፣ ተነሣ፣ ባተ* |
| ሥጋዌ | *ሥጋነት፣ ሥግና ሥጋ መኾን፣ ሰው መኾን፣* |
| ርትዕ | *የቀና፣ የተስተካከለ፣ የሚገባ ሥራ፣ እውነተኛ ፍርድ* |

| | |
|---|---|
| ሰከላ | ማሰሪያ፣ እንቅስቃሴን ለመገደብ ብዙውን ጊዜ በጋማ ከብቶች የፊትና የኋለኛ እግሮች ላይ የሚታሠር ገመድ ወይም ጠፍር ነው። |
| ሳዱላ | በገጠር አካባቢ ሴቶች መሃል ራሳቸውን ዙሪያውን ጠጉራቸውን በመተው በከቡ የሚላጩት አለሟጨት |
| ሰማዕት | ምስክር፣ የሚመሰክር፣ ለዓላማው የሚሞት (ለአንድም ለብዙም ይቀጸላል) |
| ስንክሳር | የተለያዩ ዕለታዊ ገድላትን አካቶ የያዘ ግዙፍ መጽሐፍ |
| ሸመቀ | አደባ፣ አደፈጠ፣ አደጋ ለመጣል ተደበቀ |
| ቀርቀር / መቀራቅር | ገደል፣ ለመግባትና መመውጣት የሚያዳግት ገደላገደል ቦታ |
| ቀነበበ | ከበበ፣ ከብ አደረገ፣ |
| ቀኖና | ሕግ፣ ደንብ፣ ሥርዓት፣ መመሪያ |
| ቀየደ | ከፈለ፣ መከተ፣ ጋረደ፣ ከለለ፣ ሰነከለ፣ አሰረ |
| ቢጋር | ምልክት፣ ንድፍ፣ መጠን |
| ብሂል | ማለት፣ አባባል |
| ብሕትውና | ተለይቶ፣ ተነጥሎና ተገልሎ ለብቻ መኖር፣ |
| ብራቅ | መብረቅ፣ ነጐድጓድ |
| ተመስጦ | ልዩ የአዕምሮ ትኩረት |
| ተመክሮ | ከተግባር፣ ከልምድ የተገኘ ዕውቀት ገጠመኝ |
| ተማለለ | ለመነ፣ ማለደ |
| ተረክ | ወግ፣ ነገር፣ ወሬ |
| ተብከነከነ | በቍጭት፣ በንዴት ናወዘ፣ ለፋ |
| ተካለበ | ተቻኮለ፣ ተጣደፈ፣ ተንቀዠቀዠ |
| ተውኔት | ለተመልካች በመድረክ ላይ ቀርቦ የሚታይ ቲያትር |
| ተውተበተበ | ተሳሰረ፣ ተያያዘ፣ ተጠላለፈ |
| ተዐብዮ | ትዕቢት፣ ኩራት፣ ትምክሕት |
| ተገደረ | ታበየ፣ በኩራት ተወጠረ |
| ተፍገመገመ | ተውተረተረ፣ ተንገዳገደ |
| ትሥጉት | ሥጋነት፣ ሥጋ መኾን፣ ሥጋ መልበስ፣ ሰው መኾን፣ |
| ትሩፍ / ትሩፋን | የቀረ፣ የተረፈ፣ ቅሪታ/ቅሬታ፣ ቀሪ፣ የዳነ፣ ያመለጠ |
| ትርፈሳ | አፈሳ፣ አብዝቶ መዝገን |



| | |
|---|---|
| ኅቡዕ | የተሸሸገ፣ ድብቅ፣ ስውር፣ ምስጢራዊ |
| ኅዳጣን | አናሳ፣ ትንሽ፣ ጥቂት |
| ነሆለለ | ሞኘ፣ ቂል፣ ፈዛዛ ኾነ፣ ጀለ |
| ነጋድያን | ነጋዴዎች |
| ኑባሬ | ኑሮ፣ አኗኗር |
| ኑፋቄ | ከፍሎ ማመን፣ ጥርጥር፣ በተከፈለ ልብና ሐሳብ የሚታመን፣ ሕጹጽ እምነት |
| ንግር | የተባለ፣ የተተነበ፣ አስቀድሞ የተነገረ ትንቢት |
| ንጽረት | ዕይታ፣ አመለካከት |
| አረንቋ | ማጥ፣ ረግረግ፣ ጭቃ |
| አረማዊ | አረመኔ፣ በወንጌል ያላመነ |
| አርምሞ | ዝምታ፣ ጸጥታ |
| አርቲ ቡርቲ | ምናምን፣ ከንቱ፣ የማይረባ ነገር፣ ቅብጥርሴ |
| አሰላስሎ | ስለ አንድ ነገር ለረጅም ጊዜና በተመስጦ በማውጣት ማውረድ ማሰብ |
| አስተኔ | ብጤ፣ እንደ ... ያለ፣ ... የመሰለ ለማለት |
| አሶመሶመ | አረተረተ፣ ከሶምሶማ በፊት ማኰብኰብ (ለፈረስ) |
| አብነት | ምሳሌ፣ አርአያ |
| አተካራ | ጭቅጭቅ፣ ንዝንዝ |
| አትሮንስ | ከእንጨት ወይም ከብረት ተሠርቶ፣ መጽሐፍ ተዘርግቶ የሚነበብበት ዕቃ |
| አንከሮ ሰብ | ሰው ተኰር፣ ሰው ገነን |
| እንደምታ | የአንድ ነገር ወይም ሐሳብ የተለያየ ትርጓሜ ይዘት |
| አገርጋሪ | ደንባሪ፣ ድንጉጥ |
| "እስከ ማእዜ" | እስከ መቼ? |
| እንቶ ፈንቶ | የማይረባ፣ የማይጠቅም፣ ፋይዳ ቢስ፣ ቅራቅንቦ ነገር |
| ከላ | ቈረጠ፣ ቀነጠሰ |
| ኩነት | መኾን አኳኋን፣ ኹነታ |
| ክሽፈት | ጭንገፋ፣ ብልሽት፣የተጓጐለ፣ ታቅዶ ሳይሳካ የቀረ |
| ወጭት | ከነሐስ ወይም ከሸክላ የሚሠራ ጐድጓዳ ሰሀን |
| ወጭት ሰባሪ | ውለታ ቢስ |

| | |
|---|---|
| ወየበ | ወደ ቢጫነት ተለወጠ (ለሰብል)፣ ተበላሸ |
| ወገሸ | ሮጠ፣ በረረ፣ በጣም ተቈጣ፣ ፈረጠጠ ደነበረ (ከብት) |
| "ዋጤነት" | ሽማችነት፣ ኢጋባሽነት |
| ውቅር | አንድ ነገር የተወጠነበት፣ በየደረጃው ያሉ ዋና ክፍሎች |
| ዐምድ / አዕማድ | ምሰሶ |
| ዐዘቅት | ጥልቅ ጉድጓድ |
| ዘላን | አንድ ቦታ ላይ ቋሚ የኾነ መኖሪያ የሌለውና ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ የሚኖር ሰው ወይም ሕዝብ |
| ዘልማድ | የልማድ፣ ልማዳዊ |
| ዛብ | የበቅሎ ወይም የፈረስ መግሪያ ልጓም ቋድ ወይም ጠፍር |
| ዝብዝብ | ጭቅጭቅ፣ ንትረካ፣ የተንዛዛ ወይም የተራዘመ ነገር |
| ዝንፈት | ከመስመር መውጣት፣ መንጋደድ፣ መዛባት፣ መባለጥ፣ ከልክ ተርፎ መታየት፣ መራዘም |
| ደርብ | ፎቅ |
| ዳተኛ (ነት) | ቸልተኛ(ነት) |
| ዳፋ | ጦስ፣ መዘዝ፣ ግፍ፣ ጡር |
| ድብታ | መፍዘዝ፣ መጫጫን፣ መገርዘዝ (በእንቅልፍ) |
| ድውይ | ሕሙም፣ የታመመ፣ "ከርሞ ጥጃ"፣ የተቀጨ |
| ጅብ ጥላ | የጃንጥላ ቅርጽ ኖሮት እንጉዳይ የሚመስል በየመስኩ ላይ በፍጥነት ግንፍል ብሎ የሚበቅል ዕፅ |
| ገሸረ | በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ አደረገ፣ ጎለተ |
| ጥቅመ ሰናኦር | የሰናኦር ጥቅም፣ ምኞት፣ የእኔነት ክብርና ዝና ተዐብዮ |
| ጭምብል | ከጨርቅ፣ ከሹራብ፣ ከእንጨትና ከተለያዩ ነገሮች የሚሠራና በፊት ላይ የሚጠለቅ አንድ ሰው ማንነቱ በተመልካች እንዳይታወቅ ለመሰወር የሚያገለግል |
| ጽሞና | ርጋታ፣ ዝግታ፣ ጸጥታ |
| ፀር / አፅራር | ጠላት/ ጠላቶች፣ ባላንጣ |
| ፋነነ | ፈረጠጠ፣ ቦረቀ፣ ፈነጨ፣ አውደለደለ |
| ፍንጠዛ | ፈንጠዝያ፣ ደስታ፣ ቡረቃ፣ በደስታ መዝለል |
| ፍኖት | መንገድ |
| ፎነነ | አፍንጫን ገመደ፣ አሳጠረ |



## ማስታወሻ



"ሕዝብህ በአንተ ሐሴት ያደርግ ዘንድ እንደገና አታበጀንም ወይ?"

መዝሙር 85፥6

መዝሙር 11፥3

*"እነርሱ መሠረቱን ባፈረሱ ጊዜ ጻድቅ ምን ማድረግ አለበት?"*





**በጸሐፊው ተዘጋጅተው የታተሙ መጻሕፍት**

1. የመምሩ ምርቅ እና መረቅ (2002 ዓ.ም.)
2. የትሩፋን ናፍቆት (2006 ዓ.ም.)
3. "የደነበረው በቅሎ"... (2007 ዓ.ም)

**እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊታተሙ የተዘጋጁ**

1. የእግዚአብሔር እስራኤል
2. የሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወትና መልእክታት
3. ነገረ መስቀል
4. 1ኛ ጴጥሮስ ማብራሪያ
5. በራእይ የተሞላ ሕይወት
6. እግዚአብሔር የሚሠራው ቤት

"... መንፈሳዊ መሪዎችና የቃሉ አገልጋዮች እንደ ኾንን የምናስብ ሁላችን፣ ለራሳችን ስተን ብዙዎችን ከማሳት እንድንተርፍ፣ ከጥፋትም እንድንጠበቅ፣ በሰከነ ልብ ይህን መጽሐፍ እናንብብና እንመከር፡፡ ..."

*ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)*
*ከሐዋሣ ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን*

"በርግጥም በቅሎዋ፣ እንደ ልማዷ፣ ደንብራለች። በተቀመጡባት፣ በራሷ፣ በቅርቧ ባሉት እና በንብረት ላይ አደጋ እያደረሰች ነው።... እናንተዬ! እኔስ በእግሯ ሰካላ፣ በአፏ ዛብ፣ የሚኾንበትን ቀን ናፈቅሁትም፣ ፈራሁትም። "

*በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)*
*ቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን*

"... ይህን በፍሬ ነገርና በሥነ መለኮታዊ ሚዛናዊነት ግልጽ በኾነ መንገድ የተዘጋጀ መጽሐፍ አንብቤ ተባርኬአለሁ፤ ማድረግ ያለብኝንም ተረድቼአለሁ። ... መጽሐፉን [እንድትጥቀሙበት] እመክራለሁ፤ አበረታታለሁም። "

*ሽፈራው ወልደ ሚካኤል*
*የልጆች ዕድገት ሥልጠናና ምርምር ማእከል (CDTRC)*

" ሰማዩን ጥቋቁር ደመናዎች አንግበዉበታል። ... ወንድማችን ሰሎሞን ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለችበትን እውነታ፣ በብልኃተኛ ጥጥ ፈልቃቂ አያያዝ እየጐሰጐለ አውጥቶ፣ አሳየን፤ አልባሌውን ከኹነኛው እንድንለይ አነቃን።"

*ንጉሤ ቡልቻ*
*ኮምፓስ-ኢትዮጵያ፣ "ቃሉ ያበራል" ፕሮጀክት*

"ሥጋቴ ተወግዶ ደስታዬ ፍጹም እንዲኾን፣ ይህን ጠቃሚ መጽሐፍ አማኞች ሁሉ አንብበው ራሳቸውንና ቤተክርስቲያንን ከዘመኑ የትምህርት ነፋስ እንዲጠብቁ እመክራለሁ፡፡"

*ጌታሁን ታደሰ (መጋቢ)*
*የኢትዮጵያ አማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት*

"መጽሐፉ ራሳችንን አካትተን ሁሉን እንድንፈትሽ ግድ ይለናል። ፍተሻው ተሳስቻለሁ፣ ተሳስተናል ወይም አስተውናል በማሰኘት ከከንቱ ፋጫችን ይገታናል።"

*ስሜ ታደሰ (መጋቢ)*
*የኢትዮጵያ ባይብል ባፕቲስት ቸርች ፌሎሺፕ ፕሬዚዳንት*

"ይህች መጽሐፍ፣ ... ላለንበት ዘመን ወሳኝ መልእክት ይዛለችና፣ ከማንበብ ውጭ ሌላ ምርጫ የለንም፡፡ በተለይም፣ የዩኒቨርሲቲና የኮሌጅ ተማሪዎች እንዲሁም ምሩቃን እንዲያነብቧት አበረታታለሁ፡፡"

*ዘላለም አበበ*
*የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ክርስቲያን ተማሪዎች ኅብረት (EvaSUE)ፕሬዚዳንት*



ከሁለት ደርዘን ዓመታት በፊት በእግዚአብሔር ቸርነት በተሐድሶ የወንጌል አገልግሎት ውስጥ የዳግም ልደት ብርሃንን ያየው ሰሎሞን አበበ መጋቢ ወንጌል ሲኾን በኢቫንጀሊካል ቴዎሎጂካል ኮሌጅ (ETC) እና በኢትዮጵያ ድኅረ ምረቃ ነገረ መለኮት ት/ቤት (EGST) የቅዱሳት መጻሕፍት መምህር ነው፤ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ምስባኮች በመስበክም ይታወቃል። ሰሎሞን ባለትዳርና የሁለት ሴቶች ልጆች አባት ነው።

ISBN 978-99944-970-0-3

9 789994 497003 >

ፎኖቦት አታሚዎች

ብር 55.00 $10.00